# ከሞት ወደ ሕይወት

*ሮሜ 5-8 እግዚአብሔር ስለ ደህንነት እና የድል ሕይወት ስላለው እቅድ ያስተምራል*

**ኤፍ. ዋይኒ ማክ ሊዎድ**

LIGHT TO MY PATH BOOK DISTRIBUTION
Sydney Mines, Nova Scotia, CANADA B1V 1Y5

**ከሞት ወደ ሕይወት**

የቅጂ መብት © 2022 በኤፍ. ዌይኒ ማክ ሊዎድ

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህ መጽሐፍ ክፍል ከጸሐፊው የጽሁፍ ፈቃድ በቀር በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ ሊባዛ ወይም ሊተላለፍ አይችልም።

የ(NIV) ምልክት የተደረገባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት፣ ከኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን®፣ NIV® ነው። የቅጂ መብት © 1973፣ 1978፣ 1984፣ 2011 by Biblica, Inc.™ በዞንደርቫን ፈቃድ የተሰጠው ነው። ሁሉም መብቶች በዓለም ዙሪያ የተጠበቁ ናቸው። www.zondervan.com "NIV" እና "ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን" በዩናይትድ ስቴትስ የፓተንት እና የንግድ ምልክት ቢሮ በቢቢሊካ፣ Inc.™ የተመዘገቡ የንግድ ምልክቶች ናቸው።

የ(ESV) ምልክት የተደረገባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ከESV® መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው። (The Holy Bible, English Standard Version®) ፣ የቅጂ መብት © 2001 በCrossway፣ የምሥራች አሳታሚዎች የሕትመት አገልግሎት የታተሙ ናቸው። ፈቃድ የተሰጠው ነው። ሁሉም መብቶች የተጠበቁ ናቸው።

ከተፈቀደው (ኪንግ ጀምስ) ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተጠቅሰዋል። በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ በተፈቀደው ህትመት ውስጥ ያሉ መብቶች በክራውን የተሰጡ ናቸው። በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ በክራውን ፓተንቲ ፈቃድ እንደገና ተባዝቷል።

# ማውጫ

ምዕራፍ 1 - ወደ ዓለም የገባው የሐጢአት እና ሞት ችግር ........................................................................ 5
ምዕራፍ 2- ነጻ ስጦታ ................................................ 17
ምዕራፍ 3 - አንድ ሥራ ............................................ 27
ምዕራፍ 4 - በክርስቶስ መጠመቅ .................................. 38
ምዕራፍ 5 - ከክርስቶስ ጋር መሞት........................... 45
ምዕራፍ 6 - ሐጢአት እንዲነግስ አትፍቀዱ .................. 53
ምዕራፍ 7 - ከጸጋ በታች................................................ 62
ምዕራፍ 8 - የሐጢአት ፍሬ እና ነጻ ስጦታ .................. 75
ምዕራፍ 9 - ከሕግ ነጻ መውጣት ................................... 87
ምዕራፍ 10 - ሕጉ ሐጢአት ነውን? ................................ 97
ምዕራፍ 11 - ሕጉ እና ሥጋ ........................................ 104
ምዕራፍ 12 - የውስጥ ጦርነት ..................................... 117
ምዕራፍ 13 - የሕይወት መንፈስ ሕግ ......................... 127
ምዕራፍ 14 - ሥጋው እና መንፈሱ ............................. 138
ምዕራፍ 15 - የመንፈስ ሕይወት .................................. 153
ምዕራፍ 16 - እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር እዳ የለብንም... 161
ምዕራፍ 17 - ልጆች እና ወራሾች................................. 173
ምዕራፍ 18 - የፍጥረት ሁሉ እስራት .......................... 185
ምዕራፍ 19 - የመንፈስ መቃተት ................................. 197
ምዕራፍ 20 - ነገር ሁሉ ለበጎ ይደረጋል....................... 207

ምዕራፍ 21 -ለአማኙ ያለው የእግዚአብሔር ታላቅ

ዓላማ.215

ምዕራፍ 22 - ማን ይቃወመናል? ............................ 230

ምዕራፍ 23 - ማን ይለየናል? ................................ 241

# ምዕራፍ 1 -
# ወደ ዓለም የገባው የሐጢአት እና ሞት ችግር

ሮሜ 5:12-14

*[12] ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ [13] ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም፤[14] ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና። (ሮሜ 5)*

ሮሜ 5-8 ድነት እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኝ ክርስቲያናዊ ሕይወት በጣም ጠቃሚ የሆኑ ስነ-መለኮታዊ ትምህርቶችን ይዟል። እነዚህ ምዕራፎች በዚህ አጭር ጥናት ውስጥ ልሰጥ ከምችለው በላይ ብዙ ይዘዋል፣ ሆኖም ይህ ለእኛ ጅምር ይሆናል። ጸሎቴ እዚህ ላይ የምንመረምራቸው እውነቶች በአንባቢው ወይም በአንባቢዋ መንፈሳዊ ህይወት ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ እና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእነርሱ ያደረገውን የበለጠ ያውቁ ዘንድ እንዲረዳ ነው።

ሮሜ 5፡12-14 ባለው የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ልጀምር።

*[12] ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ [13] ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም፤ [14] ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና። (ሮሜ 5)*

እነዚህ ጥቅሶች “ስለዚህ” በሚለው ቃል መጀመራቸውን አስተውሉ። ቃሉ የሚያመለክተው ተከትሎ የሚመጣውን እና ሐዋርያው ቀደም ሲል የተናገረውን መሠረት በማድረግ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ በዝርዝር አልሄድም። ሐዋርያው የሮሜ ሰዎች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መፍጠር እንደሚችሉ እና በእነርሱ ፈንታ ስለተሠራው ሥራ እውነትን ሲያስተምር ቆይቷል ማለቱ በቂ ነው። ቀጥሎ ያለው የዚህ አስደናቂ እውነት እድገት እና የዚህ ጥናት ትኩረት ነው።

በሮሜ 5፡12-14 ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች አንዳንድ መሠረታዊ እውነቶችን ያስተምራል። እስቲ በመግቢያው ላይ ያሉትን እነዚህን እውነቶች ለትንሽ ጊዜ እንመልከት።

## *ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ*

ጳውሎስ የሚጀምረው ኃጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደመጣ በመንገር ነው። የጳውሎስ መልዕክት በዘፍጥረት 3 ወዳለው የኤደን ገነት ታሪክ ይመልሰናል፤ከዚያም ሔዋን በሰይጣን ተፈትና መልካም እና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ ፍሬ በመውሰድ ወደ ባልዋ ያመጣችበትን ታሪክ ይነግረናል። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከዚህ ዛፍ እንዳይበሉ አዟቸው ነበር። አዳምና ሚስቱ ከፍሬው በመመገብ የእግዚአብሔርን

ትዕዛዝ ተላለፉ። በእነርሱ አማካኝነት ኃጢአት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ዓለም ገባ።

እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር የፈጠረውን ሁሉ አጸደቀ።

*31 እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ስድስተኛ ቀን። (ዘፍጥረት 1)*

ከኃጢአት በፊት የነበረው ፍጥረት ፍጹም ነበር። አዳም ከፈጣሪው ጋር በህብረት ይኖር ነበር። ዳሩ ግን ኃጢአት ሲገባ አዳምና ሔዋን የሚያውቁት ነገር ሁሉ ተለወጠ።

## *በሐጢአት ምክንያት ሞት ወደ ዓለም ገባ*

ጳውሎስ ሁለተኛውን ነጥብ ለማንሳት በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ይቀጠላል። ሞት በኃጢአት ምክንያት ወደ ዓለም እንደ መጣ ይነግረናል። ልንረዳው የሚገባን ሞት የሚለው ቃል አዳምና ሔዋንን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፍጥረታት ሁሉ የሚያመለክት መሆኑ ነው።

ዘፍጥረት ሞት በፍጥረት ላይ ስላለው ተጽዕኖ ግልጽ ያደርጋል። ለምሳሌ ኃጢአት ወደ ዓለም በገባበት ቅጽበት አዳምና ሔዋን በግንኙነታቸው ውስጥ ገዳይ ውጤቶች እንዳጋጠማቸው እንመለከታለን። በመጀመሪያ ዘፍጥረት 3፡7 ላይ እንዲህ ይላል፡

*7 የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፥ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ። (ዘፍጥረት 3)*

ከኃጢአት መግባት ጋር ነውር መጣ። ለመጀመሪያ ጊዜ አዳምና ሔዋን እርስ በርሳቸው ተሸሸጉ። የግንኙነታቸው ንፁህነት ጠፋ። እርስበርስ በነበራቸው ግንኙነት እውነት የነበረው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነትም እውነት ነበር። ዘፍጥረት 3 ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባ በኋላ

ከእግዚአብሔር ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘውን ይተርክልናል፦

*8 እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ። 9 እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው። 10 እርሱም አለ፦ በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም። (ዘፍጥረት 3)*

አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ ሲመላለስ የነበረውን የእግዚአብሔርን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ምላሻቸው ከእርሱ መደበቅ ነበር። አዳም ለምን እንደተደበቁ ሲጠይቃቸው ራቁቱን በመሆኑ እንደፈራ ለእግዚአብሔር በመንገር ምላሽ ሰጠ። ኃጢአት ውርደትንና ፍርሃትን አመጣ። ይህ ነውርና ፍርሃት ከእግዚአብሔር ጋር ከነበራቸው ኅብረት አራቃቸው።

ዛሬ ትዳር እና ቤተሰብ ሲፈርስ፤ኃጢአትና ሞት በግንኙነት ውስጥ የሚያሳድሩትን ውጤት እናያለን። በወዳጅነት ውስጥ በሚፈጠር ክህደት እና ምድራችንን በሚያበላሹ ጦርነቶች ውስጥ እንዲሁ እንመለከታለን። እስር ቤቶች በስርቆት፣በማንገላታት ወይም የሰውን ሕይወት በማጥፋት ለሌሎች የሰው ልጆች ርህራኄ ባላሳዩ ሰዎች ሲሞሉ እናያለን። ኃጢአት በግንኙነት ላይ ሞትን አመጣ።

እንግዲህ የተበላሹ ግንኙነቶች የኃጢአትና የሞት ብቸኛ ውጤቶች አልነበሩም። ስቃይና መከራም ወደ ምድር ገባ፣ስለሆነም ለመጀመሪያ ጊዜ አዳምና ሚስቱ በሥጋ መጎዳት ምን እንደሚመስል አወቁ፡

*16 ለሴቲቱም አለ፦ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል። 17 አዳምንም አለው፦ የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና*

*ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ (ዘፍጥረት 3)*

ለሴቲቱ በወሊድ ጊዜ ስቃይ ይሆናል፡፡ አዳም መሬትን በማረስ ወገብ-ሰባሪ በሆነ ሥራ ውስጥ ያልፋል፡፡ በዚህ ምድር ላይ ሥቃይና መከራ የኃጢአትና የሞት ውጤቶች ናቸው፡፡ ይህ የሞት እርግማን የሚመጣው ህይወታችንን ሁሉ በሚያሠቃዩ በርካታ በሽታዎች መልክ ነው፡፡ ሆስፒታሎቻችን በኃጢአትና በሞት ምክንያት በሚሰቃዩ ሰዎች ተሞልተዋል፡፡ በሽታዎች የምንወዳቸውን ሰዎች በማሰቃየት በየቀኑ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ሰዎች ህይወት ይወስዳል፡፡ እንግዲህ ወደ ኤደን ገነት በገባ ኃጢአት ምክንያት ወደዚህ ምድር የመጣው የኃጢአትና የሞት ውጤት ይህ ነው፡፡

ምድር ራሷም በኃጢአት ምክንያት በሞት ውስጥ ታልፋለች፡፡ በዘፍጥረት 3፡17-19 እግዚአብሔር ለአዳም የተናገረውን አድምጡ

*17…ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤18 እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ፡፡ 19 …በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ (ዘፍጥረት 3)*

ምድር ያለ ትግል ፍሬ አታፈራም፡፡ እንግዲህ እሾህና አሜከላ ከምድር ፍሬ ጋር አንድ ላይ ይበቅላሉ፡፡ አዳም ሕይወትን ከምድር ለማብቀል ጠንክሮ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ኃጢአት በምድር ላይ እርግማን አምጥቷልና፡፡

እንግዲህ ይህ እርግማን በጎርፍ፣በረሃብ፣ በመሬት መንቀጥቀጥ፣በኃይለኛ አውሎ ንፋስ እንዲሁም በሌሎች በርካታ የተፈጥሮ አደጋዎች አማካኝነት ታላላቅ አካላዊ ሰቆቃዎችን አስከትሏል፡፡

በመጨረሻም በዘፍጥረት 3 ላይ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን በሞት ወደ አፈር እንደሚመለሱ ነገራቸው፡፡

*ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና። (ዘፍጥረት 3)*

ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባበት ጊዜ አንስቶ አዳምና ሔዋን መሞት ጀመሩ። ያ የሞት ሂደት ለብዙ ዓመታት በሰውነታቸው ላይ ጉዳት ሲያደርስ ቆይቷል። በእድሜ ይዳከሙ ነበር። ሰውነታቸው መስራት እስኪያቅተው ድረስ ቀስ በቀስ እየዛለ ይሄዳል። ሞት ወደ አዳም እና ሔዋን መጣ።

ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ሁሉም ነገር ማርጀት ጀመረ። የሰው አካል አርጅቶ ይሞታል። ምድር ታመመች፤ በነዋሪዎቿም ላይ በሽታን አፈሰሰች። የተፈጥሮ አደጋዎች እና ውድመት በምድሪቱ ላይ ወደቀ። ግንኙነቶች ፈርሰዋል፣ሃዘን እና ስቃይ ደግሞ ውጤቱ ነው። መንግስት በመንግስት ላይ በጦርነት ይነሳሉ። ባሎች ሚስቶችን ይክዳሉ። በአንድ ወቅት ፍጹም የሆነችው ምድር የተረገመችና በኃጢአትና በሞት የተሞላች ትሆናለች። ልጆች ሊሞቱ ይወለዳሉ። በአሰቃቂ እና በወደቀ ዓለም ውስጥ ይኖራሉ። ተስፋ መቁረጥ እና ተስፋ ቢስነት ይበዛል።

## *ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ ደረሰ*

ጳውሎስ በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ሞት በአንድ ክልል ወይም በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ብቻ የተወሰነ እንዳልሆነ በማስተማር ይቀጥላል። እንዲሁም በአንድ ትውልድ ውስጥ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በዓለም ሁሉ እና አዳምና ሔዋንን ተከትሎ በመጣው ትውልድ ሁሉ እየተስፋፋ የሚሄድ ነው። ምድር በሐጢአት የተሞላች ስለሆነ ማንም ከበሽታው ማምለጥ አልቻለም።

በዘመናችን የኃጢአት ውጤቶችን በተበላሹ ግንኙነቶች እና በሁሉም ዓይነት ወንጀሎች ውስጥ እንመለከታለን። በብክለት እና የተፈጥሮ አደጋዎች ውስጥ ስናልፍ በምድራችን ላይ ያለውን ተጽዕኖ እንመለከታለን። በሽታዎች በርካታ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች ሲያጠፉ ያለምንም እርዳታ ረዳት አልባ ሆነን

እንቆማለን። ከካንሰር ወይም ከኤድስ እንዲሁም ከመሳሰሉት በሽታዎች ጋር የምናደርገው ትግል ሞት በዙሪያችን እንዳለ ያሳያል።

በሕብረተሰባችን ውስጥ ካሉት ግልጽ የኃጢአት እና የሞት ምልክቶች አልፈን በልባችን እና አዕምሮአችን ላይ ያለውን ተጽዕኖ መመልከት አለብን። የኃጢአተኛ መንገዶች እና ልምምዶች መስህብ ይሰማናል። በየቀኑ ከኃጢአት አስተሳሰቦች ጋር እንታገላለን። ከፈጣሪያችን ጋር ባለን ግንኙነት የኃጢአትን ውጤት ማየት እንችላለን። እኛም ልክ እንደ አዳምና ሔዋን ሰዎች እርቃናችንን ሆነን እና ኃጢአተኛ በሆነው ማንነታችን እንዲያዩን እንደማንፈልግ ሁሉ ከእርሱ መደበቅ ይቀናናል። በውስጣችን ልክ እንደእርሱ ውርደት ይሰማናል።

ለእግዚአብሔር ሐጢኃት ሰርተን አናውቅም የምንል ማናችንም የለንም። ጳውሎስ ሁላችንም ኃጢአት እንደሠራን በግልጽ ተናግሯል (ሮሜ 5፡12) ። ኃጢአትና ሞት ከብበውናል። ኃጢአትና ሞት ይገልፁናል። ልክ እንደ ገዳይ በሽታ፣ኃጢአት እና ሞት ወደ እያንዳንዱ ወንድና ሴት ደርሷል - ማንም ከቁጣው አያመልጥም።

## *ሐጢአት ከሕግ በፊት በዓለም ውስጥ ነበር*

በሮሜ 5፡13 ላይ ጳውሎስ ሌላ ሁለት ጠቃሚ ዝርዝሮችን ያስታውሰናል። የመጀመሪያው ሕጉ ከሌለ ሰው ሕጉን መጣስ አይችልም። ሁለተኛው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ህግን ከመስጠቱ በፊት የአዳም ዘሮች በግላቸው ከተከለከለው ዛፍ ባይበሉም እንኳን የሞት ቅጣት ወርዶባቸዋል።

*13 ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም፤14 ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም*

*ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና። (ሮሜ 5)*

ይህ የጳውሎስ መግለጫ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አዳም ክላርክ በሮሜ 5፡13 ላይ በሰጠው አስተያየት የሚከተለውን ይላል፡

*(Ro 5:13) ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና-ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ስለነገሠ፤ኃጢአትም እንዲሁ ነበር። እንግዲህ ሕግ ከአዳም ጀምሮ ለሙሴ እስከተሰጠው የተጻፈው ሕግ ድረስ ስላልነበረ፤ያሸነፈው ያ ሞት፤ ሕግ መጣስ ሊሆን አይችልም፤ሐጢአት በጊዜአዊ ሞት ይቀጣ ዘንድ፤የሐጢአት ቅጣት ሞት እንደሆነ የሚሳየው ሕግ በሌለበት ኃጢአት ሆኖ አይቈጠርምና። ስለዚህ ሰዎች በግል መተላለፋቸው የተነሳ ለሞት ቅጣት ተላልፈው አይሰጡም፤ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምክንያት በዘራቸው የሞት እና መበስበስ ዘርን ይዘው የመጡ ሁሉ፤የሞራል ዝቅጠታቸው ተጨምሮበታል።ሁሉም ሐጢአተኛ ነው-ሁሉም ሞት ይገባቸዋል። (Clark, Adam, Commentary on the Bible by Adam Clark (1831), Commentary on Romans 5:13, Laridian: Marion, Iowa, 2015).*

አዳም ክላርክ እየነገረን ያለው በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። ጳውሎስ እንደነገረን ከአዳም እስከ ሙሴ ሞት ከነገሠ (እግዚአብሔር ሕጉን ከመስጠቱ በፊት) ያለብን እርግማን በግላችን ሕግን ባለመታዘዛችን እንዳልሆነ እንድንረዳ ያደርገናል። መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ ፍሬ በልተው የማያውቁት እንኳን በሕይወታቸው ውስጥ የኃጢአትና የሞት መዘዝ ደርሶባቸዋል። በእግዚአብሔር እርግማን ሥር ያለነው በምንሰራው ሥራ ሳይሆን ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ ተጽዕኖ ስላደረገብን እና የተፈጥሯችን አካል ስለሆነ ነው።

መዝሙረኛው ዳዊት በመዝሙር 51 ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፡

*5 እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ። (መዝሙር 51)*

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች እንዲህ በማለት ይናገራል፡-

*1 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ 2 በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። 3 በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። (ኤፌሶን 2)*

ሐዋርያው በኤፌሶን ለነበሩት ለእነዚህ አማኞች "በፍጥረት የቁጣ ልጆች" መሆናቸውን እንደነገራቸው አስተውሉ። የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ከእነርሱ ዘር በተወለዱት ሰዎች ሁሉ ላይ ተጽዕኖ ነበረው - ሁሉም የሚወለዱት በኃጢአተኛ ተፈጥሮ ነው። የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ እድል ሳላገኝ እንኳን በተፈጥሮዬ ኃጢአተኛ ነኝ። ሁላችንም በአዳም ኃጢአት እርግማን ሥር ነን። በኃጢአተኛ ተፈጥሮ እና በኃጢአት እና በሞት እርግማን ለመወለድ፤በግል ኃጢአት መሥራት አይኖርባችሁም።

## *አዳም ሊመጣ ለነበረው ምሳሌ ነው*

ጳውሎስ በተስፋ ቃል ይደመድማል። አዳም ሊመጣ ላለው አምሳሉ እንደሆነ ይነግረናል (ቁጥር 17) ። አዳም የሚወክለው ማንን ነው? እርሱ ከጌታ ኢየሱስ በቀር ማንንም አይወክልም። ኃጢአትን ወደ ዓለም ያመጣው ሰው እንዴት የኢየሱስ ምሳሌ ሊሆን ይችላል? ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ በሚቀጥለው ክፍል ይመልሳል። እዚህ ላይ በአዳምና በክርስቶስ መካከል ያለው ንጽጽር፤አንዱ ንጽጽር ነው ብሎ መናገር በቂ ነው። አዳም በኃጢአት ወክሎናል። ኢየሱስ ደግሞ በድነት ወክሎናል።

በአንድ ሰው አማካኝነት ኃጢአት ወደዚህ ዓለም ገባ። በሌላኛው ሰው ደግሞ ኃጢአት ይሸነፋል። በዚህ ጥናት ውስጥ ይህንን በጥልቀት እንመረምራለን።

ጳውሎስ በዚህ ጥቅሶች ውስጥ የሰው ልጅን ሁለንተናዊ ችግር ያስመለክታል። ኃጢአት ወደዚህ ዓለም የመጣው በአዳምና በሔዋን በኩል ነው። ያ ኃጢአት ፍጥረታትን ሁሉ ነክቶ ወደ ሰው ሁሉ ደረሰ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እያንዳንዱን ትውልድ ይነካል። ሁሉም የሚወለዱት በኃጢአት እና በሞት እርግማን ሥር ስለሆነ አዳኝ ያስፈልጋቸዋል። እግዚአብሔርን ባለመታዘዜ ምክንያት ኃጢአተኛ አልሆንኩም፤ኃጢአተኛ የሆንኩበት ምክንያት የኃጢአት ተፈጥሮን ስለወረስኩ ነው። የሚጣስ ሕግ ባይኖርም እንኳን በኃጢአትና በሞት እርግማን ሥር እሆናለሁ። በዚህ ምድር ላይ የሚወለዱ ልጆች ሁሉ ከዚህ እርግማን የሚያድናቸው አዳኝ ያስፈልጋቸዋል።

ጳውሎስ እዚህ ላይ የገለጸው እውነት በዘመናችን ብዙ ተቀባይነት ያገኘ አይደለም። የሰው ልጆች መልካም እና ንጹህ ስለመሆናቸው ማመን እንወዳለን። መልካም ነገሮችን መድረግ እንደምንችል ምንም አያጠያይቅም። ዳሩ ግን ይህ በኃጢአትና በሞት እርግማን ውስጥ የመወለዳችንን እውነታ አይለውጠውም፤ስለሆነም እርግማኑ እስኪወገድ ድረስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማየት አንችልም። ከዚህ እርግማን እና ከተወለድንበት ኃጢአተኛ ተፈጥሮ የሚያድነን ሁላችንም አዳኝ እንፈልጋለን። በፍጥረት እና በመወለድ ኃጢአተኞች መሆናችንን እስክንቀበል ድረስ የመዳን ፍላጎታችንን አንረዳም። ለሐዋርያው ጳውሎስ መነሻው ይህ ነበር።

ጳውሎስ በሮሜ 5፡12-14 የሚነግረን ለክርስቲያን ሕይወት አስፈላጊ ከሆኑ እውነቶች አንዱን ነው። የአዳም ኃጢአት ሁላችንንም ይነካል። ከኃጢአትና ሞት እርግማን ሥር ስለሆንን ከእግዚአብሔር ተለይተናል። ይህን የሰው ልጅ ሁለንተናዊ ችግር እስክንቀበል ድረስ፣ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣበትን ምክንያት ሙሉ በሙሉ አናመሰግንም።

**ለምልከታ:**

*ኃጢአት ወደ ዓለም እንዴት ገባ?*

*ኃጢአት በሥጋዊ ፍጥረት፣በግላዊ ግንኙነቶች እና በአዳምና በሔዋን ሕይወት ላይ ምን ተጽዕኖ አሳደረ?*

*በግል ሕይወታችሁ እና በማህበረሰባችሁ ውስጥ ምን አይነት የኃጢአት ውጤቶችን ትመለከታላችሁ? በመልሳችሁ ውስጥ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝን ብቻ ሳይሆን ኃጢአት በሰውነታችሁ እና በአዕምሯችሁ ላይ ስላለው ተጽዕኖ አስቡ።*

*የእግዚአብሔርን ሕግ የተላለፍን ባንሆንም ኃጢአተኞች ልንሆን እንችላለን? ኃጢአተኛ መሆን እኔ በምሠራው ተግባሬ ላይ የተመሰረተ ነው ወይስ በእኔ ተፈጥሮ እና ውልደት ላይ የተመሰረተ ነው?*

*በፍጥረት ኃጢአተኞች መሆናችንን መረዳት አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? በዘመናችን ይህ እውነት በጣም ተወዳጅ ያልሆነው ለምንድን ነው?*

**ለጸሎት:**

*በፍጥረታችሁ ኃጢአተኛ መሆናችሁን ለመቀበል ትህትና እንዲሰጣችሁ ጌታን ጠይቁ።*

ሐጢአት በዚህ ምድር እና በውስጧ ያለውን ሕይወት የነካ ቢሆንም፣ዳሩ ግን ተስፋ በሚሰጠን በጌታ በኢየሱስ ማንነት መፍትሄ ስላለ ጌታ አመስግኑ።

አዳኝ የሚያስፈልጋቸው ኃጢአተኞች የመሆናቸውን ዓለም አቀፋዊ እውነትን መቀበል ለማይፈልጉት፤ጊዜ ወስዳችሁ ጸልዩላቸው። ጌታ ይህንን እውነት እንዲገልጥላቸው እና በእርሱ ያለውን መፍትሄ እንዲገልጥላቸው ጠይቁ።

ሁላችንም በሕብረተሰባችን አዕምሮ እና ልብ ውስጥ ኃጢአተኞች የመሆናችንን ይህንን እውነት እንዲያድስልን ጌታን ጠይቁ። ቤተክርስቲያናችሁ እና ማህበረሰባችሁ ይህንን እውነት ይረዱ እና ይቀበሉ ዘንድ ወደ አዳኙ እና ተስፋው ይመለሱ ዘንድ እንዲረዳቸው ጠይቁ።

## ምዕራፍ 2 -

## ነጻ ስጦታ

---

ሮሜ 5:15-17

ሐዋርያው ጳውሎስ የሮሜን ሰዎች የኃጢአት ችግር እና እርግማንን በማስታወስ እግዚአብሔር በስጦታ መልክ መፍትሔ እንዳለው ለሮም ክርስቲያኖች ይነግራቸዋል።

*15 ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ። 16 አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደ ሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም፤ ፍርድ ከአንድ ሰው ለኵነኔ መጥቶአልና፥ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ። 17 በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።*

### *ነጻ ስጦታ*

በመጀመሪያ ይህ ስጦታ ነጻ እንደሆነ አስተውሉ። እዚህ ላይ ሐዋርያው *“ካሪስማቶስ”* የተሰኘውን የግሪክ ቃል ይጠቀማል። ይህ ቃል የመጣው "ቻሪስ" ከሚለው ቃል ነው. የAMG

የተሰኘው ሙሉ የቃል ጥናት መዝገበ ቃላት “ቻሪስ” ን እንደሚከተለው ይገልፃል።

*መመለሱን ሳንጠብቅ የተደረገ ውለታ፡ ለሰዎች ሁሉ የሆነ የእግዚአብሔር ፍጹም እና በፍቅር የተሞላ ቸርነት የተገለጠበት እንዲሁም በሰጪው ችሮታ እና በጎነት ላይ ብቻ የተመሰረተ እና በሥራ ያልተገኘ እና ለተቀባዩ የማይገባ ሞገስ ጸጋ ነው። (Zodhiates, Spiros (ed.), Baker, Warren (ed.), Hadhiantoniou, George (ed.), AMG Complete Word Study Dictionary, New Testament. “Charis,” Cedar Rapids: Laridian.)*

ስጦታ በምንም መልኩ ልንገዛው ወይም በሥራ ልናገኘው የማንችለው ነገር ነው። የገዛነው ከሆነ ስጦታ አይሆንም። በዚህ ጉዳይ ላይ ጳውሎስ የተናገረለት ስጦታ በኃጢአትና በሞት እርግማን ለሚሰቃዩ ሰዎች ’የእግዚአብሔር የፍቅር እና በጎነት ነጻ ስጦታ የተገለጠበት’ ነው። በስጦታው ማድረግ የምትችሉት ብቸኛው ነገር መቀበል ነው። ለእሱ መክፈልም ሆነ ለእሱ ምንም ማድረግ አይጠበቅባችሁም - ሄዳችሁ መውሰድ ብቻ ያስፈልጋችኋል።

### *ስጦታው እንደበደሉ አይደለም*

ሐዋርያው በቁጥር 15 ላይ እግዚአብሔር ያቀረበውን ስጦታ እና በጎነት ከአዳምና ከሔዋን ኃጢአት ጋር በማነጻጸር ይቀጥላል፡

*15 ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ። (ሮሜ 5)*

በአንድ ሰው (አዳም) ኃጢአት ብዙ ሰዎች በሞት እርግማን ውስጥ ወድቀዋል። እንዲገባ ፈቃድ የተሰጠው ኃጢአት ምድርን እና በእርሷ ውስጥ የተወለዱትን የሰው ልጆች ሁሉ አጠፋ። ዓለም አቀፋዊ መዘዝ አስከትሏል። ይሁን እንጂ

ሐዋርያው በመቀጠል እግዚአብሔር ያቀረበው ነጻ ስጦታ "ለብዙዎች በዝቶላቸዋል" በማለት ለሮም ክርስቲያኖች ያስረዳቸዋል።

ጳውሎስ በአዳም ኃጢአት ምክንያት "ብዙ ሰዎች" እንደሞቱ ለሮሜ ሰዎች ያስታውሳቸዋል። ዳሩ ግን ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ሰውን እና ኃጢአት ያበላሸውን ነገሮች ሁሉ የመንካት አቅም አለው። እንዲያውም ጳውሎስ በአዳም ኃጢአት ለተጎዱ ሰዎች ሁሉ ስጦታው 'እንደሚበዛ' ለሮሜ ሰዎች ይነግራቸዋል።

የተትረፈረፈ የሚለው ቃል ከመጠን በላይ ማግኘትን እና ከሚያስፈልገው በላይ የመጨመር ስሜትን ይይዛል። በሌላ አነጋገር ስጦታው ከሞት እርግማን ይበልጣል። በኃጢአት እና በሞት የተረገመው ሰው ከሚጠበቀው በላይ ያሟላል። አትረፍርፎ ይሞላቸዋል እንዲሁም በብዛትም ያፈስባቸዋል።

በቁጥር 15 ላይ ደግሞ ኃጢአት በአንድ ሰው በኩል እንደ መጣ እንዲሁ እግዚአብሔር ሊሰጠው የሚፈልገው የጸጋ ስጦታ በአንድ ሰው በኩል እንደሚመጣ አስተውሉ። ኃጢአት ወደ ዓለም የገባው በአዳም በኩል ነው፣ስጦታው ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው።

### *የነጻ ስጦታው ውጤት*

ጳውሎስ የአዳምን ኃጢአት እና የክርስቶስን ስጦታ ውጤት ለማነጻጸር በቁጥር 16 ይቀጥላል፡

*16 አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደ ሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም፤ ፍርድ ከአንድ ሰው ለኵነኔ መጥቶአልና፥ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ። (ሮሜ 5)*

የአዳም ኃጢአት ምን ውጤት አስከተለ? ጳውሎስ “አንድ በደል ያስከተለው ፍርድ ኩነኔን አመጣ” (ሮሜ 5:16) ይለናል። የሰው ልጅ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ተለይቶ በሞት እርግማን ሥር ወደቀ።

ነገር ግን አብ በልጁ በኢየሱስ በኩል የሚሰጠው ስጦታ ጽድቅን አመጣ። መጽደቅ በእግዚአብሔር ፊት የጽድቅ ቁመና መያዝ ወይም የጽድቅ መግለጫ ነው። ኢየሱስ ያመጣው ስጦታ የኩነኔ ፍርድን እና ከእግዚአብሔር ጋር የነበረንን ዘለዓለማዊ መለያየትን የሚሽር ነው። ከአብ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንድንፈጥር አድርጎናል። ከኃጢአትና ከሞት ዘላለማዊ መዘዞች ነፃ እንድንወጣ ቅጣቱን በከፈለው በጌታ በኢየሱስ ሥራ በኩል ቀርቦልኛል።

## *የጽድቅ ስጦታው*

ሞት በአንድ ሰው ኃጢአት ምክንያት ሲነግስ፣ጳውሎስ በቁጥር 17 ላይ የክርስቶስን ስጦታ የተቀበሉ የእግዚአብሔርን ጸጋ እና ጽድቅ እንደሚለማመዱ ይነግረናል፡-

*17 በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ። (ሮሜ 5)*

እዚህ ቁጥር 17 ላይ፣ ጳውሎስ ስለዚህ የእግዚአብሔር ስጦታ አንድ ነገር ይነግረናል። ያም “የጽድቅ ስጦታ” ነው። ጽድቅ ምንድን ነው? ጽድቅ ከትክክለኛና ከመልካም ነገር ጋር ይዛመዳል። ፃ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ፊት ጥፋት የሌለበት ወይም ያልወደቀን ሰው ነው። ይህ ፍቺ ወዲያውኑ ችግር ይፈጥርብናል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ጥፋት ወይም ውድቀት የለብንም እንዴት ሊባል ይችላል? ጳውሎስ ራሱ በሮሜ 3 ላይ እንዲህ ይላል።

*10 እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፦ 11 ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ*

*የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥12 በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም። (ሮሜ 3)*

የአዳም ኃጢአት ችግር እያንዳንዱ ልጅ በኃጢአተኛ ተፈጥሮ እና በእግዚአብሔር እርግማን እንዲወለድ ምክንያት ሆኗል። ማንም ጻድቅ ሆኖ አልተወለደም። የጽድቅ ስጦታ የሚሠራው በዚህ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ኃጢአታችንን ሁሉ ይሸፍናል እናም በአብ እና በእኔ መካከል ያለውን ማንኛውንም እንቅፋት ያስወግዳል። ጻድቅ የተባልኩት ኃጢአትን ስላላደረግሁ ሳይሆን፣ ኃጢአቴ ሁሉ በኢየሱስ ሥራ ስለተከፈለ እና ስለተሰረየልኝ ነው። አሁን በእኔና በእግዚአብሔር መካከል የሚቆም ነገር የለም።

አሁን እዚህ ላይ ልንመለከተው የሚገባን አስፈላጊው ነገር በዚህ የጽድቅ ስጦታ ምክንያት አሁን ፍጹም ነኝ ማለት አይደለም። በእርግጥ ከፍጹምነት በጣም የራቅሁ ነኝ። የዚህን ማስረጃ በሕይወቴ አያለሁ። አሁንም ከኃጢአት ሃሳቦች እና አመለካከቶች ጋር እታገላለሁ። አሁንም የሰማዩን አባቴን የሚያሳዝኑ ነገሮችን አደርጋለሁ። እንግዲህ ፍጹም ካልሆንኩ የጽቅን ስጦታ ተቀብያለሁ ማለት እንዴት ይቻላል?

ይህንን ለመመለስ ወደ ብሉይ ኪዳን ዘጸአት መጽሐፍ እንመለስ። በዘጸአት 12 ላይ እግዚአብሔር በግብፅ ህዝብ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ለማምጣት እንዴት እንደተዘጋጀ እናነባለን- ያም የበኩር ልጅ ሞት ነው።

መላው ሃገሩ በሞት እርግማን ሥር ነበር። በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን በግብፅ ይኖሩ ነበር። ለዚህ አስፈሪ ሌሊት ሲዘጋጁ፣ሙሴ የእግዚአብሔርን ህዝብ ጠቦት እንዲያርዱ አዘዛቸው። የዚህን በግ ደም ወስደው በቤታቸው መቃን ላይ ይቀቡ ነበር። መልዓክ ሞት ሕዝቡን አልፎ በቤታቸው መቃን ላይ የተቀባውን ደም ሲያይ የበኩር ልጃቸውን ከሞት ፍርድ ያድነው ነበር። ህዝቡን ከፍርድ ያዳነው የበጉ ደም

ነው። ይህ ያረዱት በግ “ነውር የሌለበት” (ዘጸአት 12፡5) እንደሆነ ሙሴ ለሕዝቡ ግልጽ አድርጓል። የሞት መልዓክ ያላጠፋቸው በዚህ “ነውር የሌለበት” በግ ምክንያት ነው።

በዚያ ቤት ቅጥር ውስጥ የሚፈሩ ሰዎች ነበሩ። እነዚሁ ሰዎች የእግዚአብሔርን ትዕግስት የተፈታተኑ በምድረ በዳ የሚያጉረመርሙ እና የሚያማርሩ ናቸው። በእግዚአብሔር ላይ በማመፃቸው ምክንያት በዚያ ምድረ በዳ ይጠፋሉ። መልዓከ ሞት በላያቸው ሲያልፍ ህዝቡን ያዳናቸው ምን ነበር? በራሳቸው ፍጹማን ወይም ጻድቅ መሆናቸው አልነበረም። ፍጹሙ በግ ስለተሠዋና ደሙ ስለጠበቃቸው ነው።

በተመሳሳይም ጌታ ኢየሱስ ፍጹም የእግዚአብሔር በግ ነው። ስለ እኛ ነፍሱን በመስቀል ላይ አሳልፎ ሰጠ። የፍርዱ ቀን ሲመጣ መልዓከ ሞት በላያችን ሲያልፍ ከእግዚአብሔር ቁጣ እንዲያድነን ሞተ። እኛ ፍጹማን አይደለንም ነገር ግን በግብፅ እንደነበሩት የእስራኤል ሰዎች በፍጹሙ በግ ደም ተሸፍነናል። ጳውሎስ እዚህ እየተናገረ ያለው ጽድቅ፤ነውር የሌለበት በግ ጽድቅ ነው - እርሱም ጌታ ኢየሱስ ነው። የሸፈነን ጽድቁ ነው። ከሞት እርግማን ነፃ የወጣነው ፍጹማን በመሆናችን ወይም ያለ ነቀፋና ነውር የሌለን በመሆናችን ሳይሆን ጥፋትና ነውር የሌለበት የኢየሱስ ጽድቅ ስለሸፈነን ነው።

የዚህ እውነት አንድምታ የሚከተለው ነው፡ በዚህ ዓለም ፍፁም አትሆኑም። ሁልጊዜ በልባችሁ ከኃጢአት ጋር ትታገላላችሁ። መመዘኛዎቹን ሁሉ አሟልታችሁ በእግዚአብሔር ፊት መቆም በራሳችሁ ብርታት በፍፁም አትችሉም። እኔና እናንተ ያለን ብቸኛ ተስፋ እድፍ በሌለው በግ ደም መሸፈን ነው። ልክ እንደ እስራኤላውያን፣እናንተም እምነታችሁን በእግዚአብሔር በግ ላይ ማድረግ አለባችሁ። እሱ ብቻ ጻድቅ ነው—ስራው ብቻውን ሊሸፍናችሁ እና ሊጠብቃችሁ ይችላል።

### ***ሥጦታውን መቀበል***

እዚህ ምንባብ ውስጥ ልናስምርበት የሚገባን አንድ ተጨማሪ ነጥብ አለ። ሐዋርያው ለሮሜ ሰዎች በቁጥር 17 ላይ የነገራቸውን አስተውሉ።

*17 … ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ። (ሮሜ 5)*

እዚህ ልንመለከተው የሚገባን ሁለት ነጥቦች አሉን።

በመጀመሪያ፣የጽድቅ ስጦታ "በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ" በኩል እንደሚነግሥ አስተውሉ። በሌላ አነጋገር፤ከእርሱ በቀር ጽድቅ ሊኖር አይችልም። በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ያለኝ ድፍረት ሙሉ በሙሉ በጌታ በኢየሱስ ሥራ ላይ የተመሰረተ ነው። የራሴ የምለው ጽድቅ የለኝም። በእግዚአብሔር ፊት ያለ በደል ልሆን አልችልም። የተወለድኩት በኃጢያት ነው ስለሆነም ከእርሱ የጽድቅ ክብር ጎድያለሁ። የእኔ ብቸኛው ተስፋ የኃጢአቴን ክፍያ እና ዕዳ በሚሸፍነው በኢየሱስ ሥራ ላይ ነው። ወደ ራሴ መመልከት ስለማልችል በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የመሆን ተስፋን አገኛለሁ። ትኩረቴ በክርስቶስ በአብ ዘንድ ያለው ትክክለኛ የጽድቅ አቋም፤ፍጹም ስራው እና መስዋዕቱ ላይ መሆን አለበት። የሸፈነኝ የክርስቶስ ሥራ ነው። ተስፋዬ የእርሱ ጽድቅ ብቻ ነው። በሕይወቴ ውስጥ ጽድቅ ሊነግሥ የሚችለው "በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ" በኩል ብቻ ነው።

ሁለተኛ፣ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ይህ ጽድቅ "እጅግ የበዛውን የጸጋውን ነጻ ስጦታ በሚቀበሉ" ሕይወት ውስጥ እንደሚነግስ ይነግራቸዋል። ይህን ነጻ ስጦታ ከፈለጋችሁ ከክርስቶስ መቀበል አለባችሁ። ይህን ልንቀበለው የሚገባን የጽድቅ ስጦታ የእኛ እንዳልሆነ ያሳያል። ለእኛ የተሰጠን ነው። ብዙዎች ይህን ስጦታ አይቀበሉትም ምክንያቱም እንደሚያስፈልጋቸው አልተመለከቱምና። አሁንም በራሳቸው ጥረት ፍጹም እና ያለ ነውር መሆን እየሞከሩ ነው።

ይህንን የጽድቅ ግዛት ለማወቅ ብቸኛው መንገድ ከክርስቶስ መቀበል ነው። ይህ ማለት በራሳችሁ ያለ ነውር መሆንን ማግኘት እንደማትችሉ ማወቅ ማለት ነው። ይህ ማለት በውድቀታችሁ እንደምትቀጥሉ መረዳት ማለት ነው። ተስፋችሁ ጌታ ኢየሱስ ጥበቃችሁ እንዲሆን መፍቀድ ብቻ ነው። እንደ ፍፁም በግ ነፍሱን ስለ እናንተ መስዋዕት አድርጎ አቀረበ። ደሙ የነፍሳችሁን መቃን ይሸፍናል። ይህ የክርስቶስ መስዋዕትነት ተስፋችሁ እና መተማመናችሁ ነው። እናንተ በራሳችሁ ፍጽምና የጎደላችሁ ሆናችሁ በአብ ፊት ትቆማላችሁ ነገር ግን ፍጹም እና ጻድቅ በሆነው ተሸፍናችኋል።

**ለምልከታ**:

የጽድቅ ስጦታ ከአዳም ኃጢአት እንዴት ይበልጣል? የነጻ ስጦታው ውጤት ምንድን ነው?

መጽደቅ ምንድን ነው? ጸድቀናል ማለት ኃጢአት ሠርተን አናውቅም ማለት ነውን?

ጻድቅ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ማንም በራሱ ጥንካሬ እና ጥረት ጻድቅ ሊሆን ይችላልን?

የብሉይ ኪዳን የፋሲካ ታሪክ ጽድቅን እንዴት ያሳያል? በዚህ ታሪክ ውስጥ ያለ ጥፋት የነበረው ማን ነው?

የጽድቅን ስጦታ የተቀበሉ አሁንም ኃጢአትን ያደርጋሉን?

ፍጹምና ጻድቅ በሆነው የእግዚአብሔር በግ መሸፈን እና በራሳችን ፍጹም ለመሆን በመሞከር መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

የጽድቅን ስጦታ መቀበል ማለት ምን ማለት ነው?
ይህን ስጦታ እንዴት ትቀበላላችሁ?

**ለጸሎት:**

በኃጢአትና በሞት ኩነኔ ሥር ሳለን እግዚአብሔር ፍጹምና ጻድቅ በሆነ ልጁ በኩል መፍትሔ ስለሰጠን እግዚአብሔርን አመሰግኑ።

እኛ ፍጹማን ባንሆንም፣ልጁ ለእኛ ፍጹም መስዋዕት ነበር ስለሆነም እሱን እና በእነሱ ፈንታ የሰራውን ሥራ የሚቀበሉትን ሁሉ ኃጢአት ስለሚሸፍን ጌታን አመስግኑት።

እንደ ኃጢአተኛ ለእናንተ ስላደረገው ሥራ ጥልቅ አድናቆት እና ምስጋና እንዲሰጣችሁ ጌታን ጠይቁት።

አሁንም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ለመሆን እና በመልካም ሥራቸው መዳናቸውን ለማግኘት የሚጥሩ ሰዎችን ታውቃላችሁን? እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ትንሽ ጊዜ ወስዳችሁ ከክርስቶስ ሥራ ውጪ፣ ምንም ተስፋ እንደሌላቸው ያዩ ዘንድ ጸልዩላቸው።

## ምዕራፍ 3 -

## አንድ ሥራ

---

ሮሜ 5:18-21

*18 እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። 19 በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። 20-21 በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ፤ ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፥ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ። (ሮሜ 5)*

የአንድን ሥራ ወይም ውሳኔ አስፈላጊነት መሳት ቀላል ነው። በተሳሳተ ጊዜ የሚደረግ የተሳሳተ እርምጃ በህይወት እና በሞት መካከል ያለውን ልዩነት ሊያመለክት ይችላል። መጥፎ ምርጫ ማለት ለዓመታት ደስተኛ የሆናችሁበትን ግንኙነት ማቋረጥ ማለት ነው። አንድ ጥንቃቄ የጎደለው ቃል በአንድ ትንሽ ልጅ ሕይወት ላይ የዕድሜ ልክ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። እነዚህ የተሳሳቱ ድርጊቶች እና ቃላቶች ህይወታችሁን ብቻ ሳይሆን በዙሪያችሁ ያሉትን ሊጎዱ ይችላሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ ሰው በኤደን ገነት ውስጥ ስላደረገው ነጠላ ድርጊት የሚነግረንን ተመልከቱ፡

*18 እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ (ሮሜ 5)*

አንድ በደል ሰዎች ሁሉ እንዲፈረድባቸው አድርጓል። አዳም አሰቃቂ በሽታ ወደ ገነት እንዲገባ በር ከፈተ። አለመታዘዙ ኃጢአትን ወደ ዓለም አመጣ። ያም ኃጢአት ሞትን እና ከእግዚአብሔር መለየትን በማምጣት ምድርን አጠፋት።

የአንድን ሰው ቤት የመቆጣጠር ኃላፊነት እንደተሰጣችሁ አስቡ። ባለቤቱ በማይኖርበት ጊዜ በሩን ቆልፎ መያዝ እና ማንም እንዳይገባ ማድረግ አለባችሁ። በሩ ላይ ቆማችሁ በንቃት እየጠበቃችሁ ሳለ፣ሲንኳኳ እና ከውጭ የመጣ ድምጽ በሚፈትን እና በሚያባብል ቃላት ሲናገር ሰማችሁ እንበል። "በሩን ትንሽ እንኳን መክፈት ምን ጉዳት አለው?" በእነዚህ ቃላት ተፈትናችሁ፤በሩን በትንሹ ከፍታችሁ በስንጥቅ ውስጥ ትመለከታላችሁ። ቀጥሎ የምታውቁት ነገር፤በሩ በኃይል ተገፍቶ ውጭ ያለው ሰው በፍጥነት ወደ ውስጥ በመግባት ቤቱን ይቆጣጠራል። ይህ ሁሉ የሆነው በሩ በትንሹም ቢሆን በመከፈቱ ነው። አንድ ቀላል አለመታዘዝ ሁሉንም ነገር ለወጠው። አዳም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመናቅ የኃጢአትን በር በከፈተ ጊዜ ጠላት በቤቱ ውስጥ ላለው ሰው ሁሉ ኃጢአትንና ሞትን በማምጣት ገፍቶ ገባ።

ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ ድርጊት በሁሉም ላይ ፍርድ እንደሚያመጣ ሁሉ፤ሌላው ድርጊት ደግሞ በዚህ ፍርድ ሥር ያሉትን ሁሉ ሕይወት እንደሚሰጥ ለሮሜ ሰዎች በመናገር ይቀጥላል።

*18 ... እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። (ሮሜ 5)*

ጳውሎስ ሰውን ሁሉ ወደ ጽድቅ እና ሕይወት ስለሚመራው የጽድቅ ሥራ ይናገራል። እስቲ ይህን የጳውሎስን መልዕክት ከፋፍለን እንመርምር። ጳውሎስ ስለ መጽደቅ ይናገራል። መጽደቅ ወደ እግዚአብሔር በድፍረት መግባት ማለት ነው። ይህ መልዕክት የመጣው ጳውሎስ የአንድ ሰው ኃጢአት ኵነኔን

እንዳመጣ ለሮሜ ሰዎች ሲናገር ነው። ይህ ኩነኔ ሊቀለበስ እንደሚችል ሐዋርያው እየነገረን ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ በድፍረት መግባትን ልናገኝ እንችላለን።

በተጨማሪም ጳውሎስ ሕይወትን መለማመድ እንደምንችል እንደነገረን አስተውሉ። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ የኃጢአትን በር በከፈቱ ጊዜ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ የሞትን እርግማን አመጡ። ያ እርግማን በሰው ልጆች ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የፍጥረት ክፍል ላይ አካላዊ ሞትን አመጣ። ይሁን እንጂ አካላዊ ሞት የችግሩ አንዱ አካል ብቻ ነበር። ኃጢአት መንፈሳዊ ሞትንም አምጥቷል። አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነት ፈርሷል። ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የመፍጠር ችሎታቸውን ገፈፋቸው። በኀፍረትና በፍርሃት ከእግዚአብሔር ዘንድ ተሸሸጉ።

ጳውሎስ በሮሜ 5፡18 ላይ እንደገና በእግዚአብሔር ፊት በድፍረት መግባት እንዲኖረን ብቻ ሳይሆን በኃጢአት ምክንያት የተገፈፈብንን ሕይወት መልሰን ማግኘት እንደምንችል ይነግረናል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ሊታደስ ይችላል። በእግዚአብሔር ፊት የዘላለም ሕይወትን ማግኘት እንችላለን። ከፈጣሪያችን ጋር እንደገና የጠበቀ እና አስደሳች ህብረት ሊኖረን ይችላል። የኃጢአትና የሞት ፍርድ ሊወገድ ይችላል።

ይህ ሕብረት እንዴት ሊታደስ ይቻላል? ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ የዓመፅ ድርጊት በኃጢአትና በሞት እርግማን ላይ እንድንወድቅ እንዳደረገን ሁሉ፤አንድ የጽድቅ ሥራም ወደ መጽደቅና ወደ ሕይወት እንደሚመራ ይነግረናል።

አዳም በሩን ስለከፈተ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ። ኃጢአተኛ ለመሆን ምንም አላደረግኩም። የተወለድኩት በዚህ መንገድ ነው። በተፈጥሮዬ ከእግዚአብሔር የተለየሁ እና አዳኝ የሚያስፈልገኝ ነበርኩ። ኃጢአተኛ ሆኜ ስለ ተወለድኩ እንደ ተፈጥሮዬ ተመላልሻለሁ።

ጳውሎስ አዳም የኃጢአትን በር የከፈተበት አንድ ድርጊት ከእግዚአብሔር እንደለየን ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስም ሥራ ወደ ህብረት ሊመልሰን እንደሚችል ይነግረናል። ይህ የኢየሱስ ድርጊት “የጽድቅ ሥራ” ነው። ጳውሎስ እዚህ ላይ እየጠቀሰ ያለው ሥራ የጌታ ኢየሱስን ሞትና ትንሣኤ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ የሚያደርገን እና ወደ ሕይወት የሚመልሰን ይህ ሥራ ብቻ ነው።

ጳውሎስ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ያተኮረበት 'አንዱ ሥራ' ማለትም ኃጢአተኞች እንድንሆን ባደረገን እና ወደ ሕይወት በሚመልሰን አንድ ሥራ ላይ ነው። በሕይወታቸው አንድ ጊዜ ኃጢአት ስለሠሩ ኃጢአተኞች እንደሆኑ የሚያምኑ አሉ። የመጀመሪያውን ኃጢአት እስኪሠሩ ድረስ ኃጢአት የሌለባቸው እንደሆኑ አድርገው ያስባሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተማረው ይህን አይደለም። ኃጢአት የምንሠራው ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ስላለንና ኃጢአተኞች በመሆናችን ነው እያለ ነው። የመጀመሪያውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ከመስራታችን በፊትም ኃጢአተኞች ነን። አዳም የኃጢአትን በር ስለከፈተ፣ ያ ሥራ እያንዳንዳችንን ነካ፤ስለዚህ ኃጢአተኞች ሆነን ተወለድን። በአንዱ የአዳም ሥራ ኃጢአተኞች ነን።

በተመሳሳይ፣ ጳውሎስ እንደጻደቅን እና በአንድ የጽድቅ ሥራ ማለትም በክርስቶስ የመስቀል ሞት አማካይነት ሕይወት እንደተሰጠን ይነግረናል። ኃጢአተኛ የሚያደርገኝ እኔ የምሰራው እንዳልሆነ ሁሉ በሕይወቴ ላይ የኃጢአትንና የሞት እርግማንን የሚያስወግድልኝ የምሰራው ሥራ አይደለም። መልካም ኑሮ ከኖሩ እና እግዚአብሔርን ለማስደሰት የተቻላቸውን ሁሉ ካደረጉ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆኑ እና መዳን ይገባቸዋል ብለው የሚያምኑ አሉ። አሁንም፣ ጳውሎስ ይህ እንዳልሆነ ይነግረናል። ተስፋችን በምናደርጋቸው በርካታ ተግባራት ሳይሆን ክርስቶስ ባደረገው አንድ የጽድቅ ሥራ ላይ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ያለን ብቸኛ እምነት ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባደረገው አንድ ሥራ ነው። የእሱ ሞት ብቻ በሕይወታችን ላይ ያለውን እርግማን ይቅር ማለት እና ማስወገድ ይችላል። አዳም በሠራው ሥራ ኃጢአተኞች እንደሆንን ሁሉ ክርስቶስም ባደረገው ሥራ ይቅር

እንባላለን፡፡ ጳውሎስ በቁጥር 19 እንዲህ ሲል አጽንዖት ይሰጠዋል፡፡

*19 በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ፡፡*

ይህም ተስፋችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ላይ ያደርገዋል፡፡ በእርሱ እና በመስቀሉ የሞት መስዋዕት በቀር የመዳን ተስፋ ሊኖረኝ አይችልም፡፡ እግዚአብሔር የመዳን እና የይቅርታ ማረጋገጫዬ እንዲሆን ያለኝን ወይም የማደርገውን ማንኛውንም ነገር መመልከት አልችልም፡፡ የኢየሱስ ሞት ብቻውን በቂ ነው፡፡ ሌላው ጥረት ሁሉ ዋጋ ቢስ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት በትክክል መቆም ከፈለግን 'በአንዱ የጽድቅ ሥራ' ባደረገው ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን፡፡

የዚህን የክርስቶስን ሥራ አስፈላጊነት ለማጉላት፣ ጌታ የብሉይ ኪዳንን ሕግ ሰጥቷል፡፡ ይህ ሕግ ነፍስን ማዳን ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ወደሚሆን ትክክለኛ ህብረት ውስጥ ሊያስገባ በፍፁም አይችልም፡፡ የሕጉ ዓላማም ይህ ነበር፡፡ በወንዶችና በሴቶች ልጆች ፊት የእግዚአብሔርን መስፈርት በማስቀመጥ፣በጥረታቸው ፈጽሞ መመዘን እንደማይችሉ አሳይቷቸዋል፡፡

ዘሌዋውያን 11 በእግዚአብሔር ፊት ንጹህ መሆንን በተመለከተ የሚሰጠውን ትምህርት ተመልከቱ፡

*23 ነገር ግን የሚበርር፥ አራትም እግሮች ያሉት ተንቀሳቃሽ ሁሉ በእናንተ ዘንድ የተጸየፈ ነው፡፡ 24 በእነዚህም ርኩስ ትሆናላችሁ፤ የእነርሱንም በድን የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ ርኩስ ነው፡፡ 25 ከእነርሱም በድን የሚያነሣ ሁሉ ልብሱን ይጠብ፥ እስከ ማታም ርኩስ ነው፡፡ ዘሌዋውያን 11*

አንዳንድ ነፍሳትን መንካት እንኳን ያረክሰናል ስለዚህም ከእግዚአብሔር ጋር መለየትን ያመጣል፡፡ ተፈጥሯዊ የሕይወት ክፍል የሆኑት እነዚህ ነገሮች እንኳን አንድን ሰው ያረክሳሉ፡፡ ወንድ ልጅ የወለደች ሴት ለሰባት ቀን ርኩስ

ትሆናለች (ዘሌዋውያን 12፡2)። ርኩስ ከሆነችበት ሰባት ቀን በኋላ ለመንጻት ሌላ 33 ቀናት ትጨምራለች። ህጉ ስለዚህ የሠላሳ ሦስት ቀናት ጊዜ የሚለውን ተመልከቱ፡-

*4 ከደምዋም እስክትነጻ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ የመንጻትዋ ቀንም እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰን ነገር አትንካ፥ ወደ መቅደስም አትግባ። 5 ሴት ልጅም ብትወልድ እንደ መርገምዋ ወራት ሁለት ሳምንት ያህል የረከሰች ናት፤ ከደምዋም እስክትነጻ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ። (ዘሌዋውያን 12)*

በዚህ የመንጻት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ሕግ ሴቲቱ ወደ መቅደሱ መቅረብ እንደሌለባት ይናገራል። ሴት ልጅ ከወለደች ሴትዮዋ እስክትነጻ ድረስ ከሁለት ወር በላይ ወደ ድንኳኑ አትቅረብም!

በዘፀአት 19 ላይ እግዚአብሔር ሙሴን ከተራራው እንዲወርድ ተናገረው። ሙሴ ለእግዚአብሔር መገኘት ሲዘጋጅ ሕዝቡን እንዲህ ሲል ያዛቸዋል፡

*14 ሙሴም ከተራራው ወደ ሕዝቡ ወረደ፥ ሕዝቡንም ቀደሰ፤ ልብሳቸውንም አጠቡ። 15 ሕዝቡንም፦ ለሦስተኛው ቀን ተዘጋጁ፥ ወደ ሴቶቻችሁ አትቅረቡ አለ። (ዘጸአት 19)*

እዚህ ሙሴ ምን እንደሚፈልግ አስተውሉ። ሕዝቡ ልብሳቸውን ያጥቡ እና ከማንኛውም ጾታዊ ግንኙነት ይቆጠቡ ዘንድ ይነግራቸዋል ምክንያቱም ጌታ ስለሚወርድ እና በመካከላቸው ህልውናውን ስለሚገልጥ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የወንድና ሴት የፆታ ግንኙነት እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ርኩስ ያደርጋቸው ስለነበር ነው፡

*18 ወንዱ በሴቲቱ ቢደርስባት ሁለቱ በውኃ ይታጠባሉ፥ እስከ ማታም ድረስ ርኩሶች ናቸው። (ዘሌዋውያን 15)*

እነዚህ የኃጢያት ተግባራት ባይሆኑም ሰውን ያረክሱት ነበር፣ እናም በዚህ ሁኔታ ወደ ጌታ ፊት መግባት አይችሉም ነበ።

ከዚያም የእግዚአብሔር የሥነ ምግባር መስፈርቶች ነበሩ። እነዚህ ግዴታዎች እንደ አለመስረቅ፣ዝሙት፤መግደል የመሳሰሉ ነገሮችን ያካትታሉ (ዘጸአት 20:13-15) ይሁን እንጂ ሕጉ ከዚህ የበለጠ ጥልቅ ነበር። ስለ አለመመኘትም ተናግሯል (ዘጸአት 20፡17) ። መመኘት የአእምሮ ኃጢአት ነው። ይኸው ሕግ የእግዚአብሔር ሕዝብ በፍጹም ልባቸው፣ነፍሳቸው፣ አዕምሮአቸው እና ኃይላቸው እንዲወዱት ጠይቋል (ዘዳግም 6፡5) ። በኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ ጌታ በሕዝቡ ላይ ይፈርዳል ምክንያቱም የሚያመልኩት በአፋቸው እንጂ በልባቸው ስላልሆነ ነው (ኢሳ 29፡13) ።

የአካል ጉዳቶች እና ብልቶችን በተመለከተ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ሕግ ተመልከቱ፡-

*17 ለአሮን እንዲህ ብለህ ንገረው፦ ከዘርህ በትውልዳቸው ነውር ያለበት ሰው ሁሉ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ። 18 ዕውር፥ ወይም አንካሳ፥ ወይም አፍንጫ ደፍጣጣ፥ ወይም ትርፍ አካል ያለው፥ 19 ወይም እግረ ሰባራ፥ ወይም እጀ ሰባራ፥ 20 ወይም ጉባጣ፥ ወይም ድንክ፥ ወይም ዓይነ መጭማጫ፥ ወይም እከካም፥ ወይም ቋቁቻም፥ ወይም ጃንደረባ፥ ነውረኛ ሁሉ አይቅረብ። 21 ከካህኑ ከአሮን ዘር ነውር ያለበት ሰው የእግዚአብሔርን የእሳት ቍርባን ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ፤ ነውረኛ ነው፤ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ።*

አንድ ካህን ዕውር ወይም አንካሳ ቢሆን ወደ ጌታ ፊት ሊገባ አይችልም። በጣም ረጅም እጅና እግር ያለው ወይም የተጎዳ እግር ያለው ሰው የክህነትን ሚናውን የመጠቀም መብቱ የተከለከለ ነው። ድንክ ወይም የተሰበረ የወንድ የዘር ፍሬ ያለው ሰው በተሰጠው ኃላፊነት ላይ ስራውን በመስራት ጌታን ማገልገል አይችልም። እነዚህ ጉዳቶች በኃጢአተኛ ዓለም ውስጥ የመኖር ውጤቶች ናቸው። እነዚህ የአካል ጉዳተኞች የግድ የግል ኃጢአት ውጤቶች ባይሆኑም እነዚህ ሰዎች በሰውነታቸው ላይ የኃጢአት አሻራ ያረፈ ሲሆን ይህም እነርሱን ከጌታ አገልግሎት ለመለየት በቂ ነበር።

የእግዚአብሔር ሕግ ያደረገው አንድ ነገር ቢኖር የሰውን ልጅ ከማይቻል መስፈርት ፊት ማስቀመጥ ነው። በሰው ጥረት በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ የጽድቅ ቁመና ለመያዝ መሞከር ከንቱነት መሆኑን አሳይቷል። ሴት ልጅ የተፈጥሮ አካላዊ ግዴታዎቿ እንኳን ከእግዚአብሔር ይለዩአታል። በትዳር ውስጥ የተለመደና ተቀባይነት ያለው ነገር እንኳን ባልና ሚስቱን በእግዘአብሔር ፊት ርኩስ ያደርጋቸዋል። በዚህ ምድር ላይ መኖር እና በአጋጣሚ የረከሱ ዕቃዎችን መንካት ሰውን ርኩስ ያደርገዋል እና ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ህብረት ላይ እንቅፋት ይፈጥራል። ትክክለኛውን ነገር ማድረግ እንችል ነበር፣ ነገር ግን ልባችን ከእግዚአብሔር ጋር የማይስማማ ከሆነ፣ከእግዚአብሔር መስፈርት ጎድለናል። ጳውሎስ በሮሜ 5፡20 ላይ "ሕጉም በደልን ሊያበዛ ገባ" ሲል ይናገራል።

ሕጉ ምን አደረገ? የማይቻለውን የእግዚአብሔር መለኪያ በመግለጥ ኃጢአታችንን አሳይቶናል። በዚህ በኃጢአተኛ ዓለም ውስጥ በእነዚህ ብልሹ አካላት ውስጥ መኖር ከእግዚአብሔር እንደለየን አሳይቶናል። ለእግዚአብሔር በምናቀርበው አገልግሎት ፍጹም እንዳልሆንን አሳይቶናል። የልባችንን እና የአዕምሮአችንን ጉድለት በፊቱ ገልጧል። በአጭሩ፣ በግል ጥረታችን መዳን እንደማይቻል አሳይቶናል። ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖረን ከፈለግን ከራሳችን ውጪ የሆነ ነገር መከሰት ነበረበት። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው በክርስቶስ የተደረገውን አንድ የጽድቅ ሥራ ነው። ሕጉ የተሰጠው የሰውን ልጅ ለማዳን አይደለም፣ ነገር ግን እነርሱን ወክለው የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ እንደሚያስፈልጋቸው ለማመልከት ነው።

ጳውሎስ ሮሜ 5:20-21 ላይ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፡

*20 …ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፥ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ። (ሮሜ 5)*

ኃጢያት ሁሉን አቀፍ ሲሆን እና ሲበዛ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ "ከዚህም በላይ" ይበዛል። ጸጋ በነጻ የተሰጠ የእግዚአብሔር ሞገስ ነው። ጳውሎስ እየነገረን ያለው የሚከተለውን ነው፡- ኃጢአት በሁሉም የምድር ክፍሎች ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ከእግዚአብሔር እየለየን ቢሆንም፣ የእግዚአብሔር በነጻ የተሰጠ ጸጋ ከእርሱ ጋር ወደ ትክክለኛ ቁመና እና ህብረት እንድንመልስ ያስችለናል። ኃጢአት የበረታ ቢሆንም የእግዚአብሔር ጸጋ አሁንም ይበልጣል።

ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች "ኃጢአት በሞት ነገሠ" በማለት ተናግሯል። እዚህ ያለው ሃሳብ ኃጢአት የሕይወታችን ገዥ እና ንጉሥ ነበር - እኛ የእሱ አገልጋዮች ነበርን። በእኛ እና በእጣ ፈንታችን ላይ ፍጹም ኃይል ነበረው። በሕይወታችን ያለው የኃጢአት አገዛዝ የሞት እና ከእግዚአብሔር የመለየት አገዛዝ ነበር።

ነገር ግን ያ የኃጢአት አገዛዝ መሸነፍ ይችላል። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ ዘለአለማዊ ሕይወት የሚመራ ጸጋ በጽድቅ ሊነግስ እንደሚችል ተናግሯል።

እስቲ ይህን የጳውሎስን አባባል ለመተንተን እሱ የተናገረውን እንመርምር።

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ጸጋ በሕይወታቸው ላይ ሊነግሥ ይችላል ብሎ የነገራቸውን አስተውሉ። በነጻ የተሰጠ ጸጋ ለእኛ የሚገባ ወይም የተገባን አይደለም። ጥፋተኛ ብትሆኑም ይቅርታ መቀበል እና መፈታት ይቻላል። የእግዚአብሔርን ጸጋ ማወቅ እና ከእርሱ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖራችሁ ያስችላችኋል። እግዚአብሔርም ይህንን ሊሰጠን ፈቃደኛ ነው።

ጳውሎስ እንደተናገረው ይህ የጽድቅ ስጦታ፣በጽድቅ ይነግሣል። ጳውሎስ እዚህ ላይ የተናገረው ይህ ጽድቅ ምንድን ነው? በራሴ ጥረት በእግዚአብሔር ፊት ትክክል መሆን እንደማልችል የእግዚአብሔር ሕግ ስላሳየኝ የራሴ ጽድቅ ሊሆን አይችልም። ጸጋን የሚያመጣው ጽድቅ የክርስቶስ ጽድቅ ነው።

ጳውሎስ በቁጥር 21 ላይ የዘላለም ሕይወት "በክርስቶስ በጌታችን" እንደሆነ በመንገር ይህንን ያረጋግጣል። ይህም ጳውሎስ በቁጥር 18 ላይ እንዲህ ሲል ወደ ጀመረው የጽድቅ ሥራ ይመልሰናል፡

*18 እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። (ሮሜ 5)*

ይቅርታንና ሕይወትን የሚያመጣው ይህ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት ያደረገው አንድ ሥራ ነው። ይህ አንዱ የጽድቅ ሥራ "በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዘላለም ሕይወት" ይመራል (ሮሜ 5፡21) ። የአዳም አንድ ሥራ ኃጢአትንና ሞትን ለሁሉም አመጣ። በአንድ የክርስቶስ ሥራ፣ተስፋ ተመልሷል። የእኛ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ እና በአብ ፊት በትክክል መቆም ሙሉ በሙሉ የተደገፈው በዚያ ፍጹም በሆነው የክርስቶስ መሥዋዕት ላይ ነው። ሌላ ምንም አያድነንም። በሌላ መንገድ ይቅርታ የለምና።

**ለምልከታ**፡

በኤደን ገነት በእግዚአብሔር ላይ የተደረገው አንድ ነጠላ የአመጽ ድርጊት በምድርና በነዋሪዎቿ ላይ ምን አመጣ?

በሙሴ በኩል የተሰጠው ሕግ በእኛ ጥረት በእግዚአብሔር ፊት ትክክል መሆን የማይቻል መሆኑን የገለጠው እንዴት ነው?

ኃጢአት ስለሠራን ኃጢአተኛ መሆን እና ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ ኃጢአተኛ በመሆን መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

በክርስቶስ በኩል የተሰጠን ይቅርታ ለምን ያስፈልገናል?

ጳውሎስ ጸጋው ሊነግስ የሚችለው የዘላለም ሕይወት በሚሰጠን በጌታ በኢየሱስ አንድ የጽድቅ ሥራ እንደሆነ ይነግረናል:: ይህን ሲል ምን ማለቱ ነበር? ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራውን ይህን የጸጋ መንግሥት እንዴት እናውቃለን?

**ለጸሎት**:

በፍጥረታችሁ እና በተግባር ከእርሱ ክብር እንደጎደላችሁ ለማወቅ እና በእግዚአብሔር ፊት ለመናዘዝ ትንሽ ጊዜ ውሰዱ:: በመስቀል ላይ በሰራው ስራ የመፍትሄ ሃሳብ ስላቀረበ አመስግኑት::

ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ መልካም ለመሆን የሚጥሩ ሰዎችን ታውቃላችሁን? ይህ የማይቻል መሆኑን ጌታ እንዲገልጥላቸው ጠይቁት:: ተስፋቸው በጥረታቸው ሳይሆን በቀራንዮ መስቀል ላይ በተሰራው የክርስቶስ የጽድቅ ሥራ መሆኑን ጌታ እንዲያሳያቸው ጠይቁት::

ጌታ ኢየሱስን እና የሥራውን ውጤት በህይወታችሁ ካወቃችሁ፣ በእናንተ ላመጣው ለውጥ ትንሽ ጊዜ ወስዳችሁ አመስግኑት::

# ምዕራፍ 4 -

# በክርስቶስ መጠመቅ

ሮሜ 6:1-4

*6 እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። 2 ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? 3 ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? 4 እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። (ሮሜ 6)*

በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ፣ሐዋርያው ጳውሎስ ትኩረታችንን የዘላለምን ሕይወት በሚሰጠው በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ሥራ ላይ በማድረግ ለእኛ ሲል በመስቀል ላይ ሞት መስዋዕትነት መክፈሉን እንዴት እንዳስተማረን ተመልክተናል። በሙሴ በኩል የተሰጠው የእግዚአብሔር ሕግ እኛ አዳኝ እንደሚያስፈልገን ለማሳየት እንጂ ከፍርድ ሊያድነን እንዳልተዘጋጀ አስታውሶናል። መዳናችን በብቃታችን ወይም በድርጊታችን ላይ የተመሰረተ አይደለም። የጌታ የኢየሱስ ሥራ ብቻውን የኃጢአትን ይቅርታ የሚያመጣ እና በእርሱ የሚታመኑትን ሁሉ ከአብ ጋር ባለው ትክክለኛ ሕብረት ውስጥ የሚስቀምጥ ነው።

ይህ እውነት ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 6 ላይ ሊያነሳው ወደሚፈልገው ወሳኝ ጥያቄ ያመጣናል።

*1 እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። (ሮሜ 6)*

ጌታ ኢየሱስ የከፉ ኃጢአተኞችን እንኳን ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ከሆነ ለምን በተመሳሳይ በክርስቶስ በተሰጠን የሐጢአት ይቅርታ ውስጥ እየተደሰትን አንኖርም? ጌታ በፈቃዱ ይቅር ካለን ኃጢአትን ለማቆም የሚሆን ምን ማበረታቻ አለ? ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ህብረት ለመመሥረት ብቁ መሆን ካላስፈለገኝ፣ በዚህ ምድር ላይ ለእርሱ ለመኖር ምን ተነሳሽነት አለኝ? ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ባደረገው አንድ ሥራ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ሕብረት እንዲሰጠን የምንታመን ከሆነ፤በምንም አይነት ህይወት ውስጥ መኖራችን ምን ለውጥ ያመጣል? መዳን በግል ጥረት እንደሚገኝ ካላመንኩ፣እኔ በምፈልገው መንገድ መኖር እና የምሰራውን ኃጢአት ሁሉ ይቅር ሊለኝ እንደሚችል ማመን አልችልምን?

ጳውሎስ ይህን ጥያቄ ግልጽ ለማድረግ ይመልሳል፡

*2 በምንም መንገድ አይሆንም! ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? (ሮሜ 6)*

እዚህ ላይ ሐዋርያው እየነገረን ያለው በኃጢአት ለመቀጠል ከፈለግን የክርስቶስን ሥራ እና በመስቀል ላይ የተደረገውን መረዳት ተስኖናል። ጳውሎስ በቁጥር 2 ላይ “ለኃጢአት የሞትን እኛ እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?” ማለቱን ይቀጥላል። ሐዋርያው በዚህ አባባሉ ምን ማለቱ ነው? ለሐጢያት የሞትነው መቼ ነው? የሞተልን ጌታ ኢየሱስ አይደለምን?

ጳውሎስ ይህን በይበልጥ በሮሜ 6:3-4 ላይ በሚገባ ያስረዳል፡

*3 ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? 4 እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።*

እስቲ ለአፍታ ይህን የጳውሎስን መልዕክት ለመረዳት ጊዜ እንውሰድ።

### *በክርስቶስ መጠመቅ*

በመጀመሪያ ጳውሎስ "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ ስለ ተጠመቁት" መናገሩን አስተውሉ። ስለ ጥምቀት ስንናገር ወዲያውኑ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው የውኃ ጥምቀት ነው። ነገር ግን ጳውሎስ ይህ ጥምቀት የሞት ጥምቀት እንደሆነ ይነግረናል።

*3 ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?*

ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረውን ጥምቀት በውኃ ጥምቀት ላይ ብቻ መወሰን የለብንም። በውኃ የተጠመቁ ብዙዎች ለራስ መሞትን ፈጽሞ እንዳልተለማመዱ እናውቃለን። ብዙዎች በልምምዱ አልፈዋል ነገር ግን በእውነት በክርስቶስ አልተጠመቁም። "ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን" መጠመቅ የሕይወት ለውጥ ክስተት ነው። የውኃ ጥምቀት የአንድ ትልቅ ጥምቀት ምልክት ብቻ ነው። በማቴዎስ 3 ላይ ስለ ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ የተናገረውን አድምጡ፡-

*11 እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል፤ (ማቴዎስ 3)*

ዮሐንስ ለተከታዮቹ ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት እንደሚያጠምቃቸው ይነግራቸው ነበር። በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት መጠመቅ ህይወትን የሚለውጥ ልምምድ ነው። መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ልብ ሊያድር ሲመጣ እሱ ወይም እሷ አዲስ ሰው ይሆናሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲህ ይላቸዋል፡

*17 ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። (2ኛ ቆሮንቶስ 5)*

እንግዲህ ይህ የመንፈስ ቅዱስ እና የእሳት ጥምቀት ምንድ ነው? በማቴዎስ 3፡11 ላይ ባለው የዮሐንስ መልዕከት መሠረት መንፈስ ቅዱስ በእሳት የታጀበ መሆኑን አስተውሉ። እሳት፤በዚህ አውድ ውስጥ ለማጽዳት እና ለማጥራት ያገለግላል። መጥምቁ ዮሐንስ የሚናገረው ጥምቀት የእግዚአብሔር መንፈስ በአማኙ ልብ ውስጥ የሚያደርገው የመንጻት እና የማጥራት ሥራ ነው። ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ለደቀ መዛሙርቱ በነገራቸው ጊዜ፣መንፈስ ቅዱስ የሚሰራውን ነግሯቸዋል፡-

*7 እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ። 8 እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤ 9-10 ስለ ኃጢአት፥ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም፥ ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤(ዮሐንስ 16)*

የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ኃጢአት እና ፍርድ ሊወቅስ ከሚያነጻው እሳት ጋር ይመጣል። ጌታ ቅዱስ መንፈሱን በህይወታችን ውስጥ አፍስሶ ስለ ኃጢአት እና ስለሚመጣው ፍርድ ይወቅሰናል። የመንፈሱ እና እሳቱ መገኘት ከውስጥ ይለውጠናል። አስተሳሰባችንን እና ፍላጎታችንን እንድንቀይር በውስጣችን ይንቀሳቀሳል። በአስተሳሰብ፣ በቃልም ሆነ በተግባር ኢየሱስን እንመስል ዘንድ ይፈልጋል። አዲስ ፍጥረት

ያደርገናል። እንዲያውም ጳውሎስ ከላይ በተጠቀሰው ክፍል ላይ ለቆሮንቶስ ሰዎች “አሮጌው ነገር አልፎአል” ይላቸዋል። ከክርስቶስ ጋር አብረው የተጠመቁ ሰዎች ቀድሞ የነበሩት አይነት ሰዎች አይሆኑም። ይህ የመንፈስ ቅዱስ እና የእሳት ጥምቀት አሮጌውን መንገድ በማጥፋት አዲስ ፍላጎት እና አዲስ አመለካከት በውስጣችን ይፈጥራል። በዚህ ጥምቀት የተጠመቁ፤አዲስ ሰዎች ናቸው።

በመስቀል ላይ በተሰራው የክርስቶስ የጽድቅ ሥራ የሚታመኑ ተለውጠዋል። መንፈሳዊ ለውጥ ይካሄዳል። የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወት በእነርሱ ላይ ይፈሳል፣እነርሱም ንጹሕና ይቅር ተብለዋል። አሮጌው ሕይወታቸው ሞቶ ለክርስቶስ ይማረካሉ። ልጆቹ ይሆናሉ። ዳግምኛ ተወልደዋል። በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት በክርስቶስ ይጠመቃሉ።

ጌታ ኢየሱስ በፈቃዱ ነፍሱን ስለ እኛ አሳልፎ ሰጥቷል። የእሱ ሞት የኃጢአታችንን ዋጋ ከፍሏል እናም በአብ ፊት ለመቆም በሩን ከፍቷል፡፡ ወደዚያ መስቀል ስንቀርብ፣ እኛን የእርሱ ልጆች አድርጎ መንፈሱን ሲያፈስ ለእርሱ በመለየት እንጠመቃለን። ያ የመንፈስ ጥምቀት ሕይወትን የሚለውጥ ነው። በአንድ ወቅት ለነበረው አሮጌ ማንነታችን ሁሉ የሞት ጥምቀት ነው። በእሱ አማካኝነት ተለውጠናል፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይናገራል፡

*4 እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።*

በክርስቶስ ሥራ እና በእግዚአብሔር መንፈስ ጥምቀት፣ አዲስ የሕይወት ውል ተሰጥቶናል። ልባችን ተለውጧል። በውስጣችን በመንፈስ ቅዱስ ሥራ “በአዲስ ሕይወት” ለመመላለስ አዲስ መሻት አለ (ሮሜ 6፡4) ። ጳውሎስ በቁጥር 1 ላይ የጀመረው ጥያቄ “ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን?” የሚል ነበር። ለጳውሎስ፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆኖ የተጠመቀ እና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተለወጠ ሰው ወደ ቀድሞው መንገድ ይመለስ ዘንድ የማይታሰብ ነበር። ይህንን

የመንፈስ ጥምቀት በአንዱ የክርስቶስ ጽድቅ ሥራ የተለማመዱ ሰዎች አዲስ የህይወት መሻት አላቸው። የእግዚአብሔር መንፈስ እና የእሳት ጥምቀቱ በኃይል ቀይሯቸዋል፤ከዚያም መሻታቸው ለክርስቶስ እና ለክብሩ ይሆናል።

ብዙዎች ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንደሞተ ያምናሉ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ በውኃ የተጠመቁ ናቸው፤ነገር ግን ጳውሎስ የተናገረውን ይህን የክርስቶስ ጥምቀት አልተለማመዱም። ለመለወጥ እና አዲስ ሕይወትን ለማምጣት ስለሚፈሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ምንም አያውቁም። አዲስ የሚያደርገን ይህ የክርስቶስ መንፈስ ሕይወት ነው። ወደ ክርስቶስ መስቀል በመቅረብ የዚህን መንፈስ ሥራ የሚያውቁ ተለውጠዋል። በክርስቶስ ለተለወጡ ሰዎች፣ “ኃጢአትን እንሠራለን” የሚለው ጥያቄ የማይታሰብ ነው። ከክርስቶስ ጋር አብረው የተጠመቁ ሰዎች ፍላጎት እርሱን ማክበር ነው ምክንያቱም ልባቸው አሁን ከእሱ ጋር የተቆራኘ ነውና።

**ለምልከታ:**

ጳውሎስ እዚህ ክፍል ላይ ያስተማረው በውኃ ጥምቀት እና በክርስቶስ ጥምቀት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

የክርስቶስ ጥምቀት የሞት ጥምቀት የሆነው እንዴት ነው?

አዲስ ፍጥረት በማድረግ ረገድ የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምንድን ነው? ያለ እሱ ይህ ለውጥ ይቻል ይሆን?

መልካም ሕይወት ለመኖር በሰው ጥረት እና መንፈስ ቅዱስ አዲስ ፍጥረት እንሆን ዘንድ በሚሰራው ሥራ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

በክርስቶስ ጥምቀት ሕይወታቸው ለተለወጠ ሰዎች "ኃጢአትን እንስራ" የሚለው ጥያቄ ለምን አስጸያፊ ይሆናል?

ሕይወታችሁ በክርስቶስ እና በመንፈሱ ሥራ ተለውጧልን? በህይወታችሁ ውስጥ ስላለው ለውጥ ምን ማስረጃ አለ?

**ለጸሎት**:

ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ስለሞተ ብቻ ሳይሆን በመንፈሱ ኃይል ሕይወታችንን ሊለውጥ ፈቃደኛ ስለሆነ ጌታን አመስግኑ?

በእናንተ ውስጥ ላለው የክርስቶስ መንፈስ ሥራ የበለጠ ንቁ ትሆኑ እና ኢየሱስን ትመስሉ ዘንድ ጌታ እንዲረዳችሁ ጠይቁት::

በህይወታችሁ ከኃጢአት ጋር እየታገላችሁ ነውን? ጌታ ድል እንዲሰጣችሁ ጠይቁት:: የእግዚአብሔር መንፈስ ማንኛውንም የኃጢአት ፍላጎት ከአንተ እንዲያስወግድ ጠይቁ:: እርሱን እንደምትፈልጉ እወቁ እንዲሁም በህይወታችሁ ላለው ሥራው ራሳችሁን አሳልፋችሁ ስጡ::

## ምዕራፍ 5 -

## ከክርስቶስ ጋር መሞት

---

ሮሜ 6:5-11

*5 ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን*
*ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር*
*እንተባበራለን፤ 6 ከእንግዲህስ ወዲያ*
*ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው*
*ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ*
*ከኃጢአቱ ጸድቋልና። 7-8 ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን*
*ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን፤ 9*
*ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ*
*ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና። 10 መሞትን አንድ ጊዜ*
*ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና፤ በሕይወት መኖርን ግን*
*ለእግዚአብሔር ይኖራል። 11 እንዲሁም እናንተ ደግሞ*
*ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን*
*ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን*
*ቁጠሩ። (ሮሜ 6)*

በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚከተለውን ጥያቄ አቅርቦ ነበር፡፡

*1 እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? (ሮሜ 6)*

ጳውሎስ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጥ፤ከክርስቶስ ጋር አብረው የተጠመቁ የተለወጡ መሆናቸውን ለሮሜ ሰዎች ያስታውሳቸዋል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እና እሳቱ ውስጣዊው ሰውነታቸውን አንጽቶ ያድሳል፡፡ በሮሜ 6፡5-11፣ ጳውሎስ ለመልሱ ሌላ ገጽታ ይጨምራል፡፡ ከእነዚህ ጥቅሶች በመቀጠል ለሮሜ ሰዎች በሞቱና በትንሳኤው ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆናቸውን ይነግራቸዋል፡

*5 ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤(ሮሜ 6)*

እዚህ ላይ ልናጤነው የሚገባን ጥያቄ፡ ከክርስቶስ ጋር በሞቱ እንዴት አንድ ሆንን? የሚለው ነው፡፡ ክርስቶስ ሲሞት በአካል በዚያ መስቀል ላይ አልነበርንም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ያደረገውን እንኳን የተማርነው እሱ ከሞተ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነበር፡፡

ጳውሎስ እዚህ ላይ የተናገረው የሕግ ቃላትን ነው፡፡ መስቀል በሮማውያን ዓለም ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ሕጋዊ ቅጣት ነበር፡፡ ክርስቶስ እንደ ወንጀለኛ የሞተው ለሠራው ኃጢአት ሳይሆን ለእኔ ኃጢአት ነው፡፡ ከኃጢአትና ከሞት ቅጣት ነፃ እወጣ ዘንድ እርሱ የእኔን ቦታ ወስዶ ሞተ፡፡ ያ ሲካሄድ እኔ አልነበርኩም፡፡ ሲሞት እንኳን አላውቀውም ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን ስሙን እና የእኔን ስም ይዞ ወደ መስቀል ሄደ፡፡ በመንግሥተ ሰማያት ህጋዊ መዝገቦች ውስጥ የእኔ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ተከፍሏል፡፡ እኔ ከክርስቶስ ጋር በሞት አንድ የሆንኩት እርሱ ስለእኔ ስለሞተ እና ስሜን ይዞ ስለሄደ ነው፡፡

ጳውሎስ በመቀጠል በሮሜ 6፡5 ላይ በሞቱ ከክርስቶስ ጋር ስለተባበርኩ አሁን በትንሣኤ ከእርሱ ጋር አንድ መሆን እችላለሁ (ቁጥር 5) ይላል። በትንሣኤ ከእርሱ ጋር አንድ መሆን በኃጢአትና በሞት ላይ ድል መንሳት ማለት ነው። በእግዚአብሔር ህልውና ለመደሰት እና በክብሩ ለመኖር ከኃጢአት መዘዝ ነጻ መውጣት ነው። ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ክርስቶስ ስለሞተ ነው። ሁሉም የህግ እንቅፋቶች የሚወገዱት በጌታ በኢየሱስ ሥራ በስሜ ነው።

ጳውሎስ በሮሜ 6፡6 ከክርስቶስ ጋር ያለኝን ግንኙነትና ሞቱን በተመለከተ ሌላ ነገር ይናገራል፡-

*6 ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዎችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና።*

የጌታ ኢየሱስ ሞት ከሕግ ስምምነት የበለጠ ነበር። ሙሉ በሙሉ የሐጢአት ይቅርታን ማግኘት ነገር ግን በባህሪ ወይም በአመለካከት አለመለወጥ ይቻላል። ዳሩ ግን የጌታ የኢየሱስ ሞት ሕጋዊ ይቅርታን ከማስገኘቱም በላይ የሞተላቸው ሰዎች ባሕርይ ላይ ለውጥ አምጥቷል። በቁጥር ስድስት ላይ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች አሮጌው ሰውነታቸው ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀለ እንደነገራቸው አስተውሉ።

ያ "አሮጌው ሰው" "የኃጢአት ባሪያ" ነበር። በፍጥረት እኛ ኃጢአተኞች ነን። የልባችን ራስ ወዳድነት ገና በለጋ እድሜያችን ይገለጣል። ከእግዚአብሔር ዓላማ የመኮብለል ዝንባሌ በግልጽ ይታያል። የምንናገራቸው ቃላት ወይም የልባችን አሳብ የኃጢአተኝነታችንን ሁኔታ ያስታውሰናል። በውስጣችን በእግዚአብሔር እና በመንገዶቹ ላይ የሚያምፅ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ አለ። አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር እና ለእውነት ባለን ፍላጎት ማጣት ራሳችን እናፍራለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በቁጥር 6 ላይ የኃጢአት ተፈጥሮ "እንዲጠፋ" አሮጌው ሰውነታቸው ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀለ ተናግሯል። የክርስቶስ ሞት እኛን ይቅር ማለት

ብቻ ሳይሆን ይለውጠናል። መንፈስ ቅዱስ አዲስ ሕይወት ሊሰጠን ይመጣል። እርሱ እኛን በኃጢአት መንገድ ከመውቀስ የበለጠ ነገር ያደርጋል። እርሱ በእኛ ውስጥ ያለ የክርስቶስ ሕይወት ነው። በውስጣችን ያለው ህይወቱ ኃይል በመስጠት ከውስጥ ይለውጠናል። አሮጌውን የአስተሳሰብ መንገድ ገድሎ የክርስቶስን መልክ እንድንመስል ለውጦናል (ሮሜ 8፡9) ።

የክርስቶስ ሞት ታላቁ የመንፈስ ሥራ በእኛ እንዲጀመር መንገድ ጠርጓል። ይቅርታን ባገኘ ልብ ውስጥ ባለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተለውጠናል። የኃጢአት አካል ጠፍቶ "ወደ ምንም መጥቷል" ። የጌታ ኢየሱስ ሥራ ይቅር ይለናል ብቻ ሳይሆን ይለውጠናል።

ጳውሎስ በቁጥር 7 ላይ "የሞተው ከኃጢአት ነፃ ወጥቷል" በማለት ለሮሜ ሰዎች ያስታውሳቸዋል። እኛ የሞትነው ክርስቶስ ወደ መስቀል በሄደ ጊዜ እና በእኛ ፈንታ ሞተን ሲቀበል ነው፤ከዚያም ከሕግ የኃጢአት ቅጣት ነጻ አወጣን። አንድ ጊዜ ሞተን የነበርነው፣በእኛ ሕይወት ባለው የእግዚአብሔር መንፈስ ሕልውና ምክንያት አዲስ ሕይወት ተሰጠን። ሐዋርያው በመቀጠል ለሮሜ ሰዎች ከኃጢአት ነጻ እንደወጡ እንደነገራቸው አስተውሉ።

ኃጢአተኛ አስተሳሰብ ካለን እና በኃጢአት መንገድ መውደቃችንን ከቀጠልን ከኃጢአት ነጻ ወጥተናል እንዴት ሊባል ይችላል? ከመካከላችን እሱ ወይም እሷ ኃጢአት አልሠራም የሚል ማን አለ? እንደ አማኞችም በመደበኛነት ወደ አዳኛችን መምጣት እና ይቅርታን መጠየቅ አለብን። ጳውሎስ ከኃጢአት ነፃ እንደወጣን ሲነግረን ከኃጢአት ቅጣትና ኃይል ነጻ ስለመውጣት እየተናገረ ነው።

ጌታ ኢየሱስ ስለ እኛ ሲሞት የኃጢአታችንን ቅጣት ለራሱ ወሰደ። እሱ ይህን ስላደረገ፣ ከአሁን በኋላ ቅጣቱን መጋፈጥ አያስፈልገንም። ይቅርታ ተደርጎልን ወደ እግዚአብሔር ተመልሰናል። ቅጣታችን ተከፍሏል። ይህንንም ሐዋርያው በሮሜ 8፡1 ላይ እንዲህ ሲል አስረድቷል።

*1 እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። 2 በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና። (ሮሜ 8)*

ከኃጢአት ቅጣት ብቻ ሳይሆን ከኃይሉም ነጻ ወጥተናል። የክርስቶስ መንፈስ ያለባቸው በኃጢአት እና በኃይሉ ላይ ስልጣን አላቸው። ለእርሱ እና ለሥራው ሲገዙ የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል እና ድልን ይሰጣቸዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 8፡37፡-

*37 በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። (ሮሜ 8)*

ሐዋርያው እዚህ የክርስቶስ መስቀል ሁሉን እንደለወጠ ለሮሜ ሰዎች ያስተምራል። የኃጢአትን ቅጣት ከሕይወታቸው አስወገዶ እና በመንፈስ ውስጣዊ ሥራ ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት እንዲኖሩ ኃይል ሰጥቷቸዋል። ይህንን እውነታ ለተለማመዱ በኃጢአት ጸንቶ መኖር የማይታሰብ ነገር ነው።

የክርስቶስ መስቀል ለሥራው የተገዙትን ይቅር ይላል። በኃጢአት ላይ በድል እንዲኖሩም ኃይል ይሰጣቸዋል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ መስቀል ልናጤነው የሚገባን አንድ ተጨማሪ ዝርዝር ነገር አለ። የሐዋርያው ጳውሎስን ቃል ከቁጥር 8-11 አድምጡ፡-

*8 ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን፤9 ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና። 10 መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና፤ በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል። 11 እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ። (ሮሜ 6)*

ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልቆየም። ከሞት ተነስቶ በሰማይ ካለው አብ ጋር ለመሆን ሄደ። እንዲያውም፣ ጳውሎስ “ከእንግዲህ ወዲህ ሞት አይገዛውምና” (ቁጥር 9) በማለት ይናገራል። ጌታ ኢየሱስ የሞትን ኃይል አሸንፏል። ሐዋርያው በቁጥር 8 ላይ ለሮሜ ሰዎች ከክርስቶስ ጋር በሞቱ ስለተዋሃዱ በትንሣኤ ህይወቱም ከእርሱ ጋር እንዲተባበሩ አሳስቧቸዋል። ጌታ ኢየሱስ ከሞት እንደተነሳ እኛም እንዲሁ ይህ አስደናቂ እምነት አለን። ሞት ለኛ መጨረሻ አይደለም። በመስቀሉ ምክንያት በክርስቶስ ህልውና ፊት ለዘለአለም መኖር እንችላለን።

ቁጥር 10 ክርስቶስ ለኃጢአት መሞቱን ይነግረናል። እኛን ባሪያ አድርጎ ከአብ በለየን ኃጢአት ምክንያት ሞተ። በሕይወታችን ያለውን የኃጢያት ኃይል ለማሸነፍ ሞተ፤ከዚያም በድል ተነሳ። ለኃጢያት ሞቶ፣አሁን ልንከተለው የሚገባንን አርአያ እየሰጠ ለእግዚአብሔር እንደሚኖር ሮሜ 6:10 ይነግረናል።

በሞት ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆኑ ሰዎች አዲስ የሕይወት ዓላማ አላቸው። ልክ እንደ ክርስቶስ ራሳቸውን “በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያው” አድርገው መቁጠር አለባቸው። እነርሱን ለመለወጥ እና ለማደስ ለእግዚአብሔር መንፈስ ውስጣዊ ሥራ መገዛት አለባቸው። በመንፈስ ቅዱስ መንገድ መመላለስን መርጠው ለኃጢአተኛ ሥጋ እንደ ሞቱ መቁጠር አለባቸው።

ጌታ ኢየሱስ ላደረገልኝ ነገር ምላሽ መስጠት አለብኝ። የኃጢአቴን ቅጣት ወሰደልኝ። መንፈሱን በውስጤ አኖረ፤አዲስም ፍጥረትም አደረገኝ። ለዚህ የክርስቶስ ሥራ ምላሼ ምን ይሆን? ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የነገራቸው ብቸኛው እና ትክክለኛ ምላሽ እነርሱ ለኃጢአት እንደ ሞቱ እና ለክርስቶስ ሕያዋን አድርገው ራሳቸውን መቁጠራቸው ነው። አዲስ ሕይወት እንዲኖረን ሁሉም ነገር ተደርጎልናል። ሐዋርያው በዚህ አዲስ ሕይወት ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲመላለሱ እዚህ ጋር ይማጸናል። ይህ ሁላችንም መምረጥ ያለብን ምርጫ ነው።

**ለምልከታ፡**

በሞቱ ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

በመስቀል ላይ መታየት የነበረባቸው ምን ዓይነት የሕግ ጉዳዮች ናቸው?

የክርስቶስ መስቀል ሕይወታችሁን እንዴት ለወጠው?

በእናንተ ሕይወት ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ምን ማስረጃ አለ? የእግዚአብሔር መንፈስ እንዴት በኃጢአት ላይ ድል እየሰጣችሁ ነው?

የኢየሱስ መስቀል የዘላለም እጣ ፈንታችንን እንዴት ይለውጣል? በመስቀሉ ምክንያት በእርሱ ፊት ዘለዓለማዊ ማረጋገጫ አላችሁን?

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ለሮሜ ሰዎች የነገራቸውን ተመልከቱ:: በመስቀሉ በረከታችን መሆኑ በኃጢአት ጸንቶ ለመኖር ያለውን ማንኛውንም ስጋዊ መሻት የሚያስወግደው እንዴት ነው?

**ለጸሎት**:

በሞቱ ለእኛ ሲል ለሰጠው የሐጢአት ይቅርታ ጌታን ለማመስገን ትንሽ ጊዜ ውሰዱ::

ትለወጡ እና ለእርሱ ትኖሩ ዘንድ ለማስቻል የመንፈሱ መገኘት በሕይወታችሁ ስላለ ጌታን አመስግኑት:: ለዚህ

የመንፈስ ሥራ የበለጠ የተዘጋጃችሁ ትሆኑ ዘንድ እንዲረዳችሁ ጠይቁት።

በሕይወታችሁ ውስጥ ለቀሩት የኃጢአት ምኞቶች እግዚአብሔር ይቅር እንዲላችሁ ጠይቁት። የእግዚአብሔር መንፈስ መንገዳችሁን እንዲለውጥ እና መለወጥ ያለበትን ማንኛውንም ነገር እንዲገልጥ ጠይቁት።

በሕልውናው ስላለው የዘላለም ተስፋ ጌታን ለማመስገን ትንሽ ጊዜ ውሰዱ። እሱን በመታዘዝ ሕይወታችሁን ትኖሩ ዘንድ እንዲረዳችሁ ጠይቁት። በስማችሁ በመስቀሉ ላይ ላደረገው ሥራ አድናቆታችሁን ለማመልከት የታዛዥነት እና የመስጠት ሕይወታችሁን እንዲቀበል ጠይቁት።

## ምዕራፍ 6 -

## ኃጢአት እንዲነግስ አትፍቀዱ

---

ሮሜ 6:12-14

*12 እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፤ 13 ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ። 14 ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና። (ሮሜ 6)*

በመጨረሻው ምዕራፍ፣ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ከክርስቶስ ጋር በሞቱ አንድ ስለመሆናቸው እንዴት እንደነገራቸው ተመልክተናል። መስቀሉ የሕግ ቅጣታችንን መክፈል ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ መገኘት ለክርስቶስ እንድንኖር ኃይል ሰጥቶናል። ዳሩ ግን እነዚህ ሁለት እውነታዎች በፈተና ውስጥ ፈጽሞ እንዳንወድቅ ዋስትና አይሰጡንም። ጌታችን ኢየሱስ

በዚህ ምድር ሲኖር እንደፈተነው ሁሉ ጠላት እንደሚፈትነን እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

የኃጢአታችን ቅጣት ተሸፍኗል። የሚመራን እና የሚያጠነክረን በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው፣ ነገር ግን ጦርነት መካሄዱ ይቀጥላል። የሰይጣን ፍላጻዎች በእኛ ላይ ያተኮሩ ናቸው። እንድንወድቅ ለማድረግ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። አሁንም ንቁ መሆን አለብን። እግዚአብሔር በሰጠን ማዳን ውስጥ ስንኖር፣በመታዘዝ ለመራመድ እና ለመገዛት መምረጥ አለብን። ጠላትን እና ፈተናዎቹን ለመቋቋም መማር አለብን። ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ አማኞች ሲናገር፤ሮሜ 6፡12፡-

*12 እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፤*

በቁጥር 12 ላይ "እንግዲህ" የሚለውን ቃል ተመልከቱ። ይህ ቃል የሚያመለክተው ጳውሎስ በምዕራፍ 6 ከቁጥር 1-11 ላይ ለሮሜ ሰዎች የነገራቸውን ነው። የኃጢአት ቅጣት ተከፍሏል፣ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ህልውና በድል እንዲመላለሱ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። ክርስቶስ የሕይወታቸው ጌታ ነው። በልባቸው ዙፋን ላይ ምንም ነገር የእርሱን ቦታ እንዲወስድ መፍቀድ አልነበረባቸውም።

የሮሜ ሰዎች በሚሞት ሥጋቸው ኃጢአት እንዲነግሥ መፍቀድ አልነበረባቸውም። በሌላ አነጋገር በሕይወታቸው ውስጥ ሥልጣን ሊሰጡት አይገባም። ጳውሎስ ኃጢአት "ለምኞቱ ትታዘዙ ዘንድ አያደርጋችሁ" በማለት ይነግራቸዋል። ኃጢአት በሕይወታችሁ ውስጥ ድርጊቶቻችሁን፣

አስተሳሰባችሁን ወይም ቃላቶቻችሁን የሚገዛበትን በቂ ስልጣን ፈጽሞ አትስጡ። ማንኛውም ተግባር እና አመለካከት ለጌታ ለኢየሱስ ብቻ በመገዛት መሆን አለበት።

ጳውሎስ ይህንን ጉዳይ በሮሜ 6 ላይ መናገሩ አማኙ ለኃጢአትና ለክፉ መሻቱ መገዛት እንደሚቻል ያሳየናል። ሐዋርያው ጳውሎስ የሮሜ ሰዎች 'የሚሞተው ሥጋቸው' የጦር ሜዳ እንደሆነ ያስታውሳቸዋል። ኃጢአት ጦርነቱን ያካሂድ የነበረው በዚያ አካል ውስጥ ሥር ለማግኘት ነበር። ዳሩ ግን እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ይህን ክፉ ነገር እንዲቋቋሙ ኃይል ሰጥቷቸዋል። እያንዳንዱ አማኝ የኃጢያትን ክፉ ምኞት በመቃወም የአካሉን ታማኝነት መጠበቅ እና ለጌታ ማስገዛት አለበት።

ጳውሎስ ሰውነታቸውን ለኃጢአት የዓመፅ መሣሪያ አድርጎ ማቅረብን በተመለከተ የሮሜ ሰዎችን ያስጠነቅቃል፡

*13 ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ (ሮሜ 6)*

"ብልቶቻችሁ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "የሚሞተውን የአካላቸውን ክፍሎች" ነው። በሌላ አነጋገር ምላሳቸው የዓመፅ ቃል መሣሪያ እንዲሆን መፍቀድ አልነበረባቸውም። እግራቸው ወደ ዓመፀኛ ስፍራ እንዲወስዱአቸው መፍቀድ አልነበረባቸውም። ዓይኖቻቸው ዓመጽ በሆኑ ነገሮች ላይ እንዲያተኩሩ መፍቀድ አልነበረባቸውም። አዕምሮአቸውን በኃጢአት አስተሳሰቦች ለመታጠብ እድል መስጠት አልነበረባቸውም።

ጳውሎስ “አቅርቡ” የሚለውን ቃል እዚህ ቁጥር 13 ላይ እንደተጠቀመ አስተውሉ። ለሮሜ ሰዎች የአካል ክፍሎቻቸውን ለኃጢአት ማቅረብ እንደሌለባቸው ተናግሯል። ማቅረብ የሚለው ቃል በጣም አስፈላጊ እና ምርጫ እንዳለን የሚያሳይ ነው። ክፉ የመናገር ፈተና ወደ እኛ ሲመጣ ከሁለቱ አማራጮች አንዱ አለን። የመጀመሪያው ያንን ፈተና መቋቋም ነው። ሁለተኛው አንደበታችንን ለዚያ ክፉ ፈተና አቅርበን ለሥም ማጥፋት ወይም ለሐሜት እንዲውል መፍቀድ ነው። ጳውሎስ በሮም የነበሩትን አማኞች የትኛውንም የአካል ክፍላቸው ለጽድቅ ላልሆነ ዓላማዎች አሳልፈው ለመስጠት የሚደርስባቸውን ፈተና ሁሉ እንዲቋቋሙ አጥብቆ ያሳስባቸዋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሰውነታቸውን ለኃጢአተኛ ዓላማ ከማቅረብ ይልቅ በሮሜ የሚገኙትን አማኞች ለእግዚአብሔር እንዲገዙ ይሞግታቸዋል።

*13 ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።*

ይህ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ማቅረባቸው ሰውነታቸውን ለእርሱ፤ለክብሩና ለሕልውናው አሳልፈው የሚሰጡበት ነበር። ሐዋርያው በሮሜ 12፡1 ላይ እንዲህ ሲል ይገልጻል፡

*1 እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። (ሮሜ 12)*

በዚህ ምድር ሳለን ጌታን ማገልገል ያለብን በእነዚህ ሥጋዊ አካላት ውስጥ ነው። ሁሉም የሰውነታችን ክፍል ለፅድቅ መሣሪያነት ልንጠቀምበት ይገባል። እጆቻችን፣እግሮቻችን፣ ምላሳችን ወይም ሃሳባችን ሁሉ ለጌታ ለኢየሱስ እና ለህይወታችን ላለው ዓላማ በማስገዛት መያዝ አለባቸው። ይህ በእኛ በኩል የታሰበ ጥረት እና ውሳኔ መሆን አለበት። እግዚአብሔር የሥጋዬ ጌታ መሆን አለበት።

ይህ ለእግዚአብሔር መገዛት በፈቃድ መገዛት ቢሆንም፣ ጳውሎስ በሮም ያሉ አማኞች ራሳቸውን ከሞት ወደ ሕይወት የተመለሱ አድርገው እንዲያቀርቡ አሳስቧቸዋል (ሮሜ 6፡13) ። በሌላ አነጋገር፣ ራሳቸውን በነጻ ለእግዚአብሔር ሲያቀርቡ፣ እነርሱ ደግሞ ለእርሱ የጽድቅ ባሪያዎች ይሆናሉ። የኢየሱስ መስቀል ይቅርታንና ምህረትን አምጥቶላቸዋል። የእግዚአብሔር መገኘት፣የመንፈስ ቅዱስ ህልውና፣አሁን በእነርሱ ውስጥ ይኖራል። የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ክርስቶስ ባህሪ እየለወጣቸው እና በአገልግሎቱ ውስጥ ኃይል እየሰጣቸው ነበር። በአዳኛቸው ፊት በሞት ላይ ድል እና የዘላለማዊ ደስታ ዋስትና ተሰጥቷቸዋል። እነዚህ ለእግዚአብሔር እና ለሕይወታቸው ያለውን ዓላማ ለመገዛት አስገዳጅ ምክንያቶች ነበሩ። ይህን ያህል ተሰጥቷቸው ሳለ ከዚህ ያነሰ መሥራት ይችሉ ይሆን?

ሐዋርያው በቁጥር 14 ላይ ኃጢአት ከእንግዲህ በእነርሱ ላይ ሥልጣን እንደማይኖረው በማሳሰብ ይደመድማል ምክንያቱም ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አልነበሩምና።

*14 ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና። (ሮሜ 6)*

በመጀመሪያ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ኃጢአት እንደማይገዛቸው እንደነገራቸው አስተውሉ። “መግዛት” የሚለው ቃል ጌታ እና አለቃ መሆን ወይም መሰልጠን ማለት ነው። ሐዋርያው በቁጥር 12 የጀመረው ለሮሜ ሰዎች በሚሞት ሥጋቸው ኃጢአት እንዳይነግሥ በመንገር ነው። እንዲሁም በዚሁ ሃሳብ ይደመድማል። በሕይወታቸው ውስጥ ኃጢአት ጌታ አይሆንም። አዲስ ጌታ ነበራቸውና፤እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የክርስቶስ መስቀል ከኃጢአት፣ከቅጣቱና ከኃይሉ ነጻ አውጥቷቸዋል።

በሮሜ 6:14 ላይ ደግሞ ጳውሎስ አማኞችን ከጸጋ እንጂ ከሕግ በታች ስላልነበሩ ኃጢአት እንደማይገዛቸው ይናገራል። ይህንን መረዳታችን አስፈላጊ ነው። የሙሴ ሕግ ፍጹም ታዛዥነትን ይጠይቃል። አንድም ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ መሥፈርት ያሟላ ሊሆን አይችልም - ሁሉም ጎድሏልና። የኃጢአት ቅጣት ሞት ነበር። እኛ በሕጉ ፊት ጥፋተኞች ሆነን ቆመናል፣ሞት እና ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም መለያየት ተፈርዶብናል።

ጌታ ኢየሱስ መጥቶ የሕጉን መስፈርቶች አሟልቶልናል። የኃጢአታችንን ቅጣት በራሱ ላይ ወስዶ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ። ይህ የምህረት እና የጸጋ ተግባር አልተገባንም ነበር። ይሁን እንጂ ለኃጢአታችን ቅጣቱን በመውሰድ ጌታ ኢየሱስ በሕግ ላይ ያለንን ዕዳ አስወገደ። ከፍርዱ ነፃ አወጣን። አማኝ የክርስቶስን የመስቀል ስራ እንጂ ወደ ህግ አይመለከትም። ይህ የክርስቶስ ሥራ ኃጢአት በእኛ ላይ ያለውን ስልጣን ገፍፎታል። ከቅጣቱ ነጻ ወጥተናል። በእኛ ላይ ካለው ሥልጣን ነጻ ወጥተናል።

መስቀሉ ሁሉንም ነገር ለውጦታል፡፡ ከኃጢአት አገዛዝ እና እስራት ነጻ አውጥቶ በአዲስ ጎዳና ላይ አድርጎናል፡፡ ይህ ለክርስቶስ በፈቃደኝነት የመገዛት እና በህይወታችን ውስጥ ለሚገዛው ንግስና መንገድ ነው፡፡ በቀራንዮ መስቀል ላይ በተደረገው የክርስቶስ ይቅርታ የተነሳ በመንፈስ ቅዱስ የሚደረግ የአዲሱ ህይወት መንገድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጳውሎስ ይህ ሕይወት ያለ ትግል እንደማይሆን ያስታውሰናል፡፡ ኃጢአት ጥቃቱን ይቀጥላል፡፡ በዘፍጥረት 4፡7 ላይ ጌታ ለቃየን ጠንካራ የማስጠንቀቂያ ቃላት ይሰጠዋል፡-

*7 መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት፡፡ (ዘፍጥረት 4)*

እግዚአብሔር ለቃየን የሰጠው ቃል ዛሬም ይሠራል፡፡ ኃጢያት በደጃችሁ ያደባል፡፡ ምኞቱ ይቃወማችኋል፤ እናንተ ግን ንገሱባት፡፡ ይህ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ያቀረበው ጥያቄ ነው፡፡ የኃጢአታችን ቅጣት ተወግዷል፣ነገር ግን ኃጢአት አሁንም ሊያጠፋን ይፈልጋል፡፡ የእግዚአብሔር ኃይል በውስጣችን አለ፣ ነገር ግን ጠላት ማጥቃቱን ስለሚቀጥል መጠንቀቅ አለብን፡፡ አሁን ከኃጢአት ቅጣት ነጻ ወጥተን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ኃይል ስለተሰጠን፤ራሳችንን ከኃይሉ ልንጠቀም፣ የሚሞተውን የሰውነታችንን ክፍል ሁሉ ለእግዚአብሔር ማቅረብ እና የኃጢአትን መንግሥት መቃወም አለብን፡፡ ንጉሣችን እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ለእርሱ ብቻ እንገዛለን፡፡

**ለምልከታ:**

የኃጢአት ይቅርታ ማግኘታችን ዳግመኛ አንፈተንም ማለት ነውን?

የሚያጋጥማችሁ ፈተናዎች ምንድ ናቸው? የሚሞተው ሥጋችሁን ለኃጢአት መሻት አሳልፋችሁ ስጥታችሁ ታውቃላችሁን?

ዛሬ ሥጋችሁን ለጌታ እና ለፈቃዱ ለማስረከብ ተዘጋጅታችኋልን? ለእርሱ ለመገዛት ፈቃዳችሁን ያልሰጣችሁበት ነገር አለን?

በእናንተ ውስጥ ያለው የክርስቶስ መንፈስ እናንተን፣ አመለካከቶቻችሁንና ምኞቶቻችሁን እንዴት እየለወጠ ነው? በኃጢአት ላይ ድልን እየሰጣችሁ ያለው እንዴት ነው?

**ለጸሎት:**

በዚህ ምድር ላይ ለክብሩ ሥጋችሁን በሁሉም ክፍሎቹ ለጌታ ለማስረከብ ያላችሁን ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ ትንሽ ጊዜ ውሰዱ::

ለእርሱ ለመገዛት ፈቃደኛ ያልሆናችሁበትን ማንኛውንም ነገር እንዲገልጽላችሁ ጌታን ጠይቁት:: ይህንን የሕይወታችሁን ክፍል ለእርሱ ለመስጠት ፈቃደኛነት እንዲሰጣችሁ የእግዚአብሔርን መንፈስ ጠይቁት::

በክርስቶስ የመስቀል ሥራ በሕይወታችሁ ከኃጢአትና ከሞት አገዛዝ ነፃ ስለወጣችሁ ጌታን አመስግኑት::

አሁንም ደህንነትን ለማግኘት ብቁ ለመሆን እየሞከራችሁ ከሆነ፣ ጌታ በመስቀል ላይ ምን እንደተከናወነ በይበልጥ እንዲያሳያችሁ ለመጸለይ ትንሽ ጊዜ ወሰዱ:: በክርስቶስ መስቀል ላይ የተፈጸመውን እውነታ ለእናንተ በግላችሁ እውነት እንዲያደርግላችሁ የእግዚአብሔርን መንፈስ ጠይቁ::

## ምዕራፍ 7 -

## ከጸጋ በታች

ሮሜ 6:15-19

*15 እንግዲህ ምን ይሁን? ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላይደለን ኃጢአትን እንሥራን? አይደለም። 16 ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፥ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ። 17-18 ነገር ግን አስቀድማችሁ የኃጢአት ባሪያዎች ከሆናችሁ፥ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለ ታዘዛችሁ፥ ከኃጢአትም አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለ ተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። 19 ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኵስነትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ፥ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ። (ሮሜ 6)*

በሮሜ 6፡12-14 ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በሚሞተው ሥጋቸው ላይ ኃጢአት እንዳይነግሥ ያስተምራቸዋል። በክርስቶስ ሥራ ከግዛቱና ከሥልጣኑ ነፃ ወጥተዋል። ጳውሎስ በመቀጠል በሮሜ 6፡14 ላይ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች እንዳልሆኑ ይነግራቸዋል። ከህግ በታች መሆን ማለት ምን ማለት ነው? በአጠቃላይ በሕጉ ሥር መሆንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስላለው ወሳኝ እና ገላጭ ሃተታ እንዲህ ይላል፡

(በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለው ትችት እና ገላጭ ሃተታ ከሕግ በታች መሆንን በተመለከተ እንዲህ ይላል:)

> *"ከሕግ በታች መሆን፤መጀመሪያ፤ለሚጠይቀው ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ታዛዥ መሆን፤እና እነዚህን በመጣስ በሚመጣው እርግማን ሥር መሆን ነው" (Jamieson, Robert; Fausset A.R.; Brown, David: Commentary Critical and Explanatory on the Whole Bible: Commentary on Romans 6:14, Laridian, 1871)*

በብሉይ ኪዳን የተቋቋመው የሕግ ሥርዓት፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን ነገሮች ያስቀመጠበት እና እነዚህን መስፈርቶች እንዲከተሉ ወይም ሕግን በመጣስ ቅጣት እንዲቀጡ የሚጠብቅበት ሥርዓት ነው። የእግዚአብሔርን ሕጎች በመጣስ የሚቀጣው ቅጣት ከባድ ነበር። በዘፍጥረት 3 ላይ እግዚአብሔር ለአዳም የተናገረውን አድምጡ፡-

*16 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ 17 ነገር ግን መልካምንና ክፉን*

*ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና። (ዘፍጥረት 2)*

እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ እና የተከለከለውን የዛፍ ፍሬ በመብላቱ የአዳም ቅጣት ሞት ነበር።

በነብዩ ሕዝቅኤል ሲናገር፤ጌታ እንዲህ ይላል፡

*4 እነሆ፥ ነፍሳት ሁሉ የእኔ ናቸው፤ የአባት ነፍስ የእኔ እንደ ሆነች ደግሞ የልጅ ነፍስ የእኔ ናት፤ ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች። (ሕዝቅኤል 18)*

በሕግ ስርአት እግዚአብሔር ለሞት እና ስቃይ ፍጹም መታዘዝን ጠይቋል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይናገራል፡

*23 የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው። (ሮሜ 6)*

ሐዋርያው ያዕቆብ አንድ ሰው የትኛውን ሕግ ቢጥስ ምንም ለውጥ እንደሌለው ያስታውሰናል። አንድ ሰው አንዱን ሕግ እንኳን ቢጣስ እሱ ወይም እሷ በእግዚአብሔር ፊት ጥፋተኛ ይሆናሉ።

*10 ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤አታመንዝር ያለው ደግሞ፦ አትግደል ብሎአልና፤ 11 ባታመነዝርም፥ ነገር ግን ብትገድል፥ ሕግን ተላላፊ ሆነሃል። (ያዕቆብ 2)*

አንድ ነፍሰ ገዳይ በዳኛው ፊት ቆሞ “ሚስቴን እወዳታለሁ እናም ለእሷ ታማኝ ሳልሆን ቀርቼ አላውቅም። ጎረቤቴን ስለገደልኩ ልቀጣ አይገባኝም” ብሎ ተናገረ ብላችሁ አስቡ፤ ዳኛው እንዲህ ባለው ምክንያት ይስቃል፡፡ አንድ ሰው የቱንም ያህል ጥሩ ቢሆን በማንኛውም ጊዜ ሕጉን ከጣሰ የውጤቱ ገፈት ቀማሽ ሊሆን ይገባል፡፡ አንድ ታማኝ እና ለጋስ የሆነ ነጋዴ ወደ ስራ ሲሄድ የፍጥነት ገደቡን ሲጥስ አሁንም በፍጥነት የማሽከርከር ቅጣቱን መክፈል ይኖርበታል፡፡

የእስራኤል አምላክ ፍጹም አምላክ ነው። በዘዳግም 32 እንዴት እንደተገለጸ አድምጡ፦

*3 የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁና፤ ለአምላካችን ታላቅነትን ስጡ። 4 እርሱ አምላክ ነው፤ ሥራውም ፍጹም ነው፤መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፤የታመነ አምላክ፥ ክፋትም የሌለበት፥ እርሱ እውነተኛና ቅን ነው። (ዘዳግም 32)*

በ2ኛ ሳሙኤል 2 ላይ ሲጽፍ፤ዳዊት እንዲህ ይላል፡

*31 የአምላክ መንገድ ፍጹም ነው፤ የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው፤ በእርሱ ለሚታመኑት ሁሉ ጋሻ ነው። (2ኛ ሳሙኤል 22)*

የእግዚአብሔር መንገዶች ፍጹም ናቸው እና ቃሉም ፍጹም እና እውነት ነው። ፍጹም አምላክ እንደመሆኑ መጠን ኃጢአት በእርሱ ዘንድ አስጸያፊ ነው። በጣም ከባድ የሆነው ቅጣት የሚተላለፈው ኃጢአት ለሠሩ እና በዓላማው ላይ በሚያምፁ ሰዎች ላይ ነው። ኢየሱስ በማቴዎስ 5፡48 ላይ እንዲህ ይላል፦

*48 እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ። (ማቴዎስ 5)*

የእግዚአብሔር ሕግ "ያለ ነውር" መሆንን ይጠይቃል፡

*13 አንተ ግን በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ሁን። (ዘዳግም 18)*

ከእርሱ ጋር ፍጹም በሆነ ኅብረት እንድንመላለስ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው። ኃጢአት በመካከላችን መቆም የለበትም። እግዚአብሔር በሕጉ የምንኖርበትን መስፈርት አስቀምጧል። ለዚያ መስፈርት በመታዘዝ መሄድ ከእግዚአብሔር ጋር በሕብረት መመላለስ ነው። ከየትኛውም መንገዱ መመለስ የውጤቱን መከራ መቀበል ነው።

የሕጉ መስፈርቶች በሞት ፍርድ ሥር የኖሩትን እያንዳንዱን ሰው አስቀምጠዋል። ማንም ሰው ፍጹም ሕይወት መኖር አይችልም። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡

*23 ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ (ሮሜ 3)*

በጸጋው፣ ጌታ እግዚአብሔር ለኃጢአት የይቅርታ ዘዴን አቀረበ። እንስሳን በደለኛውን ሰው በመተካት የኃጢአት ቅጣት የሚከፈልበት የመሥዋዕት ሥርዓት ዘርግቷል። አንድ እንስሳ ለጥፋተኛው ሰው ቅጣቱን ለመክፈል በመሠዊያው ላይ ይገደላል። የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ኃጢአት ይቅር ለማለት በሚልዮን የሚቆጠሩ በጎች፣ፍየሎችና ወይፈኖች በእስራኤል መሠዊያዎች ላይ ተሠዉተው ነበር። ይህ የመሥዋዕት

ሥርዓት ለአማኞች እፎይታን ቢሰጥም፣ ኃጢአታቸውን ግን አያስወግደውም ነበር። የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ብሉይ ኪዳን የመሥዋዕት ሥርዓት እንዲህ ይላል።

*1 ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም። 2 እንደዚህማ ባይሆን፥ የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በሕሊናቸው ኃጢአትን ስላላወቁ ማቅረብን በተዉ አልነበረምን? 3 ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ፤ 4 የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና። (ዕብራውያን10)*

በእነዚህ ጥቅሶች ላይ የዘወትር የእንስሳት መሥዋዕት አምላኪውን ፍጹም እንዳላደረገው አስተውሉ (ቁጥር 1) ። የእነዚህ ወይፈኖችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን ከቶ ሊያስወግድ አልቻለም (ቁጥር 4) ። ፍጽምና የጎደላቸውና ኃጢአተኛ ሰዎች በሕይወት እንዲቀጥሉ በዚያ ዘመን የሞቱትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ እንስሳትን አስቡ።

ለተወሰኑ አመታት በሆዴ ውስጥ የአሲድ ችግር አጋጥሞኝ ነበር። ይህ በጉሮሮዬ ውስጥ እና ከሆድ በታች ባለው የሆድ ክፍል ውስጥ ማቃጠል ያስከትል ነበር። ማቃጠሉን የሚያስታግስ መድሐኒት እወስድ ነበር፤ነገር ግን ይህ መድሐኒት የችግሩን ምንጭ አይፈውስም። በሕጉ መሠረት ለእስራኤል እንዲህ ነበር። የኃጢአት ሕመም መኖሩ ይቀጥላል። የመሥዋዕቱ ሥርዓት ከእግዚአብሔር ቁጣ እፎይታን አምጥቷል ነገር ግን የችግራቸው መንስኤ የሆነውን ኃጢአት አላስወገደም ወይም አልፈወሰውም።

ጌታ ኢየሱስ ግን ይህን ሁሉ ለወጠው። ነፍሱን በመስቀል ላይ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ እንደሌላው መስዋዕት ያልሆነውን አቀረበ። የዕብራውያን ጸሐፊ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር፦

*11 ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፤ 12 እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፥ 13 ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል። 14 አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና። (ዕብራውያን 10)*

ጌታ ኢየሱስ ነፍሱን ለአንድ ጊዜ የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። በዕብራውያን 10: 14 መሠረት ይህ መሥዋዕት “የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና” ይላል። ይህ ማለት ዳግመኛ ለኃጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት አያስፈልግም ማለት ነው። ይህ የጌታ ኢየሱስ የአንድ ጊዜ መስዋዕትነት ወደ እርሱ ለሚመጡት ሰዎች ሁሉ ቅጣትን ሙሉ በሙሉ ለመክፈል ብቻ ሳይሆን ወደ እርሱ የሚመጡትንም ፍጹም የሚያደርግ ነው። በጌታ ኢየሱስ መስዋዕትነት ምክንያት አሁን በእኔና በእግዚአብሔር መካከል የሚቆም ምንም ነገር የለም። የሰራሁት ወይም የምሰራው ኃጢአት ሁሉ በዚያ የጌታ ኢየሱስ የአንድ ጊዜ መስዋዕት ተሸፍኗል። የዕብራውያን 10 ጸሐፊ በመቀጠል እንዲህ ይላል፡

*15 መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ስለዚህ ይመሰክርልናል፤ 16 ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ፤ በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እጽፈዋለሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ፥17 ኃጢአታቸውንና ዓመጻቸውንም ደግሜ*

*አሳስብም ይላል። 18 የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ፥ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም። (ዕብራውያን 10)*

የእግዚአብሔር መንፈስ የክርስቶስን ይቅርታ በተቀበሉት ህይወት ውስጥ በአዲስ መንገድ ለመስራት ነጻ ነበር። የክርስቶስ በሆኑት ሰዎች ልብ እና አዕምሮ ላይ የእግዚአብሔርን ህግ አስቀመጠ። የእግዚአብሔር ዓላማ በድንጋይ ጽላት ላይ አልተጻፈም። የተጻፈው በመንፈስ በተሞላ አማኝ ዘረ-መል ላይ ነው። በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞሉት በእግዚአብሔር ዓላማ ለመመላለስ ይፈልጋሉ። እግዚአብሔርን እና የእርሱን መገኘት የሚናፍቁ አዲስ ልቦች ተሰጥቷቸዋል። ነገሮችን ከዓለማዊ እይታ የማይመለከት ነገር ግን መንፈሳዊ አመለካከት ያላቸው አዲስ አእምሮ ተሰጥቷቸዋል። ይህ አዲስ ልብ እና የክርስቶስ ሃሳብ የእግዚአብሔር መንፈስ ስራ ነበር። ይቅርታ የተደረገላቸው እና አዲሱን የሕይወት መንፈስ የተቀበሉት ከዚህ በኋላ ያው አይሆኑም። በክርስቶስ ሞትና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተለውጠዋል።

አሁን ወደ ሮሜ ሰዎች 6፡15 ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ተናገረው ነገር እንመለስ።

*15 እንግዲህ ምን ይሁን? ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላይደለን ኃጢአትን እንሥራን? አይደለም። (ሮሜ 6)*

የክርስቶስ ሞት ከሕግ ጋር ያለንን አቋም ለውጦታል የሚለውን ሃሳብ ውድቅ ያደረጉ ሰዎች ነበሩ። የሕጉን መስፈርት ካስወገድን አማኙ የተቀደሰ ሕይወት እንዲኖር ምንም ዓይነት ተነሳሽነት እንደማይኖረው ያምናሉ።

ይህ የአሮጌው ሥጋ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን አማኙ አዲስ ሆኗል። እሱ ወይም እሷ የእግዚአብሔር ህግ በልባቸው ተጽፏል። የእግዚአብሔር መንፈስ እየወቀሰ እና ኃይልን እየሰጠ በአማኙ ውስጥ ይኖራል። ጳውሎስ በሮሜ 6፡16 እንዲህ ሲል ይቀጥላል፡-

*16 ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፥ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ። 17-18 ነገር ግን አስቀድማችሁ የኃጢአት ባሪያዎች ከሆናችሁ፥ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለ ታዘዛችሁ፥ ከኃጢአትም አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለ ተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።*

ሐዋርያው የሮሜ ሰዎች ከኃጢአትና ከሞት ቅጣት ነፃ ለመውጣት ራሳቸውን ለክርስቶስ ያቀርቡ ዘንድ እንደሚገባቸው አሳስቧቸዋል። ይህንንም በማድረግ፤ሕይወታቸውን ለእርሱ እና በእነርሱ ውስጥ ላለው የመንፈሱ ሥራ አቀረቡ። ለክርስቶስ ጌትነት እና ለመንፈሱ ተገዙ። ታማኝነታቸው ለእርሱ ነበርና። ጌታቸው እና አለቃቸው ነበር።

ይህ ታማኝነት በግዳጅ አልነበረም። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ለተሰጡለት የትምህርት ደረጃ “ከልባቸው የታዘዙ” እንደነበሩ አሳስባቸው ነበር (ሮሜ 6፡17) ። ይህ የልብ ታዛዥነት ልባቸውን እየለወጠ አዲስ መሻት ላኖረው የመንፈስ ስራ ማስረጃ ነው። የኃጢአትን ስርየት እና የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የሚያውቁ፣ በፈቃዳቸው ለክርስቶስ አገልጋዮች ይማረካሉ።

የክርስቶስ ይቅርታ ሕይወትን የሚለውጥ ነው። የእግዚአብሔርን መንፈስ የማጽዳት ሥራ የሚያውቁ ሰዎች ከእንግዲህ ያው አይሆኑም።

*17 ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። (2ኛ ቆሮንቶስ 5)*

አንድ ሰው በክርስቶስ ይቅር ተብሎ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆኖ ሳለ፤ዳሩ ግን በፈቃደኝነት በኃጢአት ለመጽናት መፈለግ ለጳውሎስ የማይታሰብ ነበር። አማኙ መፈተኑ እንደሚቀጥል ያውቅ ነበር፣ ነገር ግን ፈተናን የሚያሸንፍበት ኃይል በውስጡ አለ። የእግዚአብሔር መንፈስ ለአማኙ የክርስቶስን አዕምሮ በመስጠት ያስችለዋል። ይህንን ይቅርታ እና የመንፈስ ማደርያ የሚያውቅ አማኝ ሁሉ ለእግዚአብሔር መገዛት እና ዓላማውን በሕይወታቸው እንዲፈጽም የመፍቀድ ኃላፊነት አለባቸው።

*19 ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኵስነትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ፥ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ። (ሮሜ 6)*

የክርስቶስ ይቅርታ አዲስ ሕይወት ይሰጠናል። ልባችንን እና አዕምሯችንን ይለውጣል ነገር ግን በመታዘዝ መመላለስ እና ለእግዚአብሔር መገዛት አለብን በሚል ግዴታ ሥር ያደርገናል። ይህንን በራሳችን ልናከናውን አልተተውንም። የክርስቶስ መንፈስ በመታዘዝ እንዲሁም በመገዛት እንመላለስ ዘንድ ለማስተማር እና ፍላጎትን ለማነሳሳት በልባችን ሊኖር ይመጣል። ባለመታቀብ ራሳቸውን ለአዳኛቸው ፍጹማን

አድርገው ለክብሩ ጥቅም መዋል በክርስቶስ መንፈስ የተሞሉ ሰዎች ልብ ነው። በጸጋ እና በይቅርታ ሥር መኖር የኃጢአት ፈቃድ አይደለም። ይልቅ፤እንደ አማኞች ለጥሪያችን በሚገባን መንገድ ላይ እንመላለስ ዘንድ ጥልቅ መነሳሳትን በውስጣችን ይፈጥርልናል።

**ለምልከታ**:

ከሕግ በታች መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

ከሕግ በታች ላለ ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድን ነው? ይህንን መስፈርት ማሟላት እንችላለን?

የብሉይ ኪዳን የመሥዋዕት ሥርዓት የኃጢአትን ሥር የሰደደ ችግር አስወገደ? አብራሩ።

የክርስቶስ ሥራ በብሉይ ኪዳን ሕግ ሥር ከነበረው ከእንስሳት መሥዋዕት የሚለየው እንዴት ነው?

በዕብራውያን 10:16 መሰረት የመንፈስ ስራ በአማኙ ውስጥ ምንድ ነው?

ጌታን እና ይቅርታውን ስታውቁ በሕይወታችሁ እና በአመለካከታችሁ ላይ ምን ለውጥ ተፈጠረ?

አማኞች ኃጢአት ለመሥራት ይፈተናሉን? እንደ አማኞች በኃጢአት ረክተን መኖር እንችላለን?

**ለጸሎት**:

ከጸጋ በታች እንጂ ከህግ በታች ስላልሆናችሁ ጌታን አመስግኑት።

የኃጢአት ችግር በጌታ በኢየሱስ ማንነት ስለተፈታ ጌታ አመስገኑ።

በህይወታችሁ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን መንፈስ ሥራ ለማወቅ ትንሽ ጊዜ ውሰዱ። ስለሚያስተምራችሁ እና ልባችሁን እየለወጠ ስላለ አመስግኑት።

በሕይወታችሁ ውስጥ ፈተናዎች አሉ? የእግዚአብሔርን መንፈስ የአብን ዓላማ እንዲያሳያችሁ እና በመንገዱ ትሄዱ ዘንድ የበለጠ መሻት እንዲሰጣችሁ ጠይቁት።

## ምዕራፍ 8 -

## የሐጢአት ፍሬ እና ነጻ ስጦታ

---

ሮሜ 6:20-23

*20 የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና። 21 እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁ? የዚህ ነገር መጨረሻው ሞት ነውና። 22 አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ፥ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው። 23 የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው። (ሮሜ 6)*

በዘመናችን ለነጻነት ዋጋ እንሰጣለን። ለነጻነት የሚታገሉ ጀግኖቻችን ናቸው። ባርነት እና እስራት በማንኛውም መልኩ እንደ ክፉ ይታሰባል። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን ማንም ሰው በቃሉ ፍፁም ነጻ ሊሆን እንደማይችል ያስታውሰናል። ሁላችንም በብዙ ምክንያቶች ተሳስረናል። ሥጋችን ጥረታችንን ይገድባል። ግዴታዎቻችን እና ኃላፊነቶቻችን ጊዜያችንን ይገድባሉ። ባህላችን እራሳችንን እንዴት እንደምንገልጽ

ይፈትሻል። ጌታ ኢየሱስ ኃጢአት ብዙ ባሪያዎች ያለው ጌታ እንደሆነ አስተምሯል፡-

*ኢየሱስ መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባርያ ነው። (ዮሐንስ 8)*

ባሪያ በሌላ ቁጥጥር ውስጥ ያለ ወይም የተገዛ ማለት ነው። ጳውሎስ በቁጥር 20 ላይ የሮሜ ክርስቲያኖችን በአንድ ወቅት “የኃጢአት ባሪያዎች” እንደነበሩ ያስታውሳቸዋል።

*20 የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና። (ሮሜ 6)*

በቁጥር 20 ላይ የሮሜ ሰዎች የኃጢአት ባሪያዎች እንደመሆናቸው መጠን “በጽድቅ ረገድ ነጻ” እንደነበሩ አስተውሉ። "ነጻ" የሚለው ቃል የሚናገረው ስለ ነፃነት ወይም መለያየት ነው። በሌላ አነጋገር፣ የሮሜ ሰዎች፣የኃጢአት ባሪያዎች ሆነው፣ከጽድቅ ተለይተው ነበር። በኃጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔርን ማስደሰት አልቻሉም ነበር። ለእግዚአብሔር ጠላቶች ነበሩ በዚህም ምክንያት ሁሉም በፍርድ እና በቁጣው ስር የወደቁ ነበሩ።

በሮሜ 6፡21 ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የኃጢአት ባርነት ውጤትን በግልፅ አሳይቷቸዋል።

*21 እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁ? የዚህ ነገር መጨረሻው ሞት ነውና።*

***እፍረት***

በቁጥር 21 ላይ የኃጢአት ባርነት ፍሬ እፍረት መሆኑን አስተውሉ። ይህ ነውር እንዳልገባቸው ለማወቅ በክፉዎች መካከል የተደረገ በቂ ንግግር ሰምቻለሁ። ወንዶችና ሴቶች በሥነ ምግባር ብልግናና በስካር ሲመኩ ሁላችንም ሰምተናል። ዳሩ ግን እነዚህ ድርጊቶች፣ለእግዚአብሔር ቅድስና ብርሃን ሲጋለጡ ምን እንደሆኑ እናያቸዋለን። ነውርን የምንገልጸው ተቀባይነት ካለው እና ጥሩ ከሆነው መስፈርት ጋር በመመዘን ነው። ኃጢአት እግዚአብሔር ያስቀመጠው ክብር ዘንድ መድረስ አለመቻል ነው። ሁሌም ወደ ውርደት ይመራናል።

## ሞት

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በቁጥር 21 ላይ ኃጢአት ወደ እፍረት ብቻ ሳይሆን ወደ ሞትም እንደሚመራ ተናግሯል። ጳውሎስ እዚህ የተናገረው ሞት እንደ ሥጋ ሞት ብቻ መታየት የለበትም። አማኞችም ሆንን የማናምን ብንሆን ሁላችንም እንሞታለን። እዚህ የተነገረው ሞት ከእግዚአብሔር ሕይወት መለየትን ነው። በኃጢአት ባርነት የተያዙ ሰዎች የክርስቶስን አስፈላጊነት አይረዱም። ድምፁን አያውቁም፣ወይም በሕይወታቸው ውስጥ የእርሱን ግላዊ እና ሕይወት ሰጪ መገኘት አይለማመዱም - ለእግዚአብሔር ነገሮች የሞቱ ናቸውና። ከዚህ ሞት በኋላ ያለ የወደፊት እውነታ አለ። በዘላለም ውስጥ፣ ከክርስቶስ መገኘት እና ከበረከቱ ይለያያሉ።

የኃጢአት ባርነት ወደ ውርደትና ሞት ይመራል። ይህ ነጻ ልንወጣበት የሚገባን ባርነት ነው። ከኃጢአት ቅጣት ነጻ የሚያወጣን ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው። እኛን ባሪያ አድርጎ የሚይዘንን ኃጢአት የሚያስወግድ እርሱ ብቻ ነው።

ጳውሎስ በቁጥር 22 ላይ የተናገረው ሌላ ዓይነት ባርነት ደግሞ አለ። በሮሜ 6፡19 ሐዋርያው የሮሜ ሰዎች ራሳቸውን የጽድቅ ባሪያዎች አድርገው እንዲያቀርቡ ሞግቷቸዋል። ጳውሎስ እዚህ የሚናገርለት ባርነት በፈቃደኝነት መገዛትን ነው። ለእግዚአብሔር ባሪያዎች እንድንሆን ራሳችንን "ማቅረብ" አለብን። የእግዚአብሔር ባሪያዎች እንድንሆን ከፈለግን መሟላት ያለብን መሥፈርት እንዳለ ሮሜ 6:22 ላይ ተመልከቱ።

*22 አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ፥ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፤መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው።*

የእግዚአብሔር ባሪያ መሆን የሚፈልጉ ሁሉ መጀመሪያ ከቀድሞ ጌታቸው ነጻ መውጣት አለባቸው። የእግዚአብሔር ባሪያ መሆን የሚችሉት ከኃጢአት ነጻ የሆኑ ብቻ ናቸው። እንደ ጌታ፣እግዚአብሔር ታማኝነታችንን ይፈልጋል። ራሳችንን ለእርሱ ለማቅረብ ከኃጢአት በመመለስ እርሱን ማክበርን የሕይወታችን መሻት ማድረግ አለብን። ኃጢአትን ካገለገልን የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን አንችልም።

በቁጥር 22 ላይ ሊያመልጠን የማይገባ ሌላ ዝርዝር ነገር አለ። ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች ከኃጢአት ነጻ ሲወጡ የእግዚአብሔር ባሪያዎች እንደሆኑ ይነግራቸዋል። በዚህ ዓለም ውስጥ ሁለት ጌቶች ብቻ እንዳሉ ይናገራል - ኃጢአት እና እግዚአብሔር። የእግዚአብሔር አገልጋይ ካልሆንን የኃጢአት ባሪያ ነን። ከኃጢአት ነጻ ከወጣን በእግዚአብሔር ዘንድ አዲስ ጌታ አለን እናም በእርሱ ዘንድ ግዴታ አለብን። አንዱን ወይም

ሌላውን እናገለግላለን፤መካከለኛ ቦታ የለም፤ወይም ሁለቱንም ማገልገል አንችልም።

ሁላችንም ጌታ አለን። ያ ጌታ እግዚአብሔር ወይም ኃጢአት ነው። ሕይወታችን የሚገዛው እና የምንመራው በምናገለግለው ጌታ ነው። ኃጢአትን እንደ ጌታ ስናደርግ ለውርደትና ለሞት የሚመራን ሲሆን፣እግዚአብሔር ጌታችን ሲሆን ውጤቱ በጣም የተለየ ነው። ሮሜ 6፡22 እግዚአብሔርን እንደ ጌታችን አድርገን መቀበል ውጤቱ ሁለት እንደሆነ ይነግረናል።

***መቀደስ***

በመጀመሪያ፣እግዚአብሔር ጌታችን ሲሆን፣መቀደስን እንለማመዳለን (ሮሜ 6፡22) ። መቀደስ የእግዚአብሔርን መልክ እንድንመስል የተቀረፅንበት ሂደት ነው። ሕይወታችን ኃጢአትን ከማሸነፍ እና ከቅዱስ ባህርይ መፈጠር ጋር የተያያዘ ነው። ይህ አመለካከታችንን እና አስተሳሰባችንን የሚለውጥ በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ነው። እርሱ ስለ ኃጢአት ይወቅሰናል እንዲሁም ክርስቶስን እንድንመስል ያደርገናል። የኃጢአት አገልጋይ የመሆን ፍሬ ሃፍረት ሲሆን የእግዚአብሔር አገልጋይነት ፍሬ በባህሪ፣በአስተሳሰብና በድርጊት ቅዱሳን መሆናችን ነው። ይህ ፍፁም ነን ማለት አይደለም። መቀደስ የሕይወት ዘመን ሂደት ነው። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በየዕለቱ

የኢየሱስ ክርስቶስን መልክ እንድንመስል የመውቀስ፣የማስቻል እና የመለወጥ ሥራውን ይቀጥላል።

## ሕይወት

የእግዚአብሔር ባሪያ የመሆን ሁለተኛው ፍሬ ሕይወት ነው። ሕይወት፣ ከዚህ አንፃር፣እንደ ሥጋዊ ሕይወት ብቻ መታየት ያለበት ሳይሆን በተለይ መንፈሳዊ ሕይወት ነው። ይህ በእኛ ውስጥ ለመኖር የሚመጣው ሕይወት የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወት ነው። እግዚአብሔርን ለመስማት ጆሮአችንን ይከፍታል። የእግዚአብሔርን ዓላማ እንድንረዳ አዕምሮአችንን ይከፍታል። እሱ ኃይልን ይሰጠናል እንዲሁም ለመንፈሳችን ሕይወትን ይሰጣል። ኃጢአት ወደ ሞት እና ከእግዚአብሔር መለያየት ሲመራ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚሰጠን ሕይወት በእግዚአብሔር ኃይል እና መገኘት ይሞላናል። ከጨለማ መንግሥት ወደ ብርሃን ዓለም ይለውጠናል። አዕምሯችን ከኃጢአት እስራት ነጻ ወጥቶ የእግዚአብሔርን እና የዓላማውን እውነታ እንለማመዳለን። ከዚህ በፊት ያላየነውን እናያለን። ከዚህ በፊት ሰምተን የማናውቀውን እንሰማለን። ከዚህ በፊት ያላደረግነውን ለማድረግ ኃይል ተሰጥቶናል። ይህ ሁሉ የሆነው በእኛ ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር ሕይወት ምክንያት ነው። ከአሁን በኋላ ያው አይደለንምና።

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ያስተማረውን በማጠቃለል ይህንን ክፍል ይዘጋል፡-

*23 የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው። (ሮሜ 6)*

በመሠረታዊ ደረጃ፣ ሐዋርያው ኃጢአት ወደ ሞት እንደሚመራ፣እግዚአብሔር ግን የዘላለም ሕይወትን እንደሚሰጥ ለሮሜ ሰዎች ይነግራቸዋል። ሆኖም ጳውሎስ በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተጠቀመባቸውን ቃላት አስተውሉ። ስለ ኃጢአት ደሞዝ እና ስለ እግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ይናገራል። በደመወዛችን እና በነጻ ስጦታ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ።

ደሞዝ በሥራ የሚገኝ ነው። የተሰጠን በሰራናቸው ሥራዎች ምክንያት የተገባን ስለሆነ ነው። ለምሳሌ በሳምንት አርባ ሰዓት ሰርተን ሊሆን ይችላል፣ እና አለቃችን ለጥረታችን ክፍያ ሊከፍለን ገንዘብ ይሰጠናል። ደሞዝ በሥራ የሚገኝ ነውና።

ዳሩ ግን ነጻ ስጦታ በሥራ የሚገኝ አይገኝም። ነጻ መሆኑ ጨርሶ የሠራንበት ነገር አለመሆኑን ያመለክታል።

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ምን እየነገራቸው ነው? ሞት በሥራ የተገኘ ነው እያለ ነው። የተግባራችን፣የአስተሳሰባችን እና የሃሳባችን ውጤት ነው። የሞት ቅጣት የምንቀበለው ስለተገባን ነው። ማናችንም ለእግዚአብሔር እና እርሱ ለሕይወታችን ያለውን ዓላማ ፍጹም በመታዘዝ እንደምንኖር መናገር አንችልም። ሁላችንም እግዚአብሔር ለሕይወታችን ካለው ክብር ጎድለናል። እግዚአብሔር ሁልጊዜ በፍርዱ ፍትሃዊ ነው። በሞት እርግማን ውስጥ ከገባን፤በራሳችን ስራ ነው። የኃጢአተኛ ተፈጥሮአችንን ፍሬ እናፈራለን።

የኃጢአት ቅጣት በሥራ የተገኘ ቢሆንም፣ነገር ግን የዘላለም ሕይወት ስጦታ ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት በፍፁም በሥራ ሊገኝ አይችልም፡፡ እንደ ባሪያዎች፤ጌታችን ሆኖ በኃጢአት እስራት ውስጥ ነበርን፡፡ አንድ ባሪያ ከጌታው ነጻ የሚወጣው ሌላ ጌታ ከገዛው ብቻ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ያደረገው ይህንን ነው፡፡ የኃጢአታችን ዋጋ በመስቀል ላይ ከፈለ፡፡ ከሞትና በሕይወቴ ካለው እርግማን ነጻ እወጣ ዘንድ ቦታዬን ወስዶ ሙሉ ዋጋውን ከፍሎኛል፡፡ ደሞዝ በሥራ ሲገኝ፣ በስጦታ ማድረግ የምትችሉት ብቸኛው ነገር መቀበል ብቻ ነው፡፡

ብዙዎች እንደ ነጻ ስጦታ በተሰጠው የዘላለም ሕይወት ሃሳብ ላይ ይሳለቃሉ፡፡ ይህ ይቻላል ብለው ማመን አይችሉም፡፡ ሌሎች ደግሞ በኩራታቸው እንዲህ ያለውን ስጦታ ለመቀበል አሻፈረኝ ይላሉ፡፡ አሁንም በመልካም ስራቸው እና ጥረታቸው ይህንን ዘላለማዊ ህይወት እና ይቅርታ ማግኘት እንደሚችሉ የሚምኑ ሰዎች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የዘላለም ሕይወት በሥራ እንደማይገኝ ተናግሯል - ይህም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው፡፡

ጳውሎስ ከፊታችን ሁለት አማራጮችን አስቀምጧል፡፡ የሁላችንንም ህይወት እና እጣ ፈንታ የሚወስን ጌታ እንዳለን ያሳስበናል፡፡ ወይ የኃጢአት ባርያ ነን ወይ የእግዚአብሔር ባሪያ ነን፡፡ የኃጢአት ባሪያ መሆን ውጤቱ ውርደትና ሞት ነው፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆንን ግን ቅድስናን እና ሕይወትን እናገኛለን፡፡

የኃጢአት ባሪያ በመሆን የሚመጣው የሞት ቅጣት በሥራ የተገኘ እና የሚገባን ነው፡፡ የጽድቅ ባሪያ ከመሆን የሚገኘው ሕይወት በነጻ በእግዚአብሔር የተሰጠን ነው፡፡ የሚያስፈልገን

እሱ የሚያቀርበውን መቀበል ብቻ ነው:: ዛሬ የማን ባሪያ ናችሁ?

**ለምልከታ**:

እኛ በእውነት ነጻ ነን? አብራሩ::

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ የተናገራቸው ሁለቱ ጌቶች እነማን ናቸው? ሌላ ጌታ አለን?

የኃጢአት ባሪያ መሆን ውጤቱ ምንድ ነው?

የእግዚአብሔር ባሪያ መሆን ውጤቱ ምንድ ነው?

እግዚአብሔር ለእርሱ ለሚገዙት የሚሰጠውን ሕይወት እንዳገኘን እንዴት እናውቃለን? ይህ ሕይወት በእኛ ውስጥ ምን ለውጥ ያመጣል?

በኃጢአት የጠፉ ሰዎች ቅጣት ይገባቸዋልን? እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋልን?

የዘላለም ሕይወትን የሚያገኙ የእነርሱ ስጦታ ይገባቸዋልን? እግዚአብሔር ይህን ስጦታ ይሰጣቸዋልን?

ሰዎች የዘላለም ሕይወትን ስጦታ እንዳያገኙ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

**ለጸሎት**:

ዛሬ እውነተኛ ጌታችሁ ማን እንደሆነ እንዲያሳያችሁ ጌታን ጠይቁት።

ለሚቀበሉት የዘላለም ሕይወትን ስላቀረበ ጌታ ይመስገኑ።

ጌታን ዛሬ ካወቃችሁት አሁን እና ለዘላለም ስለሰጣችሁ ሕይወት አመስግኑት።

ጌታን የማታውቁ ከሆነ እንዲቀበላችሁ ጠይቁት። የዘላለምን ሕይወት ስጦታ ከእጁ ተቀበሉ።

በባህሪ እና በአመለካከት ኢየሱስን ትመስሉ ዘንድ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንደ ባሪያዎች አድርገው የማያውቁ ሰዎችን ታውቃላችሁን? ጌታ ልባቸውን እንዲከፍትላቸው ጠይቁ። በፍጹም ልባቸው ለእርሱ እንዲገዙ የእግዚአብሔርን መንፈስ ጠይቁ።

# ምዕራፍ 9 -

# ከሕግ ነጻ መውጣት

ሮሜ 7:1-6

*1 ወንድሞች ሆይ፥ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁና ሰው ባለበት
ዘመን ሁሉ ሕግ እንዲገዛው አታውቁምን? 2 ያገባች ሴት
ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና፤ ባልዋ
ቢሞት ግን ስለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች። 3 ስለዚህ
ባልዋ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ
ትባላለች፤ ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ አርነት ወጥታለችና ለሌላ
ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም። 4 እንዲሁ፥ ወንድሞቼ
ሆይ፥ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል፤
ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ፥ እናንተ ለሌላው፥ ከሙታን
ለተነሣው፥ ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ። 5 በሥጋ ሳለን በሕግ
የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን
ይሠራ ነበርና፤ 6 አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን፥
ከሕግ ተፈትተናል፥ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን
እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም። 7 እንግዲህ ምን
እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ*

*ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ፦ አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና።*

በሮሜ 6 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ አማኞች ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች እንዳልሆኑ ይነግራቸዋል (ሮሜ 6፡14፣15)። በሮሜ 7፡1 ይጀምራል፤ነገር ግን ሕጉ አንድ ግለሰብ በህይወት እስካለ ወይም እስካለች ድረስ የሚጸና መሆኑን ይናገራል። እነዚህን ሁለት መግለጫዎችን እንዴት እናስታርቃቸዋለን?

ሕግን በተመለከተ ልንገነዘበው የሚገባን የስልጣን ክልል እንዳለው ነው። ለምሳሌ፣ የካናዳ ህጎች በአገሪቱ ውስጥ በሚኖሩ እና በሚጎበኟቸው ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ወደ ሳውዲ አረቢያ ብሄድ ተቀባይነት ያላቸው ባህሪን የሚቆጣጠሩት ህጎች የተለዩ ናቸው። በካናዳ ሕጋዊ የሆነው በሳውዲ አረቢያ ላይሰራ ይችላል እንዲሁም በተቃራኒው። የካናዳ ህግ መኪናዬን በመንገዱ በቀኝ በኩል መንዳት እንዳለብኝ ያስገድዳል። ወደ እንግሊዝ ብጓዝ ግን ያ የካናዳ ህግ አይተገበርም። እዚያ በመንገዱ በግራ በኩል መንዳት ይጠበቅብኛል።

እንዲሁም የእግዚአብሔር ሕግ የስልጣን ክልል አለው። እንደ ጳውሎስ ገለጻ፣ ሕጉ በእያንዳንዱ በሕይወት ያለ ሰው ላይ ይሠራል። በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ምንም ዓይነት መልክዓ ምድራዊ ወሰን የለም። ሁሉም የእግዚአብሔር ፍጥረታት እግዚአብሔር በቃሉ ላስቀመጣቸው መስፈርት በመታዘዝ እንዲኖሩ ይጠበቃል። ሞት ብቻውን ሰውን ከህግ ግዴታዎች ነጻ ሊያደርገው ይችላል። ጳውሎስ በሮሜ 7፡1 ላይ “ሕግ በሰው ላይ የሚሠራው በሕይወት እስካለ ድረስ ብቻ ነው” ይላል።

ሐዋርያው በቁጥር 2 ላይ ለዚህ ምሳሌ ይሰጠናል፡

*2 ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና፤ ባልዋ ቢሞት ግን ስለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች።*

ባልና ሚስት በሚጋቡበት ጊዜ የታማኝነት እና የጋራ መረዳዳትን መስፈርት ማክበር አለባቸው። ጥንዶች የእርስ በርስ መተሳሰራቸው የህይወት ዘመን ቁርጠኝነት ነው። ያ ቃል ኪዳን በአለመግባባቶች፣በበሽታ ወይም በተለያዩ ዓይነት ፈተናዎች ሊፈተን ቢችልም እነዚህ ተግዳሮቶች አንዳቸው ለሌላው ታማኝ እንዳይሆኑ እና በቀሪው ሕይወታቸው እርስ በርስ መደጋገፍ እንዳይችሉ አያደርጋቸውም።

ሚስት ይህን ቃል ኪዳን ብታፈርስ እና ከሌላ ወንድ ጋር በመኖር ለባልዋ ታማኝ ባትሆን በዝሙት ጥፋተኛ ትሆናለች። የብሉይ ኪዳን ሕግ ሴቲቱና አብረዋት ያመነዘረችውን ወንድ በድንጋይ ተወግረው እንዲገደሉ ያዛል (ዘሌዋውያን 20፡10፤ዘዳ.22፡22) ።

ነገር ግን በሮሜ 7፡2፣3 ላይ ባሏ ከሞተ ሴቲቱ ከገባችው ኪዳን ነጻ መውጣቷን አስተውሉ። ባሏ የሞተባት ሚስት እንደገና ለማግባት ነጻ ነች። የመጀመሪያ ባሏ ቢሞት በዝሙት ጥፋተኛ አትሆንም። የባሏ ሞት ሴቲቱን ከእሱ ግዴታዎች ነጻ አውጥቷታል፡፡ የጋብቻ ህግ ስልጣን ተግባራዊ የሚሆነው ሁለቱም ጥንዶች በህይወት በነበሩበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

ይህ ሁሉ ከአማኙ ሕይወት እና ከህግ ግዴታው ጋር ምን ያገናኘዋል? ጳውሎስ በሮሜ 7፡4 ማስረዳቱን ይጥላል፡

*4 እንዲሁ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ፥ እናንተ ለሌላው፥ ከሙታን ለተነሣው፥ ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ።*

ጳውሎስ የሕግን መንገድ ከትዳር ጓደኛ ጋር ያወዳድረዋል። በህይወት እያለሁ እንደ ትዳር አጋሬ በህግ ግዴታ ውስጥ ነበርኩ። በሮሜ 6:5-11 ላይ ግን ክርስቶስ ስለ እኛ ሲሞት እኛ እንደሞትን እንደሚቆጠር ተመልክተናል።

ይህ ሞት ሁለት ገጽታዎች አሉት። በመጀመሪያ፤የሕግ ገጽታ አለው። ክርስቶስ ለእኔ እና ለኃጢአቴ ሞተ። እሱ የእኔን ቦታ ወሰደ። ይህ ማለት የእሱ ሞት ህጋዊ ቅጣቴን ሙሉ በሙሉ ከፍሏል። በጣም ብዙ ገንዘብ እንዳላችሁ አድርጋችሁ አስቡ ነገር ግን ዕዳችሁን መክፈል አልቻላችሁም። አንድ ወዳጃችሁ ያንን ዕዳ በስማችሁ ከፍሏል። አሁን በአበዳሪው መጽሐፍት ውስጥ የተመዘገበው ዕዳችሁ ሙሉ በሙሉ የከፈላችሁበት እውነታ ነው። ኢየሱስ ያደረገው ይህንኑ ነው። ቅጣቴን ሙሉ በሙሉ ከፈለ። "ሙሉ በሙሉ በሞት የተከፈለ" የሚለው መልዕክት በመንግሥተ ሰማያት መጻሕፍት ተመዝግቧል። በስሜ በኢየሱስ ሞት ከኃጢአት ቅጣት ነጻ ወጥቻለሁ።

ሁለተኛ፣የዚህ ሞት ተግባራዊ ገጽታ ደግሞ አለ። የክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔር መንፈስ በሞተላቸው ውስጥ እንዲኖር መንገድ ጠርጓል። መንፈስ ቅዱስ አሮጌውን ተፈጥሮ ገድሎ ወደ ክርስቶስ ባሕርይ ይለውጠናል። በዚያ መስቀል ላይ ከክርስቶስ ጋር ሞተናል፣ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጠኛው ሥራ ለኃጢአት እና ለራስ ማንነት ለመሞት በሂደት ላይ ነን። እንግዲህ የኢየሱስ የሆኑት ያው የሆኑ

ሰዎች አይደሉም። ሐዋርያው ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ሲል ይናገራል፡

*17 ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። (2ኛ ቆሮንቶስ 5)*

አማኙ በሕግ እና በተግባር ለሕግ ግዴታዎች ሞቷል።

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ውስጥ ጳውሎስ ስለ ትዳር ኀደኛ ሞት የሚናገረውን ምሳሌ ሲጠቀም እንደነበረ አስታውሱ። አንዲት ሴት ባሏን በሞት እንዳጣች ለአፍታ አስቡ። ከጊዜ በኋላ ሌላ ባል ታገባለች። ነገር ግን ከሁለተኛ ባሏ ጋር በትዳር ውስጥ እያለች የመጀመሪያውን ባሏን መናፈቋን ትቀጥላለች። ምንም እንኳን እሱ ቢሞትም ሃሳቧ እና ፍቅሯ አሁንም ወደ እሱ ናቸው። ስለዚች ሴት ጋብቻ ምን ማሰብ ይኖርብናል? እሷ ታማኝነት የጎደላት አይደለችምን? ሁለተኛ ባሏን ስታገባ ለእሱ ታማኝ ለመሆን እና ሌሎችን ሁሉ ለመጣል ቃል ገብታ ነበር። ይህ ቃል ኪዳን ከዚህ ዓለም በሞት የተለየውን የቀድሞ ባሏን ይጨምራል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ተስፋችሁ ነውን? ለእርሱ ብቻ ታማኝ ለመሆን ቃል ገብታችኋልን? ከሆነ፤ከቀድሞው የሕግ መንገድ መራቅ አለባችሁ። በሰው ጥረት የእግዚአብሔር ሕግ ደረጃ ላይ መድረስ የማይቻል ነው። ሕጎቹን ማክበር አንችልም። ሁላችንም እግዚአብሔር እንደሚጠብቀው መኖር አቅቶናል። በእግዚአብሔር ፊት በትክክል መቆም እንዲኖረን የሚያደርገውን ማንኛውንም የሕጉን ተስፋ መተው አለብን። የሕጉ መንገድ ለእኛ መሞት አለበት።

በሮሜ 7:5 ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡

*5 በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና፤ (ሮሜ 7)*

ይህንን ጥቅስ እና ከጽሑፉ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመረዳት ልንከፋፍለው ይገባል። ጳውሎስ የጀመረው ለሮሜ ክርስቲያኖች "በሥጋ ይኖሩ ስለነበረው" ጊዜ በመናገር ነው። "ሥጋ" የሚለው ቃል ከምድራዊው ሰውነታችን እና ከአስተሳሰብ መንገዱ ጋር ይዛመዳል። ሐዋርያው በሮሜ የሚኖሩ አማኞች እንደ ሰው አስተሳሰብ እና ተፈጥሮ የኖሩበት ጊዜ እንደነበረ አስታውሷቸዋል። ሥጋቸው እና አስተሳሰባቸው "በምኞታቸው" ሥር የተገዛ ነበር። እነዚህ አካላዊ፣ወሲባዊ፣ስሜታዊ እና ማሕበራዊ ፍላጎቶች የሚኖሩበትን መንገድ የገዛ ነው። እነዚህ ምኞቶች "ኃጢአተኛ" መሻቶች እንደነበሩ አስተውሉ። በሌላ አነጋገር፣ በእግዚአብሔር ቃል እና ለሕይወታቸው ባለው ዓላማ የተገዙ አልነበሩም። ምኞታቸው የተዛባና የተበላሸ ነበር። እነዚህን ምኞቶች መኖር ወንጀል፣እንግልት እና ራስ ወዳድነትን አስከትሏል። የኃጢአተኛ ፍላጎታቸውን ሲፈጽሙ ሕብረተሰቡ ይሰቃይ ነበር።

በተጨማሪም በሮሜ 7፡5 ላይ እነዚህ ስሜቶች "በሕግ ምክንያት የመጡ" መሆናቸውን አስተውሉ። የእግዚአብሔር ሕግ በሮሜ ሰዎች ላይ የኃጢአትን መሻት የቀሰቀሰው እንዴት ነው? ጆን ጊል ስለዚህ ጥቅስ በሰጠው አስተያየት እንዲህ ይላል፡

*እውነተኛው ግንዛቤ፣እነዚህ የኃጢአት እንቅስቃሴዎች የሚነሱት፣የሚቀሰቀሱት እና የሚጨምሩት በሕግ በመከልከላቸው ምክንያት ነው...የበሰበሰ ቆሻሻ ክምር፣ፀሃይ በኃይል ሲያርፍበት፣የሚሸት ክርፋቱ ወጥቶ አከባቢውን ይበክላል፣የሚያጥወለውለው ሽታ የመጣው ንጹህ ከሆነው የፀሃይ ብርሃን ሳይሆን ከበሰበሰው የቆሻሻ ክምር ነው። (Gill, John, John Gill's Exposition of the Entire Bible, "Commentary on Romans 7:5", Laridian: Cedar Rapids, 2013).*

የፀሐይ ብርሃን በላዩ ላይ ሲያርፍ የበሰበሰ የቆሻሻ ክምር ምን ይሆናል? የቆሻሻ ክምር መኖሩ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን አያደርገውምን? የበሰበሰው ቆሻሻ ሽታ አየሩን ይሞላል። በተመሳሳይም የእግዚአብሔር እውነት ሊቀበሉት በማይፈልጉ ሰዎች ላይ መጥፎ ነገር ያመጣል።

ትንሽ ልጅ ሳለሁ አንዳንድ ጊዜ ከድንጋይ ስር ትሎችን ለማግኘት ወደ ሜዳ ወጥቼ ድንጋይ እገለባበጥ ነበር። ካስተዋልኳቸው ነገሮች አንዱ እነዚህ በጨለማ ደስተኞች የሆኑ ትሎች ብዙውን ጊዜ የፀሐይ ብርሃን ሲመታቸው ከለላ ለማግኘት ይሮጣሉ። የእግዚአብሔር እውነት መስማት በማይፈልጉ ሰዎች ጆሮ ሲደርስ የሚሆነው ይህ አይደለምን? ይህን የእግዚአብሔርን እውነት ብርሃን የሚቃወም በሰው ልብ ውስጥ የተፈጥሮ አመጽ አለ። ኃጢአተኛ ተፈጥሮአቸው ያንን እውነት ለመቃወም ይነሣል። የእግዚአብሔር ሕግ የኃጢአተኛን ልብ ወደ ብርሃን ያመጣው ነበር። የነበሩበትን ነገር ግልጽ አድርጓልና።

ጳውሎስ በመቀጠል በሕጉ የተነቃቁት እነዚህ ኃጢአተኛ ስሜቶች "በአካላችን ውስጥ ለሞት ፍሬ እንዲያፈሩ" ይሠሩ እንደነበር ተናግሯል። ሕጉ ሥጋውን አጋልጦታል። አስከፊ ሽታውን እና አሳፋሪ መንገዶቹን ገልጦታል። ነገር ግን የሕጉ መንገድ ሕይወታችንን ያጠፋውን ኃጢአት አላጠፋም ወይም ዘላቂ ይቅርታ አላመጣም። ይህን ማድረግ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ሕጉ ማድረግ የሚችለው ኃጢአትን ማጋለጥ እና ሞትን ማምጣት ብቻ ነው።

ጳውሎስ ይህን በሮሜ 7፡6 ያለውን ክፍል ያጠናቀቀው በህጋዊ እና በተግባራዊ መልኩ ስለሞትን ከህግ መንገድ ነፃ እንደወጣን በማስታወስ ነው። ሕጉ "አስሮናል።" ልክ እንደ መጥፎ ትዳር፣ እኛን ከሚጎዳ አጋር ጋር ተቆራኝተናል። አሁን ግን ከክርስቶስ ጋር ስለሞትን ነጻ ወጥተናል።

*6 አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን፥ ከሕግ ተፈትተናል፥ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።*

አሁን ነጻ ስለወጣን በአዲስ መንገድ ማገልገል እንችላለን። ጳውሎስ ይህንን "የመንፈስ መንገድ" በማለት ገልጾታል። አሮጌው መንገድ ለተፃፉ ህጎች መታዘዝን የሚጠይቅ እና እነዚህን ህጎች በምን ያህል መጠን መታዘዝ እንደምንችል ይፈርድብናል። የመንፈስ መንገድ እኛን ወደ ክርስቶስ መልክ ለመለወጥ በእኛ ውስጥ ካለው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ጋር ይዛመዳል። አንደኛው ከኃጢአተኛ ሥጋችን ወጥተን እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚደረግ ሙከራ ነው። ሌላው በልባችን ውስጥ ላለው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ መገዛት ነው። አንዱ ወደ ውድቀት፣ሌላው ወደ ለውጥ ያመራል።

በአሮጌው የሕግ መንገድ ትታምናላችሁን? በሥጋ ለእግዚአብሔር መታዘዝ እንደሚቻል ታምናላችሁን? በኃጢአተኛ ሥጋ ጥረት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ትችላላችሁን? እግዚአብሔር ለእናንተ እና ፍጹምነታችሁ ያስቀመጠውን መስፈርት ማሟላት ትችላላችሁን? እግዚአብሔርን በዚህ መንገድ ማስደሰት እንደማይቻል ከተረዳችሁ ጳውሎስ በዚህ ምንባብ ውስጥ እያስተማረ ወደሚገኘው እውነት እና ትልቅ እርምጃ ይወስዳችኋል። በህግ የእግዚአብሔርን መስፈርቶች ልናሟላ አንችልም። ኢየሱስ የመጣው ለዚህ ነው። የመጣው ከህግ መንገድ ነፃ ሊያወጣን ነው። አዲስ መንገድ - የመንፈስን እና የሕይወትን መንገድ ሊያሳየን መጣ።

**ለምልከታ**:

ከህግ መንገድ ነጻ መውጣት ይቻላልን? ይህ እንዴት ይቻላል?

ጌታ ኢየሱስ እኛን ከህግ ነጻ ለማውጣት ምን አደረገ?

ከክርስቶስ ጋር መሞት ማለት ምን ማለት ነው?

የሕጉ መንገድ ከመንፈስ መንገድ የሚለየው እንዴት ነው?

በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ምንድን ነው? ሕጉ ፈጽሞ ሊያሳካ የማይችለውን እንዴት ይፈጽማል?

አሁንም የእግዚአብሔርን ጸጋ ለማግኘት በመልካምነታችን መታመን ምን ያህል ይቀላል?

እናንተን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት በሕግ መንገድ ያለውን ተስፋ ሁሉ ጥላችኊልን?

**ለጸሎት:**

ጌታ ኢየሱስ በእኛ ፈንታ ስለሞተ አመስግኑት። ሲሞት እዳዬ ሙሉ በሙሉ ስለተከፈለ አመስግኑት።

ሥጋን ለመስቀል እና የክርስቶስን ሕይወት ለማፍራት በእኛ ውስጥ ስለሚሠራው ሥራ የእግዚአብሔር መንፈስ አመስግኑት።

ለደህንነታችሁ እና ለመቀደሳችሁ በእርሱ ብቻ የምትታመኑበትን ጸጋ እንዲሰጣችሁ ጌታን ጠይቁት። ከእርሱ በቀር ይህ የማይቻል ቢሆንም ሊያድነን እና በእምነት ሊያሳድገን ደስተኛ ስለሆነ አመስግኑት።

## ምዕራፍ 10 -

## ሕጉ ኃጢአት ነውን?

ሮሜ 7:7-12

*7 እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም፤*
*ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ፦*
*አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና። 8 ኃጢአት ግን*
*ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ፤ ኃጢአት*
*ያለ ሕግ ምውት ነውና። 9 እኔም ዱሮ ያለ ሕግ ሕያው*
*ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ እኔም*
*ሞትሁ፤ 10 ለሕይወትም የተሰጠችውን ትእዛዝ እርስዋን*
*ለሞት ሆና አገኘኋት፤ 11 ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ በትእዛዝ*
*አታሎኛልና በእርስዋም ገድሎኛል። 12 ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ*
*ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት። (ሮሜ 7)*

የጳውሎስ ትምህርት ከሕግ በታች አይደለንም የሚለው ትምህርት በጊዜው በነበሩት አይሁዳውያን ዘንድ ከፍተኛ ግርግር ፈጥሮ ነበር። ክርስቲያኖች እንኳን እሱ ያስተማረውን ነገር ይጠራጠሩ ነበር። ለእነዚህ አማኞች፣የጳውሎስ ትምህርት የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሕግ ከንቱ አልፎ ተርፎም ኃጢአት መሆኑን ነው ምክንያቱም የሚያደርገው ሁሉ

ኃጢአትን የሚያጋልጥ እና ሞትን የሚያመጣ ነውና። ሐዋርያው እነዚህን ተቃውሞዎች ተረድቶ እና ጊዜ ወስዶ ከቁጥር ሰባት እስከ አሥራ ሁለት ያሉትን መልሶች ሰጥቷል።

ጳውሎስ ከጥያቄ ይጀምራል:

*7 እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? (ሮሜ 7)*

ጳውሎስ ጋብቻን እንደ ምሳሌ ሲጠቀም እንደነበረ አስታውሱ። ለሮሜ አማኞች ባል በሞተ ጊዜ ሚስቱ ሌላ ለማግባት ነጻ እንደሆነች ይነግራቸዋል። ለመጀመሪያ ባሏ የነበራት ታማኝነቷ ከዚህ በኋላ አይኖርም። አሁን ያለውን ባሏን ችላ በማለት የመጀመሪያ ባሏ ላይ ማተኮር ከቀጠለች የታማኝነትን ቃል ኪዳንን በማፍረስ ጥፋተኛ ትሆናለች። በተመሳሳይ፣ ወደ ሕጉ መመለስ የሚፈልግ አማኝ ለክርስቶስ ታማኝ አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ብሉይ ኪዳን የግርዛት ልምምድ ለገላትያ ሰዎች ሲናገር እንዲህ ይላል፡

*1 በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ። 2 እነሆ፥ እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ፦ ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም። 3 ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት ብዬ ለሚገረዙት ሁሉ ለእያንዳንዶች ደግሜ እመሰክራለሁ። 4 በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል። (ገላትያ 5)*

ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ከሕግ ባርነት ነፃ እንዳወጣቸው አሳስቧቸዋል። ከዚህ በኋላ ለባርነት መገዛት እንደሌለባቸው ይነግራቸዋል። በገላትያ 5 ላይ ሐዋርያው ስለ

ግርዛት ልምምድ ይናገራል። ለአይሁድ ክርስቲያኖች እንደ ሕጉ መሠረት መገረዝ ከጀመሩ ሕጉን ሁሉ የመጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸው ነግሯቸዋል። ወደ ቀድሞው የሕግ መንገድ ከተመለሱ፣ከክርስቶስ እና ከሥራው ራሳቸውን ያገላሉ ምክንያቱም ብቸኛ የመዳን መንገድ ከሆነው ከጸጋው ወድቀዋልና።

አማኝ ወደ ህግ መንገድ መመለሱ ስህተት ከሆነ ይህ ስለ ህግ ምን ይላል? ወደ ሕግ በመመለስ ራሳችንን ከክርስቶስ ብንለይ ሕጉ ኃጢአተኛ ነውን? ጳውሎስ ይህንን በቁጥር 7 ሁለተኛ አጋማሽ ላይ "በፍፁም!" በማለት በእርግጠኝነት መልስ ሰጥቷል። ይህንንም በቀሪው አንቀጽ ያስረዳል፡

*7 ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ፦ አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና። (ሮሜ 7)*

## *የሐጢአት መገለጥ*

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደገለጸው፤ሕጉ የኃጢአትን ችግር የሚገልጽ-ወሳኝ ዓላማ ነበረው። እያንዳንዱ አማኝ የሚኖርበትን መስፈርት አስቀምጧል። ትክክልና ክፉ የሆነውን ገልጿል። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የእግዚአብሔር ሕግ ባይኖር ኖር መመኘት ኃጢአት መሆኑን ፈጽሞ አያውቅ እንደነበር ይነግራቸዋል (ዘጸአት 20፡17፤ ዘዳ 7፡25 ተመልከቱ) ። እግዚአብሔር ኃጢአት አድርጎ የሚመለከተው ለእኛ ተፈጥሯዊ ይመስላል። ሕጉ እግዚአብሔር የሚጠብቀውን ያሳየናል። የእግዚአብሔር ሕግ አዳኝ የሚያስፈልገን

ኃጢአተኞች መሆናችንን ይገልጥልናል። ወደ ክርስቶስ ይጠቁመናል፣ነገር ግን ለደህንነታችን በፍጹም አይሆንም።

*ተጠያቂነት*

*ሕጉ የሚያስፈልገንን የሚጠቁመን ብቻ ሳይሆን ኃጢአትን መሥራት የሚያስቀጣ ወንጀል አድርጎታል።*

*8 ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ፤ ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና።*

ሕግ በማይኖርበት ጊዜ፤ልንቀጣ አንችልም። ነገር ግን ሕጉ የባህሪ መመሪያን ያስቀምጣል እንዲሁም ሰዎች ሁሉ ያንን መስፈርት እንዲያሚሉ ወይም አለመታዘዝ የሚያስከትለውን መዘዝ እንዲቀበሉ ያዛል።

ጳውሎስ ከሕግ ውጭ ኃጢአት የሞተ መሆኑን ለሮሜ ሰዎች አሳስቧቸዋል። በሌላ አነጋገር ኃጢአትን የሚቃወም ሕግ በሌለበት ቅጣት ሊኖር አይችልም። ግድያ በሕግ ወንጀል ካልሆነ ሰውን በነፍስ መግደል እንዴት ልትቀጡት ትችላላችሁ? ሕጉ ኃጢአትን የሚያስቀጣ ወንጀል ያደርገዋል። ጳውሎስ በሮሜ 7፡9 ላይ እንዲህ ይናገራል፡-

*9 እኔም ዱሮ ያለ ሕግ ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ፤*

ከሕጉ በተጨማሪ ጳውሎስ የፈለገውን ለማድረግ ነጻ ነበር። ሕጉ ሲመጣ ግን ጳውሎስ ለእያንዳንዱ ድርጊት ተጠያቂ ሆነ። ይህም በሞት በሚያስቀጣው ጥፋት በእግዚአብሔር ፊት ጥፋተኛ አድርጎታል።

## *ሕይወትን የመስጠት ሃሳብ*

ሐዋርያው በቁጥር 10-12 ላይ ሕጉ ለሕይወት ተስፋ እንዳለው በመንገር ይደመድማል። ይህ የእግዚአብሔር ሕግ ሐሳብ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ግንኙነት የመመሥረት ሕይወት እና ተስፋ የእግዚአብሔርን ሕግ ፍጹም ለሚጠብቁ ሁሉ ቃል ተገብቶላቸዋል። የእግዚአብሔርን ከፍተኛ የመታዘዝ ሕግ ለሕዝቡ ገልጧል። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለዚህ መሥፈርት ፍጹም ታዛዥ በመሆን ከአምላካቸው ጋር በሚስማማ መንገድ ይመላለሳሉ።

ችግሩ የነበረው በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ነበር። ሕጉ ፍጹም ነበር፡ሕዝቡ ግን አልነበሩም። በፍጹም ታዛዥነት ለሚሄዱት ሕይወትን የሰጣቸው ትእዛዝ፤ መስፈርቱን ጠብቀው መኖር ተስኗቸው በነበሩት ላይ ደግሞ ኩነኔን አመጣባቸው።

*10 ለሕይወትም የተሰጠችውን ትእዛዝ እርስዋን ለሞት ሆና አገኘኋት፤*

ጳውሎስ በቁጥር 11 ላይ ችግሩ በሕግ ላይ ሳይሆን በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ያለው ኃጢያተኛነት እንደሆነ ግልጽ አድርጓል።

*11 ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ በትእዛዝ አታሎኛልና በእርስዋም ገድሎኛል።*

ሞትን ያመጣው ኃጢአትና አለመታዘዝ ነው። ሕጉ የእግዚአብሔርን መስፈርቶች ገልጿል። ቅዱስ፣ጻድቅና መልካም ነበር፡

*12 ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት።*

ሕጉ ፍላጎታችንን ሊመልስልን ያልቻለው፣ምንም ዓይነት ስህተት ስላለበት ሳይሆን፣ልንጠብቀው ስላልቻልን እና ከመስፈርቱ ስለጎደልን ነው። በዚህ ምክንያት በሕግ ሥር ሁላችንም የተፈረደብን ስለሆንን የኃጢአትን ችግር ለመፍታት ሌላ መፍትሔ የምንፈልገው ለዚህ ነው።

**ለምልከታ:**

ለምን ወደ ህግ መንገድ አንመለስም?

ሕጉ ኃጢአትን የሚገልጠው እንዴት ነው? በሕግ ባይሆን ኖሮ የእግዚአብሔርን ዓላማ እንረዳ ነበርን?

ሕጉ ተጠያቂነትን መጠየቁ ለምን አስፈለገ? ሕጉ ተጠያቂነትን ወይም አለመታዘዝን የማይጠይቅ ከሆነ ምንም ጥቅም ይኖረዋል?

ለኃጢአት ችግር ሌላ መፍትሔ እንደሚያስፈልገን ሕጉ የሚያሳየው እንዴት ነው?

ሕጉ ከአለመታዘዝ ካልከለከለን እና በመጨረሻ የሚኮንነን ከሆነ ፍጹም ሊሆን ይችላልን?

**ለጸሎት:**

በህጉ በኩል ዓላማውን ስለገለጠልን ጌታን ለማመስገን ትንሽ ጊዜ ውሰዱ፡፡

በሕይወታችሁ ለእርሱ በመታዘዝ ትመላለሱ ዘንድ እንዲረዳችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት፡፡

መዳናችሁ የተደገፈው የእርሱን መመዘኛዎች በሚገባ በመጠበቅ ላይ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለይቅርታ ባደረገው ሥራ ስለሆነ ጌታን አመስግኑት፡፡

## ምዕራፍ 11 -

## ሕጉ እና ሥጋው

---

ሮሜ 7:13-20

*13 እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝን?
አይደለም፥ ነገር ግን ኃጢአት ሆነ፤ ኃጢአትም በትእዛዝ
ምክንያት ያለ ልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፥ ኃጢአትም
እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ
ነበር። 14 ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን
ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ። 15
የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ
ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም። 16 የማልወደውን ግን
የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደ ሆነ እመሰክራለሁ።
17 እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥
በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ። 18 በእኔ ማለት በሥጋዬ
በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን
ግን ማድረግ የለኝም። 19 የማልወደውን ክፉን ነገር
አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።*

*20 የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ። (ሮሜ 7)*

ጳውሎስ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ሕግ መልካም እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል። እንዴት አንድ ነገር መልካም ሆኖ ሳለ አሁንም ሞትን ያመጣል? ጳውሎስ በቁጥር 13 ላይ ይህንን ይናገራል፡

*13 እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝን? አይደለም፥ ነገር ግን ኃጢአት ሆነ፤ ኃጢአትም በትእዛዝ ምክንያት ያለ ልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፥ ኃጢአትም እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ ነበር። (ሮሜ 7)*

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የሕጉ ዓላማ የሰውን ልጅ ለማጥፋት ሳይሆን እግዚአብሔርን እና ዓላማውን መግለጥ እንደሆነ ተናግሯል። ሕጉ የእግዚአብሔርን ቅድስና እና ፍትህ ገልጧል። የእስራኤልን አምላክ ታላቅ ርኅራኄ እና ጽድቅ ገልጧል። ከእርሱ ጋር ተስማምተን እና በኅብረት እንዴት እንደምንኖር አሳይቶናል። ችግሩ የተገኘው ፍጹም በሆነው የእግዚአብሔር ሕግ ውስጥ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ መኖር በማይችሉ ፍጽምና በጎደላቸው የሰው ልጆች ላይ ነበር።

ሞትን እና ፍርድን ያመጣው የሰው ልጅ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ነው። ከአዳም እና ሔዋን የኤደን ገነት አለመታዘዝ ጀምሮ፣ይህ ዓለም በኃጢአት ችግር ሲታመስ ቆይቷል። በእግዚአብሔር እና በዓላማው ላይ የሚያምፅ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ይዘን

ተወልደናል። እግዚአብሔር በሕጉ ያስቀመጠውን መስፈርት ጠብቀን መኖር አንችልም። ማናችንም ብንሆን የእግዚአብሔርን ህግ መጠበቅ አልቻልንም። ሁላችንም በህይወታችን ከእግዚአብሔር ዓላማ ጎድለናል።

ከባህር ዳርቻ 1,000 ኪሎ ሜትር (800 ማይል) ርቃ ወደምትገኝ ደሴት ለመዋኘት እየሞከራችሁ እንደሆነ አስቡ። በዋና መሻገር ያለባችሁ ርቀት በጣም አስቸጋሪ በሆኑ የባህር ክፍሎች፤ትላላቅ ማዕበሎች እና አደገኛ የባሕር ፍጥረታት የተሞላ ነው። ማለፍ የሚገባችሁ የውኃ ክፍል የእረፍት ቦታ አይሰጣችሁም።

ይሁን እንጂ ያለ ምንም የውጭ እርዳታ ይህንን ራሳችሁ ለማድረግ ቆርጣችኋል። ልትደርሱባት የምትፈልጓት ደሴት በህይወታችሁ በምትፈልጉት ነገር ሁሉ የተሞላች ገነት ናት።

ልትደርሱባት የምትፈልጓት ደሴት ፍጹም የሆነች ደሴት ናት። ዓላማችሁ ክቡር ነው። ችግሩ ከማንም ሰው አቅም በላይ ነው። ይህንን ጉዞ በማድረግ ህይወታችሁን አደጋ ላይ ትጥላላችሁ። የባህር ዳርቻውን ከደሴቱ በሚለየው የውኃ አካል አንድ ሥፍራ ላይ ጥንካሬአችሁ እና ሰዋዊ ችሎታችሁ ይደክማሉ፤ከዚያም በዚያ ሰፊው ውቅያኖስ የመጨረሻው ክፍል ሰምጣችሁ ግባችሁ ላይ ሳትደርሱ ትቀራላችሁ። የሞታችሁ ምክንያት ደሴቱ ሳይሆን የችሎታችሁ ማነስ ነው። ግባችሁን ማሳካት አልቻላችሁም።

ሕጉ እንደዚያ ውብ ነው ዳሩ ግን ሩቅ ደሴት ነው። ይጠራናል ነገር ግን ልንደርስበት አንችልም። ደረጃውን በፍፁም ልንለካው አንችልም። አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ይልቅ ቀርበው ሊሆን

ይችላል ነገር ግን ማንም እዚያ አልደረሰም ምክንያቱም ማንም ኃጢአተኛ ወደዚያ ዳርቻ ለመድረስ ከአቅሙ በላይ ነውና። ጳውሎስ እሱ እንኳን ለኃጢአት የተሸጠ መሆኑን ለሮሜ ሰዎች አሳስቧቸዋል።

*14 ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ።*

ሐዋርያው ጳውሎስ ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚጠቅም ቢሆንም አሁንም ኃጢአተኛ መሆኑን ተረድቷል። ፍጹም ሕይወት መኖር እንደማይችል ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር ከእርሱ የሚጠብቀውን ሕይወት መኖር ባለመቻሉ ብዙ ጊዜ ተስፋ ቆርጦ ነበር።

*15 የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም።*

ለጳውሎስ ፍጹም ሕይወት መኖር የማይቻል ነው። እግዚአብሔር የሚፈልገው ደረጃ ላይ መድረስ አልቻለም። የሚፈልገውን ነገር ሳያደርግ ዳሩ ግን የማይፈልገውን ያደርግ ነበር። ችግሩ የፍላጎት ሳይሆን የችሎታ ጉዳይ ነበር።

ጳውሎስ ትክክል የሆነውን ነገር ማድረግ ይፈልግ ነበር። ትክክል የሆነውን ያውቅ ነበር፣ ነገር ግን በደካማና በኃጢአተኛ ሥጋው ይህን ማድረግ አልቻለም።

ጳውሎስ በሕጉ ውስጥ ከተቀመጠው የእግዚአብሔር መስፈርት ጋር መስማማቱን አስተውሉ። በመታዘዝ መመላለስ ይፈልግ ነበር። ያ ሕግ የመልካምነት እና የቅድስና መለኪያ እንደሆነ

ተመልክቶ ህይወቱ እነዚህን የእግዚአብሔርን ዓላማዎች እንዲያንጸባርቅ ይፈልግ ነበር።

*16 የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደ ሆነ እመሰክራለሁ።*

የጳውሎስ ፍላጎትና ችሎታ ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ተረድቷል። አንድ ነገር ለማድረግ ፍላጎት ሊኖራችሁ ይችላል ነገር ግን ይህን ለማድረግ ችሎታ አይኖራችሁም። ጳውሎስ ራሱን ያገኘው እዚህ ላይ ነው። የጌታን መንገድ መከተል ይፈልግ ነበር ነገር ግን ማድረግ የሚፈልገውን ማድረግ አልቻለም። ጳውሎስ እዚህ ላይ እየተናገረ ያለው እንደ አማኝ መሆኑን መረዳታችን አስፈላጊ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ፣ ለዚህ ምንም ያህል ቁርጠኛ ቢሆንም፣ በራሱ ጥረት እግዚአብሔር ከእርሱ የሚጠብቀውን ሕይወት ፍጹም በሆነ መንገድ መምራት አልቻለም።

ይህ ጦርነት ጳውሎስ አንድ አስፈላጊ ግኝት እንዲያገኝ አደረገው።

*17 እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ።*

ጳውሎስ ራሱን ሲመረምር ልቡ ከእግዚአብሔር እና ከዓላማው ጋር እንደሚስማማ ተመልክቷል–ከእግዚአብሔር ጋር መሄድ እና ከእርሱ ጋር ተስማምቶ መኖር ይፈልጋል። ችግሩ ኃጢአተኛ መሆኑ ነበር። የሚፈልገውን ከማድረግ የከለከለው በእሱ ውስጥ ያለው የኃጢአተኛ ተፈጥሮ ነው።

በቁጥር 17 ላይ ጳውሎስ በእሱ ውስጥ ባለው የኃጢአተኛ ተፈጥሮ እና በክርስቶስ ባለው ማንነቱ መካከል ያለውን ልዩነት አስቀምጧል። ኃጢአት የባህርዩ አካል ነበር፣ ይሁን እንጂ ራሱን የገለጸበት መንገድ አልነበረም። ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ኃጢአት ያመጣውን የሕግ ውጤት ተመልክቶ ነበር። ጳውሎስ ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እና ይቅርታን አግኝቶ ከኃጢአት የጸዳ እንደሆነ ይናገራል። አሁንም በኃጢአት በተፈተነ ኃጢአተኛ ሥጋ ውስጥ ይኖር ነበር፣ነገር ግን ጳውሎስ ከኃጢአተኛ ሥጋ ያለፈ ነበር። እርሱ የኢየሱስ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ውስጥ ይኖራል፣አዲስም ሰው አድርጎታል።

እግዚአብሔርን ለማክበር ፍላጎት ነበረው የሚለው እውነታ በጳውሎስ ውስጥ ያለው የመንፈስ ሥራ ማስረጃ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ አስተሳሰቡን እና አመለካከቱን ይለውጥ ነበር። ስለ ኃጢአት ይወቅሰው ነበር። ጳውሎስን ወደ ክርስቶስ መልክ ይለውጠው ነበር። ይህ ሁሉ የሆነው ኃጢአተኛ በሆነ ሥጋዊ አካል ውስጥ ነው።

*18 በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። 19 የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።*

ጳውሎስ የኖረበት ሥጋ ኃጢአተኛ እና እግዚአብሔርን እንደሚገባው ለማገልገል እንደማያስችለው ተረድቶ ነበር። በእርሱ የሚኖረው እውነተኛ እና ዘላቂ የሆነ መልካምነት የመጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ነው። ሐዋርያው ለእግዚአብሔር በፍጹም መታዘዝና መመላለስ ባለመቻሉ

የሥጋን ኃጢአተኝነት ተመልክቷል። በእርሱም በመንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ሥራ የተፈጠረውን አዲስ ፍጥረት አስተውሏል።

በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ ታላቅ ጦርነት እየተካሄደ ነበር። ሥጋ በአንድ መንገድ እንዲሁም መንፈስ በሌላ መንገድ ጳውሎስን እየመሩት ነበር። ሐዋርያው በመንፈሱ ጌታ እግዚአብሔርን አጥብቆ ይፈልግ ነበር ነገር ግን በሥጋው ውስጥ ያለው ኃጢአት የማይፈልገውን እንዲሠራ ያደርገው ነበር። ጳውሎስ ጌታውን በትክክል ማክበር ባለመቻሉ ኃጢአተኛ የሆነው ሥጋዊ ማንነቱን በቀጥታ ተጠያቂ አድርጓል። ያንን ተፈጥሮ እጅግ ጠላው።

*20 የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ።*

እዚህ ላይ ጳውሎስ እንደተናገረው፤በእኛ ውስጥ ያለው ኃጢአት ከእኛ የተለየ አለመሆኑን ዳሩ ግን ተፈጥሮአችን እንደሆነ መረዳት አለብን። ከፍላጎታችን ውጪ እኛን የወረረን የውጭ አካል አይደለም። እኛ ኃጢአተኞች ሆነን ተወልደናል፣ ከእግዚአብሔር ተለይተናል ስለሆነም ሕጉን መጠበቅ አንችልም። ጳውሎስ በክርስትና ሕይወት ውስጥ የነበረው ልምምድ ከዚህ ኃጢአተኛ እና ሥጋዊ ፍላጎቶች ጋር መታገል ነበር። የሥጋው ምኞት ከእግዚአብሔርና ከዓላማው ጋር የሚጻረር ሆኖ ተመልክቶታል።

ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ፣የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ሊኖር መጣ። በመንፈስ፣ ጳውሎስ ጌታን ለመከተል እና በመንገዱ መመላለስ ያስደስተው ነበር፣ነገር ግን ክፋት

"በቅርበት" (ቁጥር 21) ከሥጋው ጋር ይዋጋ ነበር። በኃጢአተኛ ሥጋው ውስጥ እስካለ ድረስ፣ጳውሎስ ምርኮኛ እንደሆነ ተሰምቶት ነበር (ሮሜ 7፡23 ተመልከቱ) ።

ሐዋርያው “ለሞት የተሰጠ ሰውነት” ብሎ ከጠራው ነጻ ለመውጣት ይፈልግ ነበር። ይህ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ብቻ ማድረግ የሚፈልገውን ከማድረግ እንደሚያግደው ተሰማው። በእግዚአብሔር ሐሳብ መመላለስ ይፈልግ ነበር ዳሩ ግን ሥጋው ይከለክለው ነበር። ጳውሎስ በላዩ ላይ በተንጠለጠለው በዚህ ለሞት የተሰጠ ሰውነት ኃጢአተኛነት የተሰማው ሐዘን በጣም ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ በቁጥር 24 ላይ ይጮሃል፡

*24 እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?*

ከዚህ ኃጢአተኛ ሥጋ መዳንን ይናፍቅ ነበር። ጌታውን በሚገባው ልክ ያገለግል እና ያከብር ዘንድ ነጻ ለመውጣት ይፈልግ ነበር። በምድራዊ ሥጋው ላይ ከደረሱት የኃጢአት ፈተናዎች ጋር መለያየት ይፈልግ ነበር።

በሃዘኑ ወቅት፣ጳውሎስ ወደ ጌታ ኢየሱስ ቀና ብሎ በመመልከት ለሥራው አመሰገነው። በመንፈሱ አማካኝነት አዲስ ልብ እና አዕምሮን በመቀበሉ ጌታን ያመሰግናል። ምንም እንኳን ሥጋው የዓለምን የኃጢአተኛ መንገድ ቢፈልግም በአዕምሮው ማገልገል በመቻሉ ጌታን አመሰገነ (ቁጥር 25 ተመልከቱ) ።

*25 በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ። (ሮሜ 7)*

በጌታ ኢየሱስ ሥራ ምክንያት፣የጳውሎስ ልብ እና አዕምሮ እየተለወጠ ነበር። ጌታን ለማገልገል አዲስ መሻት አገኘ። ሥጋው ማድረግ ያልቻለውን የእግዚአብሔር መንፈስ በአዕምሮው እና በልቡ እያደረገ ነበር፤ፈጣሪውን እንዲወድ እና እንዲያገለግል ያስችለው ነበር። በአዕምሮው ላይ ጦርነት ባወጀው "በሚሞት ስጋው" (ቁጥር 24) ውስጥ ቢኖርም (ቁጥር 23) እግዚአብሔር ግን አልተወውም። የእግዚአብሔር መንፈስ ይሠራ ነበር፣ እናም በዚያ መንፈስ ይሥራ ነበር፣ጳውሎስ አምላኩን መውደድ እና ማገልገል ችሏል።

በክርስትና ሕይወት ውስጥ ካሉት ጉልህ ፈተናዎች አንዱ ሥጋን ከመንፈስ ሥራ መለየት ነው። ለጳውሎስ፣ ይህ ልዩነት በጣም ግልጽ የሆነ ይመስላል። ሥጋን እግዚአብሔር በእርሱ የሚሰራውን የሚዋጋ የሞተ ሥጋ አድርጎ ተመለከተ። ጳውሎስ ራሱን እንደ እስረኛ እንጂ በዚህ ኃጢአተኛ ሥጋ ውስጥ በፈቃደኝነት እንደማይኖር አሰበ (ቁጥር 23) ። በኃጢአተኛ ሥጋው፤በማይችለው መንገድ ጌታን ለማገልገል እና ኅብረት ለማድረግ ስለ ፈለገ ቆስቋላ ሆኖ ተሰማው። ለሮሜ ሰዎች በተማረከበት ሥጋ ምንም መልካም ነገር እንደሌለ ይነግራቸዋል (ቁጥር 18) ።

ጳውሎስ በውስጣዊ ሰውነቱ በሕጉ ስለመደሰት ተናግሯል። በቁጥር 25 ላይ ጌታን በአዕምሮው ስለማገልገል (መንፈሱ እንደሚለወጥ) ይናገራል። የጳውሎስ ፍላጎት እና ትኩረት ጌታውን ማገልገል ከሥጋ ሳይሆን ከመንፈሱ እና ከታደሰ

አዕምሮው ነው። በአገልግሎት ያገኘውን ድል ከጌታ ከኢየሱስ እና በእርሱ ውስጥ ካለው የመንፈስ ሥራ የመጣ እንጂ ከሰብዓዊ መንገዱ እና ከመረዳቱ እንዳልመጣ ተረድቷል።

ሥጋችን ኃጢያተኛ እና ጌታ እግዚአብሔርን ለማክበር እንደማይችል እናምናለን? ካመንን፤በእርሱ ላይ መተማመንን እናስወግዳለን እናም በህይወታችን ውስጥ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት እና ሥራ ላይ ይበልጥ እንታመናለን። በሮሜ 8 ላይ ጳውሎስ በስጋ ሳይሆን በመንፈስ መመላለስ ምን ማለት እንደሆነ በበለጠ ለመናገር ጊዜ ይወስዳል።

**ለምልከታ**:

ሕግ ማንም ሊታዘዝለት ካልቻለ መልካም ሊሆን ይችላልን?

በሥጋችን ያለውን የእግዚአብሔርን ሕግ ፍጹም ማክበር ይቻላልን?

ያ ከሥጋ ጋር የሚደረግ ትግል እንደሆነ ተሰምቷችሁ ያውቃልን? ከግል ሕይወታችሁ ምሳሌ ስጡ።

በሕይወታችሁ ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ማስረጃ ምንድ ነው?

በሕይወታችሁ በሥጋና በመንፈስ መካከል ያለውን ጦርነት ታውቃላችሁን? አንድ ምሳሌ ስጡ።

በሥጋዊ ማስተዋል እና ብርታት የምንችለውን ሁሉ በማድረግ እና በመንፈስ፣በማስቻሉ እና በጥበብ በመመላለስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

በሥጋና በመንፈስ መካከል ያለው ልዩነት ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

**ለጸሎት:**

ዓላማዎቹ ፍፁም እና ይህንን መስፈርት ለማሟላት አለመቻላችን የእቅዱን ፍፁምነት የማይቀንሰው በመሆኑ ጌታን አመስግኑት ።

ጌታን በሰው ጥረት እንደሚገባው ማገልገል እንደማትችሉ ትረዱ ዘንድ ጌታ እንዲረዳችሁ ጠይቁት። ከሥጋ የሚበልጠውን የብርታት እና የጥበብ መሻታችሁን እንዲያሳያችሁ ጠይቁት።

መንፈሱ እየለወጠ እና ወደ አብ ዓላማ እየመራን ስለሆነ ጌታን አመስግኑት።

በመንፈሱ ምሪት ትመላለሱ ዘንድ እና በሥጋዊ ጥበባችሁ እንዳትታምኑ እንዲረዳችሁ ጌታን ጠይቁት።

# ምዕራፍ 12 -

# የውስጥ ጦርነት

ሮሜ 7:21-25

*21 እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድስወድ በእኔ ክፉ እንዲያደርብኝ ሕግን አገኛለሁ። 22 በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥ 23 ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ። 24 እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል? 25 በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ። (ሮሜ 7)*

በእነዚህ የሮሜ 7 የመጨረሻ ቁጥሮች ላይ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ትግሉን ያጋራል። በቁጥር 21 ላይ እንዲህ ሲል ይጀምራል፡

*21 እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያደርብኝ ሕግን አገኛለሁ። (ሮሜ 7)*

ከዚህ ጥቅስ በርካታ ነገሮችን እንረዳለን። በመጀመሪያ፣ ኃጢአት የእግዚአብሔርን ዓላማዎች እንዳንከተል ያደርገናል። ሁለተኛ፣ ይህ ኃጢአት ከእኛ የራቀ አይደለም– “በጣም የቀረበ” ነው። በመጨረሻም፣ በዚህ ክፉ የመሰናከላችን እውነታ እንደ ሰው የሚገዛን “ሕግ” ነው። ጳውሎስ እነዚህን ሦስት መሠረታዊ ሥርዓቶች በሚቀጥሉት ጥቅሶች ላይ በዝርዝር ገልጿል፡

ጳውሎስ በውስጣዊ ማንነቱ፣በእግዚአብሔር ህግ እንደሚደሰት ለሮሜ ሰዎች በማሳሰብ ይጀምራል። ወደ ጌታ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወቱ ውስጥ መኖር ጀመረ። መንፈስ ቅዱስ አዕምሮውንና ልቡን ወደ ክርስቶስ መልክ እየለወጠው በእርሱ ውስጥ ይሠራ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ጳውሎስን እየለወጠው እና ለእግዚአብሔር እና ለዓላማው የበለጠ መሻት እና ፍቅር ይሰጠው ነበር። ይህም በሐዋርያው ሕይወት ውስጥ በግልጽ ታይቷል። ሐዋርያው ለጌታ ኢየሱስ ነፍሱን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር። ሰውነቱ ሁሉ የጌታውን ዓላማ ለማገልገል እና በእርሱ ለመመላለስ የተሰጠ ነው። ጳውሎስ በግልጽ እንዲህ ይላል፡-

*22 በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥ (ሮሜ 7)*

ክርስቶስን ማወቅ እና ከእርሱ ጋር በታዛዥነት ለመራመድ የጳውሎስ ትልቁ እና የውስጡ መሻት ነበር። ከክርስቶስ ጋር ስላለው ሕብረት በድፍረት ተናግሯል እንዲሁም ሌሎች በጌታው ያለውን ደስታ ሲያገኙ ለማየት ይጓጓ ነበር።

ጌታ ኢየሱስን እንደ ጌታቸው እና አዳኛቸው አድርገው የሚያውቁ ሰዎች፤ጳውሎስ የሚናገረውን ይረዳሉ። የእግዚአብሔር መንፈስ ልባችንን ለውጦታል። ድሮ ያስደስተን የነበረው አሁን ወድቅ ተደርጓል። አሁን የበለጠ በጌታ ኢየሱስ ደስ ይለናል። ከእርሱ ጋር መሄድ ትልቁ መሻታችን ነው። ስንጎድል ወይም ፊቱ የተሰወረብን ሲመስለን ያሳዝነናል። የጳውሎስን ታላቅ ናፍቆት እና በእግዚአብሔር እና በዓላማዎቹ ያለውን ደስታ እናውቃለን።

ዳሩ ግን ሐዋርያው በቁጥር 23 ላይ በሕይወቱ ውስጥ እየሆነ ያለውን ሌላ ነገር መግለጹን ይቀጥላል፡

*23 ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ። (ሮሜ 7)*

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች እዚህ "በብልቶቼ የሚማርከኝ ሌላ ሕግ አያለሁ" ሲል የነገራቸውን አስተውሉ። በመጀመሪያው ቋንቋ "ብልቶች" የሚለው ቃል የአካል ክፍሎችን ያመለክታል። ሐዋርያው ትክክል የሆነውን ለማድረግ ሲፈልግ ሥጋው ወደ ሌላ አቅጣጫ እየመራው እንዳለ እየነገረን ነው።

ከተወሰነ ጊዜ በፊት አንድ ሚስዮናዊ ጓደኛዬን ለመጎብኘት ቶሮንቶ ነበርኩ። እኔ በአውራ ጎዳና በእግረኛው መንገድ ላይ ባለው የኤሌትሪክ አውቶብስ አስፋልት ላይ ነበርኩ። ወደ ጓደኛዬ ወደሚወስደው መንገድ ለመዞር ስዘጋጅ፣የሞተር ብስክሌቴ ጎማ ተንሸራቶ ወደ ኤልክትሪክ አውቶስሱ መንገድ ወረወረኝ። ሞተር ብስክሌቴ ከእኔ ርቆ ሲንሸራተት ማየቴን አስታውሳለሁ። የፍጥነቱ ኃይል በጎኑ ላይ እንዲያርፍ

አደረገው። በዚያን ጊዜ "ተነሥቼ ወደ እሱ ብፈጥን፣ከግጭት እና ጥፋት መከላከል እችላለሁ" በማለት በአዕምሮዬ አስቤ እንደነበር አስታውሳለሁ። አዕምሮዬ ያንን ቢነግረኝም፤ሰውነቴ ግን ምላሽ አልሰጠም። ሞተር ብስክሌቴ ከመቆሙ በፊት በመንገዱ በጎኑ በኩል እየተንሸራተተ እና እየተጋጨ በዚያ ቀጠለ።

በዚያን ጊዜ አዕምሮ ማድረግ በሚፈልገው እና አካል በሚሠራው መካከል ያለውን ልዩነት አወቅሁ። ጳውሎስ ጌታን የማገልገል ፍላጎት ነበረው። ዳሩ ግን ኃጢአተኛ ሥጋው ሌላ ሕግ ማለትም የኃጢአት ሕግ የተከተለ ይመስላል። በጳውሎስ ውስጥ ጦርነት ተነስቶ ነበር። እግዚአብሔርን የመታዘዝ ፍላጎት ነበረ፣ነገር ግን በመታዘዝ ለመመላለስ በሰውነቱ ታግሏል። ቁጥር 24 ላይ እንዲህ እያለ በዚህ ትግል ውስጥ ያልፋል፡

*24 እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?*

እዚህ ላይ ጳውሎስ ነጻ መውጣት ስለሚያስፈልገው "ለሞተ ስለተሰጠ ሰውነት" መናገሩን አስተውሉ። ጳውሎስ የጠቀሰው ለሞት የተሰጠው አካል በከፊል የፈለገውን የማያደርግ ሥጋዊ አካሉ ነው። "ብልቶቹ" (ሰውነቱ በአካሉ ሁሉ) ተማርኮ ነበር (ቁጥር 23) ። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የኃጢአት ሕግ ምድራዊ አካሉን በምርኮ እንደያዘው ተናግሯል (ቁጥር 23) ።

ሐዋርያው የኖረበት አካል በሌላ ሕግ ይመራ ነበር። ከእግዚአብሔር ፈቃድ እና ዓላማ ጋር በሚቃረኑ ፍላጎቶች ውስጥ አልፏል። ጌታ እግዚአብሔርን የማያከብረውን በሥጋው

ውስጥ ያለውን ኃጢአት ያውቅ ነበር። ሰውነቱ የኃጢአት ምኞትን ብቻ ሳይሆን በኃጢአት እርግማንም ሥር ነበር። የኃጢአት ቅጣት ሞት ነው (ሮሜ 6፡23 ተመልከቱ) ። የጳውሎስ ሥጋ ይህን ሞት እየተለማመደ ነበር። ሰውነቱ ለበሽታ እና ለመበስበስ የተጋለጠ ነበር። እያረጀ እና እየደከመ ነበር፤በመጨረሻ ሞቶ መቃብር ውስጥ ያርፋል። እንደ ሚች፤ ደዌ እና ኃጢአት ፍጥረቱን አጠፋው። ፍላጎቱ ለጳውሎስ አስጸያፊ ነበር። ሐዋርያው ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ይላል፡-

*27 ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ። (1ኛ ቆሮንቶስ 9)*

ጳውሎስ እንደሚለው፣የኃጢአት ጫናዎች ያለበትን አካል እየጎሰመ ማስገዛት ነበረበት። ታላቅ ክፋት ማድረግ የሚችል ነበር። ጳውሎስ ከዚህ “ለሞት ከተሰጠ ሰውነት” መዳን በጣም እንደሚያስፈልገው ተሰምቶት ነበር።

ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ለሞቱ ሲዘጋጅ እና ከአብ ጋር በጸሎት ጊዜ ለማሳለፍ ሲሄድ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲጸልዩለት ነገራቸው። ኢየሱስ በጸሎት ካደረገው ከፍተኛ ተጋድሎ ሲመለስ ደቀ መዛሙርቱ ተኝተው አገኛቸው። በማቴዎስ 26፡41 እንዲህ ሲል ሞግቷቸዋል፡

*41 ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው። (ማቴዎስ 26)*

ኢየሱስ *ሥጋዊ* አካላቸው ደካማ እንደሆነ እና ወደ ፈተና እንደሚገባ ለደቀመዛሙርቱ እንዴት እንዳሳሰባቸው አስተውሉ። ከመካከላችን በ*ሥጋ* የሚሳብ እና ድካሙን ያላወቀ ማን አለ? ሐዋርያው ጳውሎስ በ*ሥጋ*ው ውስጥ ስላለው ተጋድሎ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ "ለዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" ሲል ጮኸ። ይህንን ጥያቄ በቁጥር 25 ላይ ይመልሳል፡

*25 በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። (ሮሜ 7)*

ከዚህ የኃጢአተኛ አካል ነጻ የመውጣቱ ተስፋ ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ ነበር። ጳውሎስ ስጋ ሊገሰጽ እና በቁጥጥር ስር ሊሆን እንደሚገባ አስተምሯል። የመጨረሻው ድል ግን በኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ በሰው ልጅ ጥረት እና ተግሣጽ አይመጣም።

በሕይወት ውስጥ አንድ ትልቅ እርግጠኝነት አለ - ሰውነታችን ይሞታል። በእነዚህ *ሥጋዊ* አካላት ውስጥ ያሉትን የኃጢአት ውጤቶች ጎስመን ስናስገዛቸው የሞት እርግማን ሁልጊዜ በመጨረሻ ተሸናፊ ይሆናል። ይህን ሂደት ለማስቆም ምንም ማድረግ አንችልም።

ጌታ ኢየሱስ ግን ይቅርታንና ተስፋን አመጣልን። ከዚህ ከኃጢአትና ለሞት ከተሰጠ *ሥጋ* ነጻ የምንወጣበት ቀን ይመጣል። ነፍሳችን አዲስ እና ፍጹም አካልን እየጠበቀች ወደ ጌታ መገኘት ትገባለች። በዚያ አዲስ አካል ውስጥ፣ከህመም፣ ከስቃይ እና ከእንባ ነጻ በሆነው በአዳኛችን ፊት እንኖራለን (ራዕይ 21፡4) ። የተሰበረው እና በሐጢያት ስሜት የተበከለው ምድራዊው ሰውነታችን ይጠፋል እናም ከእንግዲህ አይኖርም።

ጳውሎስ በቁጥር 25 ላይ ግራ በሚያጋቡ ቃላት ይደመድማል፡

*25 … እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ።*

ሐዋርያው ለሮሜ ሰዎች አዕምሮው ከእግዚአብሔር እና ከዓላማው ጋር የሚስማማ ቢሆንም እንኳን አካሉ እንዳልሆነ አስተውሉ። ልቡ እግዚአብሔርን ለመከተል ባለው ፍላጎት ይመራ ነበር፤ ነገር ግን ሥጋው እንደዚያ አልነበረም። ሥጋው የዚህ ዓለም አካል ነበር እና በዚህ ዓለም ነገር ሊደሰት ይናፍቅ ነበር። ደካማ እና ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር መንገድ የራቀ ነበር።

ሐዋርያው በእግዚአብሔር ሕግ ፊት ሲቆም ራሱን ጎድሎ አገኘው። የፍቃደኝነት መንፈስ ነበረው ነገር ግን ማድረግ የማይፈልገውን ሲያደርግ እና ማድረግ የሚገባውን ሲተው ራሱን አግኝቶ ነበር (ሮሜ 7፡18) ። በአዕምሮው ሕጉን ሲያገለግል ነገር ግን በሥጋው ኃጢአትን ሲያገለግል አገኘው (ሮሜ 7፡25) ። በእርሱ ውስጥ ታላቅ ጦርነት ተነስቶ ነበር። ይህንን ጦርነት እንዴት ማሸነፍ ቻለ? በዚህ ኃጢአተኛ ሥጋው እግዚአብሔርን እንዴት ሊያከብር ቻለ? ይህንንም ሐዋርያው በሮሜ 8 ላይ ይናገራል።

**ለምልከታ:**

መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ እና ለዓላማው ያላችሁን መሻት እንዴት እየለወጠው ነው? ወደ ክርስቶስ ከመጣችሁ በኋላ በህይወታችሁ ምን አይነት ለውጦችን አይታችኋል?

ሁልጊዜ ትክክል እንደሆነ የምታውቁትን ታደርጋላችሁን? የሥጋ ምኞት ምንድን ነው? ሥጋችሁን ለማስደሰት ሐጢአትን ስታደርጉ ራሳችሁን ታገኛላችሁን?

ኃጢአተኛ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁን ኅብረት እና ከእርሱ ጋር መመላለችሁን የሚከለክለው እንዴት ነው?

ጳውሎስ ለሥጋው ኃጢአተኛ ምኞት የነበረው አመለካከት ምን ነበር? በሥጋ ምኞት ላይ ድል አግኝታችኋልን?

**ለጸሎት**:

ባህሪያችሁን የመቀየር እና ክርስቶስን የመምሰል ሥራውን እንዲቀጥል መንፈስ ቅዱስን ጠይቁት።

በኃጢአተኛ የሥጋ ተፈጥሮ ላይ ድል እንዲሰጣችሁ ጌታን ጠይቁት። አሁንም በኃጢአተኛ ሥጋ ብንኖርም፣በክርስቶስ ይቅርታ እና በእኛ ውስጥ በሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ማንነት ለኃጢአት ችግር መፍትሔ ስላዘጋጀልን አመሰግኑ።

ከህግ እና ከሰዎች ጥረቶች ውጭ የመፍትሄውን አስፈላጊነት ለማየት ጌታ እንዲረዳችሁ ጠይቁት። በእርሱ ፊት ጥፋተኛ

እንደሆናችሁ እና የእርሱን ይቅርታ እና ማስቻል እንደፈለጋችሁ ለመናዘዝ ትንሽ ጊዜ ውሰዱ።

## ምዕራፍ 13

## የሕይወት መንፈስ ሕግ

---

ሮሜ 8:1-4

*1 እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። 2 በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና። 3 ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፥ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፤ 4 እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ። (ሮሜ 8)*

ሐዋርያው በምዕራፍ 7 የመጨረሻ ክፍል ላይ በሥጋ እግዚአብሔርን ማስደሰት እንደማይቻል ለሮሜ ሰዎች አሳይቷቸዋል። አዕምሮ በእግዚአብሔር ሕግ ለመመላለስ ፈቃደኛ ሊሆን ቢችልም፣ሥጋ ግን ደካማ እና ሌላ ሕግ የሚከተል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ትግል ውስጥ አልፏል። ይህ ጦርነት በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ይካሄዳል። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ፣ ብዙዎች ሥጋን እና ኃጢአተኛ

መሻቱን ለማስገዛት ይፈልጉ ነበር። አንዳንዶች የኃጢአትን የሥጋ መሻት ለመግታት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

በ459 የሞተው ስምዖን እስታይሊስ በዘመናዊቷ ሶሪያ ውስጥ በአምድ አናት ላይ ለ37 ዓመታት ተቀምጦ ነበር። አንዳንድ የታሪክ ተመራማሪዎች ይህ አመድ እስከ 50 ጫማ ከፍታ ይደርስ እንደነበረ ያምናሉ። ይህን ያደረገው ሥጋውን በመጎሰም ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ነው (https://am.wikipedia.org/wiki/Simeon_Stylites) ። ሌሎችም ቅዱሳን ሰውነታቸውን ከክፉ ያነጹ ዘንድ በአለንጋ ይደበድቧቸው ነበር። ዛሬም በአንዳንድ አገሮች ውስጥ ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ጌታ ኢየሱስ ያደረገላቸውን በመኮረጅ በመስቀል ላይ እስከመሰቀል ይደርሳሉ።

ልንጠይቀው የሚገባን ጥያቄ፡- ሰውነታችንን ከተፈጥሯዊ ፍላጎት ማጽዳት እንችላለን ወይ? ዓይናችሁን ብታጠፉት ይህ ማየት የማትፈልጉትን ነገር እንዳታዩ ሊያደርጋችሁ ይችል የሆናል ነገር ግን አዕምሯችሁን ስለ ኃጢአት ከማሰብ አያግደውም። መሄድ ወደማትፈልጉበት ቦታ መሄድ ወይም መንካት እንደሌለባችሁ የምታውቁትን ነገሮች መንካት እንዳይችሉ እግሮቻችሁን እና እጆቻችሁን ልትቆርጡ ትችላላችሁ። ይህ ድርጊት ግን የልብን ፍላጎት አይለውጥም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሮሜ 8ን ጠንከር ያለ መልዕክት በመስጠት ይጀምራል።

*1 እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። (ሮሜ 8)*

ሐዋርያው የተናገረውን ተመልከቱ። የሞት ፍርድ ሊፈረድብን እንደማይገባ እየነገረን ነው። ለእኛ የማምለጫ መንገድ አለ። እርሱም በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት ከኃጢአት ቅጣት ነጻ መውጣታቸው ነው።

የምኖረው ካናዳ ውስጥ በሚገኝ እና ወደ ኒውፋውንድላንድ ደሴት ግዛት ከሚጓዝ ጀልባ ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ ነው። በአቅራቢያው ያለው መንገድ በጀልባ 6 ሰዓት ያህል ይወስዳል። ጀልባው ውቅያኖሱን አቋርጦ ወደ ኒውፋውንድላንድ ይወስደኛል - ማድረግ ያለብኝ ነገር በእሱ ላይ መሳፈር ብቻ ነው። በጀልባው ላይ ስሆን ሁሉንም ሥራ የሚሰራው ጀልባው ነው። በቀላሉ በጉዞው ደስተኛ ነኝ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በሮሜ 8፡1 በክርስቶስ ቢሆኑ ከኩነኔ ነጻ እንደሆኑ ይነግራቸዋል። በጀልባው ላይ መሆን እንደሚያስፈልገኝ ሁሉ በክርስቶስም መሆን ያስፈልገኛል። በዚያ ጀልባ ላይ ስሆን በጥረቴ ወደ መዳረሻዬ መድረስ እንደምችል አያሳስበኝም - ጀልባው ይህን እያደረገልኝ ነውና። ከክርስቶስ ጋር ባለኝ ግንኙነትም ይህ ተመሳሳይ ነው። በክርስቶስ ከሆንኩ፤በአዕምሮዬ ውስጥ ሊኖር የሚችለው የመጨረሻው ሃሳብ በራሴ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት እችል እንደሆነ ማሰብ ነው። በክርስቶስ በመሆኔ፣አለመቻሌን አምኜ በግል ጥረቴ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት መሞከሩን አቁሜያለሁ፣- ይልቁንስ፣ ለእርሱ በመገዛት ሥራውን እንዲሰራ ፈቅጃለሁ።

ወደ ክርስቶስ የሚመጡ፣የሚስፈልጋቸውን አምነው ይቀበላሉ። ኃጢአተኞች መሆናቸውን ይገነዘባሉ። እግዚአብሔር በሕግ የሚፈልገውን ሕይወት መኖር የማይችሉ መሆናቸውን ይናዘዛሉ። እነርሱ ከክብሩ እንደጎደሉ እና የእርሱን መስፈርቶች ለማሟላት የማይችሉ ሆነው መቀጠላቸውን ያውጃሉ። ወደ ክርስቶስ የሚመጡት ሌላ መንገድ ስለሌለ ነው። ይቅር እንዲላቸው ይፈልጋሉ። ወደ አብ እንዲያመጣቸው ይፈልጋሉ። በክርስቶስ መሆን ማለት በሰው ጥረት ደህንነትን ለማግኘት የሚደረግን የሰውን ጥረት ሁሉ መተው ነው። ወደ አብ የሚወስደው ብቸኛው መንገድ እርሱ መሆኑን መቀበል ሲሆን ከይቅርታውና በረከቱ በስተቀር ለዘላለም የጠፋን እንሆናለን።

ጳውሎስ መቀጠል በቁጥር 2 ላይ ስለ ሌላ ህግ ይናገራል። በሞት ስቃይ ላይ ፍጹም መታዘዝን ስለሚጠይቀው እና ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም መለየትን ስለሚያመጣው “የእግዚአብሔር ሕግ” ያስተምራል። በተጨማሪም ሥጋን እና ክፉ ምኞቶቹን የሚገዛ ስለሚመስለው “የኃጢአትና የሞት ሕግ” ተናግሯል። እንዲሁም “የሕይወት መንፈስ ሕግን” ያሳውቃል።

*2 በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና።*

ሐዋርያው ጳውሎስ በብርታታችን እግዚአብሔርን ማስደሰት ወይም የእሱን መሥፈርቶች ማሟላት እንደማንችል አሳይቶናል። አሁን አዲስ መንገድ ያስተዋውቀናል፤ያም የመንፈስ መንገድ ነው። ይህንን አዲስ መንገድ የመንፈስ "ህግ" ብሎ እንደጠራው አስተውሉ። ሕግ ብሎ በመጥራት፣አሁን

ባህሪያችንን መግዛት ያለበት እርሱ እንደሆነ ሐዋርያው እየነገረን ነው። አሁን የምንገዛበት ሕግ መንፈስ ቅዱስ፣መሪነቱ እና መመሪያው ነው።

በቁጥር 2 ላይ ሌላ ነገር አስተውሉ። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የሕይወት መንፈስ ህግ በክርስቶስ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ እንዳወጣቸው ተናግሯል።

የሕይወት መንፈስ ሕግ "በክርስቶስ" ያሉትን ነጻ ያወጣቸዋል። “በክርስቶስ” የሚለው ሐረግ ጠቃሚ ነው። የመንፈስ ሕግ የሚሰራው በክርስቶስ ላሉት ብቻ ነው። የመዳናችን ዋስትና የሆነው የክርስቶስ መንፈስ መገኘት ነው። በእኔ ሊያድር በመጣ ጊዜ መንፈሳዊ ሕይወትን ሰጥቶኛል። በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ የሚኖር የእግዚአብሔር መንፈስ አለ።

በክርስቶስ ያሉት ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ ወጥተው በሕይወት መንፈስ ሕግ ሥር ይኖራሉ። በክርስቶስ ከሆንን በአሮጌው የሕግ መንገድ ሥር አይደለንም። በጥረታችን ይህንን ሕግ መጠበቅ እንደማንችል ተመልክተናል። በእርሱ ሥር ሞት ተፈርዶብን ነበር። አሁን ኃጢአታችን ስለተሰረየልን ለክርስቶስ መኖር ያለብን እንዴት ነው? ጳውሎስ በሕይወት መንፈስ ሕግ ሥር መኖር እንዳለብን ይነግረናል።

ሕጋችን የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። እሱ አሁን የእኛ መሪ እና መካሪ ነው። ለእርሱ እና ለምሪቱ እንገዛለን። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ብቻ ሳይሆን በእነዚህ መሥፈርቶች እንድንመላለስ ያስችለናል። ጳውሎስ ልጁን በመላክ ሕጉ የማይችለውን በእኛ እንዳደረገ ለሮሜ ሰዎች ይናገራል፡

*3 ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፥ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፤ 4 እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ። (ሮሜ 8)*

በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረውን ለማብራራት ትንሽ ጊዜ ወስደን መቆየታችን አስፈላጊ ነው።

***እግዚአብሔር ሕጉ ማድረግ ያልቻለውን አደረገ።***

*3 ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፥ (ሮሜ 8)*

በቁጥር 3 ላይ ሐዋርያው ለሮሜ ሰዎች *ሥጋ* ሕጉን እንዳዳከመ ይነግራቸዋል። እዚህ ላይ ጳውሎስ እየነገረን ያለው በኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን የተነሳ የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ እንዳልቻልን ነው። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ከሕግ ቅጣት ነጻ የምንወጣበትን እና በእሱ ፊት የምንቆምበትን መንገድ አዘጋጅቶልናል።

*እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፤*

ትእዛዛቱን ለመጠበቅ ባለመቻላችን የእግዚአብሔር መፍትሄ ምን ነበር? ቁጥር 3 እግዚአብሔር ልጁን በኃጢአተኛ *ሥጋ* ምሳሌ እንደ ላከ ይነግረናል። የእግዚአብሔር እቅድ ልጁን ያካተተ ነበር። የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ *ሥጋን* ለበሰ። የለበሰው *ሥጋ* ለሥጋችን መከራና ፈተና ሁሉ የተገዛ ነበር።

ሰውነቱ ያረጅ እና ህመም ይሰማው ነበር። በዚያ አካል ውስጥ ጌታ ኢየሱስ መከራ ተቀብሎ ሞተ።

### *ጌታ ኢየሱስ ሐጢአትን በስጋው ኮነነ*

ጳውሎስ በመቀጠል በቁጥር 3 ላይ ጌታ ኢየሱስ ኃጢአትን በሥጋ እንደኮነነ ለሮሜ ሰዎች ያስተምራቸዋል። “ኮነነ” የሚለው ቃል በቀጥታ ሲተረጎም አንድ የፍርድ ቅጣት መናገር ወይም መፍረድ ማለት ነው። ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚናገረው ጌታ ኢየሱስ የፍርዱን ቅጣት የተናገረው በሥጋ ኃጢአት ላይ መሆኑን ነው። *ሥጋንም* በእግዚአብሔር ላይ ስላመፀ የሞት ፍርድ ፈረደበት።

### *የሕግ ትዕዛዛት ተፈጽመዋል*

ጌታ ኢየሱስ *ሥጋ* ላይ ሞት በመፍረድ የሕጉን ትዕዛዛት ይከተል ነበር። *ሥጋ* በእግዚአብሔር ላይ ያመጸ በመሆኑ ሞት ይገባዋል። ያንን ሐጢአተኛ *ሥጋ* ከእርሱ ጋር ወደ መስቀል ወስዶ ጠርቆ ገደለው።

### *የሕጉ ትዕዛዛት በእኛ ተፈጽመዋል*

በቁጥር 4 ላይ “በእኛ” የሚለውን ሐረግ አስተውሉ፡

*3 በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ። (ሮሜ 8)*

"በእኛ" የሚሉት ቃላት ጠቃሚ ናቸው። የሕጉ ትዕዛዛት በእኛ ይፈጸሙ ዘንድ ክርስቶስ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጥቷል። ቅጣቱ

ይሽፈን ዘንድ ሞተ። እሱ የሞተው በእኔ ምትክ ነው። አሁን ከሕግ ቅጣት ነጻ ወጥቻለሁ። ኢየሱስ ዕዳዬን ከፍሏል። ለኃጢአትና ለሞት ሕግ ከዚህ በኋላ የመገዛት የለብኝም።

*ከእንግዲህ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ አንመላለስም*

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ከሕግ ነጻ ስለወጡ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ እንደማይመላለሱ ይነግራቸዋል። ጥበብ የምናገኘው ከመንፈስ ቅዱስ እና የእግዚአብሔር ቃል እንጂ ከሥጋ አይደለም። ከአሁን በኋላ በማስተዋላችን አንታመንም ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ላይ እንደገፋለን። የራሳችን ያልሆነ ብርታት እንደሚያስፈልገን ተረድተናል ስለዚህ በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ላይ የምንደገፍ ነን። የኤሌክትሪክ መሰኪያውን ከሰው ጥበብ እና ብርታት ላይ ነቅለነዋል። አሁን ወደ ሌላ የኃይል ምንጭ - የመንፈስ ቅዱስ ማንነት ላይ ሰክተናል። እርሱ የእኛ ጥበብ እና መሪ ነው። እርሱ ብርታታችን እና ኃይላችን ነው። ብርታት እንዲሰጠን እንጮሃለን። ከሰው ማስተዋል ይልቅ በእርሱ መሪነት እናምናለን። እንዲያውም የሰውን ልብ ከከፋ መሻቱ እና ምኞቱ ጋር ወደመካድ ደርሰናል። ራስ ወዳድ እና ዓመጸኛ ከሆነው የሰው ልጅ አስተሳሰብ ርቀናል። ከመንፈስ ቅዱስ ስዕብና ጋር እንዴት መሄድ እንዳለብን እየተማርን ነው። የእግዚአብሔር መገኘት፣በመንፈስ ቅዱስ ስዕብና ውስጥ፣መሪና አጽናኝ ነው። አብ እንደሚፈልገው እንሄድ እና እናገለግል ዘንድ ያስችለኛል። ይህ ማለት ፍጹም የሆነ ሕይወት እኖራለሁ ማለት አይደለም። ሁልጊዜ በእግዚአብሔር መንፈስ መታመንን እየተማርኩ ነው። አንዳንድ ጊዜ መስማት ይሳነኛል። ከሱ ይልቅ ጥበቤን ለመታመን አሁንም

እፈተናለሁ:: ነገር ግን እነዚህ ኃጢአቶች በጌታ በኢየሱስ ተሸፍነዋል:: የመንፈስ ቅዱስን ህልውና ለማወቅ እና በህይወቴ ውስጥ የእርሱን አመራር እና ኃይልን ለማወቅ በሞቱ ነጻ ወጥቻለሁ:: "እንደ መንፈስ" ለመመላለስ እመርጣለሁ እንዲሁም የእርሱን ትምህርት ለማወቅ እና ለስልጣኑ እና ለምሪቱ ለመገዛት የሕይወቴ ዓላማ አደርጋለሁ:: ጳውሎስ ይህንን በእግዚአብሔር መንፈስ ጌትነት ሥር ያለውን ህይወት ለመግለጽ በምዕራፍ 8 ይቀጥላል፤

**ለምልከታ**:

*ሥጋን በማስገዛት ወይም ሰውነታችንን በመከራ በማሰቃየት ኃጢአትን ማስወገድ ይቻላልን?*

*"በክርስቶስ መሆን" ሲባል ምን ማለት ነው? ይህ ስለ ድነት ያላችሁን ግንዛቤ ቀይሮታልን?*

*የመንፈስ ሕግ ምንድን ነው?*

*የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያስፈልጋችሁ ተረድታችኋልን? በሰው ጥረት እና ጥበብ ላይ የተመሰረተው ክርስትናችሁ ምን ያህል ነው? የእግዚአብሔር መንፈስ በህይወታችሁ እንዴት እየሰራ ነው?*

**ለጸሎት:**

የኃጢያታችሁን ቅጣት ስለከፈለ ጌታን አመስግኑት።

ጌታ በመስቀል ላይ ለእናንተ በሰራው ሥራ እምነት እንዲሰጣችሁ ጠይቁት። ለድነታችሁ ከተሰራው ሌላ ምንም ነገር ስለሌለ እና በክርስቶስ በመሆናችሁ ምክንያት በአብ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት ስላላችሁ አመስግኑት።

በሕይወታችሁ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንደሚስፈልጋችሁ ያሳያችሁ ዘንድ ጌታን ጠይቁት። ለእርሱ እና ለምሪቱ መገዛት ምን ማለት እንደሆነ እንዲያስተምራችሁ የእግዚአብሔርን መንፈስ ጠይቁ። እንዲመራን ቃሉን ስለ ሰጠን እንዲሁም ቃሉን እና የአብንን ዓላማ በተግባር ላይ በማዋል ረገድ ስለሚመራን አመስግኑት።

በሥጋ የማንችለውን እናደርግ ዘንድ መንፈሱ ስላስቻለን ጌታን አመስግኑት። በሕይወታችሁ ከዚህ የእግዚአብሔር ስራ ከፍ ያለ ተስፋ እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

# ምዕራፍ 14 -
# ሥጋው እና መንፈሱ

ሮሜ 8:5-8

*5 እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። 6 ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው። 7 ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ 8 በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም። (ሮሜ 8)*

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው ሁለት የሕይወት መንገዶች አሉ። በሮሜ 8፡5 ላይ አንድ ሰው እንደ ሥጋ ወይም እንደ መንፈስ ፈቃድ መኖር እንደሚችል ለሮሜ ሰዎች ይነግራቸዋል። ሐዋርያው በሮሜ ለሚኖሩ አማኞች እየተናገረ መሆኑን አስታውሱ። ከእነዚህ ሁለት መንገዶች በአንዱ ክርስቲያናዊ ሕይወታቸውን መምራት እንደሚችሉ እየነገራቸው ይመስላል። እስቲ እነዚህን ሁለት የሕይወት መንገዶች እንመልከት።

## *እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር*

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ እንደ *ሥጋ ፈቃድ* መኖርን በተመለከተ ብዙ ነገሮችን ተናግሯል። በቁጥር 5 ላይ ለሮሜ ሰዎች የነገራቸውን አስተውሉ፡

*5 እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። (ሮሜ 8)*

እዚህን ሁለት ነጥቦች ማስቀመጥ ያስፈልገናል።

በመጀመሪያ ስለ *ሥጋ* ማሰብ፣ ክፉ መሻቱን እና ምኞቱን ለማስደሰት መፈለግ ነው። *ሥጋዊ* ደስታችን ጌታችን ይሆናል። በምድራችን እነዚያን መሻቶች እና ምኞቶች ተቀባይነት ባላቸው ባህሪያት የሚገድቡ ሕጎች እንዳሉ አይካድም። ሁሉም ሰው *ሥጋዊ* ፍላጎቱን ለማርካት የፈለገውን ማድረግ ቢችል ኖሮ ሕይወት ምን ሊመስል እንደሚችል አስቡ?

ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ሲጽፍ ስለ *ሥጋ ሥራ* እንዲህ ሲል ይገልጻል፡

*19 የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥ መዳራት፥ 20 ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ 21 ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። (ገላትያ 5)*

*እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ሰዎችን ለይቶ ለማወቅ* ብዙ ርቀት ማየት አይኖርብንም፡፡ የዝሙት እርኩሰት፣ስካር፣ቅናት፣ቁጣ እና የመሳሰሉት ነገሮች በዙሪያችን ያሉ እና የወደቀው ዓለም አስተሳሰብ አካል ናቸው፡፡

በዚህ አውድ ራሳችንን ልንጠይቀው የሚገባን ጥያቄ፡- ለአማኞች እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ይቻላልን? ለዚህ መልስ ለመስጠት፤ ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ላሉ አማኞች በ1ኛ ቆሮንቶስ 3 ላይ ወደተናገረበት ወደ ትምህርቱ ልመለስ፡

*1 እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም፡፡ 2 ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ 3 ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም፡፡ ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን? (1ኛ ቆሮንቶስ 3)*

በ1ኛ ቆሮንቶስ 3፡1 ላይ ጳውሎስ "ለወንድሞች" እንደተናገረ አስተውሉ፡፡ አንድምታው እነዚህ ሰዎች ክርስቲያኖች ነበሩ ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሐዋርያው እነዚህን ወንድሞች "መንፈሳዊ ሰዎች" ብሎ ሊጠራቸው አልቻለም፡፡ ከዚህ ይልቅ "የሥጋ ሰዎች" ብሎ መጥራት ነበረበት፡፡ እነዚህ አማኞች "ገና ሥጋውያን ናቸው" እና "በሰው ልማድ የሚመላለሱ" እንደሆኑ ይነግራቸዋል (ቁጥር 3) ፡፡ እነዚህ የቆሮንቶስ አማኞች የዓለማዊን ኑሮ ፍሬ በቅናት እና በክርክር ያሳያሉ፡፡ በዚህ መሠረት አማኞችም እንደ ሥጋ ፈቃድ ሊኖር ይችላሉ ማለት ነው፡፡ የቆሮንቶስ አማኞች በራሳቸው ፍላጎት እና መሻት ላይ

ያተኮሩ ነበሩ እናም ምኞታቸው ባልረካ ጊዜ ለቅናት እና ለጠብ ተገዢ ሆኑ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው ሁለተኛ መልዕክቱ ላይ እንዲህ ይላል፡

*20 ስመጣ፥ እንደምወደው ሳትሆኑ አገኛችሁ ይሆናል እኔም እንደምትወዱት ሳልሆን ታገኙኝ ይሆናል ብዬ እፈራለሁና፤ ምናልባት ክርክር ቅንዓትም ቁጣም አድመኝነትም ሐሜትም ማሾክሾክም ኩራትም ሁከትም ይሆናሉ፤ 21 እንደ ገና ስመጣ በእናንተ ዘንድ አምላኬ እንዲያዋርደኝ፥ አስቀድመውም ኃጢአት ከሠሩትና ስላደረጉት ርኵሰትና ዝሙት መዳራትም ንስሐ ካልገቡት ወገን ስለ ብዙዎች ምናልባት አዝናለሁ ብዬ እፈራለሁ። (2ኛ ቆሮንቶስ 12)*

በ2ኛ ቆሮንቶስ 12፡20-21 ላይ የጳውሎስ ጭንቀት የነበረው የቆሮንቶስ ሰዎች የሥጋ ፍሬ በሆኑት “በክርክር፣በቅንዓት፣በንዴት፣በጥላቻ፣በስድብ፣በሃሜት፣ በትዕቢትና በሁከት” ውስጥ በመመላለስ ስለመቀጠላቸው በመስጋቱ ነበር። እነርሱን ለማየት ቢሄድ በቤተክርስቲያን በዝሙትና በእርኩሰት ውስጥ ሆነው እንደሚያገኛቸው ይጠብቅ ነበር። እነዚህ ሰዎች ከእነዚህ የኃጢአት ልምምዶች ፈጽሞ ንስሐ እንዳልገቡና በዚያ ውስጥ መኖር እንደቀጥሉ ይፈራ ነበር። ሐዋርያው ለገላትያ ሰዎች ሲጽፍ የሥጋን ምኞት ስለመፈጸም በተለይ ያስጠንቅቃቸዋል፡

*16 ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። 17 ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። (ገላትያ 5)*

ክርስቲያን በመሆናችን ብቻ ከሥጋ ፈተና ነጻ እንደወጣን ማሰብ የለብንም። የኃጢአተኛ ተፈጥሮ መሻቶች በውስጣችን እርካታን ይፈልጋሉ። እነዚህ ምኞቶች ለእግዚአብሔር ፈቃድ እና ዓላማ ተገዥ መሆን አለባቸው።

ሐዋርያው ያዕቆብም እንኳን አንባቢዎቹን ከሥጋዊ ፍላጎታቸው ጋር እንዲዋጉ አጥብቆ ይጠይቃቸዋል፡-

*1 በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምቾቶቻችሁ አይደሉምን? 2 ትመኛላችሁ ለእናንተም አይሆንም፤ ትገድላላችሁ በብርቱም ትፈልጋላችሁ፥ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ ትዋጉማላችሁ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤ 3 ትለምናላችሁ፥ በምቾቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም። 4 አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል። (ያዕቆብ 4)*

ሐዋርያው ያዕቆብ ለሥጋ መሻታቸው ለተገዙ አማኞች እየተናገረ መሆኑን አስተውሉ። በዘመናችን በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው አብዛኛው ችግር እንደ ሥጋዊ ፍላጎታቸው ከሚመላለሱ አማኞች ጋር የተያያዘ እንደሆነ አስባለሁ።

ስለ ሥጋ ማሰብ የምንችልበት ሁለተኛ መንገድ አለ። ያም ማለት የሥጋን ደመ ነፍስ፤ብርታት እና አመክንዮትን መታመን ነው። እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ነጥብ ላይ በጣም ግልጽ ነው። የነቢዩን የኤርምያስን ቃል አድምጡ፡

*5 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው። (ኤርምያስ 17)*

ነቢዩ በሥጋ የሚታመኑ ሰዎች ምን እንደሚደርስባቸው በግልጽ ተናግሯል። ለእነሱ ምንም ተስፋ የለም። መልካምን አያዩም። ፍሬ እንደሌለው የበረሃ ተክል ይሆናሉ። ይህ ማለት በሥጋ ብዙ ታላላቅ ነገሮችን ማድረግ አንችልም ማለት አይደለም። በሰዎች ጥበብ እና ክህሎት የተገነቡ ታላላቅ የንግድ ስራዎችን በዙሪያችን እንመለከታለን። በሥጋ ጥበብና ብርታት ብዙ ሃብትና ብልጽግና ተከማችቷል። የዚህ ብልጽግና ችግር ይህችን ምድር ተሻግሮ አለመሄዱ ነው። ዝገት እና መበስበስ ይበላዋል። ለአፍታ ያብባል ከዚያም አይኖርም። ይህን ሃብት የሚያከማቹ ያረጃሉ ይሞታሉም። ከዚያም ለሕይወታቸው መልስ ለመስጠት በፈጣሪያቸው ፊት ይቆማሉ። ከእርሱ ያልሆነው ሁሉ ይጠፋል፣ ራቁታቸውንም በፈጣሪያቸው ፊት ይቆማሉ። ጌታ ኢየሱስ ራሱ እንደተናገረው፡-

*36 ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? (ማርቆስ 8)*

ኤርምያስ በመቀጠል ስለ ሰው ልብ ምኞት እና አመክንዮነት እንዲህ ሲል ይናገራል፡

*9 የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል? (ኤርምያስ 17)*

የምሳሌ 3 ጸሐፊ ለአንባቢዎቹ እንዲህ ይላቸዋል፡

*5 በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤*

የሰው ልብ ከሁሉ በላይ ክፉ ስለሆነ እና ፍጥረቱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚቃረን ስለሆነ መሻቶቹን መደገፍ አንችልም። ለአንድ ሰው ልትሰጡት የምትችሉት በጣም መጥፎ ምክር "ልብህን ተከተል" የሚል ነው። አማኞች እንኳን በልባቸው ታምነው በሰው ጥበብ ሊሳሳቱ ይችላሉ።

ጳውሎስ በሮሜ 8 ላይ በሥጋ ፈቃድ ስለ መኖር ሌላ ነገር ይናገራል፡-

*6 ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ (ሮሜ 8)*

ሃሳባችንን በኃጢአተኛ ተፈጥሮ እና በመንገዶቹ እንዲሁም ውስጣዊ ስሜቱን በመከተል ላይ ስናደርግ ምን ይሆናል? ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው ውጤቱ ሞት ነው። የሥጋ መንገዶች ከእግዚአብሔር መንፈስ ዓላማ ጋር የሚቃረኑ ናቸው። ኃጢአተኛ የሆነውን የልባችንን መሻት መከተል በኃጢአት መኖር ነው። የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና (ሮሜ 6፡23 ተመልከቱ) ።

ከዚህ ውጭ ከእግዚአብሔር እና በሕይወታችን እንዲሁም በአገልግሎታችን ካለው በረከቱ የሚለየን ነው። ለእርሱ

በመታዘዝ የሚመላለሱትን እና በሕይወታቸው እንዲሁም በአገልግሎታቸው ምሪቱን የሚከተሉትን እግዚአብሔር ይባርካቸዋል። በሥጋ በመመላለስ የሚገኝ የመጨረሻ በረከት ሊኖር አይችልም - ወደ ሞት እና ከእግዚአብሔር እና ከዓላማው መለየት ብቻ ነው። ጳውሎስ ስለ ሥጋ ማሰብ እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኘው እንደማይችል በግልጽ ይናገራል፡

*7 ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤8 በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም። (ሮሜ 8)*

የሥጋ መንገድ እና የመንፈስ መንገድ የተለያዩ ከመሆናቸው የተነሳ ጳውሎስ ስለ *ሥጋ* ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል እንደሆነ ይነግናል። "ጠላት" የሚለው ቃል "ጥላቻ" ወይም "ጠላትነት" በሚለው ቃል ሊተረጎም ይችላል። የሥጋ መንገድ የእግዚአብሔርና የመንገዱ ጠላት መሆኑን የሚያሳየን ብርቱ ቃል ነው። *ሥጋ* የእግዚአብሔርን ዓላማ ይጠላል እና በእርሱም ላይ ያምጻል። ከመንፈስ መንገድ ጋር በጣም የሚቃረን ስለሆነ ለእግዚአብሔር ሕግ መገዛት አይቻልም። *ሥጋ*ችሁን እየጎሰማችሁ ለእግዚአብሔር ማስገዛት አትችሉም።

*23 በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? በዚያን ጊዜ ክፋትን የለመዳችሁ እናንተ ደግሞ በጎ ለማድረግ ትችላላችሁ። (ኤርምያስ 13)*

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በሮሜ 8፡8 *የሥጋን መንገድ* ከተከተሉ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማይችሉ ይናገራል። ይህ ማለት እንግዲህ ከሥጋ ጋር ሙሉ በሙሉ መለየት አለበት ማለት ነው። አማኞች በሰው አእምሮ ያለውን ውስጣዊ ስሜት እና አመክንዮ አለማመን መማር አለባቸው። እግዚአብሔርን ማስደሰት ከፈለጉ የኃጢአተኛ ተፈጥሮአቸውን ግፊት ስለ መካድ መማር አለባቸው። ይልቁንም "እንደ መንፈስ ፈቃድ" መኖርን መማር አለባቸው።

### *እንደ መንፈስ ፈቃድ መኖር*

ይህ ወደ ሁለተኛው የኑሮ መንገድ ያመጣናል። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ ይህንን ብቻ ይዳስሳል ነገር ግን በሮሜ 8 ላይ የበለጠ ያዳብረዋል፡፡ ነገር ግን በሮሜ 8፡5-8 ጳውሎስ በመንፈስ ፈቃድ ስለ መኖር የሚናገራቸው ሁለት ነገሮች አሉ።

*5 …እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። (ሮሜ 8)*

በመጀመሪያ ሐዋርያው እንደ መንፈስ ፈቃድ እንድንኖር አዕምሯችንን በመንፈስ ፍሬዎች ላይ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይነግረናል። ጳውሎስ በዚህ ቁጥር ውስጥ "የመንፈስን ፍሬ" አልገለጸም። ሐሳቡ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ የእግዚአብሔርን መንፈስ ፈቃድ፣ዓላማ እና ልብ ይፈልጋሉ።

ጌታ ኢየሱስ ከዚህ ምድር ከመሄዱ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሏቸዋል፡

*7 እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ። 8 እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤ (ዮሐንስ 16)*

ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ወደ ደቀመዛሙርቱ እንደሚመጣ የተስፋ ቃልን ሰጥቷቸው ነበር። እርሱ ኃይላቸው ይሆናል እንዲሁም ዓለምን ስለ ኃጢአት እና ጽድቅ ይወቅሳል። ስለ ኃጢአት የሚወቅሰን እና ወደ እግዚአብሔር ዓላማ የሚመራን የመንፈስ ቅዱስ ልብ ነው።

ሐዋርያው ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስ የትንቢት ምንጭ እንደሆነ እና አገልጋዮቹን ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲጽፉ እንዳነሳሳቸው ለአንባቢዎቹ ይነገራቸዋል፡

*19 ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ። 20 ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ (2ኛ ጴጥሮስ 1)*

“የመንፈስ ስጦታዎች” በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ።
በእነዚህ ቃላት፣የእግዚአብሔርን ዓላማ እና ፈቃድ ለሕይወታችን ማወቅ እንችላለን።

ጳውሎስ በሮሜ 8 ላይ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፡-

*14 በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። (ሮሜ 8)*

መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአት እንዲሁም ስለ ጽድቅ መሻት በመውቀስ ራሱን ይገልጣል። በመንፈስ አነሳሽነት በተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ፈቃዱንና ዓላማውን ያሳውቃል። እንዲሁም ህዝቡን ለሕይወታቸው ልዩ በሆነው የእግዚአብሔር ዓላማ አቅጣጫ ይመራል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ በሐዋርያት ሕይወት ውስጥ ያለውን አመራር ለመመርመር ጊዜ የለንም (የሐዋርያት ሥራ 8:29፤10:19፤ 13:2፤16:6-7፤20:22-23 ተመልከቱ) ። የእግዚአብሔር መንፈስ የቀደመችውን ቤተክርስቲያን በሚናገሩት ወይም በሚያገለግሉበት ሥፍራ ሁሉ ይመራ ነበር ማለት በቂ ነው። ሐዋርያት በዕለት ተዕለት ተግባራቸው የእርሱን አመራር እና መመሪያ ለመከተል በጣም ይሹ ነበር።

በመጨረሻም፣ ጳውሎስ ስለ መንፈስ ማሰብ ውጤቱ ሕይወትና ሰላም እንደሆነ ይነግረናል፡

*6...ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው። (ሮሜ 8)*

ጳውሎስ እዚህ ላይ የጠቀሰው ሕይወት መንፈሳዊ እና የዘላለም ሕይወት ነው። አእምሯቸውን በመንፈስ ነገሮች ላይ ያደረጉ እና ለእርሱ እና ለእርሱ አመራር በመታዘዝ የሚሄዱ የእግዚአብሔርን በረከት እና ሙላት ያውቃሉ። የእግዚአብሔር መንፈስ በቃሉ ውስጥ እንደተገለጸው ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር በአንድነት ይመራቸዋል። ለመንፈሳዊ ስጦታቸው

የእግዚአብሔርን የተለየ ዓላማም ይገልጣል። ለእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት፣እምነት እና ዓላማ በመታዘዝ፣አማኙ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን ያገኛል።

እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ሁለት የሕይወት መንገዶች እንዳሉ ይነግራቸዋል። እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ይችላሉ ወይም እንደ መንፈስ ፈቃድ መኖር ይችላሉ። ከእነዚህ መንገዶች አንዱ ወደ ሞት ያመራል፣ ሌላው ከእግዚአብሔር ጋር መኖር በሰላም መኖር ነው። ይህ ጥያቄ ለኛም ነው። አማኞች እንኳን የሥጋን መሻት እና ስሜት ለመከተል ሊፈተኑ ይችላሉ። ዳሩ ግን የክርስትናን ሕይወት ለመኖር በሕይወታችን ውስጥ የኃጢአተኛ ተፈጥሮን እና ሥልጣኑን መካድ መማር አለብን። ባህሪውን እና ማምኞቱን መካድ አለብን። ይልቁንም፣ በመንፈስ ቅዱስ ብርታት እና ጥበብ ላይ መደገፍን መማር አለብን። ሥጋ ለእግዚአብሔር መገዛት እንደማይችልና ክህደትን እንደ መረጠ እና እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድና ዓላማ መመላለስ እንደማይችል መማር አለብን። ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ እንነጋገራለን።

**ለምልከታ**:

እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ማለት ምን ማለት ነው? ስለዚህ የአኗኗር ዘይቤ በዓለም ላይ ማስረጃ የሚሆን ምን ነገሮችን ትመለከታላችሁ?

ክርስቲያኖች እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ይችላሉ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህ የሚሆን ምን ማስረጃ አለ? ለዚህስ ቤተክርስቲያን ምን ማስረጃ አላት?

በራሳችሁ ህይወት ላይ የሥጋን ፈተና የሚያሳይ ምንም ማስረጃ ትመለከታላችሁ?

የሥጋን ባህሪ እና ምኞቶችን ማመን ትችላላችሁን? መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ያስተምራል?

እንደ መንፈስ ፈቃድ መኖር ማለት ምን ማለት ነው?

የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምንድን ነው? በህይወታችሁ ውስጥ ስላለው ስዕብና እና ሥራ ታውቃላችሁን?

**ለጸሎት:**

እንደ ሥጋ ፈቃድ ለመኖር የመረጣችሁበትን ጊዜያት ሁሉ ጌታ ይቅር እንዲላችሁ ጌታን ጠይቁ።

በመንፈስ ፈቃድ መኖር ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ እንዲያስተምራችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁ።

በህይወታችሁ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት እና ወቀሳ ለተቃወማችሁበት ጊዜያት እግዚአብሔር ይቅር እንዲላችሁ ጠይቁት። እርሱን እና ለህይወታችሁ ያለውን አላማ ለመታዘዝ ጸጋ እና ፍቃድ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት።

እኛን ለማስቻል እና ወደ እግዚአብሔር ዓላማ ይመራን ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ስለሰጠን እግዚአብሔርን ለማመስገን ትንሽ ጊዜ ውሰዱ።

# ም ዕ ራ ፍ 1 5 -

# የ መ ን ፈ ስ ሕ ይ ወ ት

---

ሮሜ 8:9-11

*9 እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥*
*በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ*
*የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም። 10*
*ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት*
*ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት*
*ሕያው ነው። 11 ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው*
*የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን*
*ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥*
*ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል። (ሮሜ*
*8)*

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ ለሚኖረው አማኝ ሁለት የሕይወት መንገዶች እንዳሉ ሲያስታውስ ቆይቷል። እንደ *ሥጋ* ፈቃድ ወይም እንደ መንፈስ ፈቃድ መኖር ይችላሉ። ጳውሎስ ቁጥር 9ን ሲጀምር "ነገር ግን" የሚለውን ቃል እንደተጠቀመ አስተውሉ።

*9 በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። (ሮሜ)*

“ነገር ግን” የሚለው ቃል ጠቃሚ ነው። ለሮሜ አማኞች እንደ ሥጋ ፈቃድ የመኖር አማራጭ ቢኖርም በሕይወታቸው ውስጥ ግን ወደ አዲስ አቅጣጫ እንዲመሩ ያደረጋቸው ሌላ ምክንያት ነበር። ጳውሎስ ለሮሜ አማኞች “በመንፈስ እንጂ በሥጋ እንዳይደሉ” ይነግራቸዋል።

እዚህ ውስጥ "በ" የሚለው ቃል ግራ የሚያጋባ ሊሆን ይችላል። “በሥጋ” ወይም “በመንፈስ” መሆን ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት ከፈለግን ይህች ትንሽ ቃል የተለያዩ ትርጉሞችን ትሰጣለች። የዚህን ቃል ትርጉም እንመልከት።

"ውስጥ" የሚለው ቃል የምንኖርበትን ቦታ ሊገልጽ ይችላል። ለምሳሌ “የምኖረው በቤት ውስጥ ነው” ልንል እንችላለን። በዚህ ሁኔታ “ውስጥ” የሚለው ቃል የባለቤትነት እና የታማኝነት ስሜትን ይይዛል። የምኖርበት እንዲሁም መጠለያዬን እና ምቾቴን ያገኘሁት በዚያ ቤት ውስጥ ነው።

ሰዎች እኛን እንዲያገኙን ለመርዳት ይህን ቃል ልንጠቀምበት እንችላለን። እየፈለገኝ ላለው ጓደኛዬ በአንድ የተወሰነ መደብር ውስጥ እንዳለሁ ልነግረው እችላለሁ። እንግዲህ እዚህ "ውስጥ" የሚለው ቃል አንድን ሰው እኔ የት እንዳለ እና በአከባቢው ውስጥ ካሉ ሌሎች መደብሮች ጋር በተገናኘ እንዲያውቅ ያስችለዋል።

በመጨረሻም፣ ኢየሱስ በዮሐንስ 15 ላይ “በ” የሚለውን ቃል የተጠቀመበትን ምሳሌ አለን፡

*4 በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም። (ዮሐንስ 15)*

ኢየሱስ በዮሐንስ 15፡4 “በ” የሚለውን ቃል አራት ጊዜ ተጠቅሟል። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ቅርንጫፍ “በወይኑ ግንድ እንዴት እንደሚኖር” ይገልጻል። ይህ "በ" የሚለው ቃል አጠቃቀም የወይኑ ህይወት በቅርንጫፍ ውስጥ ስለሚፈስበት ጥልቅ ግንኙነት ይናገራል።

ጳውሎስ “በሥጋ” ወይም “በመንፈስ” የሚለውን ሐረግ ሲጠቀም እነዚህን ሁሉ ፍቺዎች እያገናኘ ነው። በሌላ አነጋገር፣ ጳውሎስ “በመንፈስ” እንዳለን ሲነግረን፣በእርሱ እንዳለን እና መጠለያችንን እና ምቾታችንን እንደምናገኝ እየነገረን ነው። ታማኝነታችን ለእግዚአብሔር መንፈስ ነው። በመንፈስ መሆን በሕይወታችን ውስጥ የት ቦታ ላይ እንደቆምን ያመለክታል። በመንፈስ መሆን ማለት በእርሱ ሥልጣንና ምሪት ሥር ነን ማለት ነው። ከእርሱ እና ከዓላማው ጋር እንገናኛለን። በመጨረሻም፣በመንፈስ መሆን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ስላለን የጠበቀ ግንኙነት ይናገራል። የእርሱ ሕይወት በእኛ ውስጥ ይፈስሳል። ሃሳቡ ይመራናል፣ጥንካሬውም ይረዳናል።

ጳውሎስ በሮሜ 8፡9 ላይ በጌታ በኢየሱስ ሥራ የእግዚአብሔር መንፈስ ያድርባቸው እንደነበር ለሮሜ ሰዎች ያስታውቸዋል። እንግዲህ ታማኝነታቸው ለእርሱ ነው። የእርሱ መገኘትና ኃይሉ ሲሞላባቸው ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር ተስማምተው እንዲኖሩ አስችሏቸዋል። ቅርንጫፍ ከወይኑ ጋር እንደተጣበቀ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የተገናኙ ነበሩ። ይህ አማኝ የመሆን እድል ነበር። ይህ ትስስር አማኙን ገልጿል፡

*9 እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር… የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም። (ሮሜ 8)*

ጳውሎስ የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ማንኛውም ሰው የእሱ እንዳልሆነ ግልጽ አድርጓል። አንድን አማኝ የሚገልጸው እና ከማያምን የሚለየው ምንድን ነው? ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው በአማኙ ውስጥ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ስዕብና ነው። ሕይወትን የሚሰጠን የክርስቶስ መንፈስ ነው።

*10 ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው። (ሮሜ 8)*

በዘፀአት 33 ሙሴ እግዚአብሔርን እያናገረ በድፍረት እንዲህ አለ፡

*15 እርሱም፦ አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህስ፥ ከዚህ አታውጣን። 16 በምድርም ፊት ካለው ሕዝብ ሁሉ እኔና ሕዝብህ የተለየን እንሆን ዘንድ አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህ፥*

*እኔና ሕዝብህ በአንተ ዘንድ ሞገስ ማግኘታችን በምን ይታወቃል? አለው። (ዘጸአት 33)*

ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ የሚለየው የእግዚአብሔር መገኘት እንደሆነ ግልጽ አድርጓል። የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ ውስጥ ከሌለ፣ከማያምን በምን እንለያለን? መንፈስ ቅዱስ ኃይል ካልሰጠን እና ካላስታጠቀን በክርስትና ሕይወት ለመኖር ምን ተስፋ አለን? እሱ ሕይወታችን እና ብርታታችን ነው። ከማያምን ሰው የሚለየን የዚህ መንፈስ ህልውና ነው። የክርስቶስ ሕያው መንፈስ በአማኙ ውስጥ አለና።

በቁጥር 10 ላይ ደግሞ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጽድቅ ምክንያት መንፈስ ለእኛ ሕይወት እንደሆነ ይናገራል። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጽድቅ ምክንያት የመንፈስን ሕይወት ማወቅ እንደሚችሉ እየነገራቸው ነው። ጽድቅ ምንድን ነው? በእግዚአብሔር ፊት መቆም መቻል ነው። አማኙ የመንፈስ ቅዱስን ህይወት ይለማመዳል ምክንያቱም እሱ ወይም እሷ አሁን በእግዚአብሔር ፊት መግባትን ስላገኙ ነው። ይህ አቋም የክርስቶስ ይቅርታ እና በቀራንዮ መስቀል ላይ የሰራው ሥራ ውጤት ነው። እኛ ፍጹማን ባንሆንም እርሱ ኃጢአታችንን ሁሉ የሚሸፍን እና በእግዚአብሔር ፊት የመግባት ድፍረትን የሚሰጠን ፍጹም መሥዋዕት ነው። በጌታ ኢየሱስ ሥራ ይህንን ትክክለኛ አቋም አግኝተናል። እግዚአብሔር በመንፈሱ በእኛ ውስጥ ይህንን አቋም ያትማል።

ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው መንፈስ አዲስ ሕይወት ይሰጠናል።

*11 ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል። (ሮሜ 8)*

የክርስቶስ መንፈስ የትንሳኤ ኃይል ይህን የሚሞተውን ሰውነታችንን ሊሞላ አሁን ይመጣል። አሁን ወደ ክርስቶስ ከመምጣታችን በፊት ለእኛ ያልነበረው ኃይል በእኛ ውስጥ አለ። ይህ ኃይል ኢየሱስን ከሞት ያስነሳው ኃይል ነው። የኃጢአትን እርግማን አሸንፎ ሞትን ድል ያደረገ ኃይል ነው።

አንድ አማኝ እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ይቻላልን? በጳውሎስ መልዕክቶች ላይ ከተመለከትነው፣በእርግጥም እውነት ነው። አሁን ግን በአማኙ ውስጥ ከሥጋ የሚበልጥ ኃይል አለ። ከማያምን የሚለየን ያ መንፈስ ነው። ለእያንዳንዱ ተግባር እና ለሚገጥመን ትግል ሁሉ የሱ መገኘት እና ኃይል አለ። እርሱ ይመራናል እንዲሁም ለእያንዳንዱ ሥራ ኃይል ይሰጠናል።

እራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባን ጥያቄ፡- የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችን እያለ ወደ ሥጋና ወደ መንገዱ ለምን እንዞራለን? የእግዚአብሔር ኃይል በውስጣችን ሳለ ወደ ሰው ጥረት ለምን እንሄዳለን? የክርስቶስ መንፈስ ምሪት በእጃችን ሳለ በሰው ጥበብ ለምን እናምናለን? እኛ ከወይኑ ጋር የተቆራኘን በራሳችን ጥረት ፍሬ ለማፍራት ራሳችንን ከወይኑ ለመለየት ለምን እንወስናለን?

“እናንተ ግን በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም” ሲል ጳውሎስ ተናግሯል። በመንፈስ ያሉት በሥጋ መገለጽ አለባቸውን? ሕይወታቸውን ለመለወጥ የእርሱን ኃይል

የተለማመዱ ሰዎች እንደገና በሰው ጥበብ እና ጥንካሬ መታመን አለባቸው? በእግዚአብሔር ፊት ለመግባት ድፍረት የተሰጣቸው ሰዎች ወደ ሥጋ ድካምና ኃጢአተኝነት ይመለሱ ዘንድ ይገባቸዋልን?

የክርስቶስ መንፈስ አለን። በእርሱ ስም ሕይወት አለን። በልጁ ሥራ ወደአብ ጋር መግባት ተሰጥቶናል። አሁን የሚለየን ይህ ነው። ለሥጋ እና ለሚወክለው ሁሉ ጀርባችንን እንሰጣለን። አሁን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እና ኃይል ሥር ለመኖር እንመርጣለን። በክርስቶስ መንፈስ ምሪት እና ስልጣን በዚህ አዲስ ህይወት ለመመላለስ ስጋዊ መንገዳችንን እና ማስተዋልን እንጥላለን።

**ለምልከታ:**

በመንፈስ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

በእናንተ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ህልውና ከሌለ እውነተኛ አማኝ መሆን ትችላላችሁን?

በአማኞች ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መኖር ከማያምኑት የሚለየው እንዴት ነው?

በሕይወታቸው ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን መኖር የሚያውቁ ወደ ሥጋ መንገድ ተመልሰው በሰው ጥረትና በዓለማዊ ጥበብ የክርስትና ሕይወት እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

በሕይወታችሁ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ስለ መገኘቱ ምን ማስረጃ አለ? እንዴት አድርጎ ለወጣችሁ? እንዴትስ ኃይል ሰጣችሁ እንዲሁም መራችሁ?

**ለጸሎት**:

በእናንተ ውስጥ እንዲኖር መንፈሱን ስለሰጣችሁ ጌታን አመስግኑት። የመንፈስ ቅዱስን መኖር፤የእርሱን ምሪት እና መውቀስ የበለጠ ታውቁ ዘንድ እንዲረዳችሁ ጠይቁት።

ወደ ሥጋ እና ወደ መንገዱ ለመመለስ ለመረጣችኋቸው ጊዜያት ጌታ ይቅር እንዲላችሁ ጠይቁት።

በመንፈስ ቅዱስ እንድትኖሩ እና እንድታገለግሉ፤በሥራውም እንድትታመኑ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

በምትሠሩት ሥራ እና በምታገለግሉበት መንገድ የክርስቶስ እና የመንፈሱ ህልውና ይበልጥ እንዲታይ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

## ምዕራፍ 16 -

## እንደ ሥጋ ፈቃድ ለመኖር እዳ የለብንም

---

ሮሜ 8:12-14

*12 እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፥ እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም። 13 እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። 14 በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። (ሮሜ 8)*

ጳውሎስ ሮሜ 8፡12ን የጀመረው ለሮሜ ሰዎች እንደ ሥጋ ፈቃድ ለመመላለስ ዕዳ እንደሌለባቸው በመንገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጌታ እግዚአብሔር በዙሪያችን የተቸገሩትን ማገልገል እንደሚያስፈልገን ያስታውሰናል። በዘዳግም 15 ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንደ ምሳሌ እንውሰድ፡-

*9 ሰባተኛው ዓመት የዕዳ ምሕረት ዓመት ቀርቦአል ብለህ ክፉ አሳብ በልብህ እንዳታስብ፥ ለድሀውም ወንድምህ አንዳች የማትሰጥ እንዳትሆን፥ ዓይንህም በእርሱ ላይ ክፉ እንዳይሆን፥*

*እርሱም ወደ እግዚአብሔር በአንተ ላይ እንዳይጮህ፥ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ተጠንቀቅ። 10 እጅህን በምትጥልበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ስለዚህ በሥራህ ሁሉ ይባርክሃልና ፈጽመህ ስጠው፥ በሰጠኸውም ጊዜ በልብህ አትጸጸት።*

የእግዚአብሔር ሕዝቦች በመካከላቸው ላሉ ድሆች ልዩ ግዴታ ነበራቸው። በችግር ጊዜ የእርዳታ ጩኸታቸውን ለመስማት ፈቃደኛ አለመሆን በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ነበር። በችግራቸው ጊዜ ለድሆች እውነት የሆነው ለመበለቶች እና ወላጅ አልባ ለሆኑ ልጆችም እውነት ነበር (ዘጸአት 22፡22-24 ተመልከቱ) ።

በችግራቸው ጊዜ የሚጮኹት መበለቶችና ወላጅ አልባ ሕፃናት ብቻ አልነበሩም። *ሥጋም* በመፈለግ ይጮኽ ነበር። ዳሩ ግን ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ግን እንደ *ሥጋ* ፈቃድ ለመኖር ባለ ዕዳዎች እንዳልነበሩ ይነግራቸዋል።

*12 እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፥ እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም።*

ሐዋርያው እንደ *ሥጋ* ፈቃድ ለመኖር ዕዳ የለብንም ሲል ምን ማለቱ ነው? ለኤፌሶን ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ይላል፡

*29 ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ነገር ግን ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል። (ኤፌሶን 5)*

በኤፌሶን 5፡29 ላይ ጳውሎስ ሥጋችንን መንከባከብ እና መመገብ በዓለም ላይ እጅግ ተፈጥሯዊ ነገር ነው በማለት ይናገራል። እዚሁ ሮሜ 8፡12 ላይ ተማሳሳዩ የግሪክ ቃል ስለ ሥጋ ለመናገር ጥቅም ላይ ውሏል።

እግዚአብሔር የድሆችን፣መበለቶችን እና ወላጅ አልባ ሕፃናትን ውጫዊ ፍላጎቶች ይንከባከቡ ዘንድ ሕዝቡን አዘዛቸው። ሥጋቸው መመገብ እና መጠበቅ ነበረበት። ጌታም አማኞች ሥጋቸውን እንዲንከባከቡ ይጠብቅ ነበር። እውነታው ግን ሥጋዊ አካላችንን ካልተንከባከብን ይታመማል እንዲሁም ይሞታል። ለሥጋዊ ደህንነታችን ያለው ሁኔታ ለስሜታዊ ደህንነታችንም እውነት ነው። ሰውነታችን እና አእምሯችን ጤናማ ሊሆኑ አይችሉም ወይም ችላ ከተባሉ ሙሉ አቅማቸው ላይ መድረስ አይችሉም።

ጳውሎስ በሮሜ 8፡12 ላይ ለሮሜ ሰዎች የሥጋ ባለ ዕዳዎች እንዳልሆኑ ሲነግራቸው፣ በዚያው ጥቅስ ላይ ደግሞ "እንደ ሥጋ ፈቃድ ለመኖር" በማለት ይቀጥላል። ይህ ሐረግ አስፈላጊ ነው። "እንደ ሥጋ ፈቃድ" መኖር፤ሥጋ እና የኃጢአት መሻቶች ድርጊታችንን እና አስተሳሰባችንን እንዲቆጣጠሩ መፍቀድ እንደሆነ ተመልክተናል። "እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር" ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን የምናደርገውን ነገር እንዲወስን ማድረግ ነው። ጳውሎስ ሥጋዊ አካላችንን ቸል ማለት እንዳለብን እየነገረን አይደለም፣ ነገር ግን እነርሱን መያዝ ማለት ለእነሱ ላለው ታላቅ የእግዚአብሔር ዓላማ መስገዛት ማለት ነው።

የሥጋ ምኞትና መሻት በእኛ ላይ ሊሰለጥን አይገባም። የሥጋ ሩካቤ መኞት ለእግዚአብሔር ዓላማ መገዛት አለበት።

በሕይወታችን ውስጥ በሐጢአት የተሞላ የውስጥ ቅናት ካለ ልንናዘዘው እና በመንፈስ ቅዱስ ጌትነት ቁጥጥር ሥር ማድረግ አለበት። ለሥጋችን ምኞት መገዛት የለብንም፤ ይህን ማድረጋችን ደግሞ ኃጢአት ነው። እንደ አማኞች ያለን ግዴታ ለክርስቶስ እና ለዓላማው መገዛት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 9 ላይ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ ይህን በምሳሌ አስረድቷል፡

*24 በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡት፥ ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ። 25 የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፥ እኛ ግን የማይጠፋውን። 26 ስለዚህ እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፥ ነፋስን እንደሚጎስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም፤ 27 ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ። (1ኛ ቆሮንቶስ 9)*

ጳውሎስ *ሥጋውን* እየጎሰመ ያስገዛው ነበር። *ሥጋው* ከነሙሉ ምኞቱና መሻቱ እንዲገዛው አልፈቀደም። ፍላጎቱን የመከተል ግዴታ አልነበረበትም። ጌታው ክርስቶስ ነበርና።

ሐዋርያው ለሮሜ ሰዎች 8:13 እንደ *ሥጋ ፈቃድ* ብንኖር እንሞታለን ሲል ይቀጥላል።

*13 እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ (ሮሜ 8)*

ጳውሎስ ስለ መሞት ሲናገር እየተናገረ ያለው ስለ ሥጋ ሞት ብቻ አይደለም። ሞት በዚህ ምድር ላይ የሥጋዊ ሕይወት መቋረጥ ብቻ አይደለም። በሕይወት እየኖርን በሞት ሥር ደግሞ ልንኖር እንችላለን። ሞት ከእግዚአብሔር እና በረከቶቹ መለየትን ሊያመለክት ይችላል። ብዙ ሰዎች ይህ ዓለም የሚያቀርበው ነገር ሁሉ አላቸው ነገር ግን በእግዚአብሔር እርግማን ውስጥ ይኖራሉ። ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም፤ለእሱ ምንም ፍላጎት የላቸውም። ለክርስቶስ እና ከእሱ ጋር ላለ ማንኛውም ሕብረት በመንፈስ የሞቱ ናቸው።

ይህም ጳውሎስ በሥጋ ፈቃድ ስለ መኖር ያስተማረውን ሌላ ገጽታ ይጨምራል። ቁጥር 12ን ለሥጋ ዕዳ እንደሌለባቸው ለሮሜ ሰዎች በመንገር ይጀምራል። ነገር ግን በቁጥር 13 ላይ ሥጋቸው እንዲገዛቸው ከፈቀዱ እንደሚሞቱ እና ከእግዚአብሔር በረከት እንደሚለዩ በማሳየት ይህንን አንድ እርምጃ ይወስዳል።

እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ከእግዚአብሔር የሚለየን እና በእርግማን ሥር የሚያደርገን ነው። እዚህ ላይ ሐዋርያው የተናገረውን የተረዱ እና የሚያምኑ ጳውሎስ በቁጥር 13 ላይ ለሮሜ ሰዎች የተናገረውን ለማድረግ ቅድሚያ ይሰጣሉ፡

*13...በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ።*

በተፈጥሮአዊ መሻቶች እና የሥጋ ምኞቶች መኖር ወደ ሞት እንደሚመራ የሚያምኑ ለዚያ መሞትን ይመርጣሉ። "የሥጋን ሥራ ይገድላሉ" ። በሌላ አነጋገር ሥጋ እንዲገዛቸው

አይፈቅዱም። ለክፉ ምኞቱ አይገዙም። ይህንን ሥጋ እየጎሰሙ ያስገዙታል እንዲሁም ለጌታቸውና ለመድኃኒታቸው ክብር የማያመጣውን ማንኛውንም ከፉ ምኞት ሰቅለዋል። ሥጋን በጥንቃቄ ይመለከታሉ። ከሰዋዊ የማሰብ ችሎታቸው ይልቅ በመንፈስ ምሪት ላይ የበለጠ ክብደት እና እምነት ይጥላሉ። ጌታቸውን የማያከብሩ የሥጋ ድርጊቶችና አመለካከቶችን ሁሉ ይናዘዛሉ እንዲሁም ይተዋሉ።

ይህ ቀላል ቢመስልም የነገሩ እውነታ ግን ሥጋ ዘወትር ከመንፈሳችን ጋር ይዋጋል። እንዲያውም ሐዋርያው ጳውሎስ ከሥጋው እና ከአመለካከቱ ጋር በጣም ይታገል ነበር። በምዕራፍ 7 ላይ ለሮሜ ሰዎች የነገራቸውን ቀደም ብለን ተመልክተናል፦

*14 ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ። 15 የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም። 16 የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደ ሆነ እመሰክራለሁ። 17 እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ። 18 በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። (ሮሜ 7)*

የሥጋን ፈተና ለማሸነፍ የሚደረገው ትግል ከባድ ነው። ሥጋንና የኃጢአት መሻቶች እንዴት መዋጋት እንችላለን? ይህን ስናደርግ የራሳችንን ስሜት እና የተፈጥሮ ዝንባሌን እንዋጋለን። ሥጋችን በተፈጥሮ የሚፈልገውንና የሚመኘውን እንዴት መለወጥ እንችላለን? በሮሜ 8፡13 ያለውን የጳውሎስን ቃል አስተውሉ፡-

*13…በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ።*

"በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ" የሚለው ሐረግ ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሰጠናል። የሥጋን ክፋት የማሸነፍ ኃይል በሥጋችን ሳይሆን በእኛ ውስጥ በሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። በጥረታችን የሰውነትን ሥራ ልንገድለው አንችልም። የቤተክርስቲያን ታሪክ ራሳቸውን ይደበደቡ እና ሥጋቸውን ይክዱ በነበሩ ሰዎች የተሞላ ነው። እነዚህ ግለሰቦች አንዳንድ ባህሪያትን መለወጥ ይችሉ ይሆናል ነገር ግን የኃጢአትን ሥር መንቀል አልቻሉም። የሰውነትን ሥራ የሚገድለው መንፈስ ቅዱስ ነው። እኛ ራሳችን ይህን ማድረግ

አንችልም። የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻውን እነዚህን ድርጊቶች አስወግዶ ሙሉ ለሙሉ ሊለውጠን ይችላል።

ነቢዩ አሞጽ በዘመኑ ለነበሩት ሰዎች ሲናገር ስለ አሞራውያን እንዲህ ይላል፡

*9 እኔ ግን ቁመቱ እንደ ዝግባ ቁመት፥ ብርታቱም እንደ ኮምበል ዛፍ የነበረውን አሞራዊውን ከፊታቸው አጠፋሁ፤ፍሬውንም ከላዩ፥ ሥሩንም ከታቹ አጠፋሁ። (አሞጽ 2)*

አሞራውያን እግዚአብሔር ለእስራኤል ሊሰጣቸው በሚፈልገው ምድር ይኖሩ ነበር። ቁመታቸው እንደ ዝግባ ቁመት፥ ብርታታቸውም እንደ ኮምበል ዛፍ ተብለው የተገለጡት እነዚያ ለእስራኤል ታላቅ ጠላት ነበሩ። እግዚአብሔር ያደረገውን አስተውሉ። “ፍሬውንም ከላዩ፥ ሥሩንም ከታቹ አጠፋ።” እግዚአብሔር ከላይ ያለውን ፍሬ ብቻ ቢያጠፋ፤አሞራውያን ሌላ ቀን ተመልሰው ይኖራሉ። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ከዚህ የበለጠ አደረገ። ሥሩንም ከታቹ አጠፋ። ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ፍጹም ድል ማለት ነው። ይህ ጠላት ዳግመኛ ችግር አያመጣም። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። እርሱ የኃጢአትን ፍሬ ብቻ ሳይሆን ሥሩን በሕይወታችን ውስጥ ያጠፋል። በሥጋ ማድረግ የማንችለውን፤የእግዚአብሔር መንፈስ ያደርግልናል።

ጳውሎስ ይህንን ክፍል እንዲህ ሲል ይቋጫል፡

*14 በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።*

የእግዚአብሔር የሆኑት የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣቸው ይኖራል። የእግዚአብሔር ልጆች ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት እና መመሪያ ይገዛሉ። በዚህ መንገድ መምራት እና ኃይል ማግኘት የሚችሉት የእግዚአብሔር ልጆች ብቻ ናቸው። በእነርሱ ውስጥ የማያምን ሰው የሌለው ኃይል አላቸው። የእግዚአብሔር መንፈስ ይመራቸዋል እንዲሁም ያስችላቸዋል። እርሱ ይለውጣል እንዲሁም ያድሳል። በእኛ ውስጥ ያለ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ያልሆነውን ሁሉ ይሰቅለዋል። በራሳችን ማድረግ የማንችለውን ያደርግልናል - የሥጋንም ሥራ ይገድላል።

ከእነዚህ ጥቅሶች የምንገነዘበው አማኝ ለሥጋውና ለምኞቱ የመገዛት ግዴታ እንደሌለበት ነው። እንዲያውም ይህን ማድረግ ሞትና ከእግዚአብሔር በረከቶች መለየት ማለት ነው። ይልቁንም በውስጣችን ያለውን የሥጋን ሥራ ለሚሰቅለው ለእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ መገዛትን መማር አለብን። የሥጋን ምኞት እንደምናስተውል ሁሉ አሁን ደግሞ ለመንፈስና ለሥራው ምሪት ልባችንን መክፈት አለብን። አሁን ከሥጋ ይልቅ በመንፈስ መመራት ካለብን፣የእግዚአብሔርን መንፈስ ሥራ እና በሕይወታችን ውስጥ ስለሚመራው ምሪት የበለጠ ማወቅ የኛ ታላቅ ኃላፊነት ነው። በክርስቶስ ሕይወት ሙላት ለመኖር በሥጋ ላይ ድል መንሳት የሚሆነው በዚህ ብቻ ነውና።

**ለምልከታ**:

እግዚአብሔር ሥጋዊ አካላችንን እንድንንከባከብ ይጠብቅብናል? ሥጋዊ አካላችንን በመንከባከብና እና እንደ ሥጋ ፈቃድ በመኖር መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ጳውሎስ እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ውጤቱ ምን ይሆናል አለ? በሥጋ ፈቃድ ከኖርን ከክርስቶስ ጋር ያለን ህብረት ማደግ ይችላልን?

ጳውሎስ የሥጋን ሥራ ለመግደል የሚያስችል ኃይል የሚመጣው ከየት እንደሆነ ይነግረናል?

በመንፈስ መመራት ምን ማለት ነው? ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት በመንፈስ እንደሚመሩ ተናግሯል። መንፈስ እንዴት እንደሚመራ መረዳታችን ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

የእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራን እንዴት ነው?

**ለጸሎት:**

በአካባቢያችሁ ላሉት ውጫዊ ፍላጎቶች የበለጠ ርህራሄ እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት። ፍላጎታቸውን የምታገለግሉበት መንገድ ካለ እንዲያሳያችሁ ጠይቁት።

ሁሉንም የሥጋ ምኞቶቻችሁን ለእርሱ ለማስገዛት ጸጋን እንዲሰጣችሁ ጠይቁት፡፡

ዛሬ የምትታገሏቸው የሥጋ ምኞቶች አሉን? ከክርስቶስ ጋር የሚኖራችሁን አንድነት የሚገታውን ማንኛውንም የሥጋ ምኞት ላይ ድል እንዲሰጣችሁ የእግዚአብሔርን መንፈስ ጠይቁት፡፡

ለሥራው እና በሕይወታችሁ ውስጥ ምሪት ታገኙ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳችሁ ጠይቁት፡፡

# ምዕራፍ 17 -

# ልጆች እና ወራሾች

---

ሮሜ 8:15-17

*15 አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። 16 የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል። 17 ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፥ አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን። (ሮሜ 8)*

የጌታ የሆኑት የእግዚአብሔር መንፈስ በእነርሱ ዘንድ እንደሚኖር ተመልክተናል (ሮሜ 8፡11 ተመልከቱ) ። የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ እግዚአብሔር ዓላማ ይመራቸዋል (ሮሜ 8፡14 ተመልከቱ) ። አማኝን ከማያምን የሚለየው የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ነው። እንዲያውም፣ በሮሜ 8፡15 ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች "የእግዚአብሔር ልጆች እንደ ሆኑ አረጋግጦ የልጅነት መንፈስ እንጂ የባርነት መንፈስ"

እንዳልተቀበሉ ይነግራቸዋል። እስቲ እነዚህን ሁለት መንፈሶች እንመልከት።

## *የባርነት መንፈስ*

ጳውሎስ እዚህ ላይ የጠቀሰው ከሁለቱ መናፍስት መካከል የመጀመሪያው የሆነውን የባርነት መንፈስ ነው።

*15 እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። (ሮሜ 8)*

የባርነት መንፈስ በሙሴ ዘመን የተመሰረተውን የሕግ ሥርዓት የሚያመለክት ይመስላል። ጥብቅ ወጎች እና ደንቦች ያሉት ያ ሕግ ፍጹም ታዛዥነትን ይጠይቃል። ማንኛውም መተላለፍ ይቀጣ ነበር። ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ በፍፁም ሊጠብቅ አይችልም፤ስለዚህ ሁሉም በእርሱ ኩነኔ ሥር ነበሩ። ይህ ስርዓት ተከታዮቹን የማያቋርጥ ፍርድ እና ኩነኔን በመፍራት የሚይዝ ነበር።

በዚህ መንፈስ የሚኖሩ ሰዎችን አግኝታችሁ ታውቃላችሁን? የዘላለም እጣ ፈንታቸውን ይፈራሉ። ኩነኔን በመፍራት ይኖራሉ። እንደጎደሉ ያውቃሉ ነገር ግን በሰው ጥረት መዳናቸውን ለማግኘት የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። መቼም ሰላም የላቸውም ምክንያቱም ሁልጊዜ የሚኖሩት ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት በቂ እንዳልሆኑ በማሰብ በፍርሃት ሥር ሆነው ነውና። ጳውሎስ ይህንን መንፈስ፣ የባርነት መንፈስ ብሎ ይጠራዋል።

ነገር ግን ይህ መንፈስ ጳውሎስ እንዳለው፣ የአማኙን ሕይወት የሚመራ መንፈስ አይደለም። አማኙ በዚህ ጭቆና ውስጥ አይደለም ስለሆነም ኩነኔንና መለኮታዊ ቁጣን በመፍራት ውስጥ አይኖርም። ሕይወታቸውን የሚመራው ሌላ መንፈስ ነው።

*የልጅነት መንፈስ*

የሮሜ ሰዎች የተቀበሉት መንፈስ የልጅነት መንፈስ ነው።

*15 አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ… (ሮሜ 8)*

መንፈስ የሚለው ቃል በትልቁ መጻፉን አስተውሉ። እዚህ ያለው አንድምታ ይህ መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚለው ነው። የሮሜ ሰዎች የተቀበሉት መንፈስ ቅዱስን ነው።

መንፈስ ቅዱስ የልጅነት መንፈስ ተብሎ መጠራቱንም አስተውሉ። ይህ በአማኙ ውስጥ ያለውን የሥራውን ባህሪ ያሳያል። በእግዚአብሔርና በልጆቹ መካከል ያለውን ስምምነት ለማተም ይመጣል። ልጅነትንም ያትማል።

እግዚአብሔር እኛን እንደ ልጆቹ አድርጎ ሲቀበለን፣አባታችን ለመሆን እና እኛን ለመንከባከብ ተስማምቶ ነው። ይህ ሁሉንም ፍርሃት ያስወግዳል፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ስምምነቱን ያትማል። በህይወታችን ባለው በእርሱ መገኘት ምክንያት የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን።

የልጅነት መንፈስ በውስጣችን ስለሚኖር እግዚአብሔርን “አባ አባት” ብለን ልንጠራው እንችላለን። እነዚህ ቃላት ቀለል አደርገን የምንወስዳቸው አይደሉም። ሁሉም ሰው የሚወደውን የአንድነት እና የግንኙነት ደረጃን ይገልጻል። እግዚአብሔርን አባታቸው ብለው ለሚጠሩት የተሰጡ ልዩ መብቶች አሉ። የበረከቱ እና የማዳኑ ወራሾች ናቸው (ቁጥር 17 ተመልከቱ) ።

በባርነት መንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር የት ጋር እንደቆምን እርግጠኛ መሆን አንችልም። የልጅነት መንፈስ እኛን የእግዚአብሔር ወንድ ልጆች እና ሴቶች ልጆች በማድረግ ይህንን ጥርጣሬ ያስወግዳል።

ጳውሎስ በሮሜ 8፡16 የእግዚአብሔር መንፈስ ጥርጣሬን እንደሚያስወግድ እና በእግዚአብሔር ፊት መቆም መቻላችንን ያረጋግጥልናል በማለት ይቀጥላል።

*16 የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል። (ሮሜ 8)*

ጳውሎስ በቁጥር 16 ላይ የልጅነት መንፈስ ስለ መንፈሳቸው እንደሚመሰክር ለሮሜ ሰዎች ይነግራቸዋል። “መንፈስ” የሚለው ቃል በቀጥታ ሲተረጎም “እስትንፋስ” ማለት ነው። ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ስለ መንፈሳቸው እንደመሰከረ ለሮሜ ሰዎች ሲነግራቸው፣ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን ከውስጣዊ ማንነታቸው ማረጋገጫ እንዳገኙ እየነገራቸው ነው። የእግዚአብሔር ለሆኑት የመዳንን ማረጋገጫ ማምጣት የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ነው።

የእግዚአብሔር ልጆች ስለመሆናችን በመንፈሳችን መረጋገጥ በእውቀት ማመን ብቻ አይደለም። ለሌላ ሰው በምክንያታዊነት ማስረዳት የምትችሉት ነገር እንኳን አይደለም። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች የመዳንን መንገድ ያሳዩናል፣ነገር ግን ይህ መዳን በሕይወታችን ውስጥ እውን መሆኑን የሚያረጋግጥልን የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። የእሱ ማረጋገጫ ጥርጣሬን እና ፍርሃትን ያስወግዳል። በእርግጥም በኢየሱስ ደም ይቅር እንደተባልን እና እንደነጻን ያሳምነናል። የእግዚአብሔር ልጆች እና የመንግስቱ ወራሾች መሆናችንን ያረጋግጥልናል።

*17 ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን (ሮሜ 8)*

የእግዚአብሔር ልጅ እና ወራሽ መሆናችሁን ማወቅ ትችላላችሁ። ልጆቹ የልጅነት ደረጃቸውን እንዲጠራጠሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ርስታቸውንም መጠራጠር ዓላማው አይደለም። በሕይወታቸው ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ምስክርነት ይህንን ጉዳይ ያብራራል እንዲሁም ሁሉንም ጥያቄዎች ይመልሳል። የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፤ከክርስቶስም ጋር አብረን ወራሾች ነን።

የእግዚአብሔር ወራሽ መሆን ያቀደልንን ሁሉ መውረስ ነው። ስለ እነዚህ ሁሉ ዘላለማዊ በረከቶች ለመናገር ጊዜ አይፈቅድልንም። እነዚህ በረከቶች እንደ ትልልቅ መኖሪያ ቤቶች (ዮሐንስ 14:2) ፣ የወርቅ ጎዳናዎች (ራዕይ 21:21) እና እንባ የሌለባቸው ቁሳዊ በረከቶች ብቻ አይደሉም (ራዕይ 21:14) ። እግዚአብሔር ራሱ ርስታችን ይሆናል።

*26 የልቤ አምላክ ሆይ፥ ልቤና ሥጋዬ አለቀ፤ እግዚአብሔር ግን ለዘላለም እድል ፈንታዬ ነው። (መዝሙር 73:26)*

እግዚአብሔርን በአዲስ መንገድ እንለማመዳለን። ከእርሱ ጋር ያለንን ህብረት እና ከእርሱ ጋር በዚህ ምድር ላይ ማሰብ እንኳን የማንችለውን አንድነት እንረዳለን።

ጳውሎስ የልጅነት መንፈስን የተቀበሉ ከክርስቶስ ጋር አብረው ወራሾች እንደሚሆኑ ነግሮናል። ርስታችንን ያዘጋጀልን እርሱ ነው። የእርሱ ሞት እና ትንሳኤ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን በር ከፍቶልናል። እነዚህን ታላላቅ በረከቶች እንደ አዳኞችን ከእርሱ ጋር እንወርሳለን። ኢየሱስ ለዳግም ቤዛነታችን ዋጋ ከፍሏል፣ እናም የልጅነት መንፈስ በውስጣችን ይኖራል፣ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ተቀባይነት ማግኘታችንን አትሟል። ስምምነቱ ተጠናቅቋል። አሁን ሁሉም ነገር ህጋዊ ነው። ጌታ ኢየሱስ የሞተላቸው እና የልጅነት መንፈስ የሚኖርባቸው የእግዚአብሔር መንግስት ወራሾች ናቸው።

ጳውሎስ በቁጥር 17 ላይ የጠቀሰው አንድ ተጨማሪ ዝርዝር ነገር አለ። እነዚህ ሁሉ በረከቶች በአንድ ሁኔታ ብቻ የእኛ ናቸው፡

*17 … አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን። (ሮሜ 8)*

በመጀመሪያ ሲታይ፣ጳውሎስ በሮሜ ሰዎች መዳን ላይ ቅድመ ሁኔታ እያስቀመጠ ነው ብሎ ማሰብ ይቻል ይሆናል፡፡ ይህ በቁጥር 17 ላይ ያለው ሐረግ ወደ አሮጌው የሕግ መንገድ ይመልሰናል የሚሉ አሉ፡፡ በሌላ አነጋገር፣በዚህ ምድር ላይ ለኢየሱስ መከራ ብንቀበል ድነናል፡፡ ነገር ግን ይህ አተረጓጎም ጳውሎስ በሮሜ 5-8 ያስተማረውን ሁሉ ይቃረናል፡፡ ጳውሎስ የክርስቶስ ሥራ ብቻ ለደህንነታችን በቂ እንደሆነ የሚያምን ጠንካራ አማኝ ነበር፡፡ የእኛ የግል ጥረት አስፈላጊ አልነበረም፡፡ በሕመም አልጋ ላይ ተኝቼ ቀሪ ሕይወቴን ለጌታ ኢየሱስ አንድ ነገር እንኳን ማድረግ ሳልችል ልቀር እችላለሁ ይሁን እንጂ አሁንም ርስት ሊሰጠኝ ይችላል ምክንያቱም ክርስቶስ ሥራዬን ስለሰራ እና የልጅነት መንፈስ በውስጤ ስላለ ነው፡፡ ጳውሎስ ስለ እዚህ እየተናገረ ያለው ስለ ድነት ሳይሆን ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች ስለመሆናችን እና ስለ ርስታችን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች ነን ወይ የሚለው ጥያቄ በክርስቶስ ሥራ እና በውስጣችን ባለው የልጅነት መንፈስ መታተም ተፈቷል፡፡

ጳውሎስ በቁጥር 17 ላይ ያለውን ለመረዳት፣ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን መመርመር ያስፈልገናል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ልጆቹ መስቀላቸውን በማንሳት ምሳሌውን እንዲከተሉ ይጠይቃቸዋል፡-

*23 ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡ (ሉቃስ 9)*

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጌታ ኢየሱስ አገልግሎት እና ስለ ጌታው ሲል ሲሰደድ እና ብዙ ፈተናዎችን ሲቀበል ሊሸከመው

ስለሚገባው መስቀል በሰፊው ተናግሯል (2ኛ ቆሮንቶስ 22-28 ተመልከቱ) ። ጌታ ኢየሱስን በማይቀበለው ዓለም ውስጥ መከተል ቀላል አይሆንም። የእግዚአብሔር ልጅ መሆናችን ፈጽሞ መከራ አይደርስብንም ማለት አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ጌታ ኢየሱስን መከተል የሚፈልግ ሁሉ በዚህ ምክንያት መከራ እንደሚቀበል ይነግረዋል፡

*12 በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ። (2ኛ ጢሞቴዎስ 3:12)*

ስደት ለክርስቶስ የመኖር አንድ አካል ብቻ ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የሰማዩን አባታቸውን ለማክበር የሚፈልጉ ሁሉ ከባድ ሥራ እንደሚጠብቃቸው ተናግሯል። የእግዚአብሔር መንፈስ ለሰጣቸው ስጦታዎች ጥቅም የእግዚአብሔር ልጆች ኃላፊነት ይወስዳሉ።

*10 የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፥ ሌላውም በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ። 11 ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። 12 ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፥ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤ 13 በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፥ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። 14 ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፤ 15 የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፥*

*እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል። (1ኛ ቆሮንቶስ 3)*

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች እግዚአብሔር በሥራቸው ላይ የሚፈርድበት ቀን እንደሚመጣ ይነገራቸዋል። ይህ ፍርድ ከመዳናቸው ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረውም። ጳውሎስ በቁጥር 15 ላይ አንድ ሰው በወርቅ፣በብርና በከበረ ድንጋይ በሆነው በክርስቶስ መሠረት ላይ ቢያንጽ በፍርድ ቀን ሽልማት እንደሚቀበል በግልጽ ተናግሯል። ሥራዎቹ ቢቃጠሉ ግን አሁንም ይድናሉ ነገር ግን "በእሳት እንደሚሆን" ይሆናል። መዳን የተረጋገጠ ቢሆንም፣አሁንም የሚታጣ አንድ ነገር አለ።

ጌታ ኢየሱስ በዘመኑ ለነበሩ አማኞች ሲናገር እንዲህ ይላል፦

*1 ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም። (ማቴዎስ 6)*

በማቴዎስ 10 ደግሞ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፡

*41 ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። 42 ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም። (ማቴዎስ 10)*

ኢየሱስ ሽልማቶችን ማጣት እንደሚቻል አስተምሯል። በሌላ በኩል ግን፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት የምናደርገው ጥረት

ዋጋ የማይሰጠው አይሆንም። ስለ ክርስቶስ ሥም መከራን የሚታገሡት ዋጋቸውን ያገኛሉ፡

*22 ሰዎች ስለ ሰው ልጅ ሲጠሉአችሁ ሲለዩአችሁም ሲነቅፉአችሁም ስማችሁንም እንደ ክፉ ሲያወጡ፥ ብፁዓን ናችሁ። 23 እነሆ፥ ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ ዝለሉም፤ አባቶቻቸው ነቢያትን እንዲህ ያደርጉባቸው ነበርና። (ሉቃስ 6)*

ሐዋርያው ዮሐንስ አንባቢዎቹ ሙሉ ሽልማት ያገኙ ዘንድ እንዲሠሩ አበረታቷቸዋል፡

*8 ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። (2ኛ ዮሐንስ)*

ሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች በክርስቶስ የመዳን ዋስትና ያላቸው እና በልጅነት መንፈስ የታተሙ ቢሆንም፣ ሁሉም አማኞች ተመሳሳይ ሽልማቶችን አይቀበሉም። አንዳንድ የእግዚአብሔር ልጆች በስጦታዎቻቸው አጠቃቀም ታማኝ አይሆኑም። አንዳንዶች በድል መሄድ ይሳናቸዋል። ሌሎች ደግሞ ለጌታቸው ሰነፍ እና ፍሬ አልባ ይሆናሉ። እነዚህ አማኞች ኪሳራ ይደርስባቸዋል። የእነርሱ ሊሆን የሚችለውን የሽልማት ሙላት አይለማመዱም።

የእግዚአብሔር ልጅ መሆናችን እግዚአብሔር የሰጠንን ኃላፊነት እንዳንወጣ አያግደንም። ዘለዓለምን የት እናሳልፋለን የሚለውን ጉዳይ ያስተካክላል፣ነገር ግን ትልቅ ኃላፊነት ውስጥ እንድንገባ ያደርገናል። የእግዚአብሔር ልጆች በዚህ ምድር ላይ ስደት ይደርስባቸዋል። የእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔር

ልጆች መሆናችንን ማኅተም ማድረግ ብቻ ሳይሆን ስጦታም ይሰጠናል እናም ለመንግሥቱ አገልግሎት ይጠራናል። እንደ እግዚአብሔር ልጆች በውርስ እና በሚሰጠው ደኅንነት የሚደሰቱ አሉ። ዳሩ ግን እነርሱ በፍጹም ታዛዥነት ላለመሄድ መርጠዋል። እነዚህ አማኞች በዚህ ህይወት ብቻ ሳይሆን በሚመጣው ህይወት ኪሳራ ይደርስባቸዋል።

**ለምልከታ**:

የባርነት መንፈስ ምንድን ነው? በዚህ የባርነት መንፈስ ሥር መሆኑን ያሳየ አንድ ሰው ታውቃላችሁን? ምን አይነት ባህሪያትን አሳያል?

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን እንዴት ያትማል?

ለመዳናችን ማረጋገጫ ይኖረን ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውን? ይህንን ማረጋገጫ ሲሰጠን የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ምንድን ነው? እንደ እግዚአብሔር ልጅነት ተቀባይነት ለማግኘታችሁ ማረጋገጫ አላችሁን?

የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ያለምንም ሥራ ባለን እድል እየተደሰትን መኖር ብቻ ማለት ነውን? እንደ እግዚአብሔር ልጆች ምን ኃላፊነቶች አሉብን? የእግዚአብሔር መንፈስ እንዴት ሰጣችሁ?

የእግዚአብሔር ልጅ ሽልማቱን ሊያጣ ይችላልን?

የእግዚአብሔር ልጅ በመሆን እና ሽልማት በማጣት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ልጅ ሆናችሁ ለአባታችሁ ዓላማ ታማኝ ሆናችኋልን?

**ለጸሎት**:

በህይወታችሁ በመንፈስ ቅዱስ መገኘት ምክንያት እንደ ወንድ ወይም ሴት ልጅ ልጅነታችሁን ስላተመ ጌታን አመስግኑት፡፡

የመዳናችሁን ማረጋገጫ እና ከአብ ጋር ያለውን ህብረት የሰጣችሁን የልጅነትን መንፈስ አመስግኑ፡፡

ታማኝ ልጅ ትሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጠይቁት፡፡ ምንም ሽልማት እንዳታጡ ነገር ግን በዚህ እና በሚመጣው ህይወት በበረከቱ ሙላት ደስተኞች ትሆኑ ዘንድ በመንፈሱ እንዲመራችሁ እና ኃይል እንዲሰጣችሁ ጠይቁት፡፡

# ምዕራፍ 18 -

# የፍጥረት ሁሉ እስራት

---

ሮሜ 8:18-25

*18 ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ
ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ። 19 የፍጥረት
ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና። 20
ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና፥ በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ
በፈቃዱ አይደለም፤ 21 ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ
ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች
ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው። 22 ፍጥረት ሁሉ
እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን
እናውቃለንና። 23 እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ
በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን
ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። 24
በተስፋ ድነናልና፤ ነገር ግን ተስፋ የሚደረግበቱ ነገር ቢታይ
ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? 25
የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠባበቃለን።*

እስከዚህ ነጥብ ድረስ፣ ጳውሎስ ሲናገር የነበረው ኃጢአት በሰው ልጆች ላይ ስላለው ተጽዕኖ ነው። ነገር ግን በኃጢአት የተረገመው የሰዎች ልጅ ብቻ አይደሉም። ፍጥረት ሁሉ በተጽዕኖው ሥር ወድቆ ይሰቃያል፡፡ በዘፍጥረት 3 ላይ አዳምና ሔዋን በኃጢአት ከወደቁ በኋላ እግዚአብሔር አዳምን እንዲህ አለው፡-

*17 አዳምንም አለው፡- የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤18 እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። 19 ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና። (ዘፍጥረት 3)*

እግዚአብሔር በዚያ ቀን "ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን" በማለት ለአዳም የነገረውን አስተውሉ። (ዘፍጥረት 3:17) በምድር ላይ የተነገረው እርግማን እሾህና አሜከላን እንድታበቅል ምክንያት ሆኗል (ዘፍ 3፡18) ። አዳም የምድሪቱ አፈር ፍሬ ታፈራ ዘንድ ጠንክሮ መሥራት ነበረበት። ከምድር ፍሬ “በሥቃይ” ይበላል (ዘፍጥረት 3፡17) የአዳም ሚስት የሆነችው ሔዋን በወሊድ ጊዜ ህመም ይበዛባታል (ዘፍጥረት 3፡16 ተመልከቱ) ። በኃጢአት ምክንያት፣ስቃይና መከራ ምድርን ያጥለቀልቃል። ከእርግማኑም የተነሳ የምድር ፍሬ ይቀንሳል። ሞት እና መበስበስ ፍጥረት ሁሉ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህን ለማሸነፍ አዳም ጠንክሮ መሥራት ነበረበት፣በመጨረሻም ሥጋው ወደ አፈር ይመለሳል። ፍጥረት ሁሉ ይበሰብሳል፣ይሞታል።

ሞት፣መበስበስ፣ሕመምና መከራ የኃጢአት ውጤቶች ናቸው። እኛ እና ፍጥረት ሁሉ የምንኖረው በዚህ እርግማን ውስጥ ነው። አበባ በሙሉ ውበቱ ሲያብብ እና በመጨረሻም ሲሞት እንመለከታለን። በሽታ ሰውነታችንን ሲያበላሽ እና የምንወዳቸውን ሰዎች ሲወስድ እንመለከታለን። ታላላቅ አውሎ ነፋሶች እና የተፈጥሮ አደጋዎች አሁንም በኃጢአት እርግማን ውስጥ እንደምንኖር ያስታውሱናል። በዚህ ህይወት ውስጥ እያንዳንችን እናልፋለን። ይሁን እንጂ ተስፋ ለመቁረጥ ምክንያት አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ የሮም አማኞች የተሻለ ጊዜ እንደሚመጣላቸው ያስታውሳቸዋል፡

*18 ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ። (ሮሜ 8)*

የጌታ ኢየሱስ ለሆኑት የሚገለጥ ክብር አለ። ስለዚህ ክብር በዝርዝር አልናገርም። የሰማይ እና የሚመጣው ዓለም ክብር አሁን ካለንበት እጅግ በጣም የተሻሉ ናቸው ማለት ይበቃል።

ሐዋርያው በመቀጠል የእግዚአብሔር ልጆች የሚገለጡበትን ቀን ፍጥረት ራሱ ይናፍቃል በማለት ይቀጥላል።

*19 የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና።*

ይህ የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ ምንድን ነው? ይህንን ሐረግ ለመረዳት የተለያዩ መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ።

በመጀመሪያ ይህን “የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ” ከሚመጣው ፍርድ አንጻር ማየት ያስፈልገናል። በማቴዎስ 25 ላይ ያለውን የኢየሱስን ትምህርት ተመልከቱ:

*31 የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤ 32 አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥ 33 በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል። 34 ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። (ማቴዎስ 25)*

ኢየሱስ በአሕዛብ ላይ የሚፈርድበት ቀን እንደሚመጣ ያስታውሰናል። በዚያ ቀን የሚያምኑ ከማያምኑ የሚለዩበት ይሆናል። የእርሱ የሆኑ ሁሉ የተዘጋጀላቸውን መንግሥት ይወርሳሉ፤ዳሩ ግን እርሱን የካዱ “ለዲያብሎስና መላዕክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለማዊ እሳት ይጣላሉ (ማቴ 25፡41) ። በዚያ የፍርድ ቀን የእግዚአብሔር ልጆች ይገለጣሉ። ማን የክርስቶስ እንደሆነ እና ማን እንደካደው እናውቃለን።

ሁለተኛ “የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ” የሚለው ሐረግ የክርስቶስ ለሆኑት የሚሰጥ ሽልማትና ክብርም ነው። ጳውሎስ ትንሣኤን በተመለከተ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲናገር እንዲህ ይላል፡

*42 ደግሞ ሰማያዊ አካል አለ፥ ምድራዊም አካል አለ፤ ነገር ግን የሰማያዊ አካል ክብር ልዩ ነው፥ የምድራዊም አካል ክብር ልዩ ነው። 43 የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው፤ በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው*

*ኮከብ ይለያልና። 44 የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤ 49 የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን። (1ኛ ቆሮንቶስ 15)*

እኛ እንደ እግዚአብሔር ልጆች በአዲሱ አካላችን የምንነሣበት ቀን እንዴት ያለ ነው። እነዚህን በኃጢአት የተረገሙ ምድራዊ አካላትን አውልቀን የክርስቶስን መልክ የተሸከሙ አዲስ አካል መልበሳችን ምንያህል ክብር የሞላበት ይሆናል። በእነዚህ አዲስ እና የተከበሩ ግዛቶች የእግዚአብሔር ልጆች የሚገለጡበት ቀን ይመጣል።

በዘመናችን የኃጢአት እርግማን ማስረጃ በዙሪያችን አለ። ጳውሎስ ፍጥረት ለከንቱነት እንደተገዛ ይነግረናል። በእንግሊዘኛ ስታንዳርድ ቨርዥን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም "ከንቱነት" ተብሎ የተተረጎመው ቃል እርባና ቢስ፤ዋጋ የሌለው ወይም ባዶ የሚል ስሜት የያዘ ነው። ይህንን ለአፍታ እናስብ።

በህይወት ውስጥ ብዙ ሃብትን እና ብልጽግናን ለመሰብሰብ ጠንክሮ የሚሠራውን አንድ ሰው አስቡ። በመጨረሻ ምን ይሆናል? ይህን ሁሉ ሃብት በሞት አያጣውምን? ሰሎሞን ስለዚህ ነገር በመጽሐፈ መክብብ ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፡

*18 ከእኔ በኋላ ለሚመጣው ሰው እተወዋለሁና ከፀሐይ በታች የደከምሁበትን ሁሉ ጠላሁት። 19 ጠቢብ ወይም ሰነፍ እንዲሆን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? ከፀሐይ በታች በደከምሁበትና ጠቢብ በሆንሁበት በድካሜ ሁሉ ላይ ጌታ ይሆንበታል፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነው። 20 እኔም ተመልሼ*

*ልቤን ከፀሐይ በታች በደከምሁበት ድካም ሁሉ ተስፋ አስቈረጥሁት። 21 ሰው በጥበብና በእውቀት በብልሃትም ከደከመ በኋላ ለሌላ ላልደከመበት ሰው ያወርሰዋልና፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ትልቅም መከራ ነው። (መክብብ 2)*

ከዚህ ሁሉ ልፋት እና ጥረት በኋላ ያ ሰው ሁሉንም ነገር ከጀርባው በመተው፤ይህን ሁሉ ሃብት ለመሰብሰብ ያደረገውን ጥረት ወደማያደንቅ ሌላ ሰው ይተላለፋል። ለዚያ ሃብት ምንም አበርክቶ ለሌለው ሰው ይሰጣል። በብዙ ድካም እና ጥረት የሰበሰበው ሰው ለዘለዓለም የጠፋ ይሆናል።

ሰሎሞን ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ሲል ይጽፋል፡-

*14 የጠቢብ ዓይኖች በራሱ ላይ ናቸው፥ ሰነፍ ግን በጨለማ ይሄዳል፤ ደግሞ ለሁለቱ መጨረሻቸው አንድ እንደ ሆነ አስተዋልሁ። 15 እኔም በልቤ፦ ለሰነፍ የሚደርሰው ለእኔም ይደርሳል፤ ለምን እጅግ ጠቢብ ሆንሁ? አልሁ። የዚያን ጊዜም በልቤ፦ ይህ ደግሞ ከንቱ ነው አልሁ። 16 በሚመጣው ዘመን ነገር ሁሉ የተረሳ ይሆናልና ለዘላለም የሚሆን የጠቢብና የሰነፍ መታሰቢያ አይገኝም። አዬ ጉድ! ጠቢብ ከሰነፍ ጋር እንዴት ይሞታል! 17 ከፀሐይም በታች የተሠራው ሥራ ሁሉ ከብዶብኛልና ሕይወትን ጠላሁ፤ ሁሉም ከንቱ ነፋስንም እንደ መከተል ነው። (መክብብ 2)*

የሰለሞንን ተስፋ መቁረጥ በድጋሚ አስተውሉ። ጥበቡ ሁሉ በመጨረሻ ወዴት ያመራል? እንደ ሰነፍ ሰው በመሞት ለዘለዓለም በሚረሳበት መቃብር ውስጥ ይቀበራል። ከበሽታችን የተፈወስነው በመጨረሻ ለመሞት ነው። ሃብት የምናካብተው ጥረታችንን ሊያደንቅ ለማይችለው ሰው ለመተው ብቻ ነው።

ታላቅ ጥበብን የምናሳካው ይዘነው ወደ መቃብር ከወረደን ብቻ ነው። ይህ ሕይወት ሁሉ ቢኖርም በዚህ ከንቱነት ሥር እንኖራለን።

በሮሜ 8፡20 ጳውሎስ ፍጥረት ሁሉ በኃጢአት ምክንያት ለዚህ ከንቱነት የተገዛ መሆኑን ያሳስበናል። ያ ኃጢአት የገባው ሰይጣን አዳምና ሔዋንን በፈተናቸው እና በፈተናውም በወደቁ ጊዜ ነበር። የዚህም ውጤት የእግዚአብሔር ፍርድ ነበር። ምድርን ረገማት። ለኃጢያትና ኃይሉ ተገዢ የሆነው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው። ይህም ኃጢአት ተስፋ መቁረጥ፣በሽታ እና ሞት አመጣ።

እግዚአብሔር ግን ዓለምን በዚህ ከንቱነት አልተወውም። ጳውሎስ ፍጥረት በኃጢአት ምክንያት ከተጫነበት እስራት ነጻ የሚወጣበት ቀን እንደሚመጣ ለሮሜ ሰዎች አስታውሷል፡

*20 ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና፥ በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤ 21 ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው። (ሮሜ 8)*

በሕይወታችን ከኃጢአት እርግማን ነጻ የሚያወጣን ያው የእግዚአብሔር ጸጋ ፍጥረታትን ሁሉ ከዚህ እርግማን ነፃ ያወጣል። ፍጥረትም “የእግዚአብሔርን ልጆች ክብር እና ነፃነት” ያገኛሉ (ቁጥር 21) ። የእግዚአብሔር እቅድ ከእኔ እና ከእናንተ እቅድ ይበልጣል። ፍጥረትን ሁሉ ወደ ራሱ ለመመለስ አቅዷል። የራዕይ መጽሐፍ ስለ አዲስ ሰማይ እና አዲስ ምድር ይናገራል፡

*1 አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። 2 ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። 3 ታላቅም ድምፅ ከሰማይ፦ እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ 4 እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ። (ራዕይ 21)*

እንዴት ያለ ታላቅ ተስፋ አለን፡፡ አዲስ የከበረ አካል እንደምንቀበል ሁሉ፤የእግዚአብሔርም ፍጥረት አዲስ ይሆናል። እግዚአብሔር እርግማኑን ይቀለበሳል፣ እናም ከኃጢአት፣ ከሞት እና ከበሽታ ውጤቶች ነጻ በሆነ ዓለም ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እናደርጋለን። በዚያ አዲስ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር እነዚያን ሁሉ እንባዎች ያብሳል ስለሆነም የሃዘንና የሥቃይ እንባ የምናፈስበት ምንም ምክንያት አይኖረንም።

በሮሜ 8፡22 ላይ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ፍጥረት በምጥ ሥቃይ እንደሚቃትት ያስተምራል።

*22 ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና።*

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሁለቱንም ህመም እና ተስፋ ይገልጻል። ነፍሰ ጡር የሆች ሴት በወሊድ ህመም ትሰቃያለች። ይህ ህመም በጣም ኃይለኛ እና ስቃይ የሞላበት ነው። ዳሩ ግን ይህ ተስፋ ቢስ ህመም አይደለም፤ምክንያቱም ሴቲቱ በዚያ ውስጥ በጽናት ስታልፍ፤ሃዘኗን ወደ ደስታ እና ሃሴት የሚቀይር አዲስ ልጅ እንደምትወልድ ታውቃለችና። አዎ በዚህ ህይወት ውስጥ ከንቱነት አለ። ህመም፤በሽታ፤ስቃይ እና ሞት አለ። ዳሩ ግን ይህ ህመም አንድ ቀን እንደሚያበቃ ጌታ የተስፋ ቃል ሰጥቷል። ፍጥረት ከዚህ እርግማን ነጻ ወጥቶ የእግዚአብሔርን ልጆች ነጻነትና ክብር ያገኛል (ቁጥር 21) ።

በዚህ ምድር ላይ ስንኖር በኃጢአትና በሞት ምክንያት በሚቃትት ሥጋ ውስጥ እንኖራለን። እነዚህ አካላት ለኃጢያት እና ለውጤቶቹ ተገዢ ናቸው። ፍጥረት አንድ ቀን እንደሚታደስ ሁሉ ሰውነታችንም ይለወጣል፡

*23 እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። (ሮሜ 8)*

ሰውነታችን የሚቤዠበት ቀን እንደሚመጣ አስተውሉ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሰራው ሥራ ከኃጢአት እርግማን ነጻ ይሆናሉ። እስከዚያው ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ለክርስቶስ ለሆኑት ተሰጥቷል።

*6 በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ፥ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና። 7 ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት*

*ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን፤ (2ኛ ቆሮንቶስ 4)*

ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡6-7 ላይ በሸክላ ዕቃ ውስጥ ስላለን ውድ ሃብት ተናግሯል። እነዚህ አካላት፣ ልክ እንደ ደካማ የሸክላ እቃ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስዕብና ውስጥ የክርስቶስን እውቀት እና ኃይል ይይዛሉ። ዓላማውን ለመፈጸም በእነዚህ ደካማ አካላት በኩል ይሰራል። ለአሁኑ ድካማችን እና እርግማናችን የሚወገድበትን ቀን እንደፍጥረት ሁሉ እንናፍቃለን። ተስፋችን ይህ ነው። መተማመናችን በጌታ በኢየሱስ ሥራ እና በቃሉ ተስፋ ላይ ነው። ምንም እንኳን የዚህን ተስፋ እና ነጻ መውጣት ሙላት ባንለማመድም፣ለተስፋ ቃሉ ታማኝ በሆነው በእርሱ እንታመናለን።

*24 በተስፋ ድነናልና፤ ነገር ግን ተስፋ የሚደረግበቱ ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? 25 የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠባበቃለን። (ሮሜ 8)*

ጳውሎስ እዚህ ላይ የኃጢአትን ይቅርታ ያገኘን እና ከሚመጣው ፍርድ ነጻ የወጣን ቢሆንም አሁንም ለኃጢአትና ለክፋት በተገዛ ዓለም ውስጥ እንደምንኖር ያስታውሰናል። የምንኖርበት ዓለም በእግዚአብሔር እርግማን ሥር ነው። የምንኖርባቸው ሥጋዊ አካላትም አሁንም ለኃጢአት፣ለሕመምና ለሞት ውጤቶች ተገዢ ናቸው። ለአማኙ ግን ተስፋ አለው። እግዚአብሔር እነዚህን አካላት ጥለን ከኃጢአት፣ከመከራና ከሞት ውጤቶች ነጻ የሆነ አዲስ አካል እንደምንቀበል የተስፋ ቃል ሰጥቷል። ፍጥረት አሁን

እንደምናውቀው ሁሉ፤አንድ ቀን ይለወጣል። ሰውነታችን እንደሚጠፋና እንደሚለወጥ ሁሉ ይህችም ምድር ትጠፋለች፤አዲስም ትሆናለች (2ኛ ጴጥሮስ 3፡10፤ ራዕ. 21፡1-4 ተመልከቱ) ። የእግዚአብሔር አስደናቂ የማዳን እቅድ ለልጆቹ ብቻ ሳይሆን ለፍጥረቱም ጭምር ነው።

**ለምልከታ**:

ኃጢአት በፍጥረት ላይ ምን ተጽዕኖ አሳደረ? ኃጢአት የእግዚአብሔርን ፍጥረት የለወጠው እንዴት ነው?

ሰውነታችሁ በኃጢአት እርግማን እንዴት ይጠቃል?

ከሥጋህ ትንሣኤ በኋላ ምን ዓይነት ለውጦችን ትጠብቃላችሁ? በዚህ አዲስ አካል ውስጥ ምን ተስፋዎች አሉን?

አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ስለሚፈጠሩበት እውነታ ምን ማጽናኛ አግኝተችኋል? በዚህ አዲስ ምድር ምን ለማየት ትጠብቃላችሁ?

**ለጸሎት**:

አዲስ አካል እና አዲስ ምድርን በተመለከተ ስለተሰጠው የተስፋ ቃል ጌታን ለማመስገን ትንሽ ጊዜ ውሰዱ። በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ ስላላችሁ ተስፋ አመስግኑት።

አሁን ያለው ምድራዊ ሰውነታችሁ በእርግማን ተጽዕኖ ምክንያት ሲሰቃይ ጸጋን እና ተስፋን እንዲሰጣችሁ ጌታን ጠይቁት። በተስፋ ለመጽናት ጥንካሬን እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

በዚህ በኃጢአት በተረገመ ዓለም ይመራን እና ያበረታን ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ስለሰጠን ጌታን አመስግኑት። በመንፈሱ ኃይል እና በእርሱ መሪነት ለመመላለስ እንችል ዘንድ ጸጋ እንዲሰጠን እግዚአብሔርን ጠይቁት።

## ምዕራፍ 19 -

## የመንፈስ መቃተት

---

ሮሜ 8:26-27

*26 እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና። (ሮሜ 8)*

በመጨረሻው ምልከታ፣ፍጥረት ከኃጢአትና ከሞት ባርነት ነጻ ለመውጣት እንዴት ሲቃትት እና ሲጠባበቅ እንደነበር ተመልክተናል (ሮሜ 8:19-21 ተመልከቱ) ። የዚህ እስራት ውጤቶች በሁሉም ሥፍራ አሉ። በሽታ፣መበስበስ፤አሳዛኝ ሁኔታዎች፣ረሃብ እና መቅሰፍቶች በኃጢአት በተረገመች ዓለም ውስጥ የኑሮ አካል ናቸው። ሰዎች እንደመሆናችን መጠን በምድር ላይ ባለው እርግማን እንሰቃያለን፤ሆኖም በሕይወታችን ውስጥ የኃጢአት ውጤቶች አሉ። ኃጢአት ሰውነታችንን በበሽታ እና ደዌ ያበላሻል። ክፉ መሻቱ እና ሃሳቡ ከቅዱስ እና ጻድቅ አምላክ ስለሚለየን ነፍሳችንን ያጠፋል።

እንደ አማኞች በእነዚህ ኃጢአተኛ አካል ውስጥ እንታገላለን። ከጌታ ጋር ለመኖር ስንፈልግ በሥጋ እና የአዕምሮ ድካም ውስጥ እናልፋለን። አንዳንዴ ትግሎች ያሸንፉናል። አንዳንድ ጊዜ ለመቀጠል የሚያስችል ጥንካሬ የለንም። ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታውን ለማገልገል ሲጥር ስለ ሥጋው ድካም መስክሯል። በ2ኛ ቆሮንቶስ 4 ላይ ለቆሮንቶስ ሰዎች የተናገረውን አድምጡ፡-

*8 በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ 9 እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም፤ 10 የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን። 11 የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሥጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን ከኢየሱስ የተነሣ ዘወትር ለሞት አልፈን እንሰጣለንና። (2ኛ ቆሮንቶስ 4)*

የክርስትና ሕይወት ቀላል አይደለም። ጳውሎስ እንደተናገረው ይጨነቅ፣ያመነታ፣ይሰደድ እና ይወድቅ ነበር። ይህ ሁሉ የሆነው በምድራዊ አካሉ ከፈተናዎቹ ጋር እየታገለ ሲኖር ነው። በሮሜ 7 ላይ ሐዋርያው የሥጋውን ድካም ተገንዝቦ "እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ከዚህ ሞት ሥጋ ማን ያድነኛል? ብሎ ይጮሃል (ሮሜ 7:24) ።

በኃጢአት በተሰቃየ ሥጋ እና በእግዚአብሔር የተረገመ ዓለም ውስጥ ስንኖር ለጌታ እንዴት እንኖራለን፤በጥሪአችንስ ጸንተን እንዴት እንቆማለን? ጳውሎስ ይህንን ጥያቄ በሮሜ 8፡26-27 ውስጥ ይመልሳል:

*26 እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።*

ጳውሎስ ቁጥር 26ን የጀመረው "እንዲሁም" በሚለው ቃል እንደሆነ አስተውሉ። ይህ ወደ ቀደሙት ጥቅሶች ይመልሰናል (ሮሜ 7፡19-23) ፍጥረት ሁሉ ከመከራ እና ስቃይ ባርነት ነጻ ለመውጣት በመናፈቅ ይጮሁ እንደነበር ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ያስታውሳቸው ነበር። ፍጥረት እንደሚቃትት ሁሉ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ ስለ እኛ "በማይነገር መቃተት" ይማልድልናል (ቁጥር 26) ።

ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች በመጋደል ወቅት ብቻቸውን እንዳልነበሩ አስታውሷቸዋል። በሥጋና በአዕምሮ ድካማቸው መንፈስ ቅዱስ ይርዳቸው ነበር። እዚህ ላይ በጣም የሚያስደንቀው ነገር መንፈስ ቅዱስ ደካማ በሆኑ ሥጋዊ አካላትን ውስጥ በመኖር የሚያግዝ መሆኑ ነው። ጳውሎስ ይህንን በሸክላ ማሰሮ ውስጥ ያለ ውድ ሃብት አድርጎ ይገልጸዋል፡-

*7 ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን፤ (2ኛ ቆሮንቶስ 4)*

የእግዚአብሔር ኃይል በተራ ሥጋ ውስጥ ይኖራል። እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ግብፅ እንዲመለስ በጠራው ጊዜ የሚቃጠል ቁጥቋጦ ምልክት ሰጠው። ይህ ቁጥቋጦ የተለመደ

የበረሃ ተክል ነበር። በዚህ ልዩ ቁጥቋጦ ውስጥ የእግዚአብሔር እሳት ሳያቃጥለው ከመንደዱ በቀር ምንም የተለየ ነገር አልነበረም (ዘጸአት 3፡1-4 ተመልከቱ) ። ይህ እንዴት ያለ አስደናቂ ምስል ነው። የእግዚአብሔር ኃይል በተራው የሰው ሥጋ ውስጥ እየሠራ ነው፣ ያ ሥጋ በራሱ ኃይልና ጥበብ ፈጽሞ ሊሠራው የማይችለውን ያደርግ ዘንድ እያቃጠለና እያበረታው ነው።

ይህ እርዳታ ለእኛ የተዘጋጀ ቢሆንም እኛ ልንጠቀምበት እንደሚገባ መረዳት አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔርን መንፈስ ጥንካሬ እና መመሪያ አይፈልግም። የራሳችንን ጥበብ የምንጠቀምበት ጊዜ አለ። የእግዚአብሔርን መንፈስ እርዳታ እና መመሪያ ስላልፈለግን ብዙ ጊዜ ወድቀናል። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ እኛን ለመርዳት ፈቃደኛ መሆኑን ጳውሎስ ያሳስበናል።

ሮሜ 8፡26ን መመርመራችንን ስንቀጥል መንፈስ ቅዱስ እንዴት ሊረዳን እንደሚፈልግ አስተውሉ።

*26… እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ (ሮሜ 8)*

ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች እንደ አማኞች “እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም” እያለ ይነግራቸዋል። በቀላል አነጋገር፣ ጸሎት እግዚአብሔርን ማናገር ነው። ይሁን እንጂ ጸሎት ሁልጊዜ ቀላል አይደለም። መጸለይ እንደሚገባን ለመጸለይ የእግዚአብሔር መንፈስ እርዳታ ያስፈልጋል።

ችግር ሲያጋጥመን እና ድካም ሲሰማን “ጌታ ሆይ፣ይህን ሥቃይ አስወግድ” ብለን መጸለይ በጣም ቀላል ይሆንልናል። ነገር ግን የዚህ ጸሎት ችግር የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለማሰቡ ነው። በዚህ መከራ ውስጥ እግዚአብሔር ምን እያለ ነው? ወደ ሌላ መንገድ እየመራኝ ነውን? ንስሃ ልገባበት ስለሚገባኝ ኃጢአት እየወቀሰኝ ነውን? ትምህርት ሊያስተምረኝ ይፈልጋልን? አንዳንድ ጊዜ ታላላቅ የእግዚአብሔር በረከቶች የሚመጡት በሚገጥሙን ፈተናዎች ነው። የበረከት ምንጭ ወደሆነው እንጸልያለን?

በአንድ ወቅት ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት ሊያመልጥ ሲሮጥ፣ወደ ተርሴስ ከሚሄደው መርከብ መውረዱ አስፈላጊ መሆኑን ተገነዘበ። መርከበኞችን ወደ ባህሩ አውጥተው እንዲጥሉት ከዚያም ማዕበሉ እንደሚቆም ነገራቸው። ይህን ለማድረግ እያመነቱ ሳለ፣በማዕበል ወደሚናወጠው ባህር ከመጣል ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው ተገነዘቡ። ዮናስ ወደ ጥልቅ ባሕር ውስጥ እየሰመጠ ሳለ እግዚአብሔር አንድ ትልቅ ዓሣ ይውጠው ዘንድ ላከ። ይህንን ምስል ለአፍታ አስቡት። ዮናስን ብትሆኑ እና በባህሩ ውስጥ እየሰመጣችሁ ሳለ አንድ ትልቅ ዓሣ አፉን ከፍቶ ወደ እናንተ ሲመጣ አያያችሁ እንደሆነ አስቡ። ጸሎታችሁ ምን ይሆን ነበር? ጌታ ሆይ፥ ከዚህ ዓሣ አድነኝ ብላችሁ አትጸልዩምን? በሕይወት መዋጥ እና በዚህ መንገድ መሞት አልፈልግም፤እንግዲህ በዚህ መንገድ ከጸለያችሁ ለትልቁ በረከታችሁ እየጸለያችሁ ነው። ዮናስን ወደ ባህሩ ዳርቻ ወስዶ በደረቅ ምድር ላይ የሚተፋው ዓሣው ነበር። ያ ዓሣ የዮናስ መዳን ነው።

እንዴት እንጸልያለን? ፈተናዎች እና ውጣ ውረዶች ሲመጡ እነርሱ እንዲወገዱ ትጸልያላችሁ ወይስ እኛን ለማጥራት

እግዚአብሔር እንዲጠቀምባቸው ትጠይቃላችሁ? የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው? ወደ አዕምሯችን የሚመጣውን የመጀመሪያውን እንጸልያለን? ጳውሎስ እየነገረን ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ የሚረዳን እንዴት መጸለይ እንዳለብን ስለማናውቅ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ዓላማ እና ማድረግ የሚፈልገውን አንረዳም፡፡ የእግዚአብሔርን በረከቶች ስላላወቅናቸው እንዲወገዱ እንጸልያለን?

እዚህ ላይ ጳውሎስ በድካማችን ምን መጸለይ እንዳለብን እንደማናውቅ ያሳስበናል፡፡ እንደሚገባን ለመጸለይ፣መንፈስ ቅዱስ እና ምሪቱ በጣም እንደሚያስፈልገን መገንዘብ አለብን፡፡ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በሮሜ 8፡26 ላይ እርሱን ቢጠብቁ መንፈስ ቅዱስ እንደሚረዳቸው ይነግራቸዋል፡፡

መንፈስ በአብ ፈቃድ እና ዓላማ እንድንጸልይ ብቻ ሳይሆን በዚህ በሚያስፈልገን ጊዜም ስለእኛ ይጸልያል፡፡

*26 … ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ (ሮሜ 8)*

ይህን የጳውሎስን መግለጫ በተመለከተ ሁለት ነጥቦችን ማንሳት አለብን፡፡ በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ ስለ እኛ እንደሚማልድ አስተውሉ፡፡ መማለድ ለሌላ ሰው መማጸን ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ እኛ ወደ አብ ይጮኻል፡፡ ስለ አንድ ነገር ስንጮኽ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ እኔ ሌላ ጸሎት የሚጸልይበት ጊዜ እንዳለ እገምታለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ በአመፅ የምመላለስበት እና የእግዚአብሔር መንፈስ ደግሞ በእኔ ፈንታ ወደ አብ

የሚጮህበት ጊዜ እንዳለ እገምታለሁ። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ውስጥ ለእኔ የሚማልደው መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንዳልሆነ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ በሮሜ 8፡34 እንዲህ ይለናል፡-

*34 የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። (ሮሜ 8)*

ስለ እኛ ወደ አብ የሚጮኽ የእግዚአብሔር መንፈስ እና የእግዚአብሔር ልጅ ምልጃ አለን። የሥጋን ድክመቶች እንዴት እንጋፈጣለን? ይህንንም የምናደርገው በመንፈስ ቅዱስና በእግዚአብሔር ልጅ ምልጃ እና ኃይል ነው።

ሁለተኛ በቁጥር 26 ላይ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የሚጸልየውን ጸሎት ጥንካሬ ተመልከቱ። ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች “በማይነገር መቃተት” የእግዚአብሔር መንፈስ እንደማለዳቸው ተናግሯል። በእኛ ፈንታ ወደ አብ በመጸለይ የእግዚአብሔር መንፈስ “ይቃትታል። መቃተት የሚመጣው ከህመም እና ከነፍስ ስቃይ ነው። ሸክም ያለበት ሰው ንግግር ነው። የመንፈስ ቅዱስ መቃተት በባህርዩ ምልጃ ነው፤ይህ መቃተት የሚመነጭበት ህመም የሁኔታዎቻችን ውጤት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ህመማችን ይረዳል። ስለ እኛ በጥልቅ ስሜት ይጮኻል። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ትልቅ ህብረት አለ። የመንፈስ ቅዱስ ምልጃ የሚመጣው ለእኛ እና በመጋደላችን ካለው ጥልቅ ስሜት ነው። ስለእኛ በእንባ ይጸልያል። በአብ ፊት የሚቃትተው በጥርጣሬ ሳይሆን ከስቃያችን እና ከድካማችን በሆነ ጥልቅ ስሜት ነው። ጳውሎስ ይህን መቃተት “የማይነገር መቃተት” ሲል ገልጾታል። የእግዚአብሔር

መንፈስ ስለ እኛ የሚያደርገውን የመቃተት ጩኸት ጥልቀት ለመግለጽ ቃላት በቂ አይደሉም። እርሱ ለኛ በጥልቀት ያስባል እንዲሁም በፍቅር ከውስጣዊ ማንነቱ በመቃተት ስሜቱን ይገልፃል። ከዚህ በላይ መወደድ አንችልም። የእግዚአብሔር ልጅ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷል። የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ እና በክርስቶስ ላለን እድገት በከፍተኛ መናፈቅ እና መሻት ይቃትታል።

ጳውሎስ ሮሜ ቁጥር 27 ላይ ልብን የሚመረምረውን የመንፈስ አሳብ እንደሚረዳ አስታውሷቸዋል።

*27 ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና። (ሮሜ 8)*

ልብን የሚመረምር እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር መንፈሱ የሚማልድበትን ልብ እንደሚመረምር ሁሉ በዚያ የሚኖረውን የመንፈስ ሃሳብ ይረዳል። በማይነገር መቃተት የሚማልደውን የመንፈስን ጩኸት ተረድቷል። የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለሚማልድ ያንን ጸሎት ሰምቶ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይስማማል።

እንዴት መጸለይ እንዳለብን ባናውቅም፣ የአብ ፈቃድ እና ዓላማ በእኛ እንዲፈጸም የእግዚአብሔር መንፈስ በጋለ ስሜት ይማልዳል። የምንኖረው ኃጢአት ተጽዕኖ ባሳደረበት ሥጋዊ አካል ውስጥ ነው። አዕምሯችን እና ሃሳባችን ለኃጢአት የተጋለጡ ናቸው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ማወቅ እንችላለን? ለስሙ በሚገባው መንገድ ላይ እንዴት መጓዝ

እንችላለን? ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች እንዴት መጸለይ እንዳለብን እንኳን በማናውቅበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በማይነገር መቃተት ስለእኛ እንደሚማልድ ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር አብ ያንን መቃተት ተረድቶ፤መንፈስ ቅዱስ ስለ እኛ የጸለየውን ጸሎት ይሰማል።

የሚደግፈን የእግዚአብሔር መንፈስ ጸሎቶች አለን። እሱ መንፈሳዊ ደህንነታችንን ይፈልጋል እናም ስለ እኛ በጋለ ስሜት ይጸልያል። ለእነዚያ ጸሎቶች ምላሽ አብ በእኛ ውስጥ ይሠራል። እንደዚህ አይነት ፍቅር ምንኛ የማይገባን ነን፣ነገር ግን ይህን የእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወታችን ያለውን የጠበቀ ሥራ ማወቅ እንዴት ድንቅ ነው። ለእርሱ እንገዛ እና ጸሎቱ በሕይወታችን ውጤታማ ይሆን ዘንድ እንፍቀድ።

**ለምልከታ**:

ጸሎት ለእግዚአብሔር የምትፈልጉትን መንገር ብቻ ነውን?

ለመጸለይ የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ ለምን ያስፈልገናል?

የእግዚአብሔርን በረከቶች ልንጸልይ እንችላለን?

የመንፈስ ቅዱስ መቃተት ለእኛ ስላለው ጥልቅ ስሜት ምን ይነግረናል?

በምንጸልይበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስን መስማት ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

የመንፈስ ቅዱስን ድጋፍ እና አማላጅነትን በማወቅ ምን ማጽናኛ ታገኛላችሁ?

**ለጸሎት**:

ለመጸለይ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት እና እርዳታ እንደማያስፈልጋችሁ ስላመናችሁበት ጊዜ ጌታ ይቅር እንዲላችሁ ጠይቁ።

ለእኛ ስላለው ታማኝነት እንዲሁም በክርስቶስ እውቀት እና ፍቅር እናድግ ዘንድ ስላለው ፍቅር መንፈስ ቅዱስን እናመሰግናለን።

እርሱን እና የመንፈሱን ምሪት ባለመፈለግ ከፈቃዱ እና ከዓላማው ውጭ ለጸለያችኋቸው ጊዜያት እግዚአብሔር ይቅር እንዲላችሁ ጠይቁት።

# ምዕራፍ 20 -

# ነገር ሁሉ ለበጎ ይደረጋል

ሮሜ 8:28

*28 እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።*

ሐዋርያው ወደ ቁጥር 28 በመሄድ ለሮሜ አማኞች፣ ምንም እንኳን ብዙ መሰናክሎች ቢገጥሟቸውም፣ሁሉም ነገር ለበጎ እንደሚሠራ ያረጋግጥላቸዋል።

ይህን ጥቅስ ስንተነትን፣ "እንዲደረግ እናውቃለን" የሚሉትን ቃላት አስተውሉ። የእግዚአብሔርን ባህሀ እና ዓላማውን ማወቁ፣እግዚአብሔር በሮሜ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚያደረገውን ማንኛውንም ነገር ለበጎ የመጠቀሙ እውነታን በተመለከተ በሐዋርያው አዕምሮ ውስጥ የወደቀ ምንም ጥርጣሬ የለም።

በቁጥር 28 ላይ ደግሞ ጳውሎስ እግዚአብሔር በተመረጡ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ሁሉን ነገር ለበጎ እንደሚሠራ

ተናግሯል። ሐዋርያው በዚህ ጥቅስ ላይ የጠቀሳቸው ሰዎች ሦስት የተለያዩ ባህርያት አሏቸው።

በመጀመሪያ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን ይወዳሉ። ልባቸው ለእግዚአብሔር ተሸንፏል። ፍላጎታቸውና ደስታቸው በእርሱ እና በሕይወታቸው ያለው ዓላማ ነው።

ሁለተኛ እነዚህ ሰዎች ተጠርተዋል። ሐዋርያው እነዚህ ሰዎች እንደተጠሩ በመንገር ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ህብረት እንዳላቸው ተናግሯል። እግዚአብሔር በቀጥታ ተናግሯቸዋል እንዲሁም ወደ ዓላማው ጋብዟቸዋል። ድምፁንም ሰምተው አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

በመጨረሻም፣እነዚህ ግለሰቦች የተጠሩት በእግዚአብሔር ዓላማ መሠረት ነው። ይህም ጌታ እግዚአብሔር ለእነዚህ ሰዎች የተለየ እቅድ እንዳለው ይነግረናል።

ጳውሎስ እዚህ እየጠቀሰው ያለው ሰው የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰምቶ በፍቅር ምላሽ የሰጠ እና በታማኝነት ለህይወቱ ወይም ለህይወቷ ላለው ዓላማ ራሱን የሰጠ/ች ነው። ሐዋርያው “ነገር ሁሉ ለበጎ ይደረጋል” ያለው ለዚህ ሰው ነው።

ጳውሎስ ሁሉም ነገር ለበጎ እንደሚሠራ ሲናገር ሁሉም ነገር ቀላል እንደሚሆን መናገሩ አልነበረም። "ነገር ሁሉ" የሚሉትን ቃላት በሚጠቀም ጊዜ ቀላል እና ከባድ ስለሆነው ይናገራል። እንዲሁም ስለ በረከትና ስደቱ ይናገራል። ጳውሎስ በህይወቱ እና በአገልግሎቱ ታላቅ ስቃይ ደርሶበት ነበር። ዳሩ ግን የተገነዘበው፣ ጌታ እግዚአብሔር ያጋጠሙትን ፈተናዎች በጳውሎስ እና በጳውሎስ ህይወት ውስጥ ዓላማውን ለመፈጸም

እንደተጠቀመበት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን በመስበኩ ምክንያት እስር ቤት ከታሰረ በኋላ ለፊልጵስዩስ ሰዎች እንዲህ ሲል ጽፎላቸው ነበር፡

*12 ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። 13 ስለዚህም እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንዲሆን በንጉሥ ዘበኞች ሁሉና በሌሎች ሁሉ ዘንድ ተገልጦአል፥ 14 በጌታም ካሉት ወንድሞች የሚበዙት ስለ እስራቴ ታምነው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲነግሩ ያለ ፍርሃት ከፊት ይልቅ ይደፍራሉ። (ፊልጵስዩስ 1)*

እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም አሳዛኝ የሚመስለውን ነገር እየተጠቀመበት እንደሆነ ጳውሎስ ተረድቷል። ወደ ወህኒ መወርወሩ ጳውሎስ ለንጉሡ ዘበኛ ወንጌልን እንዲናገር በር ከፍቶለታል ብቻ ሳይሆን ሌሎች አማኞች በእምነታቸው እንዲቆሙ የበለጠ እምነት ሰጥቷቸዋል። በዚህም ሐዋርያው ታላቅ ደስታን አግኝቷል።

ሐዋሪያው ዮሐንስ እንዲህ ሲል ይጽፋል፡

*4 ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና። (1ኛ ዮሐንስ 4)*

የጠራን እግዚአብሔር በዙሪያችን ካሉ ጠላቶች ይበልጣል። እሱ በኛ ላይ ከተወረወረው ክፉ ነገር ሊጠብቀን ብቻ ሳይሆን

ጠላት ለጉዳት ያሰበውን በህይወታችን ውስጥ ዓላማውን ለመፈጸም ሊጠቀምበት ይችላል።

ዮሴፍን ለባርነት የሸጡት ወንድሞቹን ሲናገር እንዲህ ይላቸዋል:

*20 እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው። (ዘፍጥረት 50)*

የዮሴፍ ወንድሞች ለባርነት ሲሸጡት፣የእግዚአብሔር እጅ ክፉ ሴራቸውን ወደ መልካም ነገር እንዴት እንደሚለውጥ ፈጽሞ ሊገነዘቡት አይችሉም ነበር። ዮሴፍ በግብፅ ስልጣን በመያዝ እስራኤልን ከረሃብና ከሞት ለማዳን የእግዚአብሔር መሳሪያ ሆነ።

ጴጥሮስ የጴንጤቆስጤ በዓልን ለማክበር በኢየሩሳሌም ለተሰበሰቡት ሰዎች ሲሰብክ እንዲህ አለ፡

*36 እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ። (ሐዋ 2)*

የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን በመስቀል ላይ ገደሉት። ዳሩ ግን ጴጥሮስ ክፉ ድርጊታቸው የክርስቶስን መንግስት ለማራመድ ብቻ እንዳገለገለ ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከኃጢአት ነጻ ለማውጣት የኢየሱስን ስቅለት ተጠቅሟል። የሰቀሉት ሰው ጌታ እና መሲሑ ክርስቶስ መሆኑን አስመስክሯል። እርሱ የሞትን ኃይል ሰብሮ የኃጢአታችንን

ዋጋ ከፈለ። የዚያን ጊዜ መሪዎች በጌታችን ላይ ያደረጉትን የጭካኔ ተግባር እኛን ለማዳን ተጠቅሞበታል።

ከሚገጥሙን ሁኔታዎች ይልቅ እግዚአብሔር ትልቅ ነው። ጠላት እኛ ላይ የሚያደርሰውን በመውሰድ ዓላማውን ለማስፈጸም ሊጠቀምበት ይችላል። ሊጠብቀን እና የሚሆነውን ሁሉ በመጠቀም መንግስቱን ለማራመድ እና በእኛ እና በውስጣችን ተልዕኮውን ለመፈጸም በጠራን እግዚአብሔር ትምክህት ሊኖረን ይችላል።

እግዚአብሔር ለራሳችን እንድንከላከል አይተወንም። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ይኖራል። በጥልቅ መቃተት ይማልድልናል። የሚገጥሙን ፈተናዎች ሁሉ ለበጎነት ይጠቅሙናል። የምናልፍበት ሥቃይ ሁሉ ያጠራናል። የእግዚአብሔር መገኘት በሚያጋጥሙን ነገሮች ሁሉ አብሮን ይሆናል፣ እያንዳንዱን ፈተና እንዲባርከን እና ማንኛውንም ህመም ደግሞ እኛን ለማጎልበት እና ወደ ራሱ እንድንቀርብ ይጠቀምበታል። በዚህ ውብ ቃል ኪዳን ውስጥ ትልቅ ማረጋገጫ አለን።

**ለምልከታ**:

ሮሜ 8፡28 ሁሉንም ሰው ይመለከታልን? ይህ ቃል የተገባለት ሰው ምን ዓይነት ባህርያት አሉት?

በእግዚአብሔር መጠራት ምን ማለት ነው? በህይወታችሁ የእርሱን ጥሪ ሰምታችኋልን?

እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም በሕይወታችሁ ፈተናዎችን የተጠቀመበት እንዴት ነው?

አሁን እያጋጠማችሁ ያለውን ነገር ለበጎ እንዲባርክ በእግዚአብሔር ታምናችኋልን?

በሮሜ 8፡28 እና በምታምኑት የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መሠረት ለፈተናዎች የምትሰጡት ምላሽ ምን ይነግራችኋል?

**ለጸሎት**:

ዛሬ የሚያጋጥሟችሁ ፈተናዎች መልካሙን ለመፈጸም ይጠቀምባቸው እንደሆነ እንዲያረጋግጥላችሁ ጌታን ጠይቁ።

በሚያጋጥሟችሁ ፈተናዎች ሁሉ ሊባርካችሁ ፈቃደኛ በመሆኑ ጌታን አመስግኑት።

እያሳለፋችሁ በነበራችሁበት ነገር ሁሉ ለበጎ ሊጠቅምበት ይችላል ብላችሁ ላላመናችሁበት ጊዜ ጌታ ይቅር እንዲላችሁ ጠይቁት።

አሁን ትንሽ ጊዜ ወስዳችሁ በህይወታችሁ ያለውን ህመም እና ስቃይ ሁሉ ለጌታ አስረክቡ። እግዚአብሔርን ለሚወዱት እና እንደ ሃሳቡ ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲሰራ የገባውን ቃል ለማመን ጸጋን እንዲሰጣችሁ ጠይቁት።

# ምዕራፍ 21 -
# ለአማኙ ያለው የእግዚአብሔር ታላቅ ዓላማ

---

ሮሜ 8:29-30

*29 ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤ 30 አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።*

በቁጥር 28 ላይ ሐዋርያው ለሮሜ ሰዎች እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ ሃሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚሰራ ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር ለጠራቸው ዓላማው ምንድን ነው? ጳውሎስ ይህንን በቁጥር ሃያ ዘጠኝ እና ሠላሳ ላይ እንዲህ ሲል ይመልሳል፡

*29 ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤ 30 አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን*

*ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው። (ሮሜ 8)*

እዚህ ላይ ሐዋርያው ለሮሜ ሰዎች የነገራቸው ነገር እግዚአብሔር ለሚወዱት ሁለት ታላላቅ ዓላማዎች እንዳለው ነው።

*አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤ (ቁጥር 29)*

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች እግዚአብሔር አምላክ ለሕይወታቸው ያለው የመጀመሪያ ዓላማ የልጁን መልክ ይመስሉ ዘንድ እንደሆነ ያስተምራቸዋል።

*29 ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤ (ሮሜ 8)*

አስቀድሞ ማወቅ ማለት አንድ ነገር ከመከሰቱ በፊት ማወቅ ነው። እግዚአብሔር እናንተን እና እኔን የሚያውቀን ገና ሳንወለድ ነው። አስቀድሞ መወሰን ማለት አንድ ነገር ከመፈጠሩ በፊት ስለዚያ ነገር ዓላማ ማንገብ ነው። ባለቤቴ ለአዲሱ የልጅ ልጃችን ኮፍያ ለመስራት የሹራብ መርፌዋን ታነሳ ይሆናል። ምን እንደምታደርግ ስለምታውቅ ሥራውን ከመጀመሯ በፊትም ቢሆን በአዕምሮዋ ውስጥ የተወሰነ ዓላማ አላት።

በመሣፍንት 13 ላይ አንድ መልአክ ለሶምሶን እናት ተገልጦ እንዲህ እንዳላት እናነባለን፡

*3 የእግዚአብሔርም መልአክ ለሴቲቱ ተገልጦ እንዲህ አላት፦ እነሆ፥ አንቺ መካን ነሽ፥ ልጅም አልወለድሽም፤ ነገር ግን ትፀንሻለሽ፥ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ። 4 አሁንም ተጠንቀቂ፤ የወይን ጠጅን የሚያሰክርም ነገር አትጠጪ፥ ርኩስም ነገር አትብዪ። 5 እነሆ፥ ትፀንሻለሽ፥ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ልጁም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናልና በራሱ ላይ ምላጭ አይድረስበት፤ እርሱም እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅ ማዳን ይጀምራል። (መሣፍንት 13)*

የጌታ መልአክ ገና ላልተፀነሰው ልጅ እንዴት እንደተናገረ አስተውሉ። መልዓኩ ስለዚህ ሕፃን መወለድ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ዓላማ ለእናቱ አካፍሏታል። ይህ ገና የሚወለደው ሕፃን "እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅ ማዳን ይጀምራል" (ቁጥር 5) ። እግዚአብሔር ይህን ሕፃን ከመወለዱ በፊት ያውቀዋል ስለሆነም ለዚህ ሕፃን ሕይወት የተለየ ዓላማ ነበረው - አስቀድሞ የታወቀ እና ለተወሰነ የሕይወት ዓላማ እና ኃላፊነት አስቀድሞ ተወስኗል።

እግዚአብሔር አምላክ ለነቢዩ ኤርምያስ ሲናገር እንዲህ አለ።

*5 በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ። (ኤርምያስ 1)*

እግዚአብሔር ለኤርምያስ በተናገረው በእነዚህ ቃላት ውስጥ ሁለት ነገሮችን አስተውሉ። በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር

በማኅፀን ከመፈጠሩ በፊት ያውቀዋል። ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር ከመወለዱ በፊት ለእሱ ዓላማ ነበረው። ኤርምያስ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የታወቀ እና ለአንድ የተለየ ሥራና ዓላማ አስቀድሞ የተወሰነ ነበር።

ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ለገላትያ ሰዎች በሰጠው ምስክርነት እንዲህ ሲል ተናግሯል፡

*15-16 ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፥ (ገላትያ 1)*

ሐዋርያው ከመወለዱ በፊት እግዚአብሔር አስቀድሞ የለየው ስለመሆኑ ለገላትያ ሰዎች እንዴት እንደተናገረ ተመልከቱ። እንዲሁም እግዚአብሔር ጳውሎስን ለአንድ የተለየ ሥራ እንዴት አስቀድሞ እንዳወቀው እና አስቀድሞ እንደወሰነው እንመለከታለን።

በእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የምናየው እግዚአብሔር ከመወለዳችን በፊት እኛን የሚያውቀን ብቻ ሳይሆን ለሕይወታችን ዓላማ እንዳለው ነው። የተፈጠርነው ለዓላማ ነው። ወደዚህ ዓለም የመጣነው በአጋጣሚ አይደለም። በእናታችን ማኅፀን ውስጥ የሰራን (መዝሙረ ዳዊት 139፡13-14 ተመልከቱ) ለህይወታችን ዓላማ ስላለው ነው። በፊታችን ያለውን እያንዳንዱን ቀን ያውቃል፡-

*16 ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ፤ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ። (መዝሙር 139)*

ከእግዚአብሔር የተሰወረ ምንም ነገር የለም። የሕይወታችንን ዝርዝር ሁኔታ ከመገለጡ በፊት ያውቃል። ምንም አያስደንቀውም። ሕይወቴ ዓላማ አለው።

ጳውሎስ የእግዚአብሔር ዓላማ ምን እንደሆነ ለሮሜ ሰዎች ለማስረዳት በቁጥር 29 ይቀጥላል። እግዚአብሔር ሕዝቡ “የልጁን መልክ ይመስሉ ዘንድ” ይፈልጋል።

የኢየሱስን መልክ መምሰል ይበልጥ እንደ እርሱ መሆን ማለት ነው። ይህም የክርስቶስን ምሳሌ ለመከተል ከሰዎች ጥረት ያለፈ ነገርን ይጨምራል። እርሱን የመሰሉ፣በባህርይ እና በልብ ይለወጣሉ። ይህ ለውጥ በውስጣችን ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። እኛን ይወቅሰናል፣ኃጢአትንም ይገልጣል። የኃጢአትን ኃይል ሰብሮ ያድሳል። በአመለካከታችን እና በባህሪያችን ኢየሱስን ይበልጥ እየመሰልን እንሄዳለን።

ይህ ለውጥ እንደ እግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ከውስጥ የሚካሄድ ነው።

እርሱን የመምሰል ሂደት ፈጣን አይደለም። የእግዚአብሔር መንፈስ ከዓመት ዓመት በውስጣችን ይሰራል። እኛን ለመለወጥ የሕይወትን ሁኔታዎች ይጠቀማል። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ጌታን ለሚወዱት እና እንደ ሃሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚሠራ ይናገራል (ሮሜ 8፡28 ተመልከቱ) ። ምክንያቱም ጌታ እግዚአብሔር የሚገጥመንን ነገር ሁሉ የእርሱ ካልሆነው ለመለየት እና የልጁን መልክ እንመስል ዘንድ ስለሚጠቀምበት ነው።

ኢየሱስ ምሳሌ ሆኖ ከእኛ በፊት ሄዷል። የደረሰብንን መከራ ሁሉ እርሱም ተቀብሏል። የዕብራውያን ጸሐፊ እንዲህ ይለናል፡

*15 ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም። (ዕብራውያን 4)*

ጌታ ኢየሱስ ኃጢአትን አሸንፎ ከአብ ጋር ሊሆን ሄደ። ይህን ሲያደርግ እርሱ የመጀመሪያው ነበር፣በእግዚአብሔር የተጠራን እኛም በዚያ ድል ከእርሱ ጋር መቀላቀል እንችላለን። “በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ” ሞቶ በኃጢአት ላይ በድል ተነሳ። በዚህ ድል ልጁን እንከተል ዘንድ ይህ የእግዚአብሔር ልብ ነው። እግዚአብሔር ከመወለዳችን በፊት ያውቀናል፡፡ ከማኅፀን ጀምሮ በዓላማ አወቀን፤ያም የልጁን መልክ እንመስል እና በህልውናው ፊት ህብረት እና የዘለዓለም ሕይወት ይኖረን ዘንድ በኃጢአትና ሞት ላይ ድል በመንሳት እንድንከተለው ነው።

*አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ አከበራቸው። (ቁጥር 30)*

ሁለተኛው ታላቅ የእግዚአብሔር ዓላማ በቁጥር 30 ላይ ነው፡

*30 አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው። (ቁጥር 30)*

የእግዚአብሔር ዓላማ የልጁን መልክ እንመስል ዘንድ መሆኑን ተመልክተናል። ይህ ለውጥ እንዴት ይከናወናል? ጳውሎስ በመጀመሪያ እንደ እግዚአብሔር ዓላማ የተጠሩት እንደሚጸድቁ ይናገራል።

*አጸደቃቸው*

ማጽደቅ ማለት አንድ ሰው ጻድቅ ወይም በጽድቅ ቁመና ላይ መሆኑን ማወጅ ነው። ህጋዊ አዋጅ ነው። በዚህ ሁኔታ፣አሁን እርሱ ወይም እሷ በጽድቅ ቁመና ላይ እንዳሉ ለኃጢአተኛው የተሰጠ የእግዚአብሔር አዋጅ ነው።

በኃጢአት ተወልደን ከእግዚአብሔር ተለይተናል። የኃጢአት ቅጣት ሞትና ከእግዚአብሔር መለየት ነው። ጌታ ኢየሱስ ነፍሱን አሳልፎ በሰጠ ጊዜ ቅጣታችንን ከፈለ። ይህ ክፍያ ዕዳችንን የሚከፍል ነው፣እናም ይቅር ተብለን በእግዚአብሔር ፊት ትክክለኛ አቋም እንዳለን ታውጇል።

ይህ መጽደቅ እኛ በሠራነው ነገር ላይ የተመሰረተ አይደለም። በጥረታችን በእግዚአብሔር ዘንድ በፍጹም የጽድቅ ቁመና ሊኖረን አይችልም። ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ አቋም እንዲኖረን ሁለት ነገሮች መሆን አለባቸው። በመጀመሪያ፣ ዕዳችን በእግዚአብሔር ዘንድ መከፈል ነበረበት። የኃጢአት ቅጣት ሞት ነው። ሁለተኛ፣የእግዚአብሔር ይቅር ባይነት መዘርጋት ነበረበት።

አንድ ሰው በቤተሰባችሁ ውስጥ ያለን የምትወዱትን ሰው ሕይወት እንዳጠፋ አስቡ። ይህ ግለሰብ በህግ ፊት በወንጀል ጥፋተኛ ነው እንዲሁም ለእናንተ ታላቅ የህመም እና

የምትወዱትን ሰው ማጣት ምክንያት ነው:: ይህ ሰው እንዲታደስ ምን መደረግ አለበት? ወንጀለኛው በመጀመሪያ ለሰራው ወንጀል ቅጣቱን መክፈል ይኖርበታል:: መሟላት ያለበት የሕግ ድንጋጌ አለ:: ይህ ማለት የእስር ጊዜ ማለት ሊሆን ይችላል::

ይሁን እንጂ ይህ ግለሰብ በእስር ቤት ውስጥ የሚያስፈልገውን ያህል ጊዜ ታስሮ ከእስር እንደሚፈታ አስቡ:: የእሱ ወይም የእርሷ ዕዳ በሚከፈልበት ጊዜ፤እናንተ በግላችሁ ጥፋቱን ይቅር ለማለት እምቢ ትሉ ይሆናል፡፡ ከዚህ ሰው ጋር ምንም ግንኙነት አይኖራችሁም፤ከዚያም አልፎ እሱን ወይም እሷን የምትቀበሉበት መንገድ በመጸየፍ እና በንቀት ነው:: ምንም እንኳን እሱ ወይም እሷ ለወንጀሉ ሙሉ በሙሉ ቢከፍሉም በማህበረሰባችሁ ውስጥ መኖር ለዚህ ወንጀለኛ ከባድ ነው:: አያችሁ፣የቅጣት ክፍያ በህጋዊ መንገድ ሊመልሰን ይችላል፣ነገር ግን እውነተኛ ነጻነት እንድናገኝ የበደልነውን ሰው ይቅርታ ማግኘት ያስፈልገናል::

ጌታ ኢየሱስ ዕዳችንን መክፈል ብቻ ሳይሆን ከአብ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖር ዋስትና ሰጥቶናል:: ከአብ ጋር ወደነበረን የጠበቀ ግንኙነት ተመልሰናል:: በቀደመው ጊዜ የለዩን ኃጢአቶች አሁን ተረስተዋል:: እርሱን እንዳላሳዘነው ሆኖ በእግዚአብሔር ህልውና ፊት እንኖራለን::

*12 ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፥ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ:: (መዝሙር 103)*

*25 መተላለፍህን፦ ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ ኃጢአትህንም አላስብም:: (ኢሳይያስ 43)*

መጽደቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ከሚኖረን ትክክለኛ የጽድቅ አቋም ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው ህጋዊ እዳችንን በከፈለው በክርስቶስ ሞት እና ኃጢአታችንን ከእንግዲህ ላያስታውስ በመረጠው የአብ የጸጋ ይቅርታ ብቻ ነው። የጠራቸውን ከራሱ ጋር ወደ ትክክለኛው ህብረት መመለስ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው።

### *አከበራቸው*

የእግዚአብሔር ፈቃድ እኛን ይቅር ማለት እና ወደ ህብረታችን መመለስ ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር ወደዚህ ህብረት የሚመጡትንም ማክበር ነው። ጳውሎስ ለሮሜ አማኞች በደካማ እና ኃጢአተኛ አካል ውስጥ እንደሚኖሩ እያሳሰባቸው ነው። የኃጢአት እና ክፉ ፈተናዎች በአዕምሯቸው እና በተግባራቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድሩ ነበር። ከኃጢአተኛ ተፈጥሮ እና ከከበባቸው ክፉት ጋር መታገልን ይቀጥላሉ። ነገር ግን ይህ ሁሉ የሚቀየርበት ቀን እየመጣ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡

*50 ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህን እላለሁ፦ ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፥ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም። 51-52 እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን። 53 ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና። 54 ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው*

*የማይበሰብሰውን ሲለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ፥ በዚያን ጊዜ፦ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል። 55 ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ? (1ኛ ቆሮንቶስ 15)*

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የነገራቸውን አስተውሉ። *ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፤የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን ሊወርስ አይችልም* (ቁጥር 50 ተመልከቱ) ። ይሁን እንጂ ለአማኙ "*ሥጋችንና ደማችን*" የሚለወጥበት ቀን እየመጣ እንደሆነ እየነገራቸው ነው። አሁን የምንኖርበት የሚጠፋው አካል ወደማይጠፋ አካል ይለወጣል። ከ*ሥጋችን* ሰንሰለት እና ከሚፈትነን ኃጢአት ነጻ እንወጣለን። በእግዚአብሔር ህልውና ፊት ሙሉ በሙሉ አዲስ እንሆናለን። አዲስ አካል እንቀበላለን። አዲስ አዕምሮ ይኖረናል። የኃጢአት ተጽዕኖ እና እርግማን ከህይወታችን ሙሉ በሙሉ ይሰበራል፣እንዲሁም እሱ እንዳሰበው በእግዚአብሔር ፊት እንኖራለን፣ ከእርሱም ጋር ፍጹም በሆነ ሕብረት ውስጥ ለዘለአለም እንኖራለን። የተሰጠን የእግዚአብሔር ልብ ከእርሱ ጋር ላለን ኅብረት ማነቆ በሆኑት ዓለማዊ አስተሳሰባችን እና *ሥጋችን* እንዳይገደብ ያደርጋል።

ኢየሱስ በተያዘበት ቀን ሊጸልይ ወደ ጌቴሴማኒ ሄደ። ለደቀመዛሙርቱ ከእርሱ ጋር እንዲጸልዩ በመንገር ከአባቱ ጋር ብቻውን ለመሆን ሄደ። ጸሎቱን ጨርሶ ሲመለስ ተኝተው አገኛቸው። በእለቱ የተናገረውን አድምጡ፦

*41 ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው። (ማቴዎስ 26)*

በሮሜ 7 ላይ ያለውን የሐዋርያውን ቃል አስታውሱ፡-

*በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥23 ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ። 24 እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል? (ሮሜ 7)*

ሐዋርያው ለሞት ከተሰጠ ሥጋው የሚፈታበት ቀን እንደሚመጣ ያውቃል። አንድ ቀን ይቀየራል። ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ይላል፦

*20 እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤ 21 እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር፥ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል። (ፊልጵስዩስ 3)*

ሐዋርያው የሚለወጥበት ቀን እንደሚመጣ ተረድቷል። ከጌታም ኢየሱስ “የከበረ አካል” ይቀበላል።

ሐዋርያው ዮሐንስ ስለዚህ ክብር በ1ኛ ዮሐንስ 3 ላይ እንዲህ ሲል ይናገራል።

*2 ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ*

*እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን:: (1ኛ ዮሐንስ 3)*

ዮሐንስ እንዳለው ለውጦች እየመጡ ነበር:: የእነዚያን ለውጦች ባህሪ ባይገልጽም፣ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ እርሱን እንመስል ዘንድ እንደምንለወጥ ይነግረናል::

ጳውሎስ ይህንን የከበረ ሁኔታ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15 ላይ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲነግራቸው ገልጾታል፡

*42 የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው:: በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤ 43 በውርደት ይዘራል፥ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፥ በኃይል ይነሣል፤ 44 ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል:: ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ:: (1ኛ ቆሮንቶስ 15)*

ኢየሱስ ሲገለጥ እንለወጣለን (1ኛ ዮሐንስ 3፡2) :: ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡42-44 ላይ የማይጠፋውን አካል ለብሰን እንደምንነሳ ይነግረናል። ይህ አካል የከበረ፤ኃይለኛ እና መንፈሳዊ አካል ይሆናል። እነዚህ አካላት እና አዕምሮዎች ከአሁን በኋላ ለኃጢአት የማይገዙ ወይም ተጽዕኖ የማይደረግባቸው ናቸው። ዮሐንስ በራዕይ 21 ላይ እንዲህ ይለናል፡

*4 እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ:: (ራዕይ 21)*

የጠራቸውን ያከብራቸዉ ዘንድ የእግዚአብሔር ዓላማ ነዉ። መሻቱ በኃጢአት የተረገሙትን ሁሉ አስወግዶ ሥጋ እና አዕምሮ ልጁን ኢየሱስን ይመስሉ ዘንድ መለወጥ ነው። ይህ ክብር የሚፈጸመው ጌታ ሲመለስ ነው። እርሱ ሲመለስ እርሱን እንመስላለን (1ኛ ዮሐንስ 3፡2) ። ሥጋችን በትንሳኤ ሲነሳ ተለውጦ ወደ እግዚአብሔር መገኘት ይገባል። በእርግማን የተጎዱት ሁሉ ይጠፋሉ፤እኛ ደግሞ እንደ አዲስ ፍጥረት በከበረ አካል ውስጥ ለዘላለም በጌታ በእግዚአብሔር ፊት እንኖራለን። ለሚጠራቸው ሰዎች ይህ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው።

**ለምልከታ**:

ጌታ እግዚአብሔር ከመወለዳችሁ በፊት እናንተን በማወቁ እውነታ ምን ማጽናኛ አገኛችሁ?

እግዚአብሔር ለህይወታችን እቅድ ማውጣቱ ነፃነታችንን ያስወግዳል ወይንስ ምክንያት እና የህይወት ዓላማ ይሰጠናል?

የክርስቶስን መልክ መምሰል ምን ማለት ነው? ይህ በህይወታችሁ ውስጥ እንዴት እየሆነ ነው? የክርስቶስን መልክ መምሰል የሚያስፈልጋቸው በህይወታችሁ ውስጥ የትኞቹ አከባቢዎች ናቸው?

ሁለቱም ማለትም ህጋዊ ክፍያ እና የይቅርታ አስፈላጊ ክፍሎች በመጽደቅ ውስጥ የሚገኙት ለምንድ ነው?

በምድራዊ ሥጋችን ውስጥ ስንኖር ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ምን እንቅፋት ያጋጥመናል? ሥጋዊ አዕምሯችን ከፈጣሪያችን ጋር እንዳንቀራረብ የሚከለክለን እንዴት ነው? መክበር ይህን ሁሉ እንዴት ይለውጠዋል?

**ለጸሎት:**

ከመወለዳችሁ በፊት ስላወቃችሁ እና ለህይወታችሁ ዓላማ ስላለው ጌታን አመስግኑት፡፡

በዓላማ ስለተወለዳችሁ ጌታ አመስገኑ፡፡

እኛን ለማጽደቅ እና ለማክበር፣እንዲሁም የልጁን መልክ እንመስል ዘንድ የሚለውጠውን የእግዚአብሔርን እቅድ ለመመልከት ትንሽ ጊዜ ውሰዱ፡፡ ለዚህ አስደናቂ ዓላማ ጌታን አመስግኑት፡፡ በህይወታችሁ የሚያደርገውን ትቀበሉ ዘንድ ጸጋን እንዲሰጣችሁ ጠይቁት፡፡

ይህን ምድራዊ አካል አውልቃችሁ ከኃጢአት እርግማን የጸዳ አዲስ አካል የምትለብሱበት ቀን ስለሚመጣ ጌታን አመስግኑት፡፡

ባለፉት ዓመታት በህይወታችሁ ውስጥ ስላለው የእግዚአብሔር ስራ ለማሰላሰል ትንሽ ጊዜ ውሰዱ:: እየለወጣችሁ ስለሆነ ጌታን አመስግኑት::

## ምዕራፍ 22 -

## ማን ይቃወመናል?

---

ሮሜ 8:31-34

*31 እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? 32 ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም? 33 እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው? 34 የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። (ሮሜ 8)*

ሐዋርያው በሚቀጥለው ክፍል ላይ ሲጀምር ሁለት ጥያቄዎችን ይጠይቃል፡

*31 እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? (ሮሜ 8)*

በቁጥር 31 ላይ የሚጠይቀው የመጀመሪያው ጥያቄ "እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን?" የሚለው ነው:: ይህ ወሳኝ ጥያቄ ነው:: ከዘላለም ሲኦል ያዳናችሁን ምን ልትሉት ትችላላችሁ? በህይወታችሁ መልካም ነገርን ለማሳካት ያጋጠማችሁን እያንዳንዱን ሁኔታ እና አሳዛኝ ገጠመኝን ያቀነባበረውን ምን ልትሉት ትችላላችሁ? ስለ እናንተ የሚራራው እና ስለሚስፈልጋችሁ ነገር በጥልቅ መቃተት በአብ ፊት ስለሚማልደው ምን ልትሉ ትችላላችሁ? በእናንተ ፈንታ በፈቃዱ የመስቀልን ሞት የተቀበለውን ምን ልትሉ ትችላላችሁ? አሁን እንኳን በሰማይ ከእርሱ ጋር ለዘላለም ትሆኑ ዘንድ ሥፍራን ስለሚያዘጋጅላችሁ ምን ልትሉ ትችላላችሁ?

የነገሩን እውነታ ለመግለጽ የሚሆን ቃል የለንም:: ጌታ ለእኛ ስላደረገው ርህራሄ እና ፀጋ ለማመስገን ቃላቶች በቂ አይደሉም:: ለእርሱ ያለብንን ዕዳ ለመክፈል የራሳችን የህይወት መስዋዕትነት በቂ አይደለም:: ጸጋ በዝቶልናል:: እሱ ላደረገው ነገር ለዘለአለም መክፈል አንችልም:: ምን ማለት እንችላለን? ጥልቅ በሆነ እና በግላዊ መንገድ ወደ እኛ ስለደረሰው ጌታ እግዚአብሔር ያለንን ጥልቅ ምስጋና የሚገልጽ ምን ማድረግ እንችላለን? እሱ የሰጠን ለእኛ የተገባ አይደለም:: እንደዚህ አይነት ትኩረት እና እንክብካቤ በፍጹም ሊገባን አይችልም::

ቁጥር 31 ላይ ያለው ሁለተኛው ጥያቄ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?" የሚለው ነው:: በመጀመሪያ ይህንን ጥያቄ ከእግዚአብሔር ማንነት አንጻር አስቡት:: ፍጥረት ሁሉ ስለሚኖረው ሕይወት እግዚአብሔር ባለውለው ነው:: የምንተነፍሰው እያንዳንዱ እስትንፋስ በእርሱ ምክንያት

ነው፡፡ ለአፍታም ቢሆን ጀርባውን ቢያዞርብን ለዘላለም የጠፋን እንሆን ነበር፡፡

ከእኛ ጋር የሚቆመው እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለበጎ ለማድረግ ቃል ገብቷል፡፡ ከክፉ ጠላታችን ይበልጣል፡፡ መንገዱን አንረዳውም ነገር ግን ዓላማው ፈጽሞ አይሸነፍም፡፡ ይህ እግዚአብሔር እንደሆነ ተናግሯል፡፡ እኛን ለመጠበቅ እና ለመከላከል ቃል ገብቷል፡፡ በእርሱ ልንታመን እንችላለን፡፡

ጳውሎስ የሮሜ ሰዎችን ለማስታወስ በቁጥር 32 ላይ ይቀጥላል፡-

*32 ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም? (ሮሜ 8)*

"ለእኛ" የሆነው እግዚአብሔር የራሱን ልጅ በእኛ ፈንታ ይሞት ዘንድ በማቅረብ ፍቅሩን ያሳየ ነው፡፡ አብ የገዛ ልጁን በመስጠት ለእኛ ለማድረግ የፈቀደውን ሁሉ አሳይቷል፡፡ ለእርሱ እጅግ ውድ የሆነውን የገዛ ልጁን አሳልፎ ሰጠ፡፡ ይህን ሲያደርግ ለእርሱ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆንን ገልጿል፡፡

ጳውሎስ በቁጥር 32 ላይ ጌታ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ለመስጠት ካልሰሰተ “ከእሱ ጋር ሁሉን በጸጋ እንዴት አይሰጠንምን?” በማለት የሮሜ ሰዎችን በማስታወስ ይቀጥላል፡፡ ይህን ጥቅስ ስንተረጉም መጠንቀቅ አለብን፡፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን መስዋዕት ለማድረግ ከፈቀደ የማይሰጠን ምንም ነገር የለም እያሉ ይህን ጥቅስ ባልተገባ መንገድ የሚጠቀሙ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የምንፈልገውን ሁሉ

ልንጠይቅ እንችላለን እግዚአብሔርም ደግሞ ይሰጠናል። ይሁን እንጂ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ችላ ሊባሉ የማይችሉ ሁለት ቃላት አሉ። በቁጥር 32 ላይ ጳውሎስ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር "ከእርሱ ጋር" እንደሚሰጠን ሲነግረን "ለገዛ ልጁ ያልራራለት… ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?" ይላል፤ በሌላ አነጋገር፣ እዚህ እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ነገሮች ከልጁ ጋር አብረው ይመጣሉ ስለሆነም በልጁ በኩል ካለው ዓላማ ጋር የሚስማሙ ናቸው።

እግዚአብሔር በልጁ በኩል ያለው ዓላማ ምንድን ነው? ሮሜ 8፡29 የእርሱን መልክ እንድንመስል ነው ይለናል። እግዚአብሔር ልጁን ሲሰጠን፤የእርሱን መልክ እንመስል ዘንድ ነው እንዲሁም ባህሪውን ለዓለም ለማሳየት የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሰጠናል። በዚህ ዓለም በቅድስና እና እግዚአብሔርን በመምሰል ለመኖር የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ከክርስቶስ ጋር ይመጣል። እንድንጸድቅ እና እንድንከበር የሚያስፈልገን ሁሉ ከእርሱ ጋር ይመጣል። በዚህ ቁጥር ጳውሎስ የሚያስተምረን የተስፋ ቃል እንደ እግዚአብሔር ልጆች እና እንደ እግዚአብሔር ተወካዮች በዚህ እና በሚመጣው ሕይወት ለመኖር ምንም እንደማይጎድለን ነው። እግዚአብሔር ወደዚህ ምድር እንድትሄዱ በጠራችሁ ቦታ ሁሉ፣ የእርሱን መገኘት እና ብርታት ታገኛላችሁ። ምንም አይነት ውሳኔ ማድረግ ካለባችሁ ጥበቡን ታገኛላችሁ። ምንም አይነት ፈተና ቢያጋጥማችሁ የእርሱን ጥንካሬ ታገኛላችሁ። የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ያደርግ ዘንድ የጠራውን ለመፈጸም ሃብት አያጣም። በዚህ ተስፋ ውስጥ ምንኛ ማጽናኛ ማግኘት ያስፈልገናል!

ጳውሎስ በቁጥር 33 ላይ ሌላ ጥያቄ ይጠይቃል፡

*33 እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው? (ሮሜ 8)*

እያንዳንዳችን በሕይወታችን እንወድቃለን። እግዚአብሔር ለኛ ካስቀመጠው ክብር እንጎድላለን። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ለእርሱ ለመኖር የሚያስፈልገንን ሁሉ ቢሰጠንም፣ ሁልጊዜ እነዚያን ሃብቶች አንይዝም። ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስን አላውቀውም ብሎ ክዶት ነበር። ዳዊት በዝሙትና በመግደል ኃጢአት ወድቆ ነበር።

ምናልባት በዚህ ዓለም ፈተና ውስጥ ከጌታ ርቀው የተቅበዘበዙ ሰዎችን አግኝታችሁ ይሆናል። እነዚህ ሰዎች በክርስትና ሕይወታቸው ድል ለማድረግ እግዚአብሔር ቃል የገባላቸውን ሃብቶች አልያዙም። እንደ አማኞች ከጌታ ሃሳብ ልንሰናከል እንችላለን፡፡ አዎ በእርግጠኝነት እንችላለን! ሁላችንም እንደ አማኝ ማድረግ የማይገባንን አድርገናል። በሃሳብም ሆነ በተግባር ጥፋተኞች ነን። ማናችንም ብንሆን ፍጹም የሆነ ሕይወት አልኖረንም።

ይሁን እንጂ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በቁጥር 33 ላይ “እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?” ሲል የነገራቸውን አስተውሉ። ጳውሎስ እዚህ ጋር በሕግ ቃላት ይናገራል። በማንኛውም ፍርድ ቤት በአንድ ግለሰብ ላይ ክስ ሲቀርብ ሁለት ነገሮች መፈጸም አለባቸው። በመጀመሪያ ክሱ መረጋገጥ አለበት። ሁለተኛ ጥፋተኛ ከሆነ፣ጥፋተኛው ለፈጸመው ወንጀል ቅጣቱን መክፈል ይኖርበታል።

ስለ ጥፋታችን ምንም ጥያቄ የለም። አስቀድሜ እንዳልኩት፣ ጌታን ከመከተል ብዙ ጊዜ ወድቀናል እናም ለሕይወታችን ካለው ክብር ጎድለናል። ቅጣቱን በተመለከተ ግን ተከፍሏል። ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞቱ የኃጢአቴን ቅጣት ሙሉ በሙሉ ከፍሏል። ከዚህ በላይ መደረግ ያለበት ምንም ነገር የለም - ነጻ ነኝ።

ጳውሎስ የሚያጸድቀው እግዚአብሔር መሆኑን ለሮሜ ሰዎች በቁጥር 33 ላይ ያስታውሳቸዋል። በሌላ አነጋገር፣ እግዚአብሔር በእርሱ ዘንድ ትክክለኛ የጽድቅ ቁመና ይኖረን ዘንድ ሰጥቶናል። ይህ የሆነው እኛ ጥፋተኞች ሳለን ልጁ ቅጣታችንን ስለሸፈነ ነው። አሁን በጌታ በኢየሱስ ሥራ ተሸፍነን ያለፈው፣የአሁን እና የወደፊቱን ኃጢአታችንን ሁሉ ይዘን በእግዚአብሔር ፊት ቆመናል። እኛ ፍጹማን አይደለንም ነገር ግን ይቅር ተብለናል። የዓለሙ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የክርስቶስን ሥራ ለኃጢአቴ ሁሉ ክፍያ አድርጎ ለመቀበል የተሰጠውን ውሳኔ አጽድቆታል። እግዚአብሔር በልጁ ለእኛ ሲል ባደረገው ሥራ በትክክለኛ የጽድቅ ቁመና ላይ መሆናችንን ስላወጀ አሁን ምንም ዓይነት ክስ በእኛ ላይ አይጸናም።

ጳውሎስ በቁጥር 33 ላይ ክስ ስለማቅረብ ይናገራል። ስለ ኩነኔ ለመናገር ወደ ቁጥር 34 ይሄዳል። ኩነኔ ወንጀለኛ በሆኑ ሰዎች ላይ የሚደርስ ቅጣት ነው። "የሚኮንነው ማን ነው?" ጳውሎስ በቁጥር 33 ላይ ይጠይቃል። በኃጢአት ምክንያት ጥፋተኞች መሆናችን እውነት ነው፣ነገር ግን ምንም ዓይነት ፍርድ ሊወሰንብን አይችልም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በቀሪው ቁጥር 34 ላይ ነው፡

*34 የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። (ሮሜ 8)*

የኃጢአታችን ቅጣት ተከፍሏል። ቅጣቱ በተፈጸመበት ሰው ላይ ምን ዓይነት ፍርድ ሊቀርብ ይችላል? ቅጣቱ አስቀድሞ የተከፈለለትን ሰው እንዴት ልትቀጡት ትችላላችሁ? የኃጢአታችን ቅጣት ሞት ነበር፣ነገር ግን ፍርዱ ኢየሱስ በስሜ ፈጽሞታል። ከኩነኔ ነጻ ነኝ።

ኢየሱስ የሞተው የእኔን ኩነኔ ለመሸፈን ብቻ ሳይሆን ለእኔ ሊማልድ ከሙታንም ተነስቶ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጡን አስተውሉ (ቁጥር 34) ። እዚህ ላይ ጳውሎስ ልናልፋቸው የማንችላቸውን አንዳንድ ጉልህ መልዕክቶች እየሰጠን ነው።

ጌታ ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ከሞተ በኋላ ከሞት ተነሣ። ሞት ሊይዘው አልቻለም። ኃጢአታችንን ወደ መቃብር ወስዶ ሞትን አሸንፏል። ኃጢአትና ሞት አላሸነፉትም።

ኃጢአትና ሞት ቢያሸንፉት ምን ተስፋ ይኖረን ነበር? ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ ቢቀር ኖሮ፤በሞት ላይ ምን እምነት ይኖረን ነበር? ዳሩ ግን ኢየሱስ ከዚያ መቃብር በመነሳት፣በኃጢአት ላይ ድል መንሳት እና ውጤቱን ማግኘት እንደሚቻል አረጋግጦልናል። ትንሣኤ ክርስቶስ በኃጢአትና በውጤቶቹ ላይ ድል እንዳደረገ ያሳያል።

ነገር ግን ከትንሳኤ ማረጋገጫው ባሻገር፤ጳውሎስ ከሞት ከተነሳ በኋላ፣ ጌታ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ለመቀመጥ እንደሄደ ይነግረናል። እንግዲህ ይህ በድጋሚ አስፈላጊ ነጥብ

ነው። ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ለመሆን ተነሳ። ወደ አብ መሄድ ብቻ ሳይሆን በአብ ፊት በክብር ወንበር ላይ ተቀመጠ። በቀኝ መቀመጥ በክብር ቦታ መቀመጥ ማለት ነው። ይህ ቦታ የተሰጠው በኃጢአትና በሞት ላይ ስላለው ድል ነው። የሰው ሁሉ ዳኛ የሆነው ልጁ ስለ ኃጢአታችን የከፈለውን መስዋዕት ተቀብሏል። ኢየሱስ አሁን በክብር ወንበር መቀመጡ የእርሱ መስዋዕትነት ውጤታማ እንደነበረ እና ኃጢአታችንን እንደሚሸፍን ያረጋግጣል። ያ ዋጋ ተከፍሎ እና ዳኛው የልጁ የሆኑትን ሁሉ ወክሎ እና ያንን ክፍያ ሁሉ ተቀብሎ ሳለ ማን በኃጢአት ሊፈርድብን ይችላል?

ሐዋርያው ጳውሎስ በቁጥር 34 ላይ አንድ የመጨረሻ ነጥብ አስቀምጧል። ለሮሜ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ስለ እነርሱ እንደሚማልድ ይነግራቸዋል። ጳውሎስ እዚህ ህጋዊ ቃል ይጠቀማል። ኢየሱስ ስለ እኛ በህጋዊ መንገድ በአብ ፊት ይማልዳል። ተስፋ የምናደርገው በእርሱ አማላጅነት ነው። በመስቀሉ ላይ የተሰራው ሥራ በአብ እና በእኛ መካከል ባለው ክፍተት ድልድይ ነው። ምልጃው በቃላት ብቻ ሳይሆን በራሱ ሕይወት ነው። የኛን ጉዳይ በአብ ፊት ለመማለዱ መሰረት የሆነው ሞቱና ትንሳኤው ነው። የምንሰራው ኃጢአት ሁሉ በክርስቶስ መስቀል ፊት ቆሞአል። በዚያም ኃጢአት በኛ ላይ ያለውን ስልጣን እና ኃይል ገፎታል።

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ማንም ሊከሳቸው እንደማይችል ሲነግራቸው ፍጹም ሕይወት ኖረዋል ማለቱ አልነበረም። ኃጢአታቸው ሁሉ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሰራው ሥራ ምክንያት የተሸፈነ መሆኑን እየነገራቸው ነበር። ኢየሱስ ቅጣታቸውን ስለከፈለ ከክሳቸው እና ከኃጢአታቸው ቅጣት ነጻ ሆነዋል።

ኢየሱስ የኃጢአትን ችግር ተመልክቷል። ኃጢአትን እሠራለሁ፣ ነገር ግን ኃጢአቶቼ ሁሉ (ያለፉት፣የአሁን እና ወደፊት) በኢየሱስ የመስቀል ሥራ ተሸፍነዋል። በዚህ ዓለም እስካለሁ ኃጢአት ልሰራ እችላለሁ፣ነገር ግን ኃጢአቶቼ እና ድክመቶቼ ከእግዚአብሔር ፈጽሞ አያርቁኝም። የኢየሱስ ሥራ ምንም ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም ሊለየኝ እና ሊኮንነኝ እንደማይችል ያረጋግጣል። የኢየሱስ ሥራ የእርሱ ለሆኑት ሁሉ የኃጢአትን ፍርድ ያስወግዳል።

ኃጢአታችሁ እንዲሸፈን በመስቀሉ ላይ መታመን ትችላላችሁ? በዚህ ህይወት ትወድቃላችሁ ነገር ግን መስቀሉ ከእነዚያ ውድቀቶች ሁሉ ይበልጣል። የምጸጸትባቸው ነገሮች አሉ ነገር ግን መስቀሉ ከእነዚያ ጸጸቶችም ይበልጣል። የሰራሁት ወይም የምሰራው ኃጢአት ሁሉ በኢየሱስ መስቀል ተሸፍኗል። ፍፁም አይደለሁም ነገር ግን ከኩነኔ ነጻ ነኝ። ዛሬ ወደ መስቀሉ ትመጣላችሁን? ለጌታ ኢየሱስ እና ለሥራው ትገዛላችሁን? ወደ ክርስቶስ ለሚመጡት ሁሉ የሚሰጠውን ይቅርታ ትቀበላላችሁን?

ዛሬ አማኝ ከሆናችሁ፤በክርስቶስ የተቀበላችሁትን የስጦታ ታላቅነት ለማሰላሰል ትንሽ ጊዜ ወስዳችሁ ታስባላችሁን? በዚህ የክርስቶስ ሥራ የእናንተ በሆነው ነጻነትና ድል ትኖራላችሁን? ይህንን ሥራ እንደ ቀላል ነገር ልንመለከተው አንችልም። ሐዋርያው ዮሐንስ በክርስቶስ ላለን ለዚህ ተስፋ ራሳችንን ለማንጻት ብቸኛው ምክንያታዊ ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚገባ ይነግረናል፡-

*3 በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል። (1ኛ ዮሐንስ 3)*

የይቅርታችንን ዋጋ እና የይቅርታውን መጠን ስናውቅ ትክክለኛ ምላሻችን በተስፋው ድል ውስጥ መኖር ብቻ ነው። የእኛ ብቸኛው ምክንያታዊ ምላሽ እራሳችንን ማንጻት እና አሁን ባለን ድል ውስጥ መኖር ነው። ከክርስቶስ ጋር ሁሉን በጸጋ በሚሰጠን በእርሱ በኩል በይቅርታ መታመን ብቻ ሳይሆን የእኛ በሆነው ድል እንድንመላለስ እግዚአብሔር ጸጋን ይስጠን።

**ለምልከታ፡**

እግዚአብሔር ልጁን መሥዋዕት ለማድረግ ፈቃደኛ መሆኑ ለእኛ ስላለው ጥልቅ ፍቅር ምን ይነግረናል?

ጳውሎስ ሁሉም ነገር ከክርስቶስ ጋር እንዳለን ሲነግረን ምን ማለቱ ነው? ይህ ማለት የምንፈልገውን ነገር ማግኘት እንችላለን ማለት ነውን?

በዚህ ህይወት የኃጢአትን ውጤት በመቀበል እና በሚመጣው ዘመን ለእነዚያ ኃጢአቶች ቅጣትን በመቀበል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

የክርስቶስ ትንሣኤ የሐጢአትን ይቅርታ የሚያረጋግጥልን እንዴት ነው?

ኃጢአታችሁ ሁሉ ተሽፍኗል ማለት ምን ማለት ነው?

**ለጸሎት:**

የኃጢአታችሁ ቅጣት እንደተከፈለ (ያለፈው፣የአሁን እና ወደፊት) ለማሰብ ትንሽ ጊዜ ውሰዱ። ለዚህ ታላቅ ይቅርታ ጌታን አመስግኑ።

በኃጢአትና በሞት ላይ በድል በመነሳቱ ጌታን አመስግኑት፤ይህም እኛ ይህንን ድል እናውቅ ዘንድ ተስፋ እና እምነት ይሰጠናል።

መዳናችሁ በእናንተ ላይ የተደገፈ ሳይሆን ኢየሱስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ሥራ በመሆኑ ጌታን ለማመስገን ትንሽ ጊዜ ወሰዱ።

ይቅር ይለናል ብቻ ሳይሆን በድል እና በመታዘዝ እንድንኖር ሁሉንም ነገር በክርስቶስ ስለሰጠን ጌታን አመስግኑት። በድል እንድትኖሩ ጌታ እንዲረዳችሁ ጠይቁት።

## ምዕራፍ 23 -

## ማን ይለየናል?

---

ሮሜ 8:35-39

*35 ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን? 36 ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው። 37 በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። 38 ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥ 39 ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ። (ሮሜ 8)*

በሮሜ 8፡33-34 ጳውሎስ ጌታ ኢየሱስ በሰራው ሥራ ምክንያት በእግዚአብሔር ዘንድ ሕጋዊ ማረጋገጫ እንዳላቸው ለሮሜ ሰዎች ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ሥራ የተነሳ በእርሱ ዘንድ ትክክለኛ የጽድቅ ቁመና እንዳላቸው በመግለጽ ማንም ክስ ወይም ፍርድ ሊያመጣባቸው እንደማይችል ያስተምራቸዋል። በሚቀጥሉት ጥቅሶች ጳውሎስ ስለ ኃጢአታችን ክፍያ ሳይሆን ነገር ግን ክፍያውን ስለፈጸመው ፍቅር ይነግረናል። እንዲህ በጥያቄ ይጀምራል፡

*35 ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? (ሮሜ 8)*

ጳውሎስ እዚህ እየተናገረ ያለው ለክርስቶስ ስላለን ፍቅር ሳይሆን እርሱ ለእኛ ስላለው ፍቅር መሆኑን አስተውሉ። ለክርስቶስ ያለን ፍቅር ሊለያይ ይችላል። ለእርሱ ያለን ፍቅር መሆን የሚገባውን ያህል የማይሆንበት ጊዜ አለ። ለዓለም ወይም ለራሳችን ያለን ፍቅር ለክርስቶስ ካለን ፍቅር የሚበረታበት ጊዜ አለ። በብሉይ ኪዳን ያለው የእስራኤል ታሪክ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለፈጣሪያቸው ስላላቸው የሚናወጥ ፍቅር ነው። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ሕዝቡን በመንፈሳዊ ምንዝርና ይከሳቸው ነበር። ሌሎች አማልክትን ለማገልገል ፊታቸውን ከአምላካቸው መልሰው ነበር። በዚህ በፈተና በተሞላ ዓለም ውስጥ በርካታ ነገሮች ለክርስቶስ ያለንን ፍቅር እንድንቀንስ ምክንያት ይሆናሉ።

ጳውሎስ እዚህ ላይ እየተናገረ ያለው ለክርስቶስ ስላለን ፍቅር አይደለም። የሐዋርያው ትኩረት ክርስቶስ ለእኛ ባለው ፍቅር ላይ ነው። ክርስቶስ ለእኛ ያለው ፍቅር ለእርሱ ካለን ፍቅር በጣም የተለየ ነው። በቁጥር 35 ላይ ጳውሎስ ለእኛ ስላለው ዘላለማዊ የክርስቶስ ፍቅር የሚነግረንን አስተውሉ፡

*35 ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?*

*ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።*

ጳውሎስ በዚህ ጥቅስ ውስጥ በርካታ ችግሮችን ይጠቅሳል። ሐዋርያው ከመዝሙር 44፡22 በመጥቀስ "ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን" የሚለውን፤ፈተናዎችን የእግዚአብሔር ተከታይ ከመሆን ጋር ያገናኛቸዋል (ቁጥር 35፤ በሌላ አነጋገር፣አንዳንድ ጊዜ በመከራ ውስጥ የምናልፈው የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ነው። ጳውሎስ በዚህ ምድር ላይ እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር የሚፈልጉ እንደሚሰደዱ ለጢሞቴዎስ ይነግረዋል:

*12 በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ። (2ኛ ጢሞቴዎስ 3)*

የዕብራውያን ጸሐፊ ታላላቅ የእምነት ወንድና ሴቶችን ሲገልጽ እንዲህ ይላል፦

*37 በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፥ ተፈተኑ፥ በመጋዝ ተሰነጠቁ፥ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፥ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ 38 ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጕድጓድ ተቅበዘበዙ። (ዕብራውያን 11)*

እነዚህ አማኞች ችግረኞች ነበሩ። በዋሻ፣በረሃና ተራራ ውስጥ የፍየልና የበግ ቆዳ ለብሰው ይኖሩ ነበር። ኢየሱስ የራሱን ሕይወት በሚከተለው መንገድ ይገልጸዋል፡

*20 ኢየሱስም፦ ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው። (ማቴዎስ 8)*

በሁሉም እድሜ ያሉ አማኞች ለሚያምኑት እምነት ህይወታቸውን አሳልፈው መስጠት ነበረባቸው። አንዳንዶች

ለቀጣዩ ቀን ምንም ዋስትና ሳይኖራቸው በድህነት ኑሮ ውስጥ አልፈዋል፡፡

እዚህ ላይ ጳውሎስ የጠየቀው ጥያቄ ይህ ነው፡ እነዚህ ፈተናዎች ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን ይችላሉ፡፡ እነዚህ ፈተናዎች እርሱ ከእንግዲህ እንደማይወደን ያሳያሉን? ጳውሎስ በቁጥር 37 ላይ ይህንን ይመልሳል፡-

*37 በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን፡፡ (ሮሜ 8)*

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ኢየሱስ ስለሚወዳቸው እነዚህን ተግዳሮቶች ማሸነፍ እንደሚችሉ ይነግራቸዋል፡፡ በመንገዳችን የሚመጣውን ስደት እና ፈተና ማለፍ የምንችለው በእርሱ እና በእርሱ ጥንካሬ ነው፡፡ ራሳችንን በችግር ውስጥ ስናገኝ አይተወንም፡፡ እርሱ ከእኛ ጋር ቆሞ በሁሉም ይደግፈናል፡፡ በህይወት የሚገጥማቸውን ፈተናዎችን የተጋፈጡ ሰዎች ይህንን መገኘት በሚያስደንቅ ሁኔታ ያውቃሉ፡፡ በዚህ ፍቅር የተነሳ የተጽናኑ እና ድፍረት የተሰጣቸው ናቸው፡፡

በተጨማሪም ጳውሎስ በቁጥር 37 ላይ ለሮሜ ሰዎች “ከአሸናፊዎች የሚበልጡ” ስለመሆናቸው እንደነገራቸው አስተውሉ፡፡ ድላቸው ታላቅ ድል ነበር፡፡ ለፈተናቸው

ከሚያስፈልጋቸው በላይ ብርታትና ኃይል ነበር። የጌታ ደስታ፣ የጌታ ኃይል እና ድጋፍ በፈተናቸው በዝቷል። በእነዚህ ጊዜያት የክርስቶስ ፍቅር በልግስና ፈስሶላቸዋል።

የምንኖረው ኃጢአተኛ በሆነ ዓለም ውስጥ ነው። ይህን ኃጢአት በራሳችን ላይ አምጥተናል። የስህተት ማስረጃዎች በዙሪያችን አሉ። ከክፉ ፈተናዎች ጋር መታገላችን በልባችን እና በአዕምሮአችን የሚታይ ነው። በህመም፣በበሽታ እና በእርጅና መሰቃየታችን በሰውነታችን ላይ በግልጽ ይታያል። ከጥቃት፣ግድያ ወይም ስደት ጋር ስንታገል በሕብረተሰባችን ውስጥ የኃጢአት ውጤት ይታያል። ሰይጣን በማኅበረሰባችን ውስጥ ሕያው እና ንቁ ነው።

እንደ አማኞች የምንኖርበት ዓለም ይህ ነው። አዲሱን ሰውነታችንን ገና አልተቀበልንም ስለዚህ በህመም እና በበሽታ ምክንያት እንሰቃያለን። የእግዚአብሔርን ዓላማ የናቁ ሰዎች በሚያደርሱት በደል ውስጥ እናልፋለን። በእነዚህ ጊዜያት የሚጠብቀን ምንድን ነው? የክርስቶስን ፍቅር ማወቅ ነው። መቼም እንደማይተወን እናውቃለን። በዚህ ዓለም ሃዘን እና ሞት ላይ ድልን የሚሰጠን እውቀት ነው። ከእርሱ ጋር ለዘላለም የምንሆንበትን መኖሪያ በመንግስተ ሰማይ እያዘጋጀልን መሆኑን ማወቅ ነው።

መከራ፣ጭንቀት፣ስደት፣ረሃብ፣ራቁትነት፣አደጋ፣ወይም ሰይፍ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም። በፈተናዎች በተሞላ ዓለም ውስጥ ለመፅናት ብርታት ሊሰጠን የሚችለው የክርስቶስ ፍቅር ብቻ ነው።

የጳውሎስ የክርስቶስ ፍቅር ማረጋገጫ በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ በቁጥር 38 እና 39 ላይ በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ፈጽሞ ሊለዩን እንደማይችሉ የሚያውቃቸውን አስር ነገሮች ዘርዝሯል። በቁጥር 38 ላይ ያለውን የጳውሎስን ማረጋገጫ አስተውሉ። "እርግጠኛ ነኝ" በሚል ዓረፍተ ነገር ይጀምራል። በዚህ ጉዳይ ላይ ለጥርጣሬ ምንም ቦታ አይተውም። ጌታ ኢየሱስን በማወቅ እና በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ሲናገር ጳውሎስ ሊናገረው ስላለው ነገር ምንም ጥርጥር እንደሌለው ይነግረናል። ጳውሎስ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያካተተው የትኛውም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም። ከክርስቶስ ፍቅር ሊለዩን የማይችሉ በእርሱ ዝርዝር ውስጥ ያሉትን እስቲ ትንሽ እንመልከት።

### *ሞት*

ጳውሎስ የሚጀምረው ሞት በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንደማይችል በመንገር ነው።

አማኞች በህይወት ውስጥ ፈተና ይገጥማቸዋል። አንዳንዶች ሕይወታቸውን እንኳን ለጌታ ኢየሱስ አሳልፈው ይሰጣሉ። የእስጢፋኖስ ሁኔታ ይህ ነበር። በሐዋርያት ሥራ 7 አይሁድ በድንጋይ ወግረው ገደሉት። በሐዋ 7፡56 ላይ እስጢፋኖስ በድንጋይ ቢወገርም፤አይቹን ወደ ሰማይ አንስቶ እንዲህ ሲል ጮኸ፡

*56 እነሆ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ። (ሐዋ 7)*

ሊሞት ሲል እስጢፋኖስ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል” ብሎ ጮኸ (ሐዋ 7፡59) ። የእስጢፋኖስ አሰቃቂ ሞት ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየው አልቻለም። የተቆጡ የማያምኑ ሰዎች ለሞት የሚያደርስ ድብደባ ቢፈጽሙበትም፣ ጌታ ኢየሱስ አገልጋዩን በፍቅሩ ለዘለዓለም ወደሚጠበቅበት እና ደህንነት ወደሚያገበኝበት ህልውናው ተቀበለው። ሞት በእስጢፋኖስ ላይ ስልጣን አልነበረውም።

ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ይላል፡

*55 ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ? 56 የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤ 57 ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ*

*ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። (1ኛ ቆሮንቶስ 15)*

የሐጢአት መውጊያ ጌታ ኢየሱስን ለተቀበሉ ተወግዷል፡፡ ሞት ወደ ፍቅሩ እቅፍ የመግቢያ መንደርደሪያ ነውና፡፡

## *ሕይወት*

ሞት ከሕይወት የሚቀልበት ጊዜ አለ። በሽታ እና ህመም ሰውነታችንን ያበላሹታል። የተፈጥሮ አደጋዎች ንብረታችንን፣ መፅናናትን እና ደህንነትን ይገፉናል። የምንወዳቸው ሰዎች ሲለዩን ብቸኝነት እና ሃዘን ይጥሉብናል። ልጆቻችን በዚህ ዓለም ሽንገላ ተታለው በሥነ ምግባር ብልግና፣በአደንዛዥ ዕፅ እና በሁሉም ዓይነት ሱሶች ውስጥ ይወድቃሉ። ሕይወት ከአቅም በላይ ሊሆን ይችላል።

በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፡23-28 ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ ስላጋጠሙት ችግሮች ተናግሯል። በእነዚያ ጥቅሶች ውስጥ፣ እንደተደበደበ፣እንደተወገረ፣መርከብ እንደተሰበረበት እና ብዙ ጊዜ በአደጋ ውስጥ እንዳለፈ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን ያስታውሳቸዋል። ነፍሱን በሚሹት ሐሰተኛ ወንድሞች ተዘርፏል እና ለአደጋም ተጋልጧል። ያለ ምግብና ውሃ መሆን ምን እንደሚመስልም ያውቃል።

ዳዊት ሊገድለው ይፈልገው ከነበረው ከንጉሥ ሳኦል ሸሽቶ ዓመታት አሳልፏል። በዋሻ ውስጥ እየኖረ በማያቋርጥ አደጋ ውስጥ ነበር። ኢየሱስ የሚመለስበት ቀናት ሲቃረቡ በምድር ላይ ስደት እየጨመረ እንደሚሄድ ይናገራል፡

*21 ወንድምም ወንድሙን፥ አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፥ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ ይገድሉአቸውማል። 22 በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። (ማቴዎስ 10)*

ይሁን እንጂ ይህ አስቸጋሪ እውነታ እንዳለ ሆኖ፤ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወታችን ውስጥ እጅግ የከፋ ጉዳት በሚያደርስብን ጊዜም እንኳን የእግዚአብሔር ፍቅር ምንጊዜም ጠንካራ እንደሚሆን ነግሮናል። በዚህ ምድር እና በነዋሪዎቿ ህይወት ላይ የኃጢአት ተጽዕኖ ታላቅ ህመም እና ስቃይ ያመጣል። በዚህ ክፋት መካከል ግን የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ እኛ ይደርሳል። በዚህ ፍቅር ውስጥ ታላቅ ምቾት፤ጥንካሬ እና ብርታት እናገኛለን።

***መላዕክቶች***

ጳውሎስ በሦስተኛ ደረጃ መላዕክት በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለዩን እንደማይችሉ ይነግረናል። እግዚአብሔር መላዕክትን የሰማይ ፍጡራን አድርጎ ፈጠረ። በሰማይ እየኖሩ ጌታን እያመለኩ እና እያገለገሉ ያሉ መላዕክት እንዳሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምሩናል። በእግዚአብሔር ላይ ያመፁ እና የሰይጣንን ክፉ ዓላማ በዚህ ምድር ላይ የሚያገለግሉ የወደቁ መላዕክትም ደግሞ አሉ።

2ኛ ነገስት 19:35 የእነዚህን መላዕክቶች ኃይል ያሳየናል፡

*35 በዚያችም ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ወጣ፥ ከአሦራውያንም ሰፈር መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ገደለ፤ ማለዳም በተነሡ ጊዜ፥ እነሆ፥ ሁሉ በድኖች ነበሩ። (2ኛ ነገስት 19)*

አንድ መልአክ በአንድ ሌሊት 185,000 ወታደሮችን ገደለ! በሐዋርያት ሥራ 12 ጴጥሮስ በእስር ቤት እያለ አንድ መልአክ ተገለጠለትና ተነስቶ ከክፍሉ እንዲወጣ አዘዘው። ጴጥሮስ ለመልአኩ ትእዛዝ ምላሽ ሲሰጥ፣የታሰረበት ሰንሰለቶች ወደቁ፣ እናም ጠባቂዎቹ ሳያውቁ ከተዘጋው እስር ቤት ወጣ (ሐዋ 12፡7-11 ተመልከቱ) ።

የወደቁት መላዕክት የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥራ ለማፍረስ ኃይላቸውን ይጠቀማሉ። ለክፋት ሲሉ መሪዎችን እና መንግስታትን ላይ ተፅእኖ ያደርጋሉ እንዲሁም ያታልላሉ። ራዕይ 12፡9 ሰይጣን ዓለምን ሁሉ ሊያታልል እንደሚፈልግ ይነግረናል፡

*9 ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ። (ራዕይ 12)*

እነዚህ መላዕክት ኃያላን ቢሆኑም፣ ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየን አንድም እንደሌለ ይነግረናል። ከእግዚአብሔር ጋር በምናደርገው ጉዞ ሊያደናቅፉን ይፈልጉ ይሆናል። በመንገዳችን ላይ እንቅፋት ሊጥሉ ይችላሉ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የፍቅር ቁርጠኝነት መለወጥ ወይም ማስወገድ አይችሉም።

*ገዢዎች*

በታሪክ ውስጥ የፖለቲካ እና የሐይማኖት መሪዎች የክርስቶስን ሥራ ለማጥፋት ብዙ ሰርተዋል። ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ፤ንጉሥ ሄሮድስ ሊገድለው ፈለጎ ነበር። በኢየሱስ ዘመን የነበረው መሪ በመስቀል ላይ ቸነከረው። በዚህ ዓለም

ውስጥ አማኞች ጌታ ኢየሱስን እንዳያመልኩ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረጓቸው ገዥዎች አሉ።

ገዥዎች እና መንግስታት ሁልጊዜ በክርስቲያናዊ መርሆዎች አይመሩም። መጽሐፍ ቅዱስ መሪዎቻችን ውሳኔ የሚሰጡበት አይደለም። በእግዚአብሔር ቃል መሠረታዊ ሥርዓቶች ላይ ተቃውሞ እንደሚያጋጥመን መጠበቅ እንችላለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ የቆሙ አማኞች ከገዥዎች እና ከአገራቸው ህግጋት ተግዳሮት ይገጥማቸዋል።

ጳውሎስ ግን በዚህ ምድር ላይ ማንም ገዥ ወይም የፖለቲካ ኃይል በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንደማይችል ያሳስበናል። የኢየሱስ ተከታይ መሆንን አስቸጋሪ ሊያደርጉት ይችላሉ። በእምነታችን ምክንያት ሊያሳድዱን ይችላሉ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር ከእኛ ሊወስዱ አይችሉም። አንዳንድ የማውቃቸው ጠንካራ አማኞች፤የፖለቲካ እና የሐይማኖት መሪዎች የእምነታቸው ተግባር በሚገድቡባቸው አገሮች ውስጥ ይኖራሉ። እነዚህ አማኞች በእነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ስላላቸው የእግዚአብሔር ፍቅር ልምድ ብዙ የሚያስተምረኝ ነገር አለ።

***ያለውም ቢሆን***

ጳውሎስ በመቀጠል "ስላሉት ነገሮች" ተናግሯል። "አሁን ያሉት ነገሮች" ዛሬ በዙሪያችን የምናያቸውን ማንኛውንም ነገርን ያጠቃልላል። ዙሪያችሁን ስትመለከቱ ምን ታያላችሁ? በምንኖርበት ቦታ ላይ በመመስረት የተለያዩ እንቅፋቶች ይኖሩናል። ዙሪያዬን ስመለከት፤ፍቅረ ንዋይ አያለሁ። የስልጣን እና የሃብት ጥማት እንዲሁም ስግብግብነትም እመለከታለሁ። በተጨማሪም የእምነት መቀዛቀዝ እና ከእግዚአብሔር ቃል መራቅ የህይወት እና የተግባር መስፈርት እንደሆነ አውቃለሁ።

ጳውሎስ ከእነዚህ ነገሮች አንዳቸውም በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለዩን እንደማይችሉ እየነገረን ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ህብረት እና ባለንበት ሁኔታ የዚያ ፍቅር ልምምዳችን ሊለያይ እንደሚችል መረዳታችን ወሳኝ ነው። ሉቃስ 15 አባቱን ትቶ በራሱ ሥነ-ምግባር የጎደለው ሕይወት ለመምራት ስለሄደ ወጣት፤የአባካኙ ልጅ ታሪክ ይናገራል። በሥጋው በመሳቡ ምክንያት ከአባቱ ተለይቶ ሄደ። ርስቱን በከንቱ አጥፍቶ በመጨረሻ ምንም ሳይኖረው ቀረ። ወደ ቤቱ ሲመለስ ግን እጆቹን ዘርግቶ በተቀበለው የአባቱ ፍቅር ተደነቀ።

አዎን፣ "አሁኑ ያሉት ነገሮች" ሊፈትኗችሁ እና ለጊዜው ከእግዚአብሔር ሊያርቋችሁ ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህ

እግዚአብሔር ለእናንተ ያለውን ፍቅር አይለውጠውም። እርሱ እናንተን መውደዱን ይቀጥላል። እናንተን በፍቅር መፈለጉን ይቀጥላል። ሉቃስ 15 የጠፋውን በግ ሊፈልግ እንደወጣው እናንተን ይፈልጋችኋል። “በአሁኑ ነገሮች” መሳብ የተነሳ እሱን ልትቃወሙት ትችላላችሁ፣ ነገር ግን እርሱ እንዳይወዳችሁ በፍጹም ልታደርጉት አትችሉም።

## *የሚመጣውም ቢሆን*

ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለዩን የማይችሉት ያሉት ነገሮች ብቻ ሳይሆን ጳውሎስ “የሚመጡት ነገሮችም” እንደማይለዩን ይነግረናል። ማናችንም ብንሆን ነገ የሚሆነውን አናውቅም። ታላላቅ ፈተናዎች ወይም ክፋቶች ወደ ህይወታችን ሊመጡ ይችላሉ። መቼም እንጋፈጣለን ብለን ያላሰብናቸው ተግዳሮቶች ሊገጥሙን ይችላሉ። ጳውሎስ በእግዚአብሔር ፍቅር በጣም ከመተማመኑ የተነሳ ይህን የድፍረት ቃል ለመናገር ድፍረት ነበረው። በእኛ ላይ ሊደርስ የሚችል ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም። ሰይጣን በዚህ ምድር ላይ ታላቅ ክፋት ሊለቅ ይችላል፣ነገር ግን እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን አመለካከት መለወጥ አይችልም። በኃጢአት እና በከፋ ሁኔታ ውስጥ ልንወድቅ እንችላለን፣ ነገር ግን

እግዚአብሔር አሁንም ይወደናል። ስለዚያ ፍቅር ያለኝ ልምምድ እና ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝ መቀራረብ ያለ ጥርጥር ሊለያይ ይችላል፣ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍቅር የማይቋረጥ እና ጠንካራ ነው። ጠላቶቹ ሳለን ከሞተልን፤አሁን ልጆቹ ስንሆን አይወደንምን?

አንድ ቀን ለጌታ ቅርብ የሆኑ በሚቀጥለውም ቀን ደግሞ በጣም እንደራቁ የሚሰማቸው አማኞችን አይቻለሁ። ለእግዚአብሔር ቃል እውነት በፅናት የቆሙ ነገር ግን በስተመጨረሻ ወደ ስህተት የሄዱ አማኞችን አግኝቻለሁ። ኩራታቸው ውድቀታቸው የሆነባቸውን አማኞች አውቃለሁ። በዝሙት እርኩሰት ውስጥ የወደቁ እና እግዚአብሔር ለእነሱ ካለው መንገድ የራቁ ጓደኞች ነበሩኝ። በኃጢአት ውስጥ ፈጽሞ እንደማንወድቅ ማሰብ ለእኛ ቀላል ነው። ውድቀታችን እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ስለማይለውጥ ምንኛ አመስጋኞች መሆን አለብን። ለሚወድቁት ልቡ ያዝናል። ስለእነርሱ ያስባል። አይተዋቸውም። እንደ ጠፋው ልጅ ይፈልጋቸዋል። ፍቅሩ ከኃጢአታቸው አልፎ ይደርሳል።

## *ኃይላት*

በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር የማይለየን ሰባተኛው ነገር "ኃይላት" ተብሎ ተገልጿል፡፡ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው የግሪክ ቃል "ዲናሚስ" የሚለው ነው:: ቃሉ የሚያመለክተው ተአምራዊ ኃይሎችን ወይም ድንቅ ሥራዎችን ነው:: እነዚህ ሃይላት ብዙ መልክ ሊኖራቸው ይችላል:: በአንዳንድ ሁኔታዎች ኃይሉ ከሐሰት አስተማሪዎች ሊመጣ ይችላል፡፡ ኢየሱስ ይህንን በማቴዎስ 24፡24 ላይ በግልጽ ተናግሯል፡-

*24 ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ:: (ማቴዎስ 24)*

እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያት ምልክትና ድንቅ እንደሚያደርጉ አስተውሉ:: ሰዎችን ወደ ስህተት ከመምራት ባሻገር አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ይሆኑ ዘንድ ያሰበውን እንዳይሆኑ ያግዷቸዋል፡፡ በእነዚህ ኃይላት ለተሳሳቱት የእግዚአብሔር ምላሽ ምንድን ነው? በዘመኑ በሐሰተኛ እረኞች ይመሩ ለነበሩት እግዚአብሔር በሕዝቅኤል በኩል የተናገረውን አድምጡ፡

7 ስለዚህ፥ እረኞች ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ 8 ጌታ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ሕያው ነኝና እረኛ ስለሌለ
እረኞቼም በጎቼን ስላልፈለጉ እረኞችም ራሳቸውን እንጂ
በጎቼን ስላላሰማሩ፥ በጎቼ ንጥቂያ ሆነዋልና፥ በጎቼም ለምድር
አራዊት ሁሉ መብል ሆነዋልና 9 ስለዚህ፥ እረኞች ሆይ፥
የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ 10 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፦ እነሆ፥ በእረኞች ላይ ነኝ፥ በጎቼንም ከእጃቸው
እፈልጋለሁ፥ በጎቼንም ከማሰማራት አስተዋቸዋለሁ። ከዚያም
ወዲያ እረኞች ራሳቸውን አያሰማሩም፤ በጎቼንም ከአፋቸው
አድናለሁ፥ መብልም አይሆኑላቸውም። 11 ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላልና፦ እነሆ፥ እኔ ራሴ በጎቼን እሻለሁ
እፈልግማለሁ። 12 እረኛ በተበተኑት በጎች መካከል ባለ ጊዜ
መንጋውን እንደሚፈልግ፥ እንዲሁ በጎቼን እፈልጋለሁ፤
በደመናና በጨለማ ቀን ከተበተኑት ስፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ።
13 ከአሕዛብም ዘንድ አወጣቸዋለሁ ከአገሮችም
እሰበስባቸዋለሁ፥ ወደ ገዛ አገራቸውም አመጣቸዋለሁ፤
በእስራኤልም ተራሮች ላይ በፈሳሾችም አጠገብ በምድርም ላይ
ሰዎች በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ አሰማራቸዋለሁ። 14
በመልካም ማሰማርያ አሰማራቸዋለሁ ጕረኖአቸውም
በረጅሞቹ በእስራኤል ተራሮች ላይ ይሆናል፤ በዚያ በመልካም
ጕረኖ ውስጥ ይመሰጋሉ፥ በእስራኤልም ተራሮች ላይ
በለመለመ ማሰማርያ ይሰማራሉ። 15 እኔ ራሴ በጎቼን
አሰማራለሁ አስመስጋቸውማለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

*16 የጠፋውንም እፈልጋለሁ የባዘነውንም እመልሳለሁ የተሰበረውንም እጠግናለሁ የደከመውንም አጸናለሁ፤ የወፈረውንና የበረታውንም አጠፋለሁ በፍርድም እጠብቃቸዋለሁ። (ሕዝቅኤል 34)*

የእግዚአብሔር ሕዝብ እየተጠቀሙባቸው በነበሩ ሐሰተኛ እረኞች ተመርተው ነበር። በእነዚህ እረኞች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ ከዚያም በፍቅር በጎቹን በመጎብኘት ራሱ ይንከባከባቸው ነበር። ከመንጋው ወጥተው መቅበዝበዛቸው እግዚአብሔር ለበጎቹ ያለውን ፍቅር አልለወጠውም።

ጳውሎስ እዚህ ላይ የጠቀሳቸው ኃይላት ከአጋንንት ምንጮች ሊመጡ ይችላሉ። ራዕይ 13፡11-14 ይህን ከምድር የወጣውን የአውሬውን ኃይል ይገልጻል። ይህ አውሬ እሳትን ከሰማይ በማውረድ ታላላቅ ምልክቶችን ያደርግ ነበር። የዓለምን ነዋሪዎች ለማታለል እና ከባሕር ለወጣው አውሬ የማይሰግዱትን ለመግደል የተላከ ነው። እንዲህ ያለውን ኃይል የማይፈራ ማን ነው? ይህ ኃይል ከሰይጣን እንጂ ከእግዚአብሔር አልነበረም።

በዚህ ዓለም እንዲሁም በአከባቢያችን እንደዚህ ያለ ኃይል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ አለ፡፡ በጥንቆላ እና በሌሎች መናፍስታዊ ድርጊቶች ይከናወናል፡፡ እውነተኛ ኃይል ቢሆንም፣ ከእግዚአብሔር ፍቅር እና ርኅራኄ እንክብካቤ ሊለየን አይችልም። እግዚአብሔር እኛን ከመውደድ እና እኛን ከመጠበቅ የሚያግደው የትኛውም የሲኦል ኃይል የለም። ጠላት እግዚአብሔር ትቶናል ብለን እንድናምን ከማድረግ ያለፈ ምንም አይፈልግም። ምንም እንኳን ክፉ ኃይላት በዙሪያችን ቢለቀቁም በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ማረፍ እንችላለን።

*ከፍታ*

በቁጥር 39 ላይ ጳውሎስ ምንም "ከፍታ" ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንደማይችል እየነገረን እንደሆነ አስተውሉ። እዚህ ላይ ምን ማለቱ እንደሆነ አይነግረንም። ልንረዳው የሚገባው ነገር የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ እኛ የማይደርስበት ቦታ እንደሌለ ነው። "ከፍታ" የሚለውን ቃል የምንረዳባቸው ብዙ መንገዶች አሉ። እግዚአብሔር ከእኛ በላይ መሆኑን አስቡ። ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር

በሰማይ እኛም በምድር እንዳለን ይናገራል። መዝሙረኛው በመዝሙር 102 ላይ የሚነግረንን አንብቡ፡-

*18 ይህ ለሚመጣ ትውልድ ይጻፍ፥ የሚፈጠርም ሕዝብ ለእግዚአብሔር እልል ይላል፤ 19 እግዚአብሔር ከመቅደሱ ከፍታ ሆኖ ተመልክቶአልና፥ ከሰማይ ሆኖ ምድርን አይቶአልና፤ (መዝሙር 102)*

እስረኞች ይፈቱ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ ከፍታ ወደ ምድር ተመለከተ። እሱ ከኛ በጣም የራቀ ነው፤ነገር ግን በፍቅር ወደ እኛ ይደርሳል።

ከተወሰነ ጊዜ በፊት ኮንፈረንስ ላይ ነበርኩ። ጌታ በዚያን ጊዜ በህይወቴ ውስጥ አስደናቂ ሥራዎችን ይሰራ ነበር። እግዚአብሔር በእኔ እየሠራ ሳለ፣ አማኞች ለመጸለይ በዙሪያዬ ተሰበሰቡ። ያ የጸሎት ጊዜ ከ2-3 ሰዓታት የወሰደ ነበር፣ እና ስንጨርስ ሁላችንም ደክመን ነበር ነገር ግን ድል እንዳደረግን ተሰምቶን ነበር። ሁሉም ካበቃ በኋላ በዚያ ምሽት ከነበሩት መጋቢዎች አንዱ በሌሊት ወጥቶ ወደ ሰማይ

አንጋጦ ከዋክብትን ይመለከት ነበር፡፡ እየተመለከተም ሳለ፣ ጌታ እንዲህ ሲል እንደተሰማው ነገረኝ፡- “ቢል፣ ዛሬ ማታ የሆነውን አይተሃልን? ከዚህ ተነስቼ ወርጄ ዌይኒን ነካሁት፡፡” በኋላ ቢል እንዲህ ያለ ታላቅ እና አስደናቂ አምላክ አንድን ሰው በፍቅሩ ለመንካት ከሰማይ ወደ ምድር እንደሚወርድ በማሰቡ እንደተደነቀ ነገረኝ፡፡

አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጆች በትዕቢት ራሳቸውን ይክባሉ፡፡ ነቢዩ አብድዩ በመጽሃፉ የተናገረላቸው ሰዎች ሁኔታም ይህ ነበር፡፡ አብድዩ 3-4 ላይ የነገራቸውን አድምጡ፡-

*3 በተሰነጠቀ ዓለት ውስጥ የምትኖር፥ ማደሪያህንም ከፍ ከፍ ያደረግህ፥ በልብህም፦ ወደ ምድር የሚያወርደኝ ማን ነው? የምትል አንተ ሆይ፥ የልብህ ትዕቢት አታልሎሃል፡፡ 4 እንደ ንስር መጥቀህ ብትወጣ፥ ቤትህም በከዋክብት መካከል ቢሆን፥ ከዚያ አወርድሃለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡ (አብድዩ)*

ምን ያህል ጊዜ ትዕቢት እና ኩራት ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ህብረት አራቀን? እግዚአብሔር እንደማያስፈልገን አምነን ራሳችንን ከእርሱ ለይተናል። በአብድዩ ዘመን ለነበሩት ሰዎች ጌታ እንደሚያዋርዳቸው አስታውሷቸዋል። ጳውሎስ ትህትናን ለመጠበቅ "የሥጋው መውጊያ" እንደተሰጠው መስክሯል፡-

*7 ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፥ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው። (2ኛ ቆሮንቶስ 12)*

እግዚአብሔር ጳውሎስ እንዲታበይ አና ለእርሱ ካለው ፍቅር እና መሻት እንዲርቅ አልፈቀደለትም። እግዚአብሔር ጳውሎስን ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረው ይፈልግ ነበር። እግዚአብሔር ከሰማይ አይቶ ወደ እኛ መጣ። ስንታበይ ይመለከተናል እናም ፍቅሩን እንደገና ወደምናውቅበት እና ወደምንለማመድበት ያወርደናል። በትዕቢት ራሳችንን ከፍ አድርገን ከእግዚአብሔር ብንመለስም፤አይረሳንም። በፍቅር ይደርሰናል።

***ጥልቀት***

ከፍታዎች በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን ካልቻለ፣ ጥልቀትም ሊለየን አይችልም። በሰዋዊ ልምዳችን፣በስሜታዊነት ታላቅ ወደሆነ ጥልቀት መውረድ እንችላለን። ጌታ በሕይወቴ ስራውን ካጠናቀቀ ወደ ቤቱ እንዲወስደኝ የጠየቅኩበት ጊዜ ነበር ምክንያቱም ከዚህ በኋላ መቀጠል እንደምፈልግ አልተሰማኝም ነበርና። አንዳንድ ጊዜ ወደ ታላቅ ኃጢአት እና በእግዚአብሔር ላይ ወደ ማመፅ መውረድ እንችላለን። በትዕቢታችን፣ለእግዚአብሔር እና ለሕይወታችን ላለው ዓላማ ጀርባችንን መስጠት እንችላለን።

በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ ሰዎችን በመጉዳት መንከራተት እና ወደ ታላቅ ኃጢአት ልንወድቅ እንችላለን። ኢየሱስ እኛን ለማግኘት ወደዚህ ጥልቀት ወረደ። በኃጢአታችን እና በአመፃችን ውስጥ ብንሆንም ይፈልገናል። የኃጢአተኞች ወዳጅ በመባል ይታወቅ ነበር እናም በጊዜው የነበሩት የሃይማኖት መሪዎች ለመንካት ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎችን እንኳን ይነካ ነበር። ምናልባት በጣም ዝቅ ብላችሁ እና ወርዳችሁ ማንም ሊወዳችሁ እንደማይችል ታስቡ ይሆናል። ጳውሎስ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ምንም ዓይነት ጥልቀት ሊለየን እንደማይችል እርግጠኛ ነበር። የቱንም ያህል ብንቅበዘበዝ፣የቱንም ያህል ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ብንወድቅ፤ የፍቅር ክንዱ ወደ እኛ ይደርሳል።

## *ልዩ ፍጥረትም ቢሆን*

ጳውሎስ እኛን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን በማይችለው በዚህ የመጨረሻ ነገር ይደመድማል፡፡ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን የሚችል ምንም ነገር እንደሌለ እርግጠኛ ነበር፡፡ በዚህ ስነ-ፍጥረት ውስጥ ያልተፈጠረ ምን አለ? እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ ፈጠረ፡፡ እኛ እንደምናውቀው ዓለም እና ሰይጣን እንዲሁም መላእክቱ ሁሉ ፍጡራን ናቸው፡፡ በዚህ ፍጥረት ውስጥ ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም፡፡ እኔ እና እናንተ በእግዚአብሔር እንደተፈጠርን አስተውሉ፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔር እንዳይወደኝ ማድረግ አልችልም ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር በሁሉም የሕይወት ሁኔታዎች ውስጥ ጠንካራ ሆኖ ቢቆይም፣ለዚያ ፍቅር ያለኝ ልምምድ ሊለያይ ይችላል፡፡ ያን ፍቅር ልለማመደው እና ልደሰትበት እችላለሁ ወይም ጀርባዬን ለእግዚአብሔር ልሰጥ እና ይህን ፍቅር በጣም በጥቂቱ ላውቅ እችላለሁ፡፡ ጥያቄው እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ይወደናል የሚለው ሳይሆን፣ለዚያ ፍቅር ሙላት ልባችንን ለመክፈት እና በፍቅር ለእርሱ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆናችን ነው፡፡

ጳውሎስ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ስላለን አስደናቂ ማረጋገጫ ያስታውሰናል፡፡ እግዚአብሔር ለጠራቸው እና ላጸደቃቸው ፍቅሩ ፈጽሞ እንደማይሽር እርግጠኛ መሆን ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ሙሉ በሙሉ ለልጆቹ ይሰጣል፡፡ መንፈሱን በውስጣችን በማኖር ከእኛ ጋር ያለውን ስምምነት ያትማል፡፡ ሁልጊዜ ለእርሱ ብቁ ሆኜ አልሄድ ይሆናል፣ ነገር ግን ኃጢአቶቼ ሁሉ ይቅር ተብለዋል፣ እናም እሱ ፈጽሞ አይተወኝም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር ምላሽ ይጠይቃል፡፡ በምላሹ ታማኝነቴን እና መስጠቴን ይጠይቃል፡፡

**ለምልከታ**:

ክርስቶስ ለእኛ ባለው ፍቅር እና እኛ ለእርሱ ባለን ፍቅር መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ሁለቱን ለማነጻጸር ትንሽ ጊዜ ውሰዱ፡፡ ለክርስቶስ ያላችሁ ፍቅር እርሱ ለእናንተ ካለው ፍቅር ጋር እንዴት ይወዳደራል?

በዚህ ሕይወት ስለ ክርስቶስ መከራ መቀበላችን እርሱ አይወደንም ማለት ነውን? የክርስቶስ ፍቅር በመከራ ውስጥ የሚገለጠው እንዴት ነው?

ክርስቶስ እኛን በመውደዱ እና ስለዚያ ፍቅር ባለን ልምምድ ወይም ግንዛቤ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? መወደድ እና ያንን ፍቅር ሙሉ በሙሉ ማወቅ አልችልምን? መወደድ እና የዚያን ፍቅር ሙላት ፈጽሞ ሳልለማመድ እችላለሁን?

የክርስቶስን ፍቅር ሙላት እንዳናጣጥም የሚያደርገን ምንድን ነው?

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ ክርስቶስ ለእኛ ስላለው ፍቅር የሚነግረንን ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ ተመልከቱ። ይህ ፍቅር እኛ የሚገባን ነውን? እሱ የበለጠ እንዲወደን ለማድረግ ማንኛውንም ነገር ማድረግ እንችላለን?

የክርስቶስን ፍቅር ለማግኘት ማገልገል እና በፍቅሩ ደህንነት ውስጥ ባለ ሥፍራ ላይ በማገልገል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? በተነሳሽነት ውስጥ ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

**ለጸሎት:**

ለእርሱ ያለን ፍቅር ሁልጊዜ መሆን ያለበት ባይሆንም፣ ለእኛ ያለው ፍቅር ግን ፈጽሞ ስለማይለወጥ ጌታን አመስግኑት።

በሕይወታችን በሚገጥመን መከራ ውስጥ እንኳን ፍቅሩ ስለሚገለጥ ጌታን አመስግኑት። ከተግዳሮቶች ጋር በምትታገሉበት ጊዜ ይህን ፍቅር በይበልጥ ለማየት ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ ጠይቁ።

በፍቅሩ ደህንነት ውስጥ ስለሆናችሁ፣እርሱ ትኩረት ስለሚሰጣችሁ እና ከማንኛውም ፍላጎት ነጻ በሆነ ልብ እሱን ማገልገል እና ማምለክ ስለምትችሉ ጌታን አመስግኑት። ሙሉ በሙሉ ስለተወደዳችሁ አመስግኑት።

ከፍቅሩ የሚለያችሁ ምንም ነገር እንደሌለ በማወቅ ስላላችሁ ደህንነት ጌታን አመስግኑት። ዘላለማዊ አመስጋኝ የሆነ ልብ እንዲሰጣችሁ ጠይቁ።

## ላይት ቱ ማይ ፓዝ የመጽሐፍት ስርጭት

ላይት ቱ ማይ ፓዝ (LTMP) በእስያ፤በላቲን አሜሪካ እና በአፍሪካ የሚገኙ ድሃ ክርስቲያን አገልጋዮችን የሚደርስ የመጽሐፍ ስርጭት አገልግሎት ነው። በታዳጊ አገሮች ውስጥ የሚገኙ በርካታ ክርስቲያን አገልጋዮች የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና ለማግኘት ወይም ለአገልግሎቶቻቸው እና በግል ለመታነጽ የሚሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁሳቁሶችን ለመግዛት አስፈላጊ የሆኑ ሃብቶች የሏቸውም።

እስከዛሬ በሺዎች የሚቆጠሩ መጽሐፍት ከስድሳ በላይ በሆኑ አገራት ውስጥ ለስብከት፤ለማስተማር፤ለወንጌል ስርጭት አገልግሎት እና ለአጥቢያ አማኞች ማበረታቻ ይሆን ዘንድ ተሰራጭተዋል። አሁን መጽሐፍቶቹ ወደ በርካታ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ዓላማው በተቻለ መጠን ለሁሉም አማኞች ተደራሽ ማድረግ ነው።

የ(LTMP) አገልግሎት በእምነት ላይ የተመሠረተ አገልግሎት ነው፤በዓለም ዙሪያ ያሉ አማኞችን ለማበረታታት እና ለማነጽ መጽሐፍቶቹ ይሰራጩ ዘንድ ለእነዚህ አስፈላጊ ሃብቶች ጌታን እንታመናለን። ጌታ እነዚህን መጽሐፍት ለመተርጎም እና የበለጠ ለማሰራጨት በሮችን ይከፍት ዘንድ በጸሎት ታግዙናላችሁን? ስለ ላይት ቱ ማይ ፓዝ የመጽሐፍ ስርጭት

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ www.lighttomypath.ca